ለአእምሮ የሚመች አገልግሎት

የሐዋርያት ሥራ



ከኢዮብ ማሞ

ለአእምሮ የሚመች አገልግሎት

1989 ዓ. ም.

1997 እ. ኤ. አ.

ETHIOPIAN EVANGELICAL BAPTIST CHURCH
9120 FERGUSON ROAD
DALLAS, TEXAS 75228

ከኢዮብ ማሞ

ለአእምሮ የሚመች አገልግሎቶ
Reasonable Service

ይህን መጽሐፍ
ያለ ደራሲው ፈቃድ ሙሉ
በሙሉም ሆነ በከፊል ማባዛት በሕግ የተከለከለ ነው።

Copyright © 1997, by Eyob Mamo
All right reserved.
Reproduction of text in whole or in part without
the express written consent by the author is unlawful.
Cover Picture © 1997, by James H. Brown

Printed in the United States of America

For comments, questions
or to order additional copies
write to:
Word Of The Cross Ministries
3240 Adams Street
Denver, Co. 80205
USA
E-mail Address:
EMamo@aol.com

ይህንን መጽሐፍ በሕይወቴ ትልቅ ስፍራ ላላቸው
ለእጎቶቼ ለቅድስት ማሞና ለማርታ ማሞ
አበረክታለሁ።

ETHIOPIAN EVANGELICAL BAPTIST CHURCH
9120 FERGUSON ROAD
DALLAS, TEXAS 75228

ማውጫ

ማስታወሻ.....6

መግቢያ.....7

1. የምሪት ሕይወት.....9
2. የመንፈስ ቅዱስ መገኘት.....19
3. ሥፍራህን አትልቀቅ.....26
4. እውነተኛ መነቃቃት.....32
5. መገደል ያለባቸው ቀበሮች.....37
6. ወጀብ፡ ወጀብ፡ ወጀብ.....48
7. ከቤተ መቅደስ የማይጠፉ ሰዎች.....56
8. ጌታ የጠራቸውን እናገልግላቸው.....62
9. የጠራህን ጌታ አትወስነው.....68
10. እድገትህን ለካው.....75
11. ማስተዋል ይኑርህ.....81
12. በእግዚአብሔር ዕረፍ.....88
13. የሕይወት ውጣ ውረድና ጸጋው.....94
14. የመንፈስ አንድነት.....101
15. የእግዚአብሔር ልዕልና.....110
16. መገረዝ ያለባቸው ነውሮች.....116
17. ማመን የሌለብህ ውሸቶች.....129
18. ሕብረት ከእግዚአብሔር ጋር.....137
19. መጥረቢያህን ሳለው.....145
20. ለፈተና ሁሉ የተዘጋጀህ ሁን (ክፍል አንድ).....152
21. ለፈተና ሁሉ የተዘጋጀህ ሁን (ክፍል ሁለት).....158
22. ለፈተና ሁሉ የተዘጋጀህ ሁን (ክፍል ሦስት).....163

ምስጋና

ይህ መጽሐፍ በተሻለ ሁኔታ እንዲቀርብ በእርማትና በተለያዩ አሳቦች የደገፉኝን መጋቢ እንደሻው ከልከሌን፡ ወንድም ሰለሞን አሻግሬን፡ ወንድም ዳዊት ገብረ መድህንን፡ ወንድም ጌቱ ካሳን፡ ወንድም ጌታቸው መኮንንን፡ ወንድም ጠዓመ ደስታን፡ ወንድም እንዳልካቸው ሳህሌንና ወንድም ንጉሴ ቡልቻን እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካቸው እላለሁ።

በተጨማሪም የአማርኛችንን ፊደላት በኮምፒውተር መጻፍ እንዲቻል በማድረግ የጽሑፍን ከባድ ሥራ ያቀለለልንን ዶክተር አበራ ሞላን አመሰግናለሁ።

Special thanks to my brother in the Lord, Deacon James Brown of Macedonia Baptist Church for his talented contribution of the cover picture.

ከሁሉም በላይ ይህን መጽሐፍ ለክብሩ እንድጽፍ ያበረታኝ እግዚአብሔር ይመስገን።

ማስታወሻ

የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ በቀሪ ዘመናቸው የሕይወታቸውን ጌታ በሚገባ አክብረው ለማለፍ ለሚመኙ አገልጋዮች ማንም አንባቢ ሊረዳው በሚችል ቀላል አማርኛ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኘውን ዘላለማዊ እውነት መግለጽ ነው። አንባቢው ማንኛውንም የዚህን መጽሐፍ ምዕራፍ ከማንበቡ በፊት ለዚያ ምዕራፍ የተመደበውን የሐዋርያት ሥራ ክፍል ቢያነብ ለማስተላለፍ የተፈለገውን ነጥብ በሚገባ ይገነዘባል ብዬ አምናለሁ። አንባቢውን ይረዳሉ ብዬ ስላመንኩኝ የሚከተሉትን ምልክቶች አስቀምጫለሁ።



እያንዳንዱ ምዕራፍ የሚጀምረው በመጽሐፍ ምልክት ሲሆን፥ ይህም የሚያመለክተን በዚያ ክፍል ውስጥ የምንነጋገረው ወንጌላዊው ሉቃስ ሊያስተላልፍልን የፈለገውን አሳብ መሆኑን ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን ሊናገር የወደደውን በሚገባ ሳንገነዘብ ወደ ትርጉም ብንሮጥ እንስታለን።



የሻማ ምልክት ባለበት ሥፍራ የምንነጋገረው ሉቃስ ከሰጠን መግለጫ ውስጥ ለሕይወታችን ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎችን ነው። ከቃሉ እውቀታችን ውስጥ ለየዕለት ኑሮአችን ተግባራዊ መመሪያ ካላገኘን በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንደርቃለን።



አንዳንድ የምንማራቸው እውነቶች ሚዛናዊነትን ይጠይቃሉ። የሚዛን ምልክት የሚገኝባቸው አንዳንድ ስፍራዎች የሚያስተምሩን ቀደም ሲል የተነጋገርንባቸውን እውነቶች ያለ ልክ ወስደን ግትርነት እንዳያጠቃን ነው። «ይህ ብቻ ነው እውነት» በሚል ሳቢያ አንድን አመለካከት አክርረን ይዘን ዓይናችንን በምንጨፍንበት ጊዜ ሚዛናችንን ስተን በተለያየ የትምህርት ነፋስ እንፍገመገማለን።

እግዚአብሔር ይህንን መጽሐፍ ተጠቅሞ የአንባቢውን ሕይወት እንዲቀሰቅስና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተገለጡትን ግለቂያ የሌላቸው እውነቶች በበለጠ ጥልቀት ወደ ማወቅና ተግባራዊ ወደ ማድረግ ደረጃ እንዲያደርሰው ጸሎቴ ነው።

ኢዮብ ማሞ

መግቢያ

ከሰማይ የአገልግሎትን ጥሪ የተቀበለ አገልጋይ የጌታን እውነተኛ ሥራ ለማየትና ለመለማመድ መፈለጉ ጥርጥር የለውም። በዚህ ዓይነት የአገልግሎት ጥማት የተሞላ ማንኛውም አገልጋይ በጌታ ፊት ቁጭ ብሎ ቃሉን ከመስማትና መንፈስ ቅዱስ የሚለውን ከማድረግ የበለጠ ልሞክርም ቢል ምንም ማድረግ እንደማይችል ብዙም ሳይቆይ መገንዘቡ አይቀርም።

ማንኛውም የዚህ ዘመን አገልጋይ እንደ ሐዋርያት በሙላት መቆም እንዲችል፥ እነርሱ ባለፉበት ጎዳና ለማለፍ ፈቃደኛ መሆን አለበት። እነርሱ ወደ አገልግሎት ከመግባታቸው በፊት ከዓለም ይዘው የመጡት ለጌታ ሥራ የማይመች ባህሪያቸው እስኪለወጥ ድረስ ከክርስቶስ ጋር በመከራ አለፉ። ለምሳሌ፥ ሲያዕቆብና ለዮሐንስ፦ «ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆነላችሁ አታውቁም» (ሉቃ. 9፥55) ብሎ የነበረባቸውን የፍርድ መንፈስ በመቃወም፥ በሌሎች ላይ በመፍረድ አገልግሎታቸውን ሊገፉት እንደማይችሉ በግልጥ አሳያቸው። በሌላ ጊዜ ደግሞ እነዚሁን በፍርድ የተሞሉ አገልጋዮች በትዕቢት ጎዳና ላይ አግኝቶ፦ «በቀኝና በግራ መቀመጥ ለተዘጋጀላቸው ነው» (ማር. 10፥40) በማለት፥ አገልግሎት ማለት የተሻለን ስፍራ የመያዝ ውድድር ሳይሆን ከጌታ የተቀበሉትን አደራ በታማኝነት የመፈጸም ጉዳይ መሆኑን አስተማራቸው።

በሥጋቸው አንዳች ለማድረግ እንደማይችሉ ይማሩ ዘንድ በጀግንነቱ የታወቀው ጴጥሮስ በክህደት ጎዳና ሲያልፍ በዓይናቸው ተመልክተዋል። ዮሐንስ ፈጽሞ አይሞትም የሚለውም ከንቱ ወሬ ወደ ወንድሞች የወጣው በዚሁ በጴጥሮስ አማካኝነት ነበር። ጴጥሮስ ስለ ዮሐንስ የአሟሟት ሁኔታ ላቀረበው ጥያቄ ጌታ፦ «ምን አግዶህ? አንተ ተከተለኝ» በማለት፥ አገልጋይ የከበረውን የጌታውን ሥራ ቸል ብሎ የሌላ ሰው ሕይወት ውስጥ ያለ አግባብ መግባት እንደሌለበት የማይረሳ ትምህርት ትቶላቸው አለፈ (ዮሐ. 21፥21–23)።

ከዚያም በበለጠ መማር ካስፈለጋቸው የይሁዳ አሳዛኝ ምሳሌነት በፊታቸው ተደቅኖ ነበር። አገልጋይ በድብቅ ኃጢአትን እየተለማመደ

በቅዱሳን ጉባኤ መካከል ንጹህ መስሎ መቆሙ ለጥቂት ጊዜ ቢያራምደውም፥ መጨረሻው የከፋ መሆኑን በማያዳግም ሁኔታ የይሁዳ ሕይወት አስተማራቸው።

እንግዲህ፥ እነዚህንና የመሳሰሉትን አስፈላጊ ትምህርቶች ካስተማራቸው በኋላ ነበር በኃይል አስታጥቆ፥ ንቁና ብቁ አድርጎ የላካቸው። ይህ ሁሉ አሳብ በሁለት ፍሬ ነገሮች ይጠቃለላል።

- እኛም እንደ ሐዋርያት ከሁሉ በፊት ባህሪያችን በጌታ መነካት አለበት። ዘወትር የጌታን ኃይል በመፈለግና ለአገልግሎት በመሮጥ የነቃንና የተጋን ሆነን መልካም ባህሪይ ለማሳደግ በቅድሚያ ከጌታ ጋር ጊዜ ልንወስድ ይገባናል፤ ያለበለዚያ አገልግሎታችን ያማረ አይሆንም። ቅንአትና ቍክክር፥ ወገናዊነትና መከፋፈል፥ ሀሜትና የስውር ኃጢአት ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዓይን አውጥተው የሚመጡብን በሚገባ ሳንለወጥ ለአገልግሎት በምንሮጥበት ጊዜ ነው።
- በሌላው አንጻር ደግሞ፥ መልካም ባህሪይ ይዘንና ከጌታ እግር ስር ጸጥ ብለን ተምረን በዚያው ተኝተን እንዳንቀር መጠንቀቅ አለብን። እንደዚህ በምንሆንበት ጊዜ፥ ምንም ችግር የማንፈጥር ሰዎች ብንሆንም እንኳ፥ የጌታ ሥራ የሚበዛልን ሰዎች አንሆንም። ጌታ የሚያስተምረን ለክብሩ እንድንቆምለት እንጂ የመጨረሻውን ወንበር ይዘን ተመልካቾች ብቻ እንድንሆን አይደለም።

በመልካም ባህሪያቸውና ለአገልግሎት ባላቸው ትጋት ምክንያት ክርስትናን በመላት ለዓለም ካዳረሱት ከሐዋርያት የምንማራቸው ብዙ እውነቶች አሉን። እነዚህንም እውነቶች የምናገኘው የሐዋርያት ሥራን በጥንቃቄ በማጤን ነው። አንድን እውነት በልባችን ይዘን ወደ ጥናታችን እንግባ። የአገልግሎት ትጋት ከመልካም ባህሪይ ጋር ታክሎ በሚኖረን ጊዜ ብቻ እኛም እንደ ሐዋርያት ለለአምሮ የሚመች ለገልግሎት ይኖረናል።

1

የምሪት ሕይወት

ምዕራፍ 1፥1–26



ሉቃስ ወንጌሉን በቴዎፍሎስ እድራሻ አስቀድሞ ጽፎ እንደነበር ግልጽ ነው። አሁን ደግሞ ክርስቶስ ቀድሞ የጀመረውን ሥራ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ በሐዋርያቱ አማካኝነት እየሠራ እንዳለ ለቴዎፍሎስ ለመጻፍ ወሰነ። እነዚህን ወንጌላዊው ሉቃስ የጻፋቸውን ሁለት መጻሕፍት፥ (የሉቃስ ወንጌልንና የሐዋርያት ሥራን) የሚያገናኝ መካከለኛ ነገር የኢየሱስ ክርስቶስ ሕያውነት ነው። ትናንትና አይዟችሁ ሲላቸው የነበረው ኢየሱስ ዛሬ በከንቱ በበረሀ ላይ አልጣላቸውም። ከትንሳኤው በኋላ ከአንድ ወር በላይ ራሱን እየገለጠ ማድረግ የሚገባቸውን ያስተምራቸው ነበር። በእውነትም ብዙ መማር የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ነበሩ። ከሁሉ በፊት ተቀዳሚ የነበረው ጉዳይ ግን ከጌታ ኃይልንና ምሪትን ሳይቀበሉ ለአገልግሎት እንዳይወጡ የሰጣቸው ማሳሰቢያ ነበር። ለዚህ ነው በምዕራፍ አንድ ውስጥ እንደምናየው በመጀመሪያ ሐዋርያት የጌታን ምሪት የማወቅ ትምህርት ቤት ውስጥ የገቡት። ለምሳሌ፥ ለዓመታት ሲከተሉት የነበረው ክርስቶስ ኢየሱስ በድንገት ከአጠገባቸው በመለየቱ ከዚያ በኋላ ያላቸውን የሐዋርያነት ጥሪና ተልዕኮ በምን ዓይነት ሁኔታ መምራት እንደሚገባቸው ለማወቅ ምሪት ያስፈልጋቸው ነበር። በተጨማሪም፥ ይሁዳን የሚተካውን ሰው ለማወቅ ምሪት ያሻቸው ነበር።

የሐዋርያት ሕይወት በክርስቶስ ትንሳኤ እውንነት ኃይል አማኝቶ በመቀጣጠሉ፥ በእካባቢአቸው ወጥተው ሁኔታዎችን ሁሉ ለመገለባበጥ የተነሳሱ ይመስላሉ። ስለዚህም ወደ እውነት ሁሉ ሊመራቸው የሚችለውን መንፈስ ቅዱስን ሳይቀበሉ እንዳይወጡ ለመጀመሪያ ጊዜ ትእዛዝን ከጌታ ተቀበሉ። በዚያን ጊዜ እይሁድ የመሲሁን መምጣት በመናፈቅ የዛሉበት ወቅት ነበር። የናዝሬቱ ኢየሱስ ተገልጦ በድንቅና በተአምራት ሲመላለስ ሳለ፥ ሊያነግሱት እስኪመጹ ድረስ የሁሉም ዓይን በእርሱ ላይ ተተክሎ ነበር። ብዙም ሳይቆይ የእርሱ ነገር

አበቃለት እስኪሉ ድረስ በቀራኒዮ መስቀል ላይ ተቸንክሮ ሞተ። አሁን ግን ኢየሱስ ተነስቷል፥ ምናልባትም በዚያን ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ይመልሳል ብለው ተስፋ ያደረጉ ይመስላል።

ደቀ መዛሙርቱ ስለ ምድራዊ መንግሥት ለጠየቁት ጥያቄ የሰጣቸውን የጌታን መልስ በጆሮአቸው ሰምተው፥ ወደ ሰማይም ከፍ ከፍ ብሎ ሲያርግ በዓይናቸው ተመልክተው፥ ጠብቁ ተብለው ወደ ታዘዙበት ወደ ኢየሩሳሌም ከነበሩበት ከደብረ ዘይት ተራራ ተመለሱ። ከዚያች ቀን አንስቶ መንፈስ ቅዱስን እስከ ተቀበሉበት ቀን ድረስ 120 የሚሆኑት ተሰብስበው በጸሎት መትጋቱን ተያያዙት። ከእነዚህም ውስጥ፥ አስራ አንዱ ደቀ መዛሙርት፥ የኢየሱስ እናት፥ ከትንሳኤው በኋላ ክርስቶስን ወደ ማመን የመጡት ወንድሞቹ (ዮሐ. 7፥5) እና ሌሎችም ሴቶች ይገኙበት ነበር። በዚህ ጊዜ ነበር ጴጥሮስ ተነስቶ ለተሰበሰቡት ሁሉ፥ በብሉይ ኪዳን የይሁዳ ሁኔታ እንደተተነበየ ካብራራ በኋላ በእርሱ ምትክ ሌላ ሐዋርያ መመረጥ እንዳለበት የገለጠው። የሚመረጠው ሰው ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ ጌታ እስከ አረገበት ዕለት ድረስ አብሮ የነበረ መሆን ነበረበት። ይህንንም ሁኔታ ካሟሉት ከዮሴፍና ከማትያስ፥ ማትያስ የሐዋርያነትን ሹመት አገኘ። የጌታን ፈቃድ ለማወቅ የተጠቀመበት መንገድ ዕጣ የመጣጣል ዘዴ ነበር።



«ለቀባሁትም ሰው መብራትን አዘጋጃለሁ» (መዝ. 132 ፥ 17) ብሎ በብሉይ ኪዳን የተናገረው አምላክ ዛሬም ለጠራቸው አገልጋዮቹ የምሪትን መብራት ከማዘጋጀት ወደ ኋላ አላለም። ነገር ግን በመጀመሪያ ደረጃ የአገልጋዮቹን ዝግጁነት ይፈልጋል። አንድ አገልጋይ ምን ማድረግ እንደሚገባው (ጥሪውን) አውቆ፥ ነገር ግን እንዴት፥ መቼ፥ እና የት ለሚሉት ጥያቄዎቹ መልስ ሳይቀበል መራመድ በሚጀምርበት ጊዜ ለብዙ ስህተት ራሱን ያጋልጣል። ለዚህ ነው አገልጋይ ከሁሉ በፊት የጌታን ፈቃድ ለማወቅ መትጋት ያለበት። ክርስቶስ ኢየሱስ ሞቶ ከተነሳ በኋላ አርባ ቀን ሙሉ ለ ባሪያዎቹ እየታየ ወደ ፊት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ሲያሳውቃቸው በነበረበት ጊዜ፥ ለሐዋርያት ከላይ የጠቀስናቸው ሦስት ጥያቄዎች አልተመለሰላቸውም ነበር። እነዚህ ለአገልግሎት ፈጽመው እንግዳ

የነበሩ ሰዎች ለአገልግሎት መጠራታቸውን ብቻ እንዳወቁ ቸኩለው ወጥተው ቢሆን ኖሮ በምን ሁኔታ ያልፉ ነበር? በእርግጥም ብዙ ነገር ያበላሹ ነበር።

ምናልባት ዛሬ በሕይወትህ የጌታን ጥሪ ሰምተህ፥ ጌታም በምን አካባቢ ሊጠቀምብህ እንደሚፈልግ ተረድተህ፥ ነገር ግን ይህ እንዴት ይሆናል፥ መቼ ይሆናል፥ የት ይሆናል ለሚሉት ጥያቄዎችህ መልስ ትፈልግ ይሆናል። በዚህ ሁኔታ ላይ ካለህ በእንድ አሳብ ልብህን አረጋጋው። ከላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች ለመመለስ ምንም ዓይነት ችሎታ እንደሌለህ እወቅ። እነርሱን የመፈጸም ጉዳይ የጠሪህ ሲሆን፥ የአንተ ሃላፊነት ዝም ብሎ በስምህ የጠራህን ጌታ መከተል ነው።

- እንዴት ለሚለው ጥያቄህ መልስ ያገኘህ መስሎህ በሥጋዊ አስተሳሰብ መገንባት ብትጀምር፥ ብዙ የለፋህበት እቅድና መሰረት ፈርሶ ልብህን እንዳያቆስለው፥ ለወደፊቱም ለሚጠብቅህ የእምነት እርምጃ የጥርጣሬን ዘር በሕይወትህ እንዳይዘራብህ ተጠንቀቅ። ማድረግ የሚገባህን (ጥሪህን) በሚገባ ከተረዳህ፥ እንዴት ለሚለው ጥያቄ በጣም መጨነቅ የለብህም። ጥሪህን የገለጠልህ እምላክህ እንዴት ማከናወን እንደሚገባህ ያሳውቅሃልና ታገሰው።
- መቼ የሚለው ጥያቄ ብዙዎችን መልስን ሳያገኙ የተራመዱን አገልጋዮች ካለጊዜው ወደ አገልግሎት ያንደረደረ ትልቅ ችግር ነው። ይህ ጥያቄህ ካልተመለሰልህና በሥጋህ አሳብ ከተራመድክ፥ ጌታ ካቀደልህ ጊዜ ቀድመህ ወይም ዘግይተህ የመውጣት ነገር ያሰጋሃል። አሁንም፥ ጥሪህንና በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ያንን ጥሪ በሥራ ላይ ማዋል እንደምትችል ያሳወቀህ ጌታ፥ ጊዜውን የሚገልጥ ደብዳቤ በሰዓቱ እንደሚልክልህ አትጠራጠር።
- የት የሚለውም ጥያቄ ቀላል ጥያቄ አይደለም። ይህ ጥያቄ ካልተመለሰ፥ ስጦታችን፥ አገልግሎታችንና ቅባታችን ሁሉ በተሳሳተ ቦታ ላይ በከንቱ ይባክናል። አንዳንድ ጊዜ ስጦታችንን በመሳት ለማፍሰስ የቁጥርን ብዛት በመመልከት ቦታን እናማርጣለን። ሌላ ጊዜ ደግሞ ብዙ ችግር የሌለበትን ሁኔታና ስፍራ መምረጥ ይቀናናል። ነገር ግን መጨረሻው ያማረ

አገልግሎት ለማገልገል ከፈለግህ፥ ጌታ የሚመራህን ስፍራ እንዲያሳይህ ዕድል ልትሰጠው ያስፈልጋል።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አንድ ውስጥ እንደተገለጠው፥ ሐዋርያት አገልግሎታቸውን በጀመሩበት ወቅት በቅድሚያ የተጋፈጡት የጌታን ፈቃድ የማወቅን ችግር ነበር። ሐዋርያት ካሳለፉት ሁኔታ የምንማራቸው እውነቶች አሉን። ወደ አገልግሎት ጠልቀን ከመግባታችን በፊት የጌታን ምሪት አስመልክቶ ልናስተውላቸው የሚገቡን አስፈላጊ ነጥቦች በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አንድ ውስጥ ተጠቅሰውልናልና እንመልከታቸው።

I. ጌታ እንዲመራህ ጸንተህ ጠብቀው (1፥1–5)።

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት፥ ጌታ ከሞት ከተነሳ በኋላ ሐዋርያትን ሲጎበኝ በነበረበት በአርባው ቀናት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነገራቸው። ደቀ መዛሙርቱ ከተረዱት እውነት የተነሳ ሕይወታቸው በጣሙን የጋለበት ሰዓት ነበርና፥ ሁኔታቸውን ለማረጋጋትና ኃይልን ሳይቀበሉ እንዳይወጡ ስለፈለገ፦ «አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ» በማለት ሲያረጋጋቸው እናያለን። ሐዋርያት ምንም ዓይነት እርምጃ ከመራመዳቸው በፊት ወደ እውነት ሁሉ የሚመራቸውን መንፈስ ቅዱስን መቀበል ነበረባቸው። ከዚያ በኋላ ነበር ጌታ ለእነርሱ ያዘጋጀውን አገልግሎት ለመረከብ ብቁ የሚሆኑት።

ይህንን፦ «ጌታን መጠበቅ» የሚለውን አሳብ ብዙ ጊዜ ከመስማታችን የተነሳ ችላ ያልነው ቁልፍ ነገር ነው። አገልጋይ ጌታን በመጠበቅ የሚያገኘውን ምስጢር በምንም ዓይነት መንገድ ሊያገኘው አይችልም። በሰውና በሁኔታዎች የምትመራ ፍሬ ቢስ አገልጋይ እንዳትሆን፥ በሕይወትህ ጌታን ከመጠበቅ አትቦዝን።

የጌታ ኃይል በመላት ወረደብህ፥ ጌታም በአገልግሎትህ ያለውን ዓላማ ገለጠልህ፥ ደግሞ ደጋግሞ አረጋገጠልህ ማለት፥ ነገ ተነስተህ ለአገልግሎት ውጣ ማለት ላይሆን ይችላል። እንዴት፥ መቼና፥ የት የሚሉት ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው። እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ከፈለግህ ደግሞ፥ ጌታን መጠበቅ መማር አለብህ። በቂ ዝግጅት ሳታደርግ ለአገልግሎት እንደመውጣት አደገኛ ነገር የለም። በጌታ

ፊት በጸሎት እየተጋህ በመጠበቅህ ግን የእግዚአብሔር ኃይል በሕይወትህ ውስጥ ከማለፉም በላይ አንተም ጌታ በፈቀደልህ የዝግጅትና የትምህርት ዘመን ውስጥ ለስልስህ ታልፋለህ። የጌታ ኃይል በሕይወትህ ውስጥ ማለፉ ሥራውን በመሥራት ፍሬ እንድታፈራ ሲያደርግህ፥ ጌታ በፈቀደልህ የዝግጅት ዘመን ውስጥ ማለፍህ ደግሞ ትከሻህን አስፍቶ በመከራ እንድትጸና ያደርግሃል።

ጌታ የተናገረህ የተስፋ ቃል በዙሪያህ ከምታያቸው ሁኔታዎች ጋር በፍጹም የማይስማሙ ሲመስልህ፥ ጌታን ጠብቀው። የተስፋ ቃሉ እጅጉን የራቀ ሲመስልህ፥ ጌታን ጠብቀው። አስትንፋስ ያለውና የሌለው ፍጥረት ሁሉ በአንተ ላይ በአንድነት የተነሱብህ ሲመስልህ፥ ጌታን ጠብቀው። መከፈት የሚገባው በር ሲዘጋ፥ መዘጋት የሚገባው ደግሞ ሲከፈት፥ ጌታን ጠብቀው። የሰዎች ሁኔታ ከቀን ወደቀን ጥያቄ ሲፈጥርብህ፥ ጌታም በቤቱም ሆነ በውጭ እንደልባቸው በሚራመዱት ላይ ከቶ የማይፈርድ ሲመስልህ፥ ጠብቀው። ሌላው ቀርቶ ሕይወትህ ደርቆ፥ አገልግሎት ቀርቶ፥ በክርስትናህ መቆም እንኳን ሲያስፈራህ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ በፍጹም አይተውህምና ጸንተህ ጠብቀው።



ጌታ የፈቀደውን እስከሚያደርግ ድረስ እጠብቀዋለሁ በሚል ሳቢያ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ሳያደርጉ መቀመጥ የእንቅልፍ መጫወቻ መሆን ነው። በሌላው አንጻር ደግሞ፦ «እግዚአብሔር የሚረዱትን ነው የሚረዳው» በሚለው ምንጩ በማይታወቅ አጉል አምነት ተይዘን ስንለፋ ብንውል ከከንቱ ድካም አናልፍም። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ለእግዚአብሔር መንፈስ ልብህን በመክፈት ፍጹም የሆነውን ፈቃዱን ስትጠብቅ ሳለህ፥ ጌታ በጊዜው በእጅህ ያስጨበጠህን የአገልግሎት ሃላፊነት በታማኝነት ለመወጣት ከመትጋት ወደ ኋላ አትበል። ጌታን መጠበቅ መልካም ነው። ነገር ግን በመጠበቅ ዘመን እግዚአብሔር በፊታችን ያስቀመጠልንን የሥራ መስክ ማስተዋልና መጠቀምም የዚያንው ያህል አስፈላጊ ነገር ነው።

II. ጌታ እንዲመራህ ከተፈቀደልህ አትለፍ (1፥6–14)።

ደቀ መዛሙርቱ ይህን ያህል ከክርስቶስ ጋር ሲያሳልፉ እስካሁን ድረስ የእርሱ ተቀዳሚ ዓላማ ሙሉ ለሙሉ የገባቸው አይመስልም። በሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው የቀደምትነትን ስፍራ መያዝ የሚገባው ነገር ምን እንደሆነ ተዘበራርቆባቸው ነበር። ለዚህ ነው፦ «ጌታ ሆይ፥ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን?» በማለት የነገውን ለማወቅ ሲጠይቁ የሚገኙት። ኢየሱስም፦ «አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም» በማለት አሳባቸውን ወደ አስፈላጊው ነገር ሲመልሰው ይታያል። አስፈላጊው ነገር የእነርሱ በጌታ ፊት በመገዛት መቆየታቸው ሲሆን፥ በዚያን ጊዜ ጌታ ያሻውን ያደርጋል።

ሰው በተፈጥሮው የነገውን ለማወቅ የመጓጓት ባህሪይ ይታይበታል። ከዚያም በላይ አልፎ በሌላው ልብ ውስጥ ያለውን ቢያውቅ ደግሞ ደስታው ነው። ዛሬ በዓለማችን ያለው በጥንቆላና በተለያዩ እርኩሳን መናፍስት አማካኝነት የሚደረገው እንቅስቃሴ ይህንኑ የሚያሳይ ነው። የተቀናቃኙን ሁኔታ አስቀድሞ ለማወቅና አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ከሚጥር አምባ ገነን አንስቶ በጎረቤቱ ላይ በቅንአት እስከሚያሸምቅ ተራ ዜጋ ድረስ ከእርሱ በላይ ኃይል ያለውን እርኩስ መንፈስ ፍለጋ የማያደርገው ጥረት የለም።

ለመሆኑ አንድ አገልጋይ ምሪትን ፍለጋ ሁሉን ወደሚመረምር ወደ አምላኩ ሲቀርብ የመነሻ አሳቡ ምን መሆን ነው ያለበት? ማስቀደም ያለበትስ ነገር ምንድን ነው? ወደ እግዚአብሔር ፊት የምንቀርብበት ብቸኛ ዓላማ እርሱን ለማምለክና ለመገዛት መሆን አለበት። እኛ በሙሉ ልባችን ለጌታ በምንገዛበት ጊዜ ጌታ ለእኛ ሊገልጥ የፈለገውን ከመግለጥ ምንም የሚከለክለው ኃይል የለም። የዘወትር ትኩረታችንና ሩጫችን ጌታን ሳይሆን መገለጥንና ትንቢትን ፍለጋ ከሆነ፥ ከአምላካችን ጋር ያለን ግንኙነት የማያምኑት ከአምላካቸው ከዚህ ዓለም ገዢ ጋር ካለው ግንኙነት ጋር ይመሳሰልብናል።

አገልጋይ ሆይ፥ በዚህ አሳብ ላይ የበለጠ ማስተዋል ይኖርህ ዘንድ ይገባል። ዓለማውያን ወደ መናፍስት የሚሄዱበት ብቸኛ ዓላማ

መገለጥን ፍለጋ ነው። እንዲያውም መስማት የሚያስፈልጋቸው ነገር ከሌለ ስብሰባም የለም፥ ቢኖርም አሰልቺ ነው። ባጭሩ፥ ምንም ዓይነት የፍቅርና የመገዛት ሕብረት አይታይም። ብዙ ጊዜ እነዚህ ሰዎች ከልብ የሚደርስ ነገር ለመስማት ከቦታ ወደ ቦታ ሲቅበዘበዙ ይታያሉ። ከዚህ ዓይነት መንፈስ ተጠበቅ። አንተም ሆንክ ወገኖችህ ወደተፈራውና የአማልክት አምላክ ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር ስትቀርቡ ዋነኛ ዓላማችሁ አምልኮና መገዛት ይሁን። ልዑሉ እግዚአብሔር መናገር የፈለገውን ይናገር፥ ማድረግ የፈለገውን ደግሞ ያድርግ።

ከጌታ ምሪትን የሚፈልግ አገልጋይ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች የጻፈውን መልእክት በሚገባ የተገነዘበ መሆን አለበት። «የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነውን ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ» (ሮሜ 12፥2)። የምሪት ሕይወት ማለት የተለወጠ ሕይወት ማለት ነው። ለመለወጥ ደግሞ በቃሉ መተከል አለብን። በመጀመሪያ በቃሉ ሳንተከል ለተለያዩ መንፈሳዊ ምስጢራት ስንሯሯጥ በብዙ ስህተት ራሳችንንና ሌሎችን እንወጋለን።



አንዳንዶች ከትንቢት ሁሉ የጸናውን የእግዚአብሔርን ቃል ቸል ብለው ዓይናቸውንና ጆሮአቸውን «ለመገለጥና ለመንፈሳዊ ምስጢራት» ብቻ ከፍተው ይታያሉ። ሌሎች ደግሞ ጌታ ለባሪያዎቹ በመንፈስ ቅዱሱ አማካኝነት ሊያሳይ የሚችለውን የመገለጡን ኃይል ከደው ቃልን ከቃል ጋር ሲያጋጩ ይገኛሉ። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። መሰረትህን አጥብቀህ በቃሉ ላይ እየተከልክና ነገርን ሁሉ በቃሉ እየፈተንክ ለመንፈስ ቅዱስ ክፍት ሆነህ ተገኝ።

III. ጌታ እንዲመራህ በመንፈስ ቅዱስ ተደገፍ (1፥15–26)።

እነ ጴጥሮስ ማትያስን ለመምረጥ የተጠቀመባት ዕጣ የመጣጣል ዘዴ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሲጠቀምበት የነበረ፥ በአይሁድ ዘንድ የታወቀ መንገድ ነበር (ምሳ. 16፥33)። መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ልብ ውስጥ በሚኖርበትና በሚናገርበት በዚህ በአዲስ ኪዳን ዘመን

ይህ ዓይነቱ ልምምድ ብቁና አስተማማኝ ለመሆኑ ያልተመሰከረለት መንገድ ነው። ሐዋርያት ይህንን ምርጫ ባከናወኑበት ወቅት ገና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አልተመሰረተችም ነበር። ስለዚህም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያውቁ ዘንድ ሊያግዛቸው የሚችለው መንፈስ ቅዱስ አልወረደላቸውም ነበር። የብሉይ ኪዳን ዘመን አልፎ የአዲስ ኪዳን ዘመን የገባው መንፈስ ቅዱስ በወረደበት በበዓለ ኀምሳ ዕለት ነበር (የሐዋ. 2)። ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በአማኞች ልብ ማደር ከጀመረበት ከዚያ ዕለት አንስቶ፥ በዕጣ መጣጣልም ሆነ ምልክትን በመጠየቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ እንደሚቻል ሐዋርያት በልምምዳቸውም ሆነ በትምህርታቸው ሲገልጹ አይታዩም።

ይህ ክፍል አገልጋይ በአገልግሎቱ ዘመን ሁሉ የማይለየውን አንድ አስቸጋሪ ነገር እንዲያስታውስ ያደርገዋል። አንድ አገልጋይ ከክፉና ከመልካም ነገሮች መካከል እንዱን መምረጥ በሚኖርበት ጊዜ መልካሙን መምረጥ እንደሚገባው ለማወቅ አማካሪ አያስፈልገውም። ነገር ግን ከሁለት መልካም ነገሮች መካከል አንዱን መምረጥ የሚገባው ጊዜና የትኛው የጌታ ፈቃድ እንደሆነ ማወቅ የሚሳነው ጊዜ እድሜውን ሙሉ እንደተከተለው ይኖራል። ለሐዋርያት በዮሴፍና በማትያስ መካከል መምረጥ አስቸጋሪ እንደ ነበር፥ በአገልጋይም ሕይወት ውስጥ «ዮሴፎችና ማትያሶች» ዘወትር ከያሉበት ብቅ እያሉ በውሳኔና በምርጫ ሽለቆ ውስጥ እንደሚጥሉት መዘንጋት የለበትም። አንዳንድ ጊዜ አገልጋይ የሚመርጣቸው ምርጫዎች የሕይወቱንና የአገልግሎቱን መሠረት የሚያናጉ ሊሆኑ ይችላሉና ታላቅ ጥንቃቄ ሊወስድ ይገባዋል።

በአዲስ ኪዳን በተሰጠን የተሻለ ዕድል መሠረት፥ መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራን ተረጋግጦልናል (ዮሐ. 16፥13)። ይህንን የጸና የተስፋ ቃል ችል ብሎ በምልክት ብቻ ከጌታ ምሪትን ለመቀበል የሚሻ አገልጋይ በጌታ ፊት ወድቆና ጊዜን ወስዶ ምሪትን ለመቀበል በቂ ሥርአትንና ትጋትን አለማዳበሩን ያሳያል። «ጌታ ሆይ፥ ይህ ነገር ፈቃድህ ከሆነ፥ ያኛውን ነገር እንደዚያ ብታደርገው በዚያ እውቃለሁ»፤ «ፈቃድህ ከሆነ በሩን ከፈተው፥ አለበለዚያ በሩ ይዘጋ» የሚሉትና የመሳሰሉት አነጋገሮች ታላቅ ጥንቃቄ የሚጠይቁ ጉዳዮች ናቸው። የክርስቶስ መንፈስ በልቡ የሞላ አገልጋይ በምልክት

ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሪትን የተቀበለ በሚመስለው ጊዜ ሁሉ ማረጋገጫን ከመንፈስ ቅዱስ ሳይቀበል ከመራመድ መቆጠብ አለበት።



ብዙዎች ያዩት ምልክትና የተከፈተ በር ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው ብለው ስለሚያምኑ ምንም ዓይነት ማረጋገጫን ከመንፈስ ቅዱስ ሳይቀበሉ ሰተት ብለው ይገባሉ። ሌሎች ደግሞ ጌታ በሁኔታዎች በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሊናገራቸው ሲሻ ከሰማይ ተአምራትን በመጠበቅ የዛሉም አሉ። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። በዙሪያህ ያሉትን ሁኔታዎች ሁሉ ጌታ ሊጠቀምባቸው እንደሚችል አትዘንጋ፤ ነገር ግን ከመንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫን ሳትቀበል ከመራመድ ተቆጠብ።

የእግዚአብሔር ምሪት እንዲህ ነው ብሎ መርምሮና ዘርዝሮ ማንም ማንንም ለማስተማር ያስቸግረዋል ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም የጌታ ፈቃድ ተፈትኖ የሚታወቅ እውነት ስለሆነ ነው። ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ከቃሉ በተማርነው መሰረት መውሰድ የሚገባንን ጥንቃቄ መመካከር እጅግ ይጠቅመናል። ስለዚህ፥ አገልጋይ የጌታን ፈቃድ ለመለየት በሚኖረው የማያቋርጥ ጉዞ የሚጠቅሙትን ሦስት ነጥቦች ጠቅሼ አልፋለሁ።

ከጌታ ያልሆነ ነገር ወደ አንተ በሚመጣበት ጊዜ የሚከተሉትን ምልክቶች ታያለህ።

1) ነገሩን በምስጢር እንድታደርገው ይገፋፋሃል። አገልጋይ ሆይ፥ ከሰማይም ተገለጠ በሰውም በኩል መጣ፦ «ይህንን ነገር ለማንም ሳታሳውቅ በድብቅ አድርገው» የሚል ምክር ያዘለ ማንኛውም ነገር ወደ አንተ በሚመጣበት ወቅት ተጠንቀቅ። የምታደርጋቸውን ነገሮችና የምትወስናቸውን ውሳኔዎች ጌታ ማስተዋልን ለሰጣቸውና ለቀባቸው አገልጋዮች እንዲሁም እህቶችና ወንድሞችህ ብታማክራቸው ከተሳሳተ መንገድ ሊመልሱህ እንደሚችሉ ጠላትህ ሰይጣን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ በድብቅ እንድትይዘው ይመክርሃል። አንተ ግን ንቃበት። በሕይወትህ ለምታደርጋቸው ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ታማክረው ዘንድ ታማኝና እውነተኛ የሆነን የእግዚአብሔርን ሰው ከጎንህ አታርቅ።

2) ነገሩን በአስቸኳይ እንድታደርገው ይገፋፋሃል። እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ በእቅድ የሚሠራ አምላክ ሆኖ ሳለ፥ ነፍስህ እስክትጠነቅ

ድረስ አቻኩሎ በንጹህ ልቦናና በተረጋጋ መንፈስ ያልጸለይክበት ነገር ውስጥ እያስገባህም። ጌታ በዚህ መንገድ በፍጹም አይሠራም ብሎ መደምደም ባይቻልም፥ አገልጋዮቹ በተረጋጋ ሁኔታ በፊቱ ጊዜን ወስደውና በጽሞና ሁኔታዎችን ያከናውኑ ዘንድ ፈቃዱ ነው። አንዳንዶች በሥጋቸው ቸኩለውና መውጣት የማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ገብተው ነገሮች እንደተዘበራረቀባቸው ላስታውስህ እወዳለሁ። ዘወትር ምንም ነገር ከማድረግህ በፊት በቂ ጊዜን ውሰድ።

3) ነገሩን ለማድረግ ባሰብክ ጊዜ ሰላም ይርቅሃል። ይህን እውነት ብዙዎቻችን የምናውቀው በመሆኑ ብዙ ጊዜ ላላጠፋ አንድን ነገር ላስታውስህ እወዳለሁ። በውስጥህ ሰላምን እያጣህና እየተረበሽክ «ጆሮ ዳባ ልበስ» ብለህ ከመራመድ ተጠበቅ። አንዳንድ ጊዜ ፍላጎታችን ያሸንፍና ሰላም ማጣት ቀርቶ መልእክ ሰይፍ ይዞ በፊታችን ቢቆምም እንኳ የማንመለስበት ጊዜ እንዳለ አትዘንጋ።

2

የመንፈስ ቅዱስ መገኘት

ምዕራፍ 2፥1–47



ሐዋርያት ክርስቶስ ኢየሱስ የገባውን ተስፋ በመጠበቅ ላይ እንዳሉ፥ በበዓለ ኀምሳ ዕለት በድንገት ሰማያት ተከፈቱ። የተሰበሰቡትም 120 ደቀ መዛሙርት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በልሳን በመናገር ከተማውን አስገረሙ። ይህ በዓል በዘሌዋውያን ምዕራፍ ሃያ ሦስት ውስጥ የተገለጸ መለኮታዊ እቅድ ነው። በተጠቀሰው ምዕራፍ ውስጥ የተገለጹትን ዓመታዊ በዓላት ለመዘርዘር ሰፊ ጊዜን የሚወስድ በመሆኑና ከዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ጋር አብሮ ስለማይሄድ በጥቂቱ ጠቅሼአቸው አልፋለሁ። ከተጠቀሱት በዓላት መካከል የመጀመሪያው ፋሲካ ሲሆን፥ እርሱም የሚያመለክተው ለእስራኤላውያን የተሰጣቸውን አዲስ ጅማሬ ነው። ያም ፋሲካችን የሆነው የክርስቶስ አምላል ነው (1ቆሮ. 5፥7)። ሁለተኛው በዓል ለሰባት ቀናት የሚቆየው (እርሾ ያልነካው) የቂጣ በዓል ሲሆን፥ እርሱም የእማኝ ክርኩሰት የመለየት ወይም የቅድስና ሕይወት እምላል ነው (1ቆሮ. 5፥6–8)። ሦስተኛው በዓል የክርስቶስ ትንሳኤ እምላል የሆነው የበኩራት በዓል ነው (ዮሐ. 12፥24 ፤ 1ቆሮ. 15፥23)። ይህ የበኩራት በዓል ከተከናወነ ከኀምሳ ቀናት በኋላ ነበር የበዓለ ኀምሳ የሚከተለው። የዚህም በዓል አስገራሚ አምላል ይህ ነው። የክርስቶስ ትንሳኤ እምላል የሆነው የክበኩራት በዓል ከተከናወነ ከኀምሳ ቀናት በኋላ የበዓለ ኀምሳ ቀን እንደሚውል ሁሉ ክርስቶስ ከተነሳ በኀምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ ወረደ።

የመንፈስ ቅዱስ መምጣት በድምጽ፥ በእሳትና፥ በልሳን ነበር የተገለጸው። ተናጋሪዎቹ የሚናገሩትን ቋንቋ ባያውቁትም፥ በዓሉን ለማክበር ከዓለም ዙሪያ የተሰበሰቡት ሕዝብ በሚገባ ይረዱት ነበር። ይህ ቀን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተችበት ቀን ነው። የክርስቶስ አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ መውረድ እንደተረጋገጠ ሁሉ

(ማቴ. 3፥ 16)፥ የቤተ ክርስቲያንም ጅማሬ በመንፈስ ቅዱስ መውረድ ተረጋገጠ።

በዚያን ወቅት ይህንን መንፈስ ቅዱስ ያዘጋጀለትን ዕድል በመጠቀም ጴጥሮስ ወንጌልን ጥርት ባለ ሁኔታ ሰበከ። በመጀመሪያ፥ ለተሰበሰቡት ሰዎች ይህ ያዩትና የሰሙት ነገር ሊቃሉ ታማኝ የሆነው እግዚአብሔር በነብዩ ኢዩኤል የተናገረውን መፈጸሙ እንደሆነ ከገለጸ በኋላ፥ በመቀጠልም የዳዊትን መዝሙር በማስታከክ የሞተውንና ከሙታን የተነሳውን ኢየሱስን አብ ከሞት እንዳስነሳው ተረከላቸው። መዝሙረኛው ዳዊት ሞቶአል፥ ወደ ሰማይም አላረገም፥ ስለዚህም መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ አስራ ስድስት የሚናገረው ስለሌላ ሰው መሆን አለበት። ይህም ሰው እምላክ የሆነው ክርስቶስ ነው። በርግጥም ይህንን መቃብርን ፈንቅሎ የተነሳውን ክርስቶስን የሚመስል ማንም የለም።

የጴጥሮስ የስብከቱ ውጤት አስገራሚ ነበር። ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ከመዳኑም በላይ፥ ያመኑት በአንድነት ይተጉ ነበር።



አንድ ክርስቲያን፦ «በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም» (ዘካ. 4፥ 6) የሚለውን የተስፋ ቃል ዘንግቶ በራሱ ጥበብና ብርታት በሚመካበት ጊዜ፥ ነገር ይበላሻል። በአገልግሎታችን ውስጥ ጌታ በሙላት እንዲሠራ፥ የመንፈስ ቅዱስ መገኘት አማራጭ የሌለው ብቸኛ መንገድ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በተለያየ መንገድ ባለማስተዋል ልናጨናግፈው እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ፥ በመንፈሳዊ ሕይወታችንና በአገልግሎታችን ከመደንዘዛችን የተነሳ ባለማስተዋል በዘልማድ በምናደርጋቸው ድግግሞሾች ረክተን እንመላለሳለን። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፥ ውጤታማ የሆነን አዲስ መንገድ ጌታ ሊያለማምደን ሲሞክር በግትርነት እንቋቋመዋለን። እንዲያውም፥ እነዚያን አዳዲስ መንገዶች ለማምጣት ጌታ የተጠቀመባቸውን ሰዎች ስናሳድዳቸው እንገኛለን። ሌላ ጊዜ ደግሞ የአገልግሎት ስኬት መመዘኛው ይበላሽብንና የመንፈስ ቅዱስን ሥራ የሚመስሉ፥ ነገር ግን በፍጹም የጌታ እጅ የሌለባቸውን ብዙ ነገሮች አብዝተን ስንለማመድ እንገኛለን። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊነታቸው ያልተረጋገጠላቸው፥ ነገር ግን በጊዜው

ላለንበት ሁኔታና ጊዜአዊ ስሜታችን አመቺ የሆኑ ልምምዶች እናበዛለን።

አገልጋይ ሆይ፥ ከእንደዚህ ዓይነት ሕይወት ተጠበቅ። ከሁሉ በፊት በምታደርገው ነገር ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ እጅ እንዳለበትና እንደሌለበት ለመለየት ትጋ። የአገልግሎትህ ውጤቱ የሚለካው በምታደርጋቸው ነገሮችና በምታላያቸው ሁኔታዎች ላይሆን በሕይወትህ በሚገለጸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ እንደሆነ አትዘንጋ። መንፈስ ቅዱስ በአገልግሎትህ እየሠራ መሆኑንና አለመሆኑን ለማወቅ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ሊረዱህ ይችላሉ።

I. መንፈስ ቅዱስ ነፍሳትን ይሰበስባል (2፥ 1–13)።

ደቀ መዛሙርቱ በአንድ ልብ ሆነው ሲጸልዩባት በነበረችው በዚያች የተባረከች ዕለት፥ የጌታ መንፈስ ቅዱስ መገኘት ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት ሞላው። የመገኘቱ ሙላት ምን ያህል ለውጥ በቀሪው አገልግሎታቸው ላይ እንደሚያመጣ በጊዜው ባይገነዘቡትም፥ ብዙም ሳይቆዩ የጅማሬውን ጣዕም ቀመሱት። ይኸውም የመጀመሪያ ምልክት የሰዎች ከየቦታው መከማቸት ነበር። ሕዝቡ በኢየሩሳሌም ከተማ የተሰበሰቡበት ዋና ምክንያት በዓሉን ሰማክበር ቢሆንም፥ ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት አካባቢ ተሰበው መከማቸታቸው መንፈስ ቅዱስ በመውረዱ በተደረገው ምልክት ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው። ያስገርማል! በዚያ ስፍራ መሰብሰባቸውን በተለያየ የዜና ማሰራጫ አላስተዋወቁም ነበር። በየቦታውም እየዞሩ ኑ ተሰብሰቡልን አላሉም። መንፈስ ቅዱስ በመካከላቸው በመገኘቱ ምክንያት ከተደረገው አዲስ ነገር የተነሳ በዓሉ ጎምላን ለማክበር የተሰበሰቡ ሰዎች ከያሉበት ተከማቹ። «ይህ ድምፅ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ» (ቁ. 6) ከሚለው የሉቃስ አገላለጽ መንፈስ ቅዱስ ሕዝብን የመላብ የራሱ የሆነ መንገድ እንዳለው እንገነዘባለን።

የእግዚአብሔር ጥሪ በሕይወቱ ያለበት አገልጋይ በውስጡ ዘወትር የአገልግሎቱ መላካት ጉዳይ መመላለሱ አይቀርም። ይህ ጥማት የከበረ ሆኖ ላለ፥ ከዚያ ጥማት የተነሳ ነፍሳትን ለመሰብሰብ ሲል የራሱን ጥበብ ብቻ በመጠቀም ከመንፈስ ቅዱስ መገኘት የተነሳ ብቻ

ሊመጣ የሚችለውን ውጤት እንዳይዘነጋ ጥንቃቄ ያሻዋል። እንደ መንፈስ ቅዱስ ነፍሳትን ወደ አገልግሎታችን ሊስብ የሚችል ምንም ኃይል በዓለም ላይ አይገኝም። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሥራ ዓይተው ከሚገረሙት፥ ከሚጠራጠሩትና፥ ከሚያፌዙት ሁሉ ወደ አገልግሎታችን የመሳብ ኃይል አለው። ከእርሱ መገኘት ተለይቶ ማንኛውም አገልግሎት ባዶ ነው። ጌታ መንፈስ ቅዱስ ግን ተገቢውን ቦታ ቢይዝ፥ አገልጋይ ለሚኖረው የአገልግሎት በርና ስኬት ወሰን የለውም።



መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው ወደ አገልግሎታችን ነፍሳትን የሚስበው በሚል እንከን በማይወጣለት እምነት ያለአግባብ ተወስደን ነፍሳትን ለመድረስ ምንም ዓይነት እቅድ ሳናወጣና ሳንንቀሳቀስ በራችንን ዘግተን መቀመጥ ጊዜ ማባከን ነው። በሌላው አንጻር ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ ችላ ብለን እኛ ካልሮጥን ምንም ነገር የማይሠራ ከመሰለን እቅድን ከእቅድ ጋር ስናጋጭ እንደክማለን። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። እቅድም ለማውጣት የመንፈስ ቅዱስ ጥበብና ምሪት እንደሚያስፈልግ አትዘነጋ። ቁም ነገሩ እቅድ ማውጣትህና አለማውጣትህ ሳይሆን በምታደርገው ነገር ሁሉ ጌታ መቅደሙ ነው። የጌታ ድርሻ ባሪያዎቹን መምራት ሲሆን፥ የአገልጋዮቹ ድርሻ ደግሞ እግዚአብሔር በሰጣቸው ማንኛውም ነገር ተጠቅመው ለክብሩ መሮጥ ነው።

II. *መንፈስ ቅዱስ መልእክትን ይሰጣል* (2፥14–36)።

በአንዲት ገረድ ፊት እውነትን መናገር ተስኖት የነበረው ጴጥሮስ በበዓለ ኀምሳ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና መገኘት ታጅቦ በሚያስገርም ግልጽነት የወንጌልን እውነት ሰበከ። ሆኖም፥ ቁም ነገሩ ግልጽነቱ ላይ ብቻ አልነበረም። የሰብኩቱም ፍሬ ነገርና ይዘት አስፈላጊነት ነበረው፤ ንጹህና ያልተሸቃቀጠ ወንጌል ነበር የተሰበከው።

ያለንበት ዘመን የአገልግሎት ስኬት በሰው ቁጥር ብቻ የሚለካበት ክፉ ዘመን በመሆኑ፥ ከሰዎች ልብ ዘልቆ የሚገባን መልእክት ላለማስተላለፍ ብዙ ምክንያቶች ሲሰጡ ይሰማል። ሁሉንም ለማቀፍና ለማስደሰት ከምናደርገው ጥረት የተነሳ ወንጌልን መሸፋፈንና

የወንጌልን ገሚስ ገጽታ ማንጸባረቅ እደገኛ ተግባር ነው። ሰዎች በመልእክታችን ተሰናክለው እንዳይርቁና ቁጥር እንዳይቀንስ በመልእክታችን ማባበልም ከዚያው ያላነሰ ጥፋት ነው።

በአገልግሎትህ መተላለፍ የሚገባውን መልእክት ማነው የሚወስነው? በመንፈስ ቅዱስ ተመርተህ ከጌታ ትቀበላለህ ወይስ እንደየሁኔታው ትለዋወጣለህ? እውነትን በግልጽነት ብታስተላልፍ ሰዎች ከአገልግሎትህ የሚርቁ ይመስልሃል? የጌታህን ወንጌል ለማሰራጨት ስትወጣ፥ ሰዎች መልእክትህን ሰምተው ሊሰጡት የሚችሉትን ምላሽ እያነጻጸርክ ከሆነ የምትዘጋጀው፥ መልእክትህን የተቀበልከው ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከሁኔታዎች ነው። ምናልባት በዚህ በመጨረሻው ዘመን፥ መስማት የሚፈልጉትን ብቻ ይነግሯቸው ዘንድ ለራሳቸው አስተማሪዎችን ማከማቸት የሚሹ ሰዎች አንተንም እንዳይመለምሉህ ተጠንቀቅ። ኃጢአትን በስሙ ጠርተህ ከመናገር እትቆጠብ። መጽናናት የሚያስፈልገውን ከማጽናናት፥ መገሰጽ የሚያስፈልገውን በፍቅር ከመገሰጽ፥ መመከር የሚያስፈልገውን ደግሞ ከመምከር ምንም ሁኔታ አይከልክልህ። ከሁሉ በላይ፥ በየጊዜው ከሚመጡ አዳዲስ ትምህርቶች ራስህን በመጠበቅ የክርስቶስን ሞት፥ ትንሳኤና፥ ዳግም ምጽአት መናገርን በፍጹም አትተው። ይህንን ብታደርግ፥ የሰዎችን ዓይን በመስቀሉ ላይ እንዲተክል ከማድረግህም በላይ፥ ጌታህ በእንተ ደስ ይለኛል። አስተውል፥ ዘመኑ የተሰያዩ «ወንጌሎች» ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልከው የገቡበትና ወንጌል ለተሰያየ ዓላማ ማስፈጸሚያ እንዲሆን የሚሰበክበት ዘመን ነው።



እንዳንዶች ከጌታ የሆነን መልእክት ማምጣት ማለት በፍጹም ምንም ዓይነት ዝግጅት ሳያደርጉ በጌታ ብቻ ተማምኖ በሰአቱና በቦታው መገኘት ብቻ ነው ብለው ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ ለጌታ እድልን ሳይሰጡ በአእምሮአቸው የማያወጡትና የማያወርዱት መልእክት የለም። እንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ቃሉን ለማሰራጨት ከመውጣትህ በፊት በቂ ጊዜን ከጌታ ጋር መውሰድን የዘወትር ተግባርህ እድርግ። ጌታን ግን በዚያ ብቻ አትወስነው። በፍጹም ባልተዘጋጀህበት ወቅትና ቦታም በድንቅ ሁኔታ ሰማያዊ መልእክቱን ለማስተላለፍ ሊጠቀምብህ ይችላልና ዘወትር የተዘጋጀህ ሁን።

III. መንፈስ ቅዱስ ነፍሳትን ይነካል (2፥37–47)።

የሐዋርያት የአገልግሎት ፍሬ የታየው በሁለት መልኩ ነበር። በመጀመሪያ ደረጃ ነፍሳት ተጨመሩ (ቁ. 41)። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ያመኑት በቃሉ እየታነጹ በአንድነት ይተጉ ነበር (ቁ. 42)። እውነተኛ የአገልግሎት ፍሬ ማለት ይህ ነው።

በአገልግሎትህ ውጤታማነትህን የምትለካው በምንድነው? አንዳንዶች አገልግሎታቸውን የሚመዝኑት በቁጥር ብዛትና በሆታ ብዛት ሲሆን፥ ሌሎች ደግሞ የተቀባ አገልጋይ ነው ብለው የሚያምኑት ሰው ያደረገውን ነገር ማድረግ ሲቀናላቸው አገልግሎታቸው የተባረከ ይመስላቸዋል። ስማቸው በብዙ ቦታ እየታወቀ ሲሄድ አገልግሎታቸው ያደገ የሚመስላቸውም አሉ። በጣም የሚገርመው ነገር፥ ከላይ በጠቀስናቸው መለኪያዎች ተለክቶ ምንም ጉድለት የለበትም የሚባል አገልጋይ ራሱን ከጌታ ሥራ በጣም ርቆ ሊያገኘው መቻሉ ነው።

ምንም ዓይነት ስጦታ ይኑርህ፥ በብዙም ሰዎች ታውቀህ ዝናህ ይውጣ፥ እንዲያውም በዓለም ትልቅ የተባለውን አገልግሎት መስርት፥ አገልግሎትህ የቆመው ነፍሳትን ለማዳንና የዳኑትም በቃሉ እውነት ለማነጽ ካልሆነ፥ የሰራኸውን አፍርሰህ እንደገና መሰረትን ብትጥል ይቀልሃል። እውነተኛ አገልግሎት የሚከናወነው በአገልግሎትህ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ተገቢውን ስፍራ ሲይዝ ብቻ ነው።



አንዳንዶቻችን በሰው በቁጥር ብዛት የአገልግሎታችንን ፍሬአማነት እየለካን ከልክ ያለፈ ውድድር ውስጥ ገብተናል። ስለሆነም የሰዎች ቁጥር ይብዛልን እንጂ ስለ ሕይወታቸው መለወጥና በቃሉ መታነጽ ብዙም ግድ አይለንም። ሌሎቻችን ደግሞ የሰዎችን ሕይወት ጌታ እንዲለውጥ ጊዜን መስጠትና ተገቢውን ነገር ማድረግ ጠፍቶብን ከክርስቶስ ጸጋ ውጪ ሊሸከሙት የማይችሉትን ቀንበር እንጭንባቸዋለን። እንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። የሰዎችን መከማቸት ብቻ ስታሳድድ ከልብ የማይደርስና ለአክሊል የማይበቃ አገልግሎት ውስጥ ራስህን እንዳታገኘው ተጠንቀቅ። ነገር ግን በአደራነት የተቀበልካቸውን ነፍሳት የራስህንም ሆነ የእነርሱን ፍላጎት

ሳይሆን የጌታን ጤናማ ቃል እየመገብክ ታምነህ ቁም። እውነትን የሚሻና አብ የተከለው ከእንተ ጋር ይቆማል።

የመንፈስ ቅዱስን ስፍራ ቀምተህ በጌታ ስም የራስህን ሥራ ከመስራት ለመጠንቀቅ፥ የሚከተሉትን ነጥቦች እስተውላቸው። ያን ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን የሚመስለው አስመሳይ ሥራ ይወጣና እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ይተካል።

1) እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ድምጽ በአገልግሎታችን ይሰማ ዘንድ፥ ማንኛውም ከጌታ ያልሆነ ትንቢትና መገለጥ መቆም አለበት። ይህ ችግር ብዙዎችን በሙላት እየሠራ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲጠራጠሩ ያደረገ አሳሳቢ ሁኔታ ነው። አገልጋይ እግዚአብሔር ፈጽሞ ያልተናገረውን ነገር በስሙ ከመናገር፥ ወይም ደግሞ እግዚአብሔር በተናገራቸው ነገሮች ላይ የራሱን አሳብ ከማከል መቆጠብ አለበት።

2) በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ብቻ ሳይሆን በሃላፊነት የመጠየቅ ጉዳይ ላይም ማተኮር አለብን። ከጌታ ያልሆነ ነገር ከጌታ እንደመጣ መስሎ በሚቀርብበት ጊዜ አገልጋዮች በፍቅር፥ በትህትና፥ በታላቅ ጥንቃቄ ነገሩን የማረም ሃላፊነት አለባቸው። ይህንን እውነት በምንዘነጋበት ጊዜ፥ ጩኸታችን ብዙ፥ የምናከናውናቸው ሥራዎችና ፍሬአችን ግን ባዶ ከመሆኑም በላይ፥ የጌታም ስም እየተናቀ ይሄዳል።

3) ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ቤት ለመሳብ ስንል የወንጌልን እውነት መቀነስ የለብንም። ከብሩን ለሌላ በማይሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ብቻ እንደገፍ። አለበለዚያ፥ እኛም እንደ ዓለማውያን ከውድድር መንፈስ አናመልጥም።

3

ሥፍራህን አትልቀቅ

ምዕራፍ 3–4



በሐዋርያት ሥራ በምዕራፍ ሦስት ውስጥ ስንመለከት፥ አይሁዳዊ የሆነ ሁሉ እንደሚያደርግ፥ ጴጥሮስና ዮሐንስ ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስ ወጡ። አይሁዳውያን በቀን ውስጥ ከነበራቸው ከሦስቱ የጸሎት ልማዶች (ማለዳ፥ ቀትርና፥ ምሽት) ይህ ሁለተኛው ነበር። በዚያም ስፍራ ለመጸለይ ሳይሆን ለመለመን የመጣ አንካሳ ሰው አገኙ። ይህ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ አንካሳ የነበረ ሰው በየዕለቱ በሰዎች እርዳታ ወደ መቅደስ ደጅ በመሄድ የልመና ተግባሩን ያከናውን ነበር። የእነ ጴጥሮስ ይህን አንካሳ ሰው ማግኘት ለተመልካቹም ሆነ ለሰሚው አጋጣሚ ይመስል ይሆናል፥ እግዚአብሔር ግን ለዓላማው ነበር ያንን ያደረገው። ይህም አንካሳ ሰው፦ «ብርና ወርቅ የለኝም ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፥ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሳና ተመላለስ» የሚለውን የጴጥሮስን ድምጽ ሰምቶ በእግሩ ቀጥ ብሎ ቆመ። እግዚአብሔርም ለመጀመሪያ ጊዜ የሐዋርያትን አገልግሎት በተአምራት አጸና። ከተደረገውም ተአምራት የተነሳ አስደናቂ የወንጌል በር ለጴጥሮስ ተከፈተ። በመልእክቱም የእምነትን ኃይልና የክርስቶስን ማንነት ካብራራ በኋላ የንስሐን ጥሪ አደረገ።

ወደ ምዕራፍ አራት ስንሻገር፥ ጴጥሮስና ዮሐንስ የጌታን ሞትና ትንሣኤ ስለሰበኩ ተከሰሰው በወኅኒ ተጥለው እናገኛቸዋለን። በዚያም በግልጽነት ለእምነታቸው ከተከራከሩ በኋላ ተፈትተው ወደ ወገኖቻቸው በመሄድ ነገሩን ሁሉ አጣወቷቸው። በዚያም ስፍራ ከጸለዩ በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ እስኪናወጥና የእግዚአብሔርን ቃል በግልጥነት እስኪናገሩ ድረስ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው። በገንዘብም ሆነ በጸጋ ከጌታ የተቀበሉትን በረከት በአንድነት እየተካፈሉ ይመላለሱ ነበር። በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ነው ሉቃስ ለመጀመሪያ ጊዜ በርናባስን ያስተዋወቀን። ይህ በአጽናኝነቱ የታወቀ

ብሩክ ሰው ያለውን እርሻ «ሽጦ ገንዘቡን አምጥቶ ከሐዋርያት እግር አጠገብ አኖረው» (ቁ. 37)።



የእግዚአብሔርን መለኮታዊ አሠራር ሰው ሊመረምረው አይችልም። ለዚህ ነው ነብዩ ኢሳይያስ፦ «አሳቤ እንደ አሳባችሁ መንገዳችሁም እንደ መንገዴ አይደለምና» (55 ፥ 8) ሲል በእግዚአብሔር ስም የተናገረው። ከዚያም በመቀጠል፦ «ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው» (ቁ. 9) በማለት ያብራራዋል።

የጌታን አሳብና አሠራር በማናስተውልበት ጊዜ፥ እርሱ በሕይወታችን የጀመረውን ሥራ አከናውኖ እስኪጨርስ ድረስ በትዕግስት ባለንበት ስፍራ መቆየት ያስቸግረናል። አንድን ነገር ጀምረን ሳንጨርሰው ወደ ሌላ ነገር እንዘላለን። ከአንድ አገልግሎት ወደ ሌላ አገልግሎት፥ ከአንድ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ስንወጣና ስንገባ እንገኛለን። ስለዚህም፥ ለጌታ ፈጽሞ የማንመች አገልጋዮች እንሆናለን። በራሳችን ግምት ጌታ ይሠራበታል የምንለው መንገድ ብዙ ጊዜ የተሳሳተ ሆኖ ስለምናገኘው፥ ስፍራችንን ለቅቀን ምንም ዓይነት እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት ጌታ ምን ይላል የሚለውን ጥያቄ መመለስ አለብን።

ጌታ ያስቀመጠንን ስፍራ ለመልቀቅ ምንም ዓይነት በቂ ምክንያት ቢኖረንም እንኳ፥ በተረጋጋ መንፈስ በስፍራችን በምንገኝበት ጊዜ በሕይወታችን ድንቅን ማየት እንጀምራለን። ከነጴጥሮስ የምንማረው ይህንን ነው፥ በስፍራችን በመገኘታችን ምክንያት መንፈስ ቅዱስ የሚከተሉት አስፈላጊ በሮች ይከፍትልናል።

I. የተአምራት በር (3፥1–10)።

ጴጥሮስና ዮሐንስ በጸሎት ጊዜ ወደ መቅደስ ሲወጡ የተወያዩትን ማን ያውቃል? ከጥንት ጀምሮ የነበራቸውን ወደ ቤተ መቅደስ የመሄድ ልማድ ለማቋረጥ ብዙ በቂ ምክንያቶች ነበሯቸው። አሁን እኮ እንደድሮው አይደሉም፤ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ተሸጋግረው ወደ አዲስ ኪዳን ዘመን ገብተዋል። ከዚያም አልፎ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው አዲስ ራእይ ተቀብለዋል። ስለዚህም ቀድሞ የነበሩበት

ስፍራ ለመቆየት ብዙም የሚያጓጓ ነገር የላቸውም። ለነጴጥሮስ ግን እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ስፍራቸውን ይለቁ ዘንድ በቂ አልነበሩም። ስለዚህም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገው ተአምራት በእነርሱ እጅ ተከናወነ።

አንዳንድ ጊዜ ጌታ ድንቅንና ተአምራትን ሊያሳየን ወዳስቀመጠን ስፍራ ሲመጣ ያጣናል። ስለዚህም ለረጅም ዘመናት የገነባነውን አገልግሎት ትተን አዲስ ጅማሬን ስናቅድ እንገኛለን። ለብዙ ዘመን ጌታ ለውጥ እንዲያሳየን ስናነባበት የነበርነውን ስፍራ ለቅቀን ወደ ሌላ ጎዳና እናቀናለን። ተአምራት ለማየት ከፈለግን ያለንበት ሁኔታ የማያዛልቅ መስሎ ቢታየንም እንኳ ያስቀመጠን አምላክ እስኪያነሳን ድረስ ተስፋ ሳንቆርጥ መቆየትን መማር አለብን። መቆየት የማያሳየን ተአምራት የለም።



አንዳንዶች የተአምራት ሁሉ ምንጭ የሆነውን ጌታ አረስተው ተአምራትን ብቻ ሲያሳድዱ ይታያሉ። ሌሎች ደግሞ በዘመናችንም ሲሠራ የሚችለውን መለኮታዊ ኃይል ክደው ከዚህ ዓለም ገዢ ጋር በሥጋ ክንድ ይታገላሉ። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ጥሪህ ተአምራትን የማሳደድ ጥሪ ሳይሆን ወንጌልን የመስበክ ጥሪ መሆኑን አትዘንጋ። ነገር ግን አገልግሎትህን ጌታ በተአምራት ሊያጸናው እንደሚፈልግ ሳትዘነጋ የልብህን በር ከመክፈት አትቦዝን።

II. የወንጌል በር (3፥11–4፥22)።

ጴጥሮስ በጌታ ስም የፈወሰው ይህ አንካሳ ሰው በዚያ አካባቢ ወደ ጸሎት የሚሄዱ ሰዎች በሙሉ በሚገባ እንደሚያውቁት አያጠራጥርም። ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ተራምዶ የማያውቅን ፍጥረት የገናናው የኢየሱስ ስም አጽንቶ ሲያቆመው ከማየት የበለጠ ምን ተአምራት አለ? ለዚህም ነው የተደረገውን ነገር የማይወዱ የክርስቶስ ጠላቶች መናገር እስኪሳናቸው ድረስ ድንጋጤ የወረደባቸው። ከዚያም አልፎ፥ ይህ ተአምራት ባይደረግ ኖሮ በፍጹም ለወንጌል በራቸውን የማይከፍቱ ሰዎች የወንጌል ምርኮኞች ሆኑ።

«እምነት ተአምራት ያመጣል እንጂ ተአምራት እምነትን አያመጣም» የሚባለው አነጋገር እውነትነት አለው። ተአምራት እምነትን

አያመጣም ይሆናል፥ ነገር ግን ተአምራት ለእምነት በር ለሆነው ለወንጌል መንገድን የመጥረግ ታላቅ ኃይል አለው። ወንጌላችን ከተአምራት ተለይቶ ባዶ ነው። ተአምራት ደግሞ ከወንጌል ተለይቶ ከንቱ ነው። ተአምራት ካለ ለወንጌል በር አለ። ጌታ በሠራው ተአምራት ምክንያት በተከፈተው የወንጌል በር ተጠቅሞ ተገቢውን ሥራ መሥራት ደግሞ የታማኝ አገልጋይ ምልክቱ ነው። ነገር ግን ሐዋርያት በመከራ ውስጥ ወንጌልን በመስበክ እንደጸኑና በስፍራቸው እንደተገኙ፥ ከእኛም እንዲሁ ይጠበቅብናል። ዘወትር ጌታ በድንቅና በተአምራት ወንጌል እንዲሰበክ በሚፈቅድበት ጊዜ ስደት ይነሳል። አገልጋይ ግን ስፍራውን መልቀቅ የለበትም። «ሥራ የሞላበት ትልቅ በር ተከፍቶልኛልና ተቃዋሚዎችም ብዙ ናቸው» (1ቆሮ. 16 ፥ 9) በማለት በቦታው መገኘት አለበት።

III. የበረከት በር (4 ፥ 22–37) ።

እነ ጴጥሮስ ምንም ተአምራት ከጌታ ባልተቀበሉበት ወቅት እንኳ በስፍራቸው በመቆየታቸው ተአምራት አዩ። በዚያም ምክንያት የተከፈተላቸውን የወንጌል በር እንደሚገባ በመጠቀማቸው ስፍራቸውን ይለቁ ዘንድ ስደት ተፈታትኗቸው ነበር። እነርሱን ግን ይህም አልበገራቸውም። ስለዚህም ታላቅ የበረከት በር ተከፈተላቸው። እንደገና በመንፈስ ቅዱስ መላት ከመታደሳቸውም አልፈው፥ ከመካከላቸው ችግረኛ እስኪጠፋ ድረስ ሕብረት ነበራቸው። በእውነትም ጌታ በመንፈስም በሥጋም ሕዝቡን የሚባርክ አምላክ ነው!

የእግዚአብሔር መንገድና የእኛ መንገድ የሚለያየው እዚህ ላይ ነው። በርን በበር ላይ ይከፍትልን ዘንድ፥ ከሁሉ በፊት ባስቀመጠን ስፍራ ያገኘን ዘንድ ይሻል። በዚያን ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ድንቅና ተአምራት እናያለን። በተአምራት ሕይወት ውስጥ ስንመላለስ በሚነሳው ፈተና ሳንበገር በምንጸናበት ጊዜ ደግሞ የበለጠ የወንጌል በር ሲከፈት እናያለን። ወንጌልን በመስበክ በምንጸናበት ጊዜ ደግሞ ጌታ የበረከትን ሕይወት ሳያሳየን አይተወንም። መቆየት በረከትን ያሳየናል።

እንደተመለከትነው፥ ስፍራችንን አለመልቀቃችን የእግዚአብሔርን እሳብ እንድንፈጽም ያደርገናል። ነገር ግን ከዚያ አልፈን መመለስ

የሚገባን ጥያቄ አለ። ለመሆኑ ለምንድነው አገልጋይ በቀላሉ ስፍራውን የሚለቅቀው? አገልጋይን ከስፍራው የሚነቅሉና የሚያቅበዘብዙትን ስድስት ምክንያቶች እዘረዝራለሁ።

1) በበረከት መጎብኘት። አንዳንድ ጊዜ ጌታ በልዩ በረከት ሲጎበኘን ካለንበት ስፍራ፥ አገልግሎትም ሆነ ቤተ ክርስቲያን መልቀቅና አዲስ ነገር መጀመር ያለብን ይመስለናል። ካላስተዋልን በድንገት ከሁሉ የበለጥን ልዩ ሰዎች የሆንን ይመስለንና ካለንበት ስፍራ ወጥተን በእኛ እስተላሰብ የተሻለ ነው ብለን ወደ አመንንበት ስፍራ እንሄዳለን። አገልጋይ ሆይ፥ ጌታ በልዩ በረከት የሚጎበኝህ ካለህበት ሁኔታ እንድትለይ ሳይሆን ድምጹን ሰምተህ እንድትታዘዘው ነው። ጌታ የሚልህን እስክታውቅ ድረስ በትህትና በስፍራህ መቆየት ይበጅሃል። ጌታ ከእንተ የሚፈልገውን ከተረዳህ በኋላም ምንም እርምጃ ከመውሰድህ በፊት ለሕይወትህ ይጠነቀቅ ዘንድ እግዚአብሔር በአጠገብህ ያቆመልህን አገልጋይ ማማከር ትልቅ ማስተዋል ነው።

2) ተሰፋ መቁረጥ። እንድ አገልጋይ በአገልግሎቱ የጠበቀውን ፍሬ ያላገኘ ሲመስለው፥ በቶሎ ሌሎችን አገልጋዮች መውቀስ ይቀናዋል። ስለዚህም፥ በእርሱ እስተላሰብ የተቻለውን አድርጎ የቢቃው ሲመስለው፥ ስፍራውን ለቅቆ «ወደ ተሻለ ቦታ» ይሄዳል። አብዛኛውን ጊዜ በሄደበት ስፍራ ሁሉ ተመሳሳይ ነገር ማግኘቱ ጥርጥር የለውም። ይህ የሚያሳየን መለወጥ ያለበት የአገልጋዩ ልብ መሆኑን ነው። የአገልጋዩ ልብ በሚለወጥበት ጊዜ ያሉትን ችግሮች በሌላ ዓይን ማየት ይጀምርና በዚያው ባለበት ስፍራ ለውጥን ለማምጣት ጌታ የሚጠቀምበት ትሁት አገልጋይ ይወጣዋል።

3) አለመብሰል። እንድ አገልጋይ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ካልበሰለ የቆመለትን ግብና ዓላማ በሚገባ አያውቅምና በሰዎች በቀላሉ በመሰናከል ስፍራውን በቶሎ የሚለቅቅ አገልጋይ ይሆናል። በቃሉ የበሰለ አገልጋይ በሚሆንበት ጊዜ ግን የሚያገለግለውን ስለሚያውቅ ሰው አሰናከለኝ በማለት ለጌታ ክብር የቆመበትን ስፍራ ትቶ አይሄድም። በሰው ስለተሰናከልን ስፍራን መልቀቅና አገልግሎት ማቆም ምንጩ አለመብሰል ነው። የበሰለ አገልጋይ ዓይኑን በመስቀሉ ላይ የተከለ አገልጋይ ነው።

4) መሰልቸት። ካለንበት ሁኔታ የተነሳ ሰልችተን ስፍራችንን በምንለቅበት ጊዜ፥ በአንድ አገልግሎት ላይ ፍሬን እስከምናገኝ ድረስ በታማኝነት ለመቆየት በቂ ሥርአት እንደሌለን ያሳያል። በተለይ በአሁኑ ዘመን ይህ ችግር ጎልቶ ይታያል። ስንቶቻችን በታማኝነታችን የሌሎችን አገልጋዮች ልብ እንዳሳረፍን ጌታ ብቻ ያውቃል። «እርሱ ስላለ ሥራው እንደሚከናወን እርግጠኞች ነን» ብለው ሌሎች የሚያርፉብን አገልጋዮች እንድንሆን ጌታ ያብቃን።

5) ሰሚታዊነት። በእምነት ሳይሆን በስሜት የሚመላለስ አገልጋይ፥ በኮረኮንች መሬት ላይ የምናነጥረውን ኳስ ይመስላል። ይህ ኳስ የሚቀጥለው ጉዞው ወዴት እንደሆነ እንደማይታወቅ ሁሉ፥ በስሜቱ የሚመራ አገልጋይም በአንድ ስፍራ አይረጋም። «በውስጤ አልተሰማኝም» እና «እንዲህ እንዳደርግ ተሰምቶኛል» የሚሉትም የተባረኩ ክርስቲያናዊ አባባሎች ጣዕማቸውን የምናሳጣቸው የጌታ እጅ ፈጽሞ የሌለባቸውን ከስሜታዊነታችን የመነጩ እርምጃዎቻችንን መንፈሳዊ ለማስመሰል ስንጠቀምባቸው ነው።

6) ሉጉል ምክር። «አንተን የመሰለ የተቀባ አገልጋይ እዚህ ምን ይሠራል»፤ «ይልቁንስ ጊዜህን ከምታባክን ከዚህ አገልግሎት ውጣ» የሚሉና እነዚህን የሚመሳስሉ አሁን ዘርዝሬ ልዘልቃቸው የማልችል ብዙ አጉል ምክሮችን በአዋር የአገልግሎት ዘመኔ ሰምቻለሁ። ከጌታ ከመስማት ይልቅ እነዚህን የሥጋ ምክሮች ሰምቶ የተራመደም አገልጋይ በተለያየ የጌታ ሥራ ላይ ያስከተለውን የመከፋፈል መቅስፍትም ተመልክቻለሁ። በዚህ ሁሉ አንድን ነገር ተምሬአለሁ፥ ከጌታ ያልሆነ ምክር አይጸናም።



በሆነ ባልሆነ ምክንያት አገልግሎትንና ራእይን መለዋወጥ ፍሬ ቢስ ያደርጋል። በሌላው ጎኑ ደግሞ ስፍራዬን አልለቅም በሚል በጎ አስተሳሰብ በፍጹም ለበረከት፥ ለመታነጽና ለጌታ ክብር የማይውል ስፍራ ውስጥ ችክ ማለትም ኋላ ቀር ያደርጋል። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ከሁሉ በፊት የእግዚአብሔር አሳብ ምን እንደሆነ ለማወቅ ትጋ። እርሱ ከተከለህ፥ በበረሃ ውስጥም ቢሆን ትለመልማለህ። የእርሱ እጅ ከሌለበት ደግሞ የለማውም መሬት ፍሬን ይነፍግሃል።

4

እውነተኛ መነቃቃት

ምዕራፍ 5፥1–42



ቤተ ክርስቲያን ከተመሰረተች ብዙ ሳይርቅ ሐዋርያት ከአንድም ሁለት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተጥለቅልቀዋል። ከዚያም አልፎ፥ ቀድሞ በክርስቶስ አገልግሎት ውስጥ በመገረም ሲመለከቱት የነበረውም ፊውስ ዛሬ በእጃቸው ተከናውኖአል። ባጭሩ፥ አንድ ቤተ ክርስቲያን ልትደርስበት የምትችልበት የመነቃቃት ደረጃ ደርሰዋል።

ሐናንያና ሰጲራ ትልቅ ስህተት ሠሩ። የበርናባስን መሬት መሸጥና ለእግዚአብሔር ማበርከት ተመልክተው ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ የሞከሩ ይመስላሉ። ነገር ግን ልባቸው ያላቸውን በሙሉ ለመስጠት የተዘጋጀ አይመስልም። ለዚህ ነው ከሽያጩ ግማሽ አስቀርተው ሙሉ በሙሉ እንዳበረከቱ አስመስለው ቢሐዋርያት እግር ስር ያስቀመጡት። ጴጥሮስ እንደተናገረው፥ የሠሩት ኃጢአት ከሙሉው ቀንሰው መስጠታቸው ሳይሆን፥ ያሳቸውን በሙሉ እንዳመጡ አስመስለው በውሸት መቅረባቸው ነበር። በዚህም አድራጎታቸው በመንፈስ ቅዱስ ላይ ለመዋሸትና ሐዋርያትንም ለማታለል የሞከሩት መከራ ሳይቀጣ አላለፈም።

«ቤተ ክርስቲያን» የሚለው ቃል በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በተጠቀሰበት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በሐዋርያት እጅ ብዙ ድንቅና ተአምራት ይታያል። ከዚያም ሁሉ በላይ የሚያስገርመው ነገር እነዚህ የክርስቶስ አገልጋዮች በውጭም ሆነ በውስጥ የነበራቸው ሞገስ ነው (ቁ. 13)። የጌታ ተአምራት በፊውስ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። የወንጌል ተቃዋሚዎች ሐዋርያትን ወደ እስር ቤት ቢጥሏቸውም እንኳ፥ ጌታ መልአኩን ልኮ አስወጣቸው።

ሐዋርያትም እንደገና በሽንጎ እስኪያቆሟቸው ድረስ ወንጌልን መስበክ አላቋረጡም ነበር። በዚያም ጌታ የታወቀውን የሕግ መምህር ገማልያልን ተጠቅሞ ከሞት አዳናቸው። ከዚህ በፊት ሕብረተሰቡን

በተለያየ አመጽ ያነሳሱ መሪዎች እንደምናምን እንደሆኑና ከእግዚአብሔር የሆነ አሳብ ብቻ እንደሚጸና አስረድቶ በግርፋት ብቻ እንዲፈቱ ምክንያት ሆናቸው። ሐዋርያት ግን በሕይወታቸው የመንፈስ ቅዱስ እውነተኛ እሳት ተቀጣጥሎ ነበርና ስለ ክርስቶስ ማስተማርንና መስበክን በፍጹም አይተውም ነበር።



«ለሞትም እንዳልተኛ ዓይኖቼን አብራ» (መዝ. 13፥4) በማለት ዳዊት የጸለየው ጸሎት ዛሬም ለእኛ ያስፈልገናል። የዚህን ምዕራፍ ርእስ እውነተኛ መነቃቃት ብዬ የሰየምኩት፥ ውሸተኛ መነቃቃትም አለ ብዬ ስለማምን ነው። ለማንኛውም እውነተኛ ነገር ውሸተኛ ግልባጭ እንዳለው ሁሉ፥ ለእውነተኛ መነቃቃትም ውሸተኛ ግልባጭ አለው።

አንዳንድ ሰዎች በእኩለ ሌሊት ልክ እንደነቃ ሰው ተነስተው ሲናገሩና ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ። ተመልሰውም ወደ እንቅልፍ ይሄዳሉ። ማለዳ ከእንቅልፋቸው ሲነሱ በእንቅልፍ ልባቸው ስለተናገሩትና ስላደረጉት ነገር ሲጠየቁ፥ ምንም ነገር እንደማያስታውሱ ይናገራሉ። አንዳንድ ጊዜም በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ይከሰታል። አንድ ቤተ ክርስቲያን በጣሙን የተነቃቃች የሚያስመስላትን ቋንቋ እየተናገረችና ተግባርን እያከናወነች፥ ምንም ፍሬ ሳታፈራ ተኝታ ስትቀር ያሳዝናል። እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚታይበት ወቅት አገልጋዮች ራሳቸውን መጠየቅ አለባቸው።

በዚህ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አምስት ውስጥ የተጠቀሱትን የእውነተኛ መነቃቃት ምልክቶች እንመልከት።

I. ጌታ ሕዝቡን ያጠራል (5፥1–11)።

ቀደም ብለን በተነጋገርንባቸው ምዕራፎች ውስጥ እንደተመለከትነው፥ ሰይጣን የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን በጅማሬ ለመቅጨት ከውጪ ባለ ስደት አብዝቶ ታገለ። ያ ጥረቱ አልሳካ ሲለው፥ አሁን ደግሞ በውስጥ ችግር ሊያናውጣት ሞከረ። ስለ ሥራው ግድ የሚለው የናዝሬቱ ኢየሱስ ግን በዝምታ አላለፈም። መጥራት የሚገባውን አጥርቶ አለፈ። በሐናንያና በሰጲራ ሕይወት የሆነውም

የዚያ ውጤት ነው። እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት በመዋሸታቸው ምክንያት ለሌሎች ምሳሌ የሚሆን ቅጣት ተቀበሉ።

በእጁ የሐናንያና የሰጲራ ቅጣት ሲክናወን የተመለከተው ጴጥሮስ ሲናገር እንዲህ ይላል፦ «ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነስቶ የሚጀምርበት ጊዜ ደርሶአልና» (1ጴጥ. 4፥17)። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሥጋ ሥራ እንዳሻው እየፈነጨ፥ ጌታ በመካከላችን እየሠራ ነው ብንል ውሸተኞች ሆነን እንገኛለን። አገልጋዮች በስውር ኃጢአት ሕይወታቸው አድፎ ለአገልግሎት ሲቆሙ፥ ቅንአትና መከፋፈል በጌታ ቤት ሞልተው ሲተርፉ፥ በክርስቲያኖች ምክንያት የጌታ ስም ሲሰደብ፥ ጌታ ሕዝቡን የሚያጠራበት ዘመን ይመጣ ዘንድ ያሻናልና ወደ አምላካችን እንጩህ። እውነተኛ መነቃቃት በክንፉ ቅድስናንና እግዚአብሔርን መፍራት ሳያቅፍ አይመጣም። መንፈስ ቅዱስ በሙላት በሚንቀሳቀስበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የስውር ኃጢአት ስፍራ የለውም።



አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ቤቱን ያጠራል በሚል ያልተሳሳተ አሳብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያልሞላን ነገር ብቻ እየቆጠርን በአገልጋዮች ላይ ስንፈርድ እንገኛለን። ሌላ ጊዜ ደግሞ የጌታ ቤት ስንፍናንና ኃጢአትን ተሞልቶ እያየን በዝምታ ስማለፋችን ምክንያትን እየሰጠን እንዳዛለን። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ጌታ የቤቱ ቅንአት የሚበላውና ሕዝቡንም ሊያጠራ የሚነሳ አምላክ እንደሆነ በንግግርህም ሆነ በሕይወትህ ማስጠንቀቅን አትዘንጋ። ሆኖም ፍርድ የእርሱ እንጂ የአንተ እንዳልሆነም በማሰብ ከፍርድ መንፈስ ተጠበቅ።

II. ጌታ ለሕዝቡ ሞገስን ይሰጣል (5፥12–16)።

የሰሎሞን ደጅ መመላለሻ ዋነኛ የሐዋርያት መሰብሰቢያ ሆኖ ነበር። በዚያም በድንቅና በተአምራት እየተመላለሱ ሳሉ፥ ሁሉም ያከብሯቸው እንደነበር ሉቃስ ይነግረናል (ቁ.14)። ይህም እርስ በርስ መከባበር በመካከላቸው ለነበረው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አንደኛው ምልክቱ ነው ብዬ አምናለሁ።

እንደ አገልጋዮች እርስ በርሳችን መከባበር እንዳይጠፋብን ትልቅ ማስተዋል ያስፈልገናል። ይህ የመከባበር ባህሪይ ከሌሰን አገልጋይን

ከአገልጋይ እያማረጥን የመከፋፈል ችግር ያሰጋናል። እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በመካከላችን በሚኖርበት ጊዜ፥ የእግዚአብሔር ሰዎች እርስ በርሳቸው ሲከባበሩና በአንድነት ሲሠሩ ይታያሉ። ዛሬ ለአዳጊ አገልጋዮች ምሳሌነት የሚበቁ በአንድነት የቆሙ መሪዎች የት ናቸው? አገልጋይ በጌታ ለሚያሳድጋቸው ወገኖቹ መልካም እርእያ ለመሆን ከመረጠ፥ ሌሎችን አገልጋዮች መተቸት፥ መንቀፍና መዝለፍ በመተው አብሯቸው መቆምን መማር ያስፈልገዋል።

III. የማያቋርጥ እሳት ይነድዳል (5፥17–42)።

ይህንን ነጥቤን በቀላሉ ለመረዳት ገማልያል የተናገረውን አሳብ ደግሞ ማጤን በቂ ነው። «ይህ አሳብ ወይም ይህ ሥራ ከሰው እንደ ሆነ ይጠፋልና፤ ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ግን ታጠፉአቸው ዘንድ አይቻላችሁም» (ቁ. 38–39)። ገማልያል እንደተናገረው፥ በሐዋርያት ዘንድ ይታይ የነበረው እንቅስቃሴ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለነበረ ነው ጌታ መልአኩን ልኮ ወንጌልን ይሰብኩ ዘንድ ከእስር ቤት ያስወጣቸው። እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ ማንም ሊያቆመው አይችልም።

ይህ እውነተኛና የማያቋርጠው የጌታ ሥራ በሚጠፋበት ጊዜ፥ በሥጋችን እርሱን የሚመስልን ሥራ ለማከናወን እንጥራለን፥ ብዙም ሳይቆይ ይጠፋል። ነፍሳትን እንሰበስባለን፥ ሕይወታቸው ግን አይለወጥም። ከየቤተ ክርስቲያኑ በግራና በቀኝ እንከፈላለን፤ እርስ በርሳችንም ሃሰተኞች ተባብለን እየተጠራራን በእግዚአብሔር ስም እስክመናገርም እንደርሳለን፤ ስለዚህም ሌሎችን ለማስታረቅ የተጠራን ቅዱሳን ከራሳችን ጋር ተጣልተን ቁሞ እንላለን። ስለዚህም እገልግሎታችን እንዴ ከፍ እንዴ ዝቅ ሲል ይታያል። ብዙ የእገልግሎት እሳቶች በየቦታው ይነሳሉ፥ መንፈስ ቅዱስ የጀመረው እሳት ብቻ እስከፍጻሜ ይነድዳል።

እውነተኛውን የጌታን እጅ እንመለከት ዘንድ ይህንን ጽሑፍ የሚያነብ አገልጋይ ሁሉ የሚከተሉትን ነገሮች ለማድረግ እንዲተጋ አበረታታዋለሁኝ።

1) ንስሐ። በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሁሉ የማያቋርጥ የንስሐ መንፈስ ያስፈልገናል። በተለይም፥ ምእመኑን ዘወትር በንስሐ ይቀርብ

ዘንድ በእግዚአብሔር ቃል የሚገስጹት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና የተለያየ ራሱን የቻለ የአገልግሎት ድርጅት የሚያካሂዱ መሪዎች የንስሐን ሕይወት የዘወትር ተግባራቸው ያደርጉት ዘንድ አሳስባለሁ። አለበለዚያ፥ ወደፊት የመሪነትን ሥፍራ የሚረከቡት የዛሬ ምእመናን በንጹህና በጤናማ መንፈስ መታነጻቸው ቀርቶ፥ በየአገልግሎቱ ሰርጾ በገባው በቡድንና በመከፋፈል መንፈስ ተጣምመውና ተመርዘው ያድጋሉ። መልእክተኛ ከላከው እንደማይበልጥ ሁሉ፥ ተማሪም ከአስተማሪው በልጦ መሄዱ ያጠራጥራል (ዮሐ. 13፥16)።

2) መስቀሉን መመልከት። የጌታን ሥራ በአፍሩ ከሚቀጩት ነገሮች አንዱ፥ ከክርስቶስ መስቀል ላይ ዓይንን ማንሳት ነው። ይህ ሁኔታ በብዙ መልኩ ሊገለጥ ይችላል። ለጌታ ክብር መሮጥ ትተን የራሳችን አገልግሎት ብቻ እንዲያድግ ስንታገልና ለሰው ብለን ስናገለግል፥ ዓይናችን ከመስቀሉ ተነስቶአል። በእጠቃላይ የመነሻ አላባችን የክርስቶስን ሞትና ትንሳኤ በንጹህ ልቦና ማብሰር መሆኑ ቀርቶ ሌሎች ነገሮችን ስንከታተል፥ ዓይናችን ከመስቀሉ ተነስቶአል።

3) የምልጃ ጸሎት። እውነተኛ መነቃቃት የሚመጣው ከመንፈስ ቅዱስ ብቻ ስለሆነ፥ የምልጃ ጸሎት ቁልፉ ነው። የሥጋ ጥረት እንዲቆምና የጌታ ሥራ ብቻ እንዲሠራ አገልጋዮቹ በጸሎት መትጋት አለባቸው። ከሰው ጋር በማውራት ከምናሳልፈው ጊዜ የበለጠ ከጌታ ጋር መነጋገር እስክንማር ድረስ እውነተኛውን የጌታን እጅ እንደማናይ መገንዘብ ትልቅ ማስተዋል ነው።

5

መግደል ያለባቸው ቀበሮች

ምዕራፍ 6፥1–15



የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ሌላ ችግር ገጠማት። ይኸውም የአድልዎ ችግር ነበር። ከግሪክ መጥተው የነበሩት አይሁድ በይሁዳ ይኖሩ በነበሩት አይሁድ ላይ የአድልዎ ክስ አቀረቡ። በይሁዳ ይኖሩ የነበሩት አይሁድ ከግሪክ መጥተው የነበሩትን መበለቶች በየዕለቱ በነበረው የምግብ አገልግሎት ችላ ያሉባቸው ይመስላል። ስለችግሩ መከሰት እውነተኛነትና በምን ዓይነት መልኩ እንደተከሰተ ሉቃስ ያደረገው ገለጻ ባይኖርም፥ ደቀ መዛሙርቱ ላይዘገዩ እርምጃ ሲወስዱ ይታያሉ። መፍትሄውም ለዚያ ተግባር ብቻ የሚውሉ አገልጋዮችን መሾም ነበር። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስንና ጥበብን የተሞሉ ሰባት አገልጋዮች መረጡ። ሉቃስ እነዚህን የተመረጡ አገልጋዮች ዲያቆናት ብሎ ባይጠራቸውም እንኳ፥ ያከናውኑት የነበረው ተግባር ጳውሎስ በ1ጢሞ. 3፥8–13 ውስጥ የጠቀሰውን የዲያቆናት አገልግሎት መልክ የያዘ ይመስላል።

ደቀ መዛሙርቱ ጊዜ እግኝተው በየጥሪያቸው እንዲሰለፉ የተቀሩት አገልጋዮች በሙሉ ድርሻቸውን ማበርከት ነበረባቸው። ስለሆነም የእግዚአብሔር ቃል እየሰፋ ሄደ። ከእነዚህም ለአገልግሎት ከተሾሙት መካከል የነበረው «እስጢፋኖስም ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅንና ታላቅ ምልክትን ያደርግ ነበር» (ቁ. 8)። ሲናገር የነበረውን የጥበብ ቃልና ሲያከናውን የነበረውን ተአምራት መቋቋም ያቃታቸው ተቃዋሚዎችም ስደትን አስነስተው እስጢፋኖስን ይዘው ወደ ሸንጎ አመጡት። ሸንጎው በሃሰት ክስ የተሞላ ነበር። የእስጢፋኖስ ፊት ግን እንደ መልአክ ፊት ያበራ ነበር።



«ወይናችን አብቦአልና የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ቀበሮች፥ ጥቃቅኑን ቀበሮች አጥምዳችሁ ያዙልን» (መኃ. 2፥15)። ገበሬ ለብዙ ጊዜ የለፋበት የወይን ስፍራው በማይረቡ ጥቃቅን ቀበሮች ሲጠፋበት ማየት አይፈልግም። በአንጻሩ፥

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም ብዙ ዋጋ የተከፈለበትን ህልውናዋን የሚቦጠቡጡትን «ጥቃቅኑን ቀበሮች» አትፈልግምና አጥምዳ መያዝ ብቻ አይደለም ማጥፋትም አለባት።

በአሁን ዘመን ቤተ ክርስቲያናችን እያበበች ስትሄድ እድገቷን በአጭሩ ለመቅጨት የሚነሱ ቀበሮች አሉ። የሚያስገርመው ነገር እነዚህ ቀበሮች ቤተ ክርስቲያን በደነዘዘች ጊዜ፥ በተለይም በቁጥር ባነሰች ጊዜ የመነሳት ባህሪይ የላቸውም። ሁኔታዎች ሲያምሩና ሲያብቡ ግን ባጭር ሊያስቀሯት ይነሳሉ። ሉቃስም እንደተረከው፦ «በዚያም ወራት ደቀ መዛሙርት እየበዙ ሲሄዱ» ነበር በኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር የተነሳው።

የአንድን አገልግሎት እድገት በአጭሩ ለመቅጨት ሰይጣን የሚጠቀምባቸው ብዙ ዘዴዎች እንዳሉት ግልጽ ሆኖ ሳለ፥ በአጭሩ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በግልጽ የምናያቸውን ቤተ ክርስቲያንን በቀላሉ ሊያጠቋት የሚችሉትንና በጣሙን የተለመዱትን ሦስት ነጥቦች ጠቅሼ አልፋለሁ።

I. ወገናዊነት (6፥ 1)።

ደቀ መዛሙርቱ እየበዙ በነበሩበት በዚያን ወቅት በድንገት ወደ ብርሃን የወጣው የወገናዊነት መንፈስ የሚያሳዝን ሁኔታ ነው። ከግሪክ መጥተው የነበሩት አይሁድ በይሁዳ በነበሩት አይሁድ ላይ የአድልዎ ክስ ማቅረባቸው ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ቢሆን ኖሮ ሐዋርያት ስለጉዳዩ ያን ያህል ባላሰቡበት ነበር። መቼም በተቀደሰችው በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ አጸያፊ ነገር መሰማቱ ያሳዝናል። በአጭሩም ካልተቀጨ መሰረትን የሚያናጋ ችግር ነው።

በዛሬይቱስ ቤተ ክርስቲያን ይህ ጉዳይ እንዴት ይሆን? በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነገር ሞቅ ሞቅ ሲል፥ አገልግሎቶች ሲበዙና ነፍሳት ሲጨመሩ፥ ያን ጊዜ እንዴት ነው የምንመላለሰው? በተለይም በቤተ ክርስቲያን በኩል ለምእመናኖች መሰራጨት የሚገባው የሥጋ በረከት በሚኖርበት ጊዜ አብዝተን መጠንቀቅ አለብን። ከእግዚአብሔር በአደራ በተቀበልነው ማንኛውም ጉዳይ ላይ ወገናዊነት ሲታከልበት ጤንነት በነቀርሳ ተተካ ማለት ነው። ጳውሎስም ሲመክረን እንዲህ ይለናል፦

«ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ» (ፊልጵ. 2፥ 3)።

አገልጋይ ከሚከተሉት የወገናዊነት መንፈስ መንስኤዎች ሊጠነቀቅ ይገባዋል።

1) የዘር ወገናዊነት። ሕዝብ በሕዝብ ላይ፥ መንግሥትም በመንግሥት ላይ በተነሳበት በዚህ በመጨረሻው ዘመን ከዚህ መንፈስ አብዝተን መጠንቀቅ አለብን። በቋንቋና በባህል ለመከፋፈል አመቺ በሆነችውም በሃገራችን ይህ ችግር አስጊ ነው። አገልጋይ ከስውር ዘረኛነት ልቡን መጠበቅ አለበት። በቋንቋና በባህል፥ እንዲሁም በአገር ሰውነት ወገንህ ስለሆነ ለማንም ሰው አታድላ። ቅን ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር ያዝንብሃል፥ ለወንጌልም እንቅፋት ይሆናል።

2) የአብሮ አደግ ወገናዊነት። ለረጅም ጊዜ በሥጋ ኑሮም ሆነ በመንፈሳዊ አገልግሎት አብረው ያደጉ አገልጋዮች በአገልግሎት ውስጥ የመጠቃቀም ዝንባሌ ሲታይባቸው የጌታን ሥራም ሆነ የሰውን ልብ ያቆስላልና መጠንቀቅ ያሻናል። አንድ ሰው አብሮህ በብዙ ነገር ስላለፈና ስለተላመዳችሁ ወደ እርሱ አታድላ። የእግዚአብሔር መንፈስ ያዝንብሃል፥ ለሰዎችም በረከት መሆን ይላንሃል።

3) የሥጋ ዝምድና ወገናዊነት። ይህ ዓይነቱ ወገናዊነት የሚያጠቃው አገልጋይ፦ «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜ እህቴም እናቴም ነውና» (ማቴ. 12፥ 50) የሚለውን የጌታን ቃል ገና አላነበበም፥ ቢያነብም ትርጉሙ አልገባውም። ሁሉም የአንድ አባት ልጆች በሆኑበት በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ገብተህ ለዘመድህ አታድላ። የሰውን ሁኔታ አይቶ የማያደላው አምላክህ ያዝንብሃል።

4) የቡድን ወገናዊነት። አገልጋዮች በየምክንያቱ የቡድን ስሜት እንዳያጠቃቸውና እንዳያዳሉ ሊጠነቀቁ ያስፈልጋል። ከተወሰኑ አገልጋዮች ጋር ቡድን በመፍጠር ለእነርሱ አታድላ። ወደ እርሱ የመጡትን ሁሉ ካለምንም አድልዎ ከመቀበል የማይቦዝነው ክርስቶስ ኢየሱስ ያዝንብሃል።



ወገናዊነት በእግዚአብሔር ቤት ተገቢ አይደለም በማለት በተለያየ መልኩ የሚዛመዱንን ወገኖቻችንን እርግፍ አድርጎ

መጣሉ ተገቢ አይመስለኝም። በእንጻሩ ደግሞ ጌታ እኛን በእነርሱ፥ እነርሱን ደግሞ በእኛ ይባርክ ዘንድ ባጠገባችን ላስቀመጠልን የቅርብ ወገኖቻችን እያደላንና በዚያም ምክንያት ጌታንና ሌሎችን ሰዎች መበደሉም የከፋ ኃጢአት ይሆንብናል። እንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ባጠገብህ ጌታ ላስቀመጣቸው የቅርብ ወገኖችህ ያለብህን ሃላፊነት ቸል አትበል። ሆኖም አድልዎን እያደረግህና ወገኖችህን ብቻ ያለአግባብ እየጠቀምክ ሌሎችን ከመጉዳት ተጠንቀቅ።

II. ሁሉን እኔ ላድርግ ባይነት (6፥2–6)።

ደቀ መዛሙርቱ፥ መሴ ከዘመናት በፊት የተማረውን ትምህርት እንደ አዲስ ተማሩ (ዘጸአ. 18)። እርሱ ሥራውን ሁሉ ለብቻዬ አልችልም ብሎ ለሰባዎቹ እንዳከፋፈለ፥ ሐዋርያትም ይህንኑ ነገር ማድረግ ነበረባቸው። እነርሱ የእግዚአብሔርን ቃል እደራ በሚገባ ይወጡ ዘንድ የተቀረውን የሥራ ሃላፊነት ለሌሎች ሲያከፋፍሉ ይታያሉ።

ዛሬ ስንቶቻችን ይህ አገልግሎትን ለሰዎች እንደየስጦታቸው የማሰራጨት ምስጢር እንደገባን እኔ አላውቅም። አንድ ነገር ግን ግልጽ ነው፥ በሁሉም አገልግሎት እኛ ብቻ ከቆምንና ሁሉን ነገር ለመቆጣጠር ከታገልን፥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ አገልግሎትን የማከፋፈል ምስጢሩ አልገባንም ወይም ያንን እውነት ለመለማመድ ፈቃደኞች አይደለንም። እግዚአብሔር የተቀባ አገልጋይ እንዲያስነሳ ከመጸለያችን በፊት፥ ከዚያም አልፈን፦ «አንድ የረባ አገልጋይ የለም» እያልን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከማማታችን በፊት፦ «አገልጋይ ሁሉ በየጥሪው ተሰልፏል ወይ?» የሚለውን ጥያቄ መመለስ አለብን።

ለመሆኑ ለምንድነው ለሌሎች አገልግሎትን ከማከፋፈል ይልቅ ሁሉንም እኛው ለማድረግ የምንሮጠው? የሚከተሉትን ነጥቦች እንመልከት።

1) ለለመተማመን። ሌሎች አገልጋዮች እኛ የያዝነውን ቦታ የሚቀናቀኑን ሲመስለን፥ በፍጹም በአገልግሎት እንዲላተፉ እንፈልግም። ስለዚህም እነርሱ በጸጋቸው መቆም በሚገባቸው ቦታ ላይ ዘወትር ራሳችንን ስናቆም እንታያለን። ይህንንም አድራጎታችንን የተለያዩ

ምክንያቶችን በመስጠት እንሸፋፍነዋለን። ይህ ዓይነቱ ድካም ካለብን፥ በተለይም በምእመናን ፊት ሞገስን እያገኘ የመጣን አገልጋይ አገልግሎትን በመንፈግ መጨቆን ይቀናናል። እንዲህ ዓይነት አገልጋዮች በምንሆንበት ጊዜ፥ የያዝነው የአገልግሎት ስፍራ ጌታ የሰጠን ሳይሆን በብልጠታችን ያገኘነው መሆኑን ያሳያል። ጌታ እንዳቆመው የሚያውቅና የሚያምን አገልጋይ፥ ሰው ያወርደኛል ብሎ አይሰጋም። ስለዚህም በነጻነትና በደስታ ለሌሎች ሥራን ሲያከፋፍል ይታያል።

2) ብቁ ሳይደሉም ብሎ ማሰብ። ጌታ አገልጋዮቹን ያቆመው ብቁ ያልሆኑትን ወደ ብቃት እንዲያደርሱ እንጂ ብቁ አይደሉም በሚል ሰበብ እንዲቀብሯቸው አይደለም። ማንኛችንም ብንሆን ወደ አገልግሎት ስንመጣ ብቁ አልነበርንም፥ አሁንም ብቁ አይደለንም። ንስር ፈጽሞ ለመብረር እንግዳ የሆኑትን ጫጩቶቿን ወደ ሰማይ አውጥታ በመልቀቅ መብረርን እንደምታለማምድ ሁሉ፥ እኛም የጌታ ጥሪ ያለባቸውን ሰዎች የቀመስነውን እንዲቀምሱና የደረስንበት እንዲደርሱ ማደፋፈር እንጂ ማዳፈን የለብንም።

3) የችሎታ ማነስ። እንዳንዶቻችን የእስተዳደር ችሎታ ስለሌለን፥ ፕሮግራሙ ሁሉ ለሌሎች የማከፋፈያ ጊዜው ካለፈ በኋላ ነው ትዝ የሚለን። ስለዚህም አንደኛችንን እኛው እንገባበታለን። ይህ ድካም ለእኛ ብዙም ባይታውቀንም እንኳ ሌሎችን እጅግ ይጎዳልና ልናስብበት ይገባል። እንዲያውም አገልግሎትን የማከፋፈሉን ኃላፊነት የማስተዳደር ስጦታው ላላቸው አገልጋዮች በማስረከብ ይህንን የበረከት ሕይወት መለማመድ መጀመር እንችላለን።

III. አገልጋይን ያለ ስጦታው ማሰለፍ (6፥7–15)።

እንደ ሉቃስ ትረካ ከሆነ፥ እስጢፋኖስ ለድቁና አገልግሎት ነበር የተሾመው። ሆኖም፥ በተመደበበት የአገልግሎት ዘርፍ አንዳችም አገልግሎት ለመስጠቱ የተገለጸልን ነገር የለም። ይህንን ሁኔታ በመመልከት የተለያዩ ሰዎች ልዩ ልዩ አሳቦችን ይሰነዝራሉ። አንዳንዶች እስጢፋኖስ ተመድቦበት የነበረው የድቁና አገልግሎቱ ቀድሞውኑ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስላልነበረ ነው እግዚአብሔር ከዚያ

አውጥቶ በሥልጣን ያወጣው ብለው ያምናሉ። ይህ አመለካከት መልካም ሆኖ ሳለ እስጢፋኖስ ካለጌታ ፈቃድ ለድቁና አገልግሎት ለመመደቡ ምንም ዓይነት ትንታኔ ስላልተሰጠን እንደዚያ ብሎ ለመደምደም ትንሽ አስቸጋሪ ይሆናል። በሌላው ጎኑ ደግሞ፥ እስጢፋኖስ በተሰጠው የድቁና አገልግሎት ታማኝ ሆኖ በመገኘቱ እግዚአብሔር ወደ ትልቅ ደረጃ አሳድጎ ድንቅንና ተአምራትን ወደማድረግ አገልግሎት አሸጋግሮታል ብለው የሚያምኑ አሉ። ይህም መልካም አሳብ ነው። ነገር ግን ይህንን አሳብ በምንሰነዝርበት ጊዜ እግዚአብሔር ለሰዎች የሚሰጠውን የጸጋ ስጦታ አበላለጥነው ማለት ነው። ድንቅና ተአምራት ማድረግ ከድቁና አገልግሎት በምንም አይበልጥም። አንድ አገልጋይ በማንኛውም አገልግሎት የሚቆመው ለዚያ አገልግሎት እግዚአብሔር ጸጋ ስለሰጠው እንጂ ያ ሰው ትልቅ ወይም ትንሽ ስለሆነ አይደለም። የእስጢፋኖስን ለድቁና አገልግሎት ተመርጦ ሳለ ይህንን ሹመቱን አንዴም እንኳ ለመጠቀሙ ሳይገለጽ ድንቅና ተአምራት ለማከናወን መውጣት አንብበን በእውነትም ካለስጦታው የተሰለፈ አገልጋይ ነበር ብለን ለመደምደም ያስቸግራል። የዚያንው ያህል እስጢፋኖስ በድቁና አገልግሎት ጀምሮ ተአምራትን ወደማድረግ አገልግሎት ያደገ አገልጋይ ነው ለማለትም ትንሽ አስቸጋሪ ይሆንብናል። ይህን አከራካሪ ሁኔታ ለመመለስ ብዙ ጊዜ ከማባከን ይልቅ ከሁኔታው የምንማረውን መመልከቱ ለእድገታችን ይሆንልናል። በአጭሩ፥ እስጢፋኖስ በጥሬው ተሰለፈም አልተሰለፈ አንድን ጉዳይ ተመልክተን እንድናልፍ ይገፋፋናል። ይህ አገልጋይን ካለጥሪው የማሰለፍ ሁኔታ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊከሰት ይችላል ወይ? አዎን ሊከሰት ይችላል። ይህንንም ስለማምን ስለሁኔታው በጠለቀ ሁኔታ ለመተንተን እፈልጋለሁ።

በአንድ በሕይወቱ የአገልግሎትን ጥሪ በተቀበለ ሰው ልብ ውስጥ የሚቃጠለውን እሳት ማንም ሰው ሊገነዘብለት አይችልም። ይህ ሰው ለጥሪው ምላሽን ሰጥቶ ለጌታው ማደርን በሚጀምርበት ጊዜ ብዙ ጦርነቶች በሕይወቱ ይታወጃሉ። ብዙዎቹ ጦርነቶች ከሰውም ሆነ ከሰይጣን በግላጭ የሚመጡ ውጊያዎች ናቸው። ነገር ግን የአገልጋይን ሕይወት እንደ ምስጥ በስውር የሚበላ ውጊያ አለ፥ ይኸውም አንድ አገልጋይ ካለ ጥሪው በሚቆምበት ጊዜ ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፥ ያ

አገልጋይ ሃኪም በሽታውን እንዳላወቀለት ህመምተኛ ይሆናል። በውስጡ የጥሪው እሳት እንደ እሳት ይነዳል።

እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ጌታ እያስነሳቸው ያሉት ወገኖቻችን በመላት እንዲወጡ እውነተኛ ምኞት ካለን፥ አገልጋዮችን ተስፋ የሚያስቆርጡ ንግግሮች ከአንደበታችን በማስወገድ ተነቃቅተውና በስጦታቸው ተሰልፈው ጌታን በመላት የሚያገለግሉበትን መንገድ ልንፈልግላቸው ይገባናል። «አትቸኩል፥ ገና ብዙ ይቀርሃል» ከሚለውና ይህንን ከመሳሰለው ለአገልግሎት በመነሳት ላይ ያሉን አገልጋዮች ተስፋ ከሚያስቆርጥ አነጋገር መቆጠብ የአስተዋይ አገልጋይ ምልክቱ ነው። «እርሱ ለመታወቅ የሚሮጥ ሰው ነው»፤ «ሁል ጊዜ መድረክ ላይ ለመቆም ነው ትግሉ»፤ «ቤተ ክርስቲያንን ለመክፈል የተነሳ ሰው ነው» የሚሉት የተለመዱ አባባሎች ከአስተዋይ አገልጋይ አንደበት ፈጽሞ አይጠበቁም።

አገልጋይን ካለቦታው የማሰለፍን ችግር ለአንባቢዬ እንዲቀልለው በማለት በሁለት ከፍለን እንድናየው እፈልጋለሁ። አንደኛ፥ አገልጋዮች ለምን መቆም በማይገባቸው ቦታ ይቆማሉ? ሁለተኛ፥ አገልጋዮች መያዝ የሚገባቸውን አገልግሎት ለምን አይዙም?

በመጀመሪያ አገልጋዮች ለምን መቆም በማይገባቸው የአገልግሎት ቦታ ይቆማሉ? ለሚለው ጥያቄ የሚከተሉትን አሳቦች እናጤናቸው።

1) በክርስትና ስለቆየ። በክርስትና መቆየት አስፈላጊና ለቤተ ክርስቲያንም ትልቅ በረከት የሚሆን ሃብት ነው። ነገር ግን አንድን አገልጋይ በጌታ ቤት ያሳለፈውን ዘመን ቆጥረን ብቻ ባልተጠራበትና በፍጹም ለበረከት በማይውልበት አገልግሎት ላይ ስናስቀምጠው ትልቅ ስህተት እንሠራለን። አገልጋይ በጌታ ቤት ባሳለፈው ዘመን ብዛት ብቻ ሳይሆን፥ በመልካም ባህሪው፥ በመንፈሳዊ ብስለቱና ለዚያ አገልግሎት በመጠራቱ ጭምር ለአገልግሎት መቆም አለበት።

2) ብዙ ትምህርት ስላለው። አንድ ሰው ለረጅም ጊዜ በመንፈሳዊም ሆነ በዓለማዊ ትምህርት ማሳለፉና የሚጠበቅበትን ሁሉ በሚገባ ማጠናቀቁ የሚያሳየን ያ ሰው ምን ያህል የዳበረ ስነ ስርአት እንዳለው ነው። ይህ ባህሪው ለወገኖች ትልቅ ምሳሌና ማበረታቻ ሊሆን ይገባዋል። የቀሰመውም እውቀቱ ደግሞ ብዙዎችን እንዲያስተምር ብቁ

ያደርገዋል። ሆኖም፥ አንድ ሰው ብዙ ትምህርት ስላለው ብቻ ላልተጠራበት አገልግሎት ማሰለፍ ለምንም አይበጅም። አገልጋይን ውጤታማ የሚያደርገው በሕይወቱ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ቅባት እንጂ በቄንቅላቱ ውስጥ ያለው የእውቀት ብዛት ብቻ አይደለም።

3) አንድ ልብ ነን የሚል ሰበብ። የምናመጣቸውን አዳዲስ አሳቦችና የምንወስናቸውን ውሳኔዎች በአንድ ልብ ሆኖ የሚስማማንን ሰው እንደማግኘት ደስ የሚያሰኝ ነገር የለም። እንደሚገባ ከተጠቀምንበትም ትልቅ የበረከት ምንጭ ነው። ነገር ግን ይህንን ብቻ ምክንያት አድርገን አገልጋዮችን በምንሾምና በምንሽርበት ጊዜ ወደ ስህተት ልናመራ እንችላለን። እውነተኛ አገልጋዮች ስንሆን፥ ያልነውን ሁሉ አሜን እያሉ የሚቀበለንን ሰው ብቻ ሳይሆን፥ በፍቅርና በትጎትና የሚመክረንንና የሚገስጸንንም ሰው እንናፍቃለን። ደግሜ እላለሁ፥ አንድ አገልጋይ ለአገልግሎት መቆም ያለበት ለዚያ አገልግሎት ስለተጠራ ብቻ መሆን አለበት።

4) የቅርብ ወዳጅነትና ጓደኝነት። ይህን አሳብ በዚሁ ምዕራፍ፦ «ወገናዊነት» በሚለው ክፍሌ ውስጥ በመጠኑ ጠቅሼዋለሁኝ። ባጭሩ፥ ምንም እንኳ ለአገልግሎት የሚመቸን ቢመስለንም፥ አንድ አገልጋይ የቅርብ ወዳጃችንና ጓደኛችን ስለሆነ ብቻ ባልተሰጠው ቦታ ማሰለፍ ከጌታ ፈቃድ ያስወጣናል።

5) የአገልግሎት ዝና። የአንድን አገልጋይ የቀድሞ አገልግሎት መስማት ልብን ያሳርፋል። ወገኖችም ደግሞ በዚያ ሰው ጌታ ያደረገውን ድንቅና ያለማመደውን ልምምድ እየሰሙ ጌታን ማክበር አለባቸው። ነገር ግን የትናንት ዝና ለዛሬ የማይጠቅምበት ጊዜ እንዳለም መዘንጋት የሰብንም። ከዚህ በፊት ጌታ በተለያዩ ቦታዎች የተጠቀመባቸውን አገልጋዮች አጣድፈን በዚህና በዚያ አገልግሎት ውስጥ ስናስገባቸው ከሁሉ በፊት አነርሱን ግራ እናጋባቸዋለን። እግዚአብሔር ብቻ ማንን በየትና መቼ እንደሚጠቀም ይወስናል። ስለዚህ በአገልግሎት ዝናና በልምምድ ብቻ ሳንወሰን የእግዚአብሔርንም ምሪት እንጠብቅ።

6) በሰዎች ዘንድ የደስ ደስ ያላቸው አገልጋዮች። ቤተ ክርስቲያን ከተባረከችበት በረከት አንዱ በውስጥዋ የተለያየ ችሎታ

ያላቸው ሰዎች መኖራቸው ነው። በሰዎች ዘንድ የደስ ደስ ያላቸው፥ የሚያዝናኑ፥ ገና ስናያቸው የምንቀበላቸውና በሁሉ ዘንድ በመልካምነታቸው የታወቁ ሰዎች አሉንና ጌታን ልናመሰግን ይገባናል። የአገልግሎት ምስጢር የገባን ሰዎች ከሆንን ግን ይህን የተጠቀሰውን የሰዎችን ሁኔታ ለአገልግሎት ከመጠራት ጋር በፍጹም አናምታታውም። አንድ አገልጋይ ሰዎችን ስለሚያዝናና ወይም ብዙዎች ስለሚወዱትና ስለሚቀበሉት ብቻ መቆም የማይገባው አገልግሎት ላይ እንዳናቆመው ማስተዋል አለብን። እግዚአብሔር ለዚህ ሰው የሰጠውን ተቀባይነትና የደስ ደስ በምን የአገልግሎት ዘርፍ ሊጠቀምበት እንደሚወድ እንዲያሳውቀን ዕድሉን እንስጠው።

7) የአገልጋይ እጥረት። በተለይም የአገልጋዮች ቁጥር ባነሰበት አካባቢ፥ ሁሉ አምልኮ መሪ፥ ሁሉ ዘማሪና ሰባኪ ሆኖ ይታያል። ለጎደሰው የአገልግሎት ዘርፍ ጥሪ ባይኖራቸውም እንኳ ያንን ስፍራ የሚሸፍን አገልጋይ ጌታ እስኪያስነሳ ድረስ ለጊዜው አገልጋዮችን ማቆም መልካም ሆኖ ሳለ፥ ሁለት መጠንቀቅ ያለብን ሁኔታዎች አሉ። በመጀመሪያ፥ የአገልጋይ እጥረት አለ የሚለውን ሰበብ ያሻነውን ለማድረግ እንዳንጠቀምበት መጠንቀቅ አለብን። ያንን ጥንቃቄ ከወሰድንና በእውነትም ችግሩ እውን ከሆነ፥ አገልጋዮች ከልክ ያለፈ ሃላፊነት ውስጥ ገብተው ፍሬ ቢስ እንዳይሆኑ ሁሉን በማስተዋል እናድርግ።

ሰዎችን መቆም የማይገባቸው አገልግሎት ውስጥ ስናቆማቸው፥ በዚያ ቦታ መቆም የሚገባቸው አገልጋዮችን ስፍራቸውን በመንፈግ እንደምንበድላቸው ግልጽ ነው። ከዚህ ቀጥሰን ደግሞ አገልጋዮችን ከጥሪያቸው የሚያስወርዱና መያዝ የሚገባቸውን አገልግሎት እንዳይዙ የሚያደርጉትን ጠንቆች እንመልከት።

1) እንደ ቃሉ ያልሆነ ራሰን ማዋረድ። ጌታ ከሰጠን አገልግሎት፦ «እኔ ለዚህ አልገባም» በሚል ምክንያት ወደ ኋላ ስናፈገፍግ፥ ጌታን እንወስነዋለን። ከልቡ ትሁት የሆነ አገልጋይ ጌታ የሰጠውን አገልግሎት ካከናወነ በኋላ ነው፦ «እኔ ለዚህ የማልገባ ሰው ነኝ፥ ማድረግ የሚገባኝን ብቻ በጌታ ጸጋ አደረግሁ» በማለት ራሱን የሚያዋርደው።

2) *ሰለመግባባት።* አንድ አገልጋይ እኛ ያመጣነውን አሳብ የማይቀበል መስሎ ሲታየን፥ ችግሩን ለመፍታትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መፍትሄ ለማግኘት ከመጣር ይልቅ በውስጣችን ቂምን በመያዝ በዚያ አገልጋይ ላይ የአገልግሎት በርን መዝጋቱ ተገቢ አይደለም። ይህ አድራጎት በወቅቱ በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት ያለብንን እልህ በመወጣት ለጊዜው እንድንረካ ቢያደርገንም እንኳ፥ በጌታ ፊት አጸያፊ ድርጊት መሆኑን አንዘንጋ።

3) *ቅንአት።* የቅንአት ችግር ያለበት አገልጋይ ሌሎች አገልጋዮች ጌታ ሲጠቀምባቸው ማየትና መስማት አይወድም። እንዲያውም እርሱ ስላልተሳተፈበት አገልግሎት የበረከት ዜና መስማትን አይፈልግም። ስለዚህም በጌታ ፊት ሞገስን እያገኘ የመጣን አገልጋይ ሰራሱና ለጌታ ብቻ ግልጽ በሆነ የቅንአትና የጥላቻ ዓይን ይመለከተዋል። ይህ ቅንአት በምን ይገለጣል ብንል መልሱ፥ የአገልግሎትን በር በመዝጋት ነው። ይህንንም ሁኔታ ጌታ አይወደውም።

4) *ለተሃድሶ እድልን መንፈግ።* አገልጋይ በጎጢአት ወይም በስህተት መንገድ በሚገኝበት ጊዜ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣንና ሃላፊነት ነው። ነገር ግን ጌታ በደሙ ያጠበውን ያለፈ ኃጢአት እየነተተን የተቀባውን ሰው ደፍቀን ማስቀረት የለብንም። የወደቁ አገልጋዮች ቤተ ክርስቲያን የደነገገችውን ተገቢውን የተሃድሶ መንገድና ሥርአት ከተከተሉ በኋላ ወደ አገልግሎታቸው እንዲመለሱ እንጣርላቸው።

5) *የአገልጋይ መብዛት።* ይህንን ምክንያት በቂ ለማድረግ፦ «መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው» የሚለውን ቃል ከማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ዘጠኝ ውስጥ አውጥተን መጣል አለብን። ነገር ግን ይህንን ምክንያት በጥሬው መቆም የሚገባውን ሰው በዚያ አገልግሎት እንዳይቆም ለምናደርገው የረቀቀ ዘዴ እንዳንጠቀምበት እናስተውል። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ አገልጋይ ጠፍቶ እንደማያውቅ ሁሉ ሞልቶ ተርፎም አያውቅምና፥ አገልጋይ በዝቶአል በማለት አገልጋዮችን መቆም የሚገባቸውን ስፍራ እንንፈጋቸው።

6) *ቀሰልኩ ማለት።* በሌሎች አገልጋዮች ምክንያት ቆስያለሁ ብሎ አገልግሎቱን የሚያቆም አገልጋይ፥ ማንን እንደሚያገለግል ገና ያልተረዳ አገልጋይ ነው። ዳዊት ከንጉስ ሳኦል ፊት ሸሸ እንጂ ከእግዚአብሔር ፊት አልሸሸም። ነብያት ስለ እግዚአብሔር ስም ሲመቱ አጸፋ ከመመለስ ተገቱ እንጂ በውስጣቸው የሚቃጠለውን የአምላካቸውን ቃል ከመናገር አልተገቱም። በዘመናቸው ጌታን አክብረው ያለፉ አገልጋዮች ሁሉ ስለ ስሙ ተረገጡ እንጂ አገልግሎታቸውን ረግጠው አልሄዱም።

7) *የሰውን ማንነት አለመቀበል።* ሁላችንም የሚስማማን ዓይነት የሰው ባህሪይ አለን። ለምሳሌ፥ እንዳንዶቻችን ፈጣን ሰው ይስማማናል፤ ሌሎቻችን ደግሞ የተረጋጋ ሰው ይማርከናል። የሰው ማንነቱ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ስጦታ በመሆኑ ልንቀበለውና ጌታንም ልናመሰግን ሲገባን የምንናናቅበት ከሆነ ጉዳቱ እጅግ የከፋ ይሆንብናል። ለምሳሌ፥ ከአራቱ የተቀቡ ሰባኪዎቻችን አንዱ ነገር ስለሚያረዝም ሌላው ደግሞ ስለሚያሳጥር ከአገልግሎት በብልሃት እያገለልናቸው ከሄድን፥ ሁሉት አገልጋዮች ይቀሩናል። ምናልባት ደግሞ ከቀሩን ከሁሉቱ፥ አንዱ በጣም ስለሚሮህ፥ ሌላኛው ደግሞ በጣሙን የለሰለሰ ስለሆነ ከናቅናቸው፥ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ባዶዋን ቀረች ማለት አይደለምን? እባካችሁ፥ እግዚአብሔር ተቀብሎ ያነሳውን አገልጋይ የሚያድግበትን መንገድ እንፈልግለት እንጂ መልሰን አንጣለው።

6

ወጀብ፥ ወጀብ፥ ወጀብ

ምዕራፍ 7፥ 1–60



በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በርዝመቱ የታወቀው ንግግር በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ይገኛል። ሊቀ ካህናቱ በእስጢፋኖስ ላይ የተሰነዘረውን ክስ ካደመጠ በኋላ መድረኩን ለእስጢፋኖስ ሰጠው። እርሱም አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ ለተሰበሰቡት ሁሉ የመከላከያ ምላሹን ይናገር ጀመር።

አብርሃም የሚሄድበትን ሳያውቅ እግዚአብሔርን በመታዘዝ የነበረበትን ሥፍራ መልቀቅ ነበረበት። ይህንንም ለማድረግ እምነት አስፈልጎት ነበር። አብርሃም እርሱ ራሱ ሳይሆን ዘሩ የተስፋውን ቃል እንደሚቀበል በእምነት ተመለከተ።

እስጢፋኖስ ብዙም ሳይቆይ ወደ ዮሴፍ ተሸጋገረ። እግዚአብሔር ከሰጠው ራእይና በአባቱ ፊት ከነበረው ሞገስ የተነሳ ወንድሞቹ ዮሴፍን ቀኑበት፥ ሸጡትም። እግዚአብሔር ግን የግብፅን ንጉሥ ተጠቅሞ ለዮሴፍ ሞገስን ሰጠው። ዮሴፍም ከራሱ አልፎ ለቤተሰቡ ሁሉ በረከት ሆነ።

በመቀጠልም እስጢፋኖስ የሙሴን አስደናቂ ሕይወት ይተነትን ጀመር። ሙሴ የራሱ ወገኖች በጥርጣሬ ዓይን የሚመለከቱት ሰው ነበር። በሰው አገር ተወለደ (ቁ. 20)፥ በሰው አገር ተማረ (ቁ. 22)፥ ጥሪውን በሰው አገር ሆኖ ተቀበለ (ቁ. 30)፥ አገልግሎቱን በሰው አገር ተቀምጦ አከናወነ (ቁ. 34)። በዚህ ሁሉ ግን እግዚአብሔር አልተወውም ነበር።

እስጢፋኖስ የእነዚህን የእምነት አርበኞች ታሪክ ባጭሩ ከተነተነ በኋላ ቀስ በቀስ ሊናገር ወደፈለገው ፍሬ ነገር የደረሰ ይመስላል። የንግግሩ መሪ አሳብ እስራኤላውያን የተላከላቸውን መሪ አለመቀበላቸው ላይ ያተኮረ ነበር። እግዚአብሔር በሙሴ እጅ ያደረገውን ድንቅና ተአምራት በመናቅ እስራኤላውያን አመጹ። ፈታቸውንም አዘውትረው ወደ ጣኦት መለሱ። ይህንን ሁሉ ዝርዝር ሃተታ በማስታከክ ነበር

እስጢፋኖስ በሸንጎው የተሰበሰቡትን የከሳሾቹን አንገተ ደንዳናነት በግልጽ የተናገረው። በዚህም አንገተ ደንዳናነታቸው ምክንያት የተቀባውን ክርስቶስን ገደሉት። ይህንን እውነት በሰሙ ጊዜ በጣም ተቆጥተው ከዚህ በፊት በነቢያት ላይ እንዳደረጉት ሁሉ በእስጢፋኖስም ላይ የሞትን ፍርድ ፈረዱበት። እስጢፋኖስ ግን የእምነቱ ጀማሪና ፈጻሚ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳደረገው ለገዳዮቹ ምህረትን እየለመነ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያውን የሰማዕትነትን ማእረግ ተጎናጸፈ።



ከቀደሙን የእግዚአብሔር ሰዎች የምንማረው ይህንን ነው። አንድ የእግዚአብሔር ሰው ከሰማይ የተሰጠውን ጥሪ ተቀብሎ የመጀመሪያውን እርምጃ መራመድ በሚጀምርበት ጊዜ የፈተና ወጀብ ከያለበት መጉረፍ ይጀምራል። ነገር ግን ተስፋ የማይቆረጥበት ጌታ ዛሬም «በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው» (ናሆ. 1፥ 3)። አገልጋይ በሚያልፍበት ሁኔታ ሁሉ የጠራውን ጌታ ቢጠብቅ፥ የኋላ ኋላ ድል የጌታ ነው።

ከከሃዲዎች የሚነሳውን ወጀብ ሳንቆጥር፥ በጥንት የነበሩ አገልጋዮች ከውስጣቸው፥ ማለትም ከግል ሕይወታቸው ይነሳ የነበረ ወጀብ ነበራቸው። ከዚያም አልፎ ደግሞ አሉልኝ ከሚሏቸው ወገኖቻቸው አቅጣጫ ያልተጠበቀ የወጀብ ጎርፍ ሲያጥለቀልቃቸው ይታዩ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከተው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሰባት ውስጥ የተጠቀሱትን በአገልጋይ ላይ የሚመጡትን በጣም የተለመዱ አራት የወጀብ ዓይነቶችን ይሆናል።

I. የውሳኔ ወጀብ (7፥ 1–8)።

ይህ ዓይነቱ ወጀብ አብርሃምን አንገዳግዶ ያለፈ ወጀብ ነው። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት፥ አብርሃም የሚሄድበትን ሳያውቅ እግዚአብሔርን በመታዘዝ የሚኖርበትን ሥፍራ መልቀቅ ነበረበት። ይህንንም ለማድረግ እምነት አስፈልጎት ነበር። አብርሃም እርሱ ራሱ ሳይሆን ዘሩ የተስፋውን ቃል እንደሚቀበል በእምነት ተመለከተ። አብርሃም፦ «ከአገርህና ከዘመዶችህም ወጥተህ ወደማሳይህ ወደማንኛውም ምድር ና» ተብሎ ሲነገረው በአእምሮው ያለፈውን

የውሳኔ ውጣ ውረድ መገመት አያዳግትም። የለመደውን ስፍራ በቀላሉ መልቀቅ ያን ያህል የቀለለው አይመስለኝም። ሰመሆኑ አብርሃም ያላለፈው የውሳኔ ዓይነት ምን አለ? አብርሃም የሚቀጥሰው ማደሪያው የት እንደሆነ ሳያውቅ በዘላንነት በኖረበት ዘመን ሁሉ፦ «በዚህ ሁኔታ እስከመቼ?» ብሎ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይልቅ ለጊዜው የተመቻቸ ሕይወት የሚሰጠውን ምርጫ መከተል ይችል ነበር። አንተም በዚህ ሁኔታ እንደምታልፍ አስታውስ፤ ልብህንም አዘጋጅ። አብርሃም የሚቀጥለው ምግቡ ከወዴት እንደሚመጣ በማያውቅበት ጊዜ ምግብ ፍለጋ ወደ ግብፅ መሄዱ፦ «የእግዚአብሔር ሰው ሆኜ እንዴት በዚህ ሁኔታ ውስጥ አልፋለሁ» የሚያሰኝ ሕይወት ነው። አንተም፤ አገልጋይ ሆይ፤ በዚህ ሁኔታ የምታልፍበት ጊዜ ሊኖር እንደሚችል አትዘንጋ፤ በታማኝነትም ለመቆም ተዘጋጅ። አብርሃም በዓይኑ ለማያየው የተስፋ ቃል በእምነት ሲሮጥ ማየት ያስገርማል፤ በቱሎ የሚገኝን ሁኔታ ለመጨበጥ ጥላችሁ ጥፉ ያሰኛል። አንተም ለጊዜው ፍሬ ለማታይበት ሁኔታ ለጌታ ስትል ብቻ በእምነት መሮጥም የሚገባህ ጊዜ አለና ጸንተህ ቁም። አብርሃም የጌታ ዓላማ በሕይወቱ እንዲፈጸም ሲል ከወንድሙና ከዘመዶቹ ሁሉ መለየቱ ትልቅ ውሳኔን የሚጠይቅ ነው። አንተስ ይህንን የመሰለ ውሳኔ ለጌታ ክብር መወሰን ቢያስፈልግህ ለዚያ ተዘጋጅተሃል? አብርሃም ከጌታ የተቀበላት ሣራ ለጊዜው ልትሰጠው ያልቻለችውን ዘር ለማግኘት ወደ አጋር ሮጠ። አንተስ ከዚህ ምን ትማራለህ? አብርሃም የጌታን ፈቃድ ለመከተል ሲል አንድያ ልጁን ለመሰዋት ፈቃደኛ በመሆን የጌታን ፈቃድ መረጠ። አንተስ ለዚህ ዓይነቱ ምርጫ ተዘጋጅተሃል? እነዚህ ሁሉ አብርሃም ያለፈባቸው ሁኔታዎች ውሳኔን የሚጠይቁ ጉዳዮች ናቸው። አገልጋይ ሆይ፤ እኔና አንተ በሕይወታችን የውሳኔ ወጀብ ሲያናውጠን በጌታ ታምነን ብንጸና፦ «እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም» (2 ቆሮ. 4፥8)።



አንዴ የወሰኑትን ውሳኔ መለወጥ መሸነፍ መስሎ የሚታያቸው ሰዎች ግትረኛነት ይነዳቸዋል። በተቃራኒው ደግሞ፤ ሁኔታዎች በተለዋወጡ ጊዜ ሁሉ አሳባቸውንና ውሳኔያቸውን የሚለዋውጡ ሰዎች ጀምረው የሚፈጽሙት ቁም ነገር አይኖራቸውም። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። እንደየሁኔታው የማትቀያየር የውሳኔ ሰው ብትሆን ከተቀበልከው ራእይና ካወጣሃቸው

እቅዶች ፈጥነህ የማትናወጥ ታማኝ አገልጋይ ትሆናለህ። ሆኖም በጎዳናህ ላይ መለወጥ የሚገቡህ እቅዶችህን ጌታ እንዲያሳይህ የምትመች አገልጋይ ለመሆን ትጋ።

II. የቅንአት ወጀብ (7፥9–19)።

አንዱን አገልጋይ የሚያስጨንቀው ወጀብ ለሌላው አገልጋይ ምኑም አይደለም። ለዮሴፍ የውሳኔ ወጀብ ጸጥ እንዳለ ባህር ነበር። ማንም ሊፈታ ያልቻለውን ሕልም በእግዚአብሔር ስም እፈታዋለሁ ብሎ መጋፈጥ ለዮሴፍ ቀላል ነበር። ለጊዜው ከሚገኝ የፍትወት ደስታ ይልቅ ለእግዚአብሔር መቀደስን በመምረጥ ለኃጢአት በጋበዘችው ሴት ላይ ጨርቁን ጥሎ መሮጥም የዮሴፍን ቆራጥነት የሚያሳይ ነው።

ዮሴፍን የፈተነ ወጀብ የቅንአት ወጀብ ነበር። ይህም ወጀብ የተነሳው ከወንድሞቹ ዘንድ ነበር። ምናልባት ዮሴፍ ለዚህ የቅንአት ወጀብ የተጋለጠው የራእይ ሰው በመሆኑ ነው ብዬ አምናለሁ። እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ለወንድሞቹ ባያካፍል ኖሮ ይህ የቅንአት ወጀብ ባልተነሳ ነበር።

ዛሬም በብዙ አገልጋዮች ላይ ይህ ዓይነቱ የቅንአት ወጀብ ይነሣል። አንድ አገልጋይ ጌታ ጠርቶኛል ብሎ ቆርጦ በሚነሳበት ጊዜ በመንገዱ ላይ በቅንአት የሚቃጠሉ «ወገኖች» እንደሚያጋጥሙት መዘንጋት የለበትም። እግዚአብሔር ግን በዚያ ወጀብ ውስጥ መንገድ አለው። አገልጋይ ሆይ፤ ጌታ የመራህን ነገር ከመፈጸም አንተን ሊያስቆምህ የሚችል ኃይል ቢኖር የራስህ ውሳኔ ነው። የአገልግሎት ነገር ገና ያልገባቸው ሰዎች በቅንአት ቢያስቸግሩህም፤ ለጌታ ክብር ከመሮጥ አይከልክሉህ። በጌታ ታምነህ ሩጫህን በትዕግስት ቀጥል። በቅንአት ወጀብ ለመናወጥ ልብህን ብትከፍት ግን፤ በልብህ እንደ እሳት የነደደውን ራእይ በዓይንህ ሳታየው ታልፋለህ። ቅንአት ለነገሠባቸው ሰዎች መሸነፍ በጣም አደገኛ ነገር ነው። ቅንአት ያለበት ሰው በወንድሙ ላይ ምንም ከማድረግ አይመለስም። ስምህን ሰዎች በከንቱ ሲያጠፉት አትናወጥ። ያላደረከውን አድርገሃል ስትባል በርታ፤ ልብህም ይጽና። በክፉ ቅንአት የተሞሉ ሰዎች ለሚያደርጉት የተንኮል ሥራ በቀላሉ እጅህን ከሰጠህ፤ አወዳደቅህ አያምርም፦ «ቅንዓትም

እንደ ሲአል የጨከነች ናትና» (መኃ. 8፥6)። አገልጋይ በሕይወቱ ላይ የሚነሳውን የቅንአት ወጀብ በጌታ ኃይል መቋቋም ብቻ ሳይሆን፥ እርሱም በሌሎች ላይ በቅንአት ከመነሣት ልቡን ሊጠብቅ ይገባዋል።

III. የንቀት ወጀብ (7፥20–43)።

አብርሃምን ከውስጡ የተነሳ የውሳኔ ወጀብ አናወጠው። ዮሴፍን ደግሞ ከወንድሞቹ
የመነጨ የቅንዓት ወጀብ ፈተነው። ሙሴ ደግሞ በተራው የወጀብን ጽዋ ይጎነጭ ጀመር። መሴን የተፈታተነ ወጀብ የንቀት ወጀብ ይባላል። ሙሴ ለአገልግሎት ሊሰማራ ከወሰነበት ጊዜ አንስቶ እስከሞተባት ቀን ድረስ ያገለግላቸው ዘንድ ከእግዚአብሔር የተቀበላቸው ወገኖቹ አገልግሎቱን የተቋቋመባት ሰው ነበር። እስጢፋኖስ በሚገባ እንደተረከው፦ «ወንድሞቹም እግዚአብሔር በእጁ መዳንን እንዲሰጣቸው የሚያስተውሉ ይመስለው ነበር፥ እነርሱ ግን አላስተዋሉም» (ቁ. 25)። ለመሆኑ ሙሴ ያልጠገበው ዛቻ ምን ነበር? «አንተን በእኛ ላይ ሹምና ፈራጅ እንድትሆን የሾመህ ማን ነው?»፤ «ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ ምን እንደሆነ አናውቅምና» (ዘጸአ. 32፥1)፤ «በውኑ እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ ተናግሯልን? በእኛስ ደግሞ የተናገረ አይደለምን?» (ዘኍል. 12፥2)፤ «ሕዝቡም ሙሴን ተጣሉት» (ዘኍል. 20፥3)። በእውነትም ሙሴ ንቀትን የጠገበ ሰው ነበር። እግዚአብሔር ግን በዚያ ሁሉ ወጀብ ውስጥ መንገድ ነበረውና ሙሴን ከፍ ከፍ አደረገው።

ሌሎች አገልጋዮች ማንነትህን፥ ጥሪህን፥ አገልግሎትህንና ከጌታ የተቀበልከውን መንፈሳዊ ነገር ሁሉ አልቀበልም ያሉ ሲመስልህ በቶሎ አትረበሽ፤ ጌታ በዚያም ውስጥ መንገድ አለው። ብልጠትን ተጠቅመህ፥ ወይም ደግሞ በጉልበትህ ተጣልተህና ተጨቃጭቀህ ወደ አገልግሎት ለመውጣትና ተቀባይነት ለማግኘት ከመጣጣር ተጠበቅ። ጊዜ የማይፈታው ነገር የለምና፦ «ይህም በጌታ ጸጋ ያልፋል» እያልክ በትዕግስት ጉዞህን ቀጥል። የእርሱ ወደሆኑት መጥቶ ተቀባይነትን ያላገኘውን የጦር መሪህን ክርስቶስን አስብ (ዮሐ. 1፥11)።



አንዳንዶች ጌታን በሙላት ለማገልገል በጣሙን የተከበሩና በሁሉ ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ መሆን የሚገባቸው ይመስላቸውና አገልግሎታቸው ላይ ከማተኮር ይልቅ ሰዎች በእነርሱ ላይ ያላቸውን አስተሳሰብ ለማወቅ ሲጨነቁ ይታያሉ። ሌሎች ደግሞ ስለ ስሙ መናቅ አለብኝ በሚል ሳቢያ ለራሳቸው በረከትም ሆነ ለጌታቸው ክብር ለማይውል ጥልና ክርክር ራሳቸውን አጋልጠው ይሰጣሉ። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ቁም ነገሩ በሌሎች ዘንድ መናቅህና አለመናቅህ ሳይሆን ነገር ሁሉ ለጌታህ ክብር መከናወኑ መሆኑን አትዘንጋ። እግዚአብሔር በመከበርህም ሆነ በመናቅህ ውስጥ መንገድ አለው። ያንን የመወሰኑ መብት ግን ለአንተ አልተሰጠህምና ጌታ በሚያሳልፍህ ጎዳና በትህትናና በማስተዋል ተመላለስ።

IV. የሞት ወጀብ (7፥44–60)።

አብርሃም፥ ዮሴፍና ሙሴ ያለፉበትን ወጀብ እስጢፋኖስ ካብራራ በኋላ፥ በመጨረሻ እነዚህን ሁሉ የወጀብ ዓይነቶች አልፎ ለሞት የተሰጠውን አዳኛችንን ክርስቶስን በንግግሩ ጠቀሰ። ይህንን ሁሉ ከተነተነ በኋላ እርሱም ያንኑ የሞት ጽዋ ተነነጨ። ክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ክብርና ለሰው ልጅ መዳን ሲል ከተቃዋሚዎች በመጣ የሞት ወጀም ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ። እስጢፋኖስም የዚህ ጽዋ ተካፋይ ነው። በክርስቶስ የነበረው ጽናት በእስጢፋኖስ ዘንድም ነበር። በክርስቶስ የነበረው የይቅርታ መንፈስ በእስጢፋኖስም ዘንድ ነበር። ይህ ሁኔታ ዛሬም ከእኛ ይጠበቃል።

ይህ ዓይነቱ ወጀብ (የሞት ወጀብ) አንድ አገልጋይ ለክርስቶስ ስም ሲል የሚያልፍበት የመጨረሻው ደረጃ ነው። ሲያልፉበት መራራ ነው፥ ውጤቱ ግን ይጣፍጣል። ሲያስቡት ያስፈራል፥ ሲገቡበት ግን በደስታ ያስፈነድቃል። ሲቀርቡት ድቅድቅ ጨለማ ነው፥ ነገር ግን ብርሃኗ ወደማይጠፋው ዘላለማዊ ቤት መሸጋገሪያ በር ነው። የወጀቡን መንስኤዎች ለፍርድ፥ በወጀቡ የተመቱትን ደግሞ ለእክሊል ያዘጋጃል።

አገልጋይ ሆይ፥ በአገልግሎትህ ዘመን የሞትን ድምጽ የምትሰማባቸው ጊዜያት አይጠፉምና ልብህን አዘጋጅ። ውሳኔህ ከባድ ነውና ዋጋህን ተምን። ወስኛለሁ ካልክ፥ እንተም እንደ ጳውሎስ

ወጀቡን ካለፍክ በኋላ፦ «እዎን፥ ሙታንን በሚያስነሳ በእግዚአብሔር እንጂ በራሳችን እንዳንታመን፥ እኛ ራሳችን የሞትን ፍርድ በውስጣችን ሰምተን ነበር» (2 ቆሮ. 1፥9) እያልክ ከሚገጥምህ የሞት ወጀብ ያዳነህን የክርስቶስን ክብር ትመሰክራለህ። ጌታ የፈቀደልህም የዚህን የሞት ጽዋ ጠጥተህ ታልፍ ዘንድ ከሆነ፦ «ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፥ ሞትም ጥቅሜ ነውና» (ፊልጵ. 1፥21) የሚል ዜማ ከፀባኦት እንደሚላክልህ አትርሳ።



«የሞት ወጀብ? ጌታን ካመንን እንዴት ለሞት አልፈን እንሰጣለን?» በማለት የጌታን ልዕልና የሚጠይቁ ጥቂቶች አይደሉም። በሌላ ጎኑ ደግሞ ጌታን ማገልገል ማለት የሁሉ መጫወቻ ሆኖ መቅረት እንደሆነም የሚመስላቸው ብዙዎች ናቸው። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። በምን ዓይነት ሁኔታ እንደምታከብረው ጌታ ጠንቅቆ ስለሚያውቀው የጀመረውን እስኪጨርሰው ድረስ ሁሉን ለእርሱ ተውለት። ጌታ ካልፈቀደ ከጸጉርህ አንዳችም እንዳትወድቅ እወቅ። ፈቃዱ ከሆነ ደግሞ ከአንተ ቀድመው ያለፉ የጌታ ባሪያዎች ባለፉበት ሁሉ ታልፍ ዘንድ እድሉንና ጸጋውን ሊያጎናጽፍህ ይችላልና ለሚመጣው ሁሉ የተዘጋጀህ ሁን። ዘወትር ከጌታ ጋር የምትቆም አስተዋይ አገልጋይ ከሆንክ በወጀብ ላይ እየጋለብክ ከአንዱ የጌታ ፈቃድ ወደ ሌላው ትሸጋገራለህ። ይህንን ለማድረግ ግን ብዙ ማስተዋል የሚያስፈልጉህ ነገሮች አሉ። በወጀብ ውስጥ ባለፍክ ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች ማስታወሱ ይጠቅምሃል ብዬ አምናለሁ።

1) ነገር ሁሉ በጌታ ቁጥጥር ስር መሆኑን አትዘንጋ። እግዚአብሔርን ካስቀደምክ፥ እርሱ ተራምዶበት ያልፈተነው ወጀብ ውስጥ አትግባምና አትፍራ። ሐዋርያት ለወንጌል ከመሰደዳቸው በፊት ክርስቶስ ተሰድዷል፥ ከመገደላቸውም በፊት ተገድሏል። ክርስቶስን ለማናወጥ መጥቶ የነበረ ወጀብ መንስኤው ከማያምኑት ሰዎች ብቻ አልነበረም። ነገር ግን እግዚአብሔርን እናውቀዋለን የሚሉትም ሰዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ መከራውን አላይተውት አልፈዋል። ክርስቶስ ሁሉን መዝኖና ወስኖ አልፏልና አንተም በክርስቶስ ሁሉን ትችላለህ።

2) ለሚያምኑም ሆነ ለማያምኑ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን ነገር ከማማት ተጠንቀቅ። በወጀብ ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ ያለህበትን ሁኔታ ሌሎች ሰዎች እንዲያደምጡህና እንዲገነዘቡልህ ትሻለህ፥

ብዙውን ጊዜ ግን ላታገኝ ትችላለህ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፥ ላገኘኸው ሰው ሁሉ የሆነውንና ያልሆነውን ታሪክ ከማውራት ተቆጠብ። በተለይም የምታልፍባቸው ወጀቦች ከክርስቲያኖች አቅጣጫ የመጡ ሲመስልህ በክርስቲያኖች ላይ መልካም ያልሆኑ ቃላቶችን ከመሰንዘር አንደበትህን ግታ።

3) ከእልህ ልብህን ጠብቅ። የምታልፍበት ወጀብ በጌታ ቁጥጥር ስር ከሆነ፥ ከሰዎች ጋር እልህ መያያዝ አይገባህም። እንደውም ከምታልፍበት ሁኔታ የምታገኘውን ትምህርት በምስጋና መንፈስ መቀበል አለብህ። ለእልህ ልብህን መክፈትህ አገልግሎትን ወደማቆም ደረጃ ያደርስሃልና አስብበት። ለማን ብለህ ደሙን እንደውሃ ያፈሰሰልህን ጌታህን ከማገልገል ትርቃለህ?

4) ጌታ ያልፈቀደው ወጀብ ውስጥ እንዳትገባ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ውሰድ። አብርሃም እንዴ ወደ አጋር በመሄድ፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሣራ እህቴ ነች ብሎ በመዋሸት እንዳደረገው፥ በፊትህ ከሚደነቀረው ወጀብ ማምለጫ አቋራጭ መንገድ ከመፈለግ ተቆጠብ። ዮሴፍ እንደተሳሳተው፥ ጌታ በልብህ ያስቀመጠውን ሁሉ ካለጊዜውና ካለቦታው ለሰዎች ሁሉ አታካፍል። ሙሴ እንዳጠፋው፥ የጌታ ቀን እስከሚመጣ ድረስ ከመታገስ ይልቅ በሥጋህ ወደ አገልግሎት ለመውጣት እትቸኩል።

7

ከቤተ መቅደስ የማይጠፉ ሰዎች

ምዕራፍ 8፥1–40



የእስጢፋኖስ ተወግሮ መሞት የብዙዎችን አክራሪ አይሁዳውያን ቁጣ አባባሰው። ስለዚህም ኢየሩሳሌም ለክርስቲያኖች የማትመች ስፍራ ስለሆነች ከሐዋርያት በቀር ሁሉም ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ። ሐዋርያት በኢየሩሳሌም ቆይታቸው ከእስራት በምን ዓይነት ሁኔታ እንደዳኑ ባይገለጽም፥ በአካባቢው ባሉ መልካም ፈቃድ በሞላባቸው ተራ ዜጎች ተተግነው ከእስራት አመለጡ ብሎ መገመት ከእውነት የራቀ አይሆንም። ከሐዋርያት በስተቀር ክርስቲያኖች ሁሉ ተሰድደው ከኢየሩሳሌም በመውጣታቸው፥ እስጢፋኖስን የቀበሩት ሰዎች በጸሎት ይተጉ የነበሩ ፈሪሳውያን ናቸው ብሎ ከማሰብ በስተቀር የተሻለ ማብራሪያ አይገኝለትም። እነዚህ ሰዎች ምናልባት የሽንኀው ውሳኔ ከልክ ያለፈ ጭካኔነት የተሞላው ነው ብለው ያመኑ ይሆናሉ። የሽንኀው ውሳኔ ግን ሳውል በክርስቲያኖች ላይ ያለበትን እልህ ያረካው አይመስልም። ስለዚህም፥ የቤተ ክርስቲያን ማፍረስ ጥረቱን ቀጠለ።

የክርስቲያኖች መሰደድ ያልተጠበቀ ውጤት በየስፍራው አስከተለ። ከእነዚህ ስፍራዎች አንዱ ሰማርያ ሲሆን፥ በዚያም በፊልጶስ አማካኝነት ወንጌል በመላት ተሰበከ፥ አጋንንት ከሰዎች ወጡ፥ ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ። ሲሞንም የዚህ ታላቅ ንቅናቄ ውጤት ነበር። በሰማርያ እየጠነቆለ ሕዝብን ያስት የነበረ ይህ ሰው በክርስቶስ አምኖ ከፊሊጶስ ጋር ይተባበር ነበር። የሲሞን ለውጥ እውነተኛ መሆኑና አለመሆኑ አከራካሪ ጉዳይ ሲሆን፥ አምኖ ለመጠመቁ ግን ሉቃስ ምስክር ነው።

በስደት ምክንያት የተበተኑት ክርስቲያኖች በሰማርያ ያበሰሩትን ወንጌል ለማጠናከር ሐዋርያት ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው። የሰማርያም አዲስ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ተጥለቀለቁ። በዚያን ጊዜ ነበር ሲሞን የመንፈስ ቅዱስን ሥልጣን በገንዘብ ሊገዛ የሞከረው። ይህም መከራው ጠማማ ልብ እንደነበረው ሲያስመሰክር፥ ፈጥኖ

መጸጸቱ ደግሞ የንስሐ ልብ እንደነበረው ያሳያል። ጴጥሮስ ሲሞንን ፊት ለፊት ከገሰጸው በኋላ ከዮሐንስ ጋር በሰማርያ ባሉ ብዙ መንደሮች ወንጌልን ሰብከው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።

የፊልጶስ ተልእኮ ገና ያለቀ አይመስልም። በእግዚአብሔር መልአክ ተመርቶ ወደ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ቀረበ። ጃንደረባው ያነብበው የነበረውን የነብዩን የኢሳይያስን ትንቢት አልተረዳውም ነበርና ፊልጶስ በሚገባ አስረዳው። ጃንደረባውም አምኖና ተጠምቆ መንገዱን በደስታ ቀጠለ። ፊልጶስን ግን የጌታ መንፈስ ነጥቆ በአዛጦን ለወንጌል ሥራ አሰማራው።



«ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና» (ዮሐ. 2፥24)።

በእርግጥም ጌታ ሰዎችን የሚያውቀው እንደ ሰውነቱ ካሳለፈው ልምምድ፥ እንደ አምላክነቱ ደግሞ ልብንና ኩላሊትን ስለሚመረምር ነው። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ብዙ ዓይነት ሰዎች አሉ። ስለዚህም የሰዎችን ማንነት ማወቅ ለአገልግሎታችን ብዙ ይጠቅመናል። የሰዎችን ማንነት ለማወቅ ደግሞ ከጌታ መማር ያሻናል። ወደ ቤተ ክርስቲያን ያዘወተረ ሁሉ የተሰወጠ አይደለም። ለአገልግሎት የሮጠ ሁሉ በቅን ልቦና የሚሮጥ አይደለም። አንገቱን ያቀረቀረ ሁሉ እየጸለየ አይደለም። ከንፈሩን የመጠጠ ሁሉ ሩሀሩህ አይደለም። ዝም ያለ ሁሉ አዋቂ አይደለም። የሁሉንም ልብ ጌታ ብቻ ያውቃል፥ እኛም ሁሉንም ከፍሬው እናውቅ ዘንድ ይህንን መክሮናል።

ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ዓይነት ሰዎች አሉ። እንደ አገልጋዮች፥ ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ የማወቅ ሃላፊነት ያለብህ ሲሆን፥ በተለይም ከዚህ በታች የምንመለከታቸው ሰዎች ከቤተ መቅደስ ውስጥ ዘወትር አይታጡምና ጠንቅቀን እንወቃቸው። ባህሪያቸውን እናጥናው። በአጠገባችን እያሉ ሳናውቅ ዝም ብለን ሩጫችንን ብንቀጥል ፍሬያማነታችን ይቀንስብናልና እናስተውላቸው። ጌታ በሚሰጠን ጥበብ እየታመንን እንደየሁኔታቸውም እንያዛቸው።

I. እስጢፋኖስን የሚተኩ ሰዎች (8፥1–8)።

ሙሴ ቢሞት ኢያሱ ተነሳ፤ ኤሊ ቢደክም ብላቴናው ሳሙኤል በረታ፤ ሳኦል ቢስት ታናሽ የሆነው ዳዊት በአምላኩ ስም ወጣ፤ ኤልያስ ሲነጠቅ መጎናጸፊያው በኤልሳዕ ላይ ወደቀ። አሁን ደግሞ እስጢፋኖስ ተወግሮ ሲሞት ቅባቱ በፊልጶስ ላይ የተንጠባጠበ ይመስላል። ምንም እንኳ እስጢፋኖስ ተወግሮ ቢሞት፥ እርሱ ሲሠራ ከነበረው ያላነሰ ድንቅ ሥራ በጌታ ስም እየሠራ ፊልጶስ ተነሳ።

አንዳንድ ጊዜ ካለ እኛ አገልጋይ የሌለ ሲመስለን አገልግሎታችንን ያቆምን ቀን የጌታ ቤት ባዶ የሚቀር ይመስለናል። ወይም ደግሞ አንድ አገልጋይ አገልግሎቱን ትቶ ለመሄድ የተነሳ እንደሆነ፦ «ምን ይሻላል?» ብለን እንጨነቃለን። እግዚአብሔር ግን ዘወትር የተቀባ አገልጋይ አለው። እግዚአብሔር የሚፈልገው የተቀቡትን ዓይቶና አክብሮ በስፍራቸው የሚያሰልፍ አገልጋይ ነው። ግና ምንም ያልተሞከሩ፥ በውስጣቸው የጌታ እሳት እንደ ችቦ እየነደደ ያሉ አገልጋዮች በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሞልተዋል። እነዚህን ብላቴኖች እኛ እየለየን ካላወጣናቸውና ለአገልግሎት ካላሰለፍናቸው የተሰፋ መቁረጥ መንፈስ ብዙዎችን ላጋደመበት እንቅልፉ የሚመለምላቸው ጊዜ ሩቅ አይሆንም። በተለይም ለረጅም ጊዜ በአገልግሎት ላይ የቆዩ አገልጋዮች የራሳቸውንና ለብዙ ዘመን አብረዋቸው ያገለገሉትን አገልጋዮች ስጦታ ብቻ ለማየት ዓይናቸውን በቄላንቄል የሚከፍቱበት ጊዜ ሊያበቃ ያስፈልገዋል። በዚያ ምትክ ዓይናቸው በሰፈው ተከፍቶ በአካባቢያቸው ወንበር አሟቂ ሆነው የቀሩትን የተቀቡ አገልጋዮች ጸጋ የሚያዩበትን ዘመን ጌታ ያምጣልን።



እግዚአብሔር የሰው ድጋ አይደለም በሚል ሰበብ አገልጋዮችን ዛሬ ከፍ ነገ ደግሞ ዝቅ እንድናደርጋቸው የጌታ ፈቃድ አይደለም። በሌላ ጎኑ ደግሞ ይህ አገልጋይ ከዚህ ቦታ ከተነሳ አገልግሎቱ ባዶውን ይቀራል ብሎም መጨነቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ጌታ በአጠገብህ ያቆመልህን አገልጋዮች ጌታ በሰጣቸው ክብር እያከበርክ ስትጓዝ፥ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚጎድለው የአገልግሎት ስፍራ ሁሉ በእርግጥም የሰው ድጋ ሆኖ

የማያውቀው እግዚአብሔር በጊዜው ሊሞላው እንደሚችል በሙሉ ልብህ እመን።

II. የዓመጽ እስራት የያዛቸው «ክርስቲያኖች» (8፥9–25)።

በቤተ መቅደስ ውስጥ እንደ ፊልጶስ እስጢፋኖስን የሚተኩ አገልጋዮች ብቻ አይደሉም ያሉት። እንደ ሲሞንም በእስራት የተተበተቡ «ክርስቲያኖች» አሉ። ራሳችንን ከዚህ ዓይነቱ እስራት ካልጠበቅንና ሌሎችንም በዚህ ዓይነት እስራት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ካላወቅናቸው፥ ሁኔታው የሌላውን የንጹሁን ሕይወት ይበክላልና ታላቅ ጥንቃቄ ያሻናል። የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የግልን ፍላጎት ለማጠናከርና ሁኔታዎችን እንደምኞታችን ለመምራት የምንጠቀምበት በዚህ ዓይነቱ ትብታብ ስንያዝ ነው። «እኔ ከእገሌ የተሻለ ስጦታ አለኝ» የሚለውም አስተሳሰብ የዚሁ እስራት የመጀመሪያው ደረጃ ነው። ይህ እስራት እየጠነከረ ሲሄድ፥ ሰዎችን ለመማረክ በእግዚአብሔር ስም የማናደርገውና የማንናገረው ነገር አይኖርም። በሥጋችን አንድን አሳብ አውጠንጥነን ለሰዎች በምንናገረው ጊዜ ተቀባይነት እንድናገኝ ብቻ የጌታን ስም ስናክልበት ልባችንን እንመርምር፥ ንስሐም እንግባ። «የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጎድለው፥ ብዙዎቹም የሚረክሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ» እንጠንቀቅ (ዕብ. 12፥15)።

III. የደህንነት ምስጢር የማይገባቸው ሰዎች (8፥26–40)።

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ከፊልጶስ ጋር ሲገናኝ የትንቢተ ኢሳይያስን መጽሐፍ ሁለት ሦስተኛ አገባድዶ ነበር። የክርስቶስ ነገር ግን ፈጽሞ የገባው አይመስልም። ፊልጶስ በጌታ መንፈስ ተመርቶ የደህንነትን ምስጢር መግለጥ ነበረበት። ይህ ዓይነቱም የደህንነት ምስጢር ፈጽሞ አልገባህ የሚለው ሰው በቤተ መቅደስ አለ።

አንድን ሰው አምስት ጊዜ ጌታን ለመቀበል ሲነሳ ስታየው፥ ችግሩ ይገባህ። ለብዙ ጊዜ በጌታ ቤት ሲመላለስ፥ ነገር ግን አሁንም ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ ካለምንም ቅሬታ ተጠምዶ ስታየው፥ ይህን ሰው አስተውለው። ቋንቋው ሁሉ ሲያስደነግጥህ፥ አስተሳሰቡ

ከተማረው የደህንነት ቃል ጋር አልስማማ ሲልህ፥ ተግባሩ ባህላዊ፥ አረማመዱ ልማዳዊ ሲሆን፥ ለዚያ ሰው ከጌታ ጥበብን መጠየቂያህ ጊዜ ነውና አስብበት። የተለያየ የትምህርት ነፋስ እንደገለባ በቀላሉ አያነሳ የሚወስደውም ከእነዚሁ ውስጥ ነውና ሳይቀድምህ ቅደመው።



አንዳንዶች ዘወትር እየተማሩ ወደ ደህንነት የማይደርሱትን ሰዎች፦ «እርሱ በፍጹም የሚገባው ሰው አይደለም» በማለት በቸልተኝነት ከሃላፊነት ይሸሻሉ። ሌሎች ደግሞ ሰዎችን የመለወጡ ኃላፊነት የእነርሱ ይመስል በስጋቸው በከንቱ ሲደክሙ ይታያሉ። እንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ጥበብን ከጌታ እየለመንክ ሰዎች የሕይወት ለውጥ የሚያገኙበትን ማናቸውም ዋጋ ለመክፈል ተዘጋጅ። ሕይወትን ለመለወጥ የሚችለው ግን አንዱ የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አትርሳ።

ታዲያ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ስላሉት የተለያዩ ሰዎች ለማወቅ ማድረግ የሚገባን ነገር ምንድን ነው? ግሩም ጥያቄ ነው። የሚከተሉትን ነጥቦች ሰንዝሬ አልፋለሁ።

1) ዘወትር መንፈስን የመለየትን ስጦታ ከጌታ እንለምን። ካለመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ማንኛችንም ብንሆን የእግዚአብሔርን መንጋ ልናውቀው ስለማንችል የቅኖችን ቦታ ለጠማሞች፥ የጠማሞችን ደግሞ ለቅኖች እንሰጣለን። ጌታ ይህንን የተባረከ መንፈስን የመለየት ስጦታ በሕይወታችን እንዲሠራ በሚፈቅድበት ጊዜ፥ የሰዎችን ምስጢር እንድናውቅ ሳይሆን ለሚገጥመን ማንኛውም ሁኔታ አስፈላጊውን ምላሽ እንድንሰጥ ጥበብ ይኖረን ዘንድ ነው። ከማንኛውም እንቅስቃሴ ጀርባ ያለን መንፈስ ለማወቅ፥ መንፈስን የመለየት ስጦታ እማራጭ የሌለው መሣሪያችን ነው።

2) አረማመዳችንን ከጌታ ጋር እናድርግ። ከጌታ ጋር መራመድ ስንጀምር ነገሮችን በእርሱ መነጽር ማየት ስለምንችል፥ ሁሉን እንደ አመጣጡ እንመልሰዋለን። አሰበለዚያ አቀራረባችን፥ ፍርዳችን፥ ውሳኔያችንም ሆነ አመለካከታችን ሥጋዊ ይሆንብናል። ከእግዚአብሔር ጋር ያልተጣበቀ አገልጋይ ዘወትር የሚሳሳትና አንድን ነገር ካደረገ በኋላ የሚጸጸት አገልጋይ ነው።

3) ከግምት ሕይወት እንራቅ። በግምት የሚመላለስ አገልጋይ በሰው ሕይወት ውስጥ የሌለውን አለ፥ ያለውን ደግሞ የለም የሚል አገልጋይ ነው። በተለይም ጌታ ለእኛ የሚገልጠውን ነገር ከራሳችን ጥርጣሬና ግምት ጋር ማማታት እይገባንምና መጠንቀቅ ያሻናል። አሳባችንን ለሰዎች በምንገልጽበት ጊዜ፥ የእኛ የግላችን አሳብ ከሆነ ያንን በግልጽ ማስታወቅ ትልቅ ማስተዋል ነው። የምንናገረው አሳብ ደግሞ የመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሆነ ያንንም በግልጽ ማስታወቅ አለብን። የእኛ አሳብና የእግዚአብሔር ድምጽ ሊለይበት የማይችልን ቃላት እየሰነዘርን መንታ አሳብን ያዘለ ነገር መናገር የለብንም።

8

ጌታ የጠራቸውን እናገልግላቸው

ምዕራፍ 9፥1–31



እስጢፋኖስ ሲገደል ሳውል የገዳዮቹ ልብስ ጠባቂ ነበር። ከዚያም በክርስቲያኖች ላይ ያለው ጥላቻ እየተባባሰ በመሄዱ ማሳደዱን ተያያዘው። በዚሁ የሰይጣን ተልዕኮው ተይዞ ወደ ደማስቆ ሲጓዝ ሳለ፥ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ የሆነው ክርስቶስ በመንገድ ተገናኘው። ከእርሱ የበለጠ ኃይል ስለከበበው ሳውል ወድቆ ምህረትን ከመለመን በቀር ምንም አማራጭ አልነበረውም። ከዚያ የሚከተለው የጳውሎስ ታሪክ ለለሚው ሁሉ የሚያስገርም ነው።

ሐናንያ መቼና እንዴት ክርስቲያን እንደሆነ የተገለጸልን ነገር ባይኖርም፥ በደማስቆ የሚኖርና ሕይወቱን ለጌታ አሳልፎ የሰጠ ክርስቲያን እንደነበር ከሉቃስ ገለጻ መረዳት እያዳግትም። ሐናንያ ሳውልን በክፋቱ ነበር የሚያውቀው። ዛሬ ግን ሳውል የተሰበረ ሰው ነው። ብዙዎችን ይጠግን ዘንድ መሰበር ነበረበት። ለብዙዎች ብርሃንን ያስተዋውቅ ዘንድ መታወር ነበረበት።

ሐናንያ ከላይ ለመጣለት ትእዛዝ እሜን ብሎ ቅን ወደሚባለው መንገድ በመሄድ ሳውልን ተገናኘው። ሳውልንም፦ «ወንድሜ» ብሎ ሊጠራው አላፈረም ነበር። ወንጌልንም ካበሰረለትና ከጸለየለት በኋላ እንደ ቅርፊት ያለ ከሳውል ዓይን ወደቀ። የክርስቶስን ወንጌል ለመስበክ ጊዜ ያላባከነው ሳውል፥ በደማስቆ የተቀመጡትን አይሁድ መልስ ያሳጣቸው ጀመር። ያላቸው አማራጭ ሳውልን መግደል ነበርና ይህንኑ ለማድረግ ሲያሸምቁ፥ በደቀ መዛሙርት እርዳታ ከከተማ ወጥቶ ሊያመልጥ ቻለ። የሳውል ለውጥ አስገራሚ ከመሆኑ የተነሳ አይሁድ ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያኖች እንኳ ሊያምኑት አልቻሉም። በዚያን ጊዜ ነበር በርናባስ ሳውልን ከሐዋርያት ጋር እንዲተዋወቅ ያደረገው። ከሳውል ለውጥ በኋላ የምንመለከተው በክርስቲያኖችና በአይሁድ መካከል የነበረው ሁኔታ ለጊዜው መረጋጋቱን ነው። አብያተ ክርስቲያናትም እየታነጹና እየበዙ ይሄዱ ነበር።



እግዚአብሔር «ለሙሴ መንገዱን አስታወቀ፥ ለእስራኤል ልጆችም አደራረጉን» (መዝ. 103፥7)። ከዚህ መዝሙር የምንማረው፥ እግዚአብሔር ለአገልግሎት ለለየው ለሙሴ መንገዱን እንዳስታወቀው ሲሆን፥ ለተቀሩት ሕዝብ ደግሞ ሥራውን ብቻ እንደገለጸ ነው። ቁም ብሎ እግዚአብሔር በሌሎች የሚሠራውን ሥራ መመልከትና ጌታን ማመስገን አንድ ነገር ሲሆን፥ የእግዚአብሔር ሥራ በሚገባ ይሠራ ዘንድ መንገዱን ማወቅና የሥራው ተካፋይ መሆን ደግሞ የተለየ ነገር ነው። እነዚህ ሁለት ነገሮች በደረጃም ሆነ በክብደት ይለያያሉ። የእግዚአብሔርን ሥራ ብቻ ሳይሆን መንገዱንም ያስተውሉ ዘንድ ለአገልግሎት የተጠሩ ሰዎች የተለየ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ለዚህ ነው። እነርሱም የእግዚአብሔርን መንገድ ስላወቁ የበለጠ ሃላፊነት ይጠብቅባቸዋል።

ለመሆኑ ዛሬ ለአገልግሎት የተጠሩትንና ከጌታ ራእይ ተቀብለው በእግራቸው ለመሄድ የሚንገዳገዱትን አገልጋዮች ለመደገፍና ጌታ የጠራቸው ደረጃ እስኪደርሱ በፍቅር ለማቀፍ የሚበቃና ፈቃደኛ የሚሆን አገልጋይ ማን ይሆን? በተለይም በዚህ አገልጋዮችን ተስፋ በሚያስቆርጥ ክፉ ዘመን፥ ጌታ በአጠገባችን ያስነሳልንን አገልጋዮች እኛ በሙሉ ልባችን እብረናቸው ካልተሰለፍን ማን ይቆምላቸው ይሆን? የእግዚአብሔር ሕዝብ ድንቅና ተአምራትን እያየ፥ ጌታን እያመሰገነ በመታነጽ ይኖር ዘንድ የጌታን መንገድ የሚያስተውሉ ጥሪ ያላቸው አገልጋዮች በሚገባ ሊያዙ ያስፈልጋል። እንዴት ነው እነዚህን ለአገልግሎት የተጠሩ ሰዎች የምንይዛቸው? ከዚህ ቀጥዬ መልስን እሰጣለሁ።

I. ለተጠሩት ዓይን ገላጭ (9፥1–19)።

ሳውል ምንም እንኳ ሕይወቱ ከመቀየሩ በፊት በነበረበት ስርአት ወደር የማይገኝለት አዋቂ የነበረ ቢሆንም፥ ወደ ጌታ ከዚያም አልፎ ወደ አገልግሎት ጥሪ ሲመጣ የአገልግሎትን ጉዞ «ሀ» ብሎ መጀመር ነበረበት። ይህንንም ጅማሬ ለመጀመር ሐናንያ አስፈልጎት ነበር። ሐናንያም የእግዚአብሔርን ድምጽ በመታዘዝ ጳውሎስን ወደ ጉያው ተቀበለው፥ ጸለየለትም። ሁል ጊዜ በእርሱ የጸሎት ብርታት

ተደግፎ የሚኖር ጥገኛ ክርስቲያን ሆኖ እንዳይቀር የሸፈነውን ቅርፊት በጸሎት በመግፈፍ ነጻነቱን አጎናጸፈው። የራሱን አሳብ ሳይሆን የእግዚአብሔርን አሳብ መከረው። ሐናንያ እጁን ዊኖ በመጸለይ የላከውን ጳውሎስን እግዚአብሔር እጁን ዘርግቶ ተቀበለው፥ ወደ አገልግሎትም አወጣው።

በዘመናችንም እግዚአብሔር ከተለያየ የሕይወት ጎዳና ውስጥ እያወጣ ወደ ለማያዊ አገልግሎት የሚያለማራቸው ሰዎች ጥቂቶች አይደሉም። እነዚህ ገና ልምምድ የሌላቸው ትኩስ አገልጋዮች ከዕለት ወደ ዕለት የአገልግሎት ዓይናቸው እየጠራ ይሄድ ዘንድ የሸፈናቸውን ቅርፊት የሚያስወግድ አስተዋይ አገልጋይ ያስፈልጋቸዋል። አዳዲስ አገልጋዮች ፍቅርን እንጂ ፍርድን አይፈልጉም። አቃፊን እንጂ ገፊን አይፈልጉም። የሚጸልይላቸውን እንጂ የሚያማቸውን አይፈልጉም። ከጌታ የተቀበሉትን አደራ ይወጡ ዘንድ ተገቢውን ነገር አድርጎ የሚልካቸው እንጂ የበታች አድርጎ አፍኖ የሚያስቀራቸውን አይፈልጉም። አስፈላጊውን የትምህርት ዘመን አልፈው በታላቅ ቅባት እንዲወጡና በሙላት እንዲያገለግሉ የሚያበረታታቸው እንጂ ሁል ጊዜ ተማሪዎች ሆነው እንዲቀሩ አደንዝዞ የሚያስቀምጣቸው አይፈልጉም። እጁን እየጫነና እየባረከ የሚልካቸው፥ ከወጡበትም ሲመለሱ ምስክርነታቸውን የሚሰማቸውና ጌታ በእነርሱ ተጠቅሞ ያደረገውን ወደ ብርሃን የሚያወጣላቸው አገልጋይ ይፈልጋሉ። ይህንን ለማድረግ ፈቃደኞች ነን?



አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ጥሪ ሰምተው በመነሳት ላይ ያሉትን አገልጋዮች ተቀብለንና አበረታተን ማውጣት አለብን ብለን ማለፍ የሚገባቸውን የዝግጅት ዘመን እናሳጥረውና ለተስፋ መቁረጥ እናጋልጣቸዋለን። ሌላ ጊዜ ደግሞ ሳናስተውለው አገልጋዮችን ከልክ ያለፈ ታናሽ ግምት እንሰጣቸውና አገልግሎታቸው ታፍኖ እንዲቀር መሣሪያ እንሆናለን። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ጌታ በሕይወትህ የሚያመጣቸውን አገልጋዮች በመደገፍ ጥሪያቸው በሙላት የሚወጣበትን መንገድ የምታመቻች ታማኝ ባሪያ ሁን። ታማኝነትህን ግን በዚህ ብቻ አትወስነው። አገልጋዮች ካለጊዜው ወጥተው እንዳያበላሹ ማስተዋል ሁንላቸው።

II. ለተጠሩት ጠባቂ (9፥20–25)።

ጳውሎስ ወደ አገልግሎት ለመውጣት የቸኮለ ይመስላል። ስለዚህም በማስተዋል ማድረግ ያለበትን በሚገባ ስላላወቀ ራሱን ለሞት አጋልጦ ነበር። አይሁድ ሊገድሉት እንደፈለጉ እያወቀ ምንም እርምጃ ሲወስድ ሲያደርግ አይታይም። ምንም እንኳ በአካባቢው የነበሩት ክርስቲያኖች ላልደረሱበት ለየት ላለ የጥሪ ደረጃ የታጨ ታላቅ አገልጋይ ቢሆንም በልምምድና በማስተዋል ይበልጡት ነበርና በቅርጫት እድርገው ከሚጠብቀው ሞት የሚወጣበትን መንገድ አሳዩት።

ለአገልግሎት መጠራትና በብዙ ልምምድ ውስጥ ማለፍ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ብዙውን ጊዜ ለአገልግሎት በመውጣት ላይ ያሉ ጀማሪ አገልጋዮች የሚሳሳቱት እዚህ ላይ ነው። የደረሱበት ደረጃ በጥሪ እሳት የመንደድና በእምነት ሁሉን የመጋፈጥ ደረጃ እንጂ የማስተዋል ደረጃ አይደለም። በአጠገባቸው ግን ከመፍረድ ይልቅ በፍቅር የሚንከባከባቸው አገልጋይ አብሯቸው ቢቆም በከባድ ሁኔታ ቆስለው ከመማር ይድናሉ። ይህ በአጠገባቸው ለመቆም የወሰነ አገልጋይ ግን የማይፈርድ፥ አንደበቱን የሚገዛና የሰው ሳይሆን የጌታ ነገር ብቻ ግድ የሚለው አገልጋይ መሆን ይገባዋል።

«እርሱ ለቁም ነገር የማይበቃ ያልሰለጠነ አገልጋይ ነው»፤ «ገና ብዙ ማደግ ይቀረዋል»፤ «ቢነግሩት አይሰማም፥ ዛሬም እንደገና አበሳሽ» የሚሉትና እነዚህን የመሳሰሉት አነጋገሮች አገልጋዮችን ተስፋ የሚያስቆርጡ የጠላት መጠቀሚያዎች ናቸውና ሊቆሙ ይገባቸዋል። ሐናንያ ለጳውሎስ እንዳደረገው ጸልዮና ባርኮ መላክ ብቻ ሳይሆን የተቀሩት ደቀ መዛሙርትም ጳውሎስን ከሞት እንዳዳኑት አገልጋዮች ከጥፋት የሚጠበቁበትን መንገድ መፈለግ ትልቅ ማስተዋል ነው።

III. ለተጠሩት አጽናኝ (9፥26–31)።

የበርናባስ አገልግሎት የትም የማይገኝ አገልግሎት ነው። ከአይሁድ ተቃውሞ ይልቅ የክርስቲያኖች አለመቀበል የሳውልን ልብ በቀላሉ ሊሰብረው ይችል ነበር። እውነትም በርናባስ እንደ ስሙ ትርጉም የመጽናናት ሰው ነው። በዚህ ጸጋው ነበር በጥርጣሬ የተሞላውን የክርስቲያኖችን ልብ አሸንፎ በሳውልና በእነርሱ መካከል

መተማመንን የዘራው። በእርሱ ዘንድ እርቅ እንጂ ጥል የለም። በእርሱ ዘንድ ማሰባሰብ እንጂ መበታተን አይገኝም።

አገልጋዮችን ዓለማውያን ቢቃወሙአቸውና ባይቀበሏቸው ክርስቲያኖች ያቅፍቸዋል። ነገር ግን አገልጋዮች አገልጋዮችን ለመቀበል አሻፈረኝ ሲሉና በሆነ ባልሆነው ሲጠራጠሯቸው እነዚህ አገልጋዮች ወደ ማን ይሄዱ ይሆን? ይህ ችግር ብዙዎችን አገልጋዮች ጠራርጎ የወሰደ ድልድይ የሚያስፈልገው አደገኛ ጎርፍ ነው። ይህንንም ድልድይ ከበርናባሶች በስተቀር ማንም ሊገነባው አይችልም። ለአገልግሎት አዲስ የሆኑት አገልጋዮች ነገር ግራ ሲገባቸው፥ ከወገኖቻቸው ጋር ያላቸው ሕብረት ሲሻክርና ሁኔታዎች አልያዝ አልጨበጥ ሲሉአቸው፥ አብሮአቸው በመቆም፦ «አይዞአችሁ» የሚላቸው አገልጋይ አስተዋይ አገልጋይ ነው።

እውነተኛውን ከአስመሳዩ እየለየ አገልጋይን ከአገልጋይ አብሮ የሚያሰልፍ አስተዋይ ሰው ጌታ ቀብቶ ያስነሳልን ዘንድ እየተመኘሁ፥ ለአገልጋዮች በዚህ መልኩ ብንተጋላቸው መልካም ይሆናል ብዬ የማምንባቸውን ነጥቦች እሰነዝራለሁ።

1) ጥሪ ላላቸው አገልጋዮች ለዝግጅት የሚያስፈልጋቸውን ማናቸውንም ድጋፍ መስጠት ያስፈልገናል። ጌታ ለሁሉም የራሱ የሆነ አጠራር አለው። አንዳንዶቹን በቀጥታ ወደ አገልግሎት ሲያወጣ፥ ሌሎቹን ደግሞ በትምህርት ቤት ተዘጋጅተው እንዲያልፉ ይፈቅዳል። የማይማሩት በሚማሩት ላይ፦ «በእውቀት የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ትሞክራላችሁ» እያሉ አይፍረዱባቸው። የሚማሩት ደግሞ የማይማሩትን አይናቋቸው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ደግሞ ሁለቱንም ይደግፍ።

2) ጥሪ ያላቸው አገልጋዮች የኑሮ ሸክም ከብዷቸው ቅባታቸው እንዳይደፈን አስፈላጊው ድጋፍ አይለያቸው። አንዳንዶች በሥራም ሆነ በንግድ ዓለም ተሰማርተው በተደላደለ ሁኔታ እየኖሩ በአገልግሎታቸው ጌታን እያስከበሩ አሉ። በአንጻሩ ደግሞ ሙሉ ጊዜአቸውን እንዲሰጡ ጌታ የሚፈልጋቸውም አሉ። እነዚህ አገልጋዮች ለጌታ ሥራ ብለው ወጥተው ላለ አንዳች ,እንዳይጎድልባቸው መጠንቀቅ የእግዚአብሔር ሕዝብ ኃላፊነት ነው።

3) ጥሪ ያላቸው አገልጋዮች የተለየ ጸሎትና እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል። ሰይጣን አንድን ምእመን እንደሚዋጋ ብቻ ሳይሆን ከዚያም በከረረ ሁኔታ አገልጋይን ይዋጋል። የብቸኝነትና የተስፋ መቁረጥ መንፈስ አብዝቶ አገልጋዮችን ያጠቃል። አገልጋዮች ተቀባይነት ያጡ የሚመስላቸውም ጊዜ ጥቂት አይደለም። በትእቢት፥ በክፉ ምኞትና በገንዘብ ፍቅር ይነደፉ ዘንድ ዘወትር የማይተኛውን ዲያቢሎስን የእግዚአብሔር ሕዝብ በክርስቶስ ኢየሱስ ስም እየተቃወመ ከአገልጋዮቹ አጠገብ ቢሰለፍ የሚያስጠንቃቸው ቅጥር ይፈርሳል።

9

የጠራህን ጌታ አትወስነው

ምዕራፍ 9፥32–10፥1–48



ሉቃስ በምዕራፍ ስምንት ውስጥ ያቋረጠውን የጴጥሮስን ታሪክ በምዕራፍ ዘጠኝ ውስጥ ሲቀጥል ይታያል። ጴጥሮስ ሲዘዋወርባቸው ከነበሩት ስፍራዎች ልዳ አንዷ ነበረች። በዚያም በነበሩት ክርስቲያኖች መካከል ሲመላለስ ሳለ፥ የአልጋ ቁራኛ የነበረውን ኤንያን ተገናኝቶ የክርስቶስን ፈዋሽነት አበሰረለት። ከእንግዲህ ወዲህ አልጋውን ማታ ለመተኛ ብቻ ነውና የሚፈልገው ተነስቶ አልጋውን አነጠፈ። በውጤቱም በልዳና በሰሮና የነበሩ ሁሉ ወደ ጌታ ዘወር አሉ።

ብዙም ሳይቆይ ለጴጥሮስ ከኢዮጴ የአገልግሎት ጥሪ ደረሰው። ወደዚያ የተጠራበትን ምክንያት ለጊዜው ባያውቀውም፥ ምንም ሳይጠይቅ ጌታ የሚያደርገውን ለማየት ሄደ። በወገኖች ሁሉ ዘንድ እጅግ የተወደደች አንዲት እህት ታማ ሞታ ነበር። ይህቺ ደቀ መዝሙር ጣቢታ በመባል የምትጠራ ስትሆን፥ በመልካምነቷ የታወቀችና ለመበለቶች ልብስን በመስፋት ታገለግል የነበረች መልካም ሴት ነበረች። ጴጥሮስ ከመጸለዩ በፊት ሁሉን ወደ ውጭ ማስወጣትን ከክርስቶስ የተማረ ይመስላል (ማር. 5፥38–42)። ያደረገው የፈውስ ስርአት ብቻ ሳይሆን ውጤቱም ቄምር ልከ እንደ አስተማረው እንደ ክርስቶስ ነበር። ይህንን ታላቅ ተአምራት ካከናወነ በኋላ ከቁርበት ፋቂው ከስምዖን ጋር ለብዙ ቀናት ተቀመጠ።

ወደ ምዕራፍ አስር ስንሸጋገር አንድን ነገር እናስተውላለን። በምዕራፍ ስድስት ውስጥ እንደተገለጸው በመጀመሪያ ወንጌል ለአይሁድ ደረሰ። ከዚያም በመቀጠል በግማሽ ጎናቸው አይሁድ ለነበሩት ለሰማሪያ ሰዎች እንዴት ወንጌል እንደደረሳቸው ሉቃስ በምዕራፍ ስምንት ውስጥ ተረክልን። በዚህ በምዕራፍ አስር ውስጥ ደግሞ ሉቃስ የሚነግረን የክርስቶስ ወንጌል ወደ አሕዛብ መዳረሱን ነው። ታሪኩ ይህንን ይመስላል።

ቆርኔሌዎስ ከነቤተሰቡ ከአሕዛብ ወገን ነበር። ይህ ሰው በቀትር በጸሎት ሲተጋ ሳለ፥ የእግዚአብሔር መልአክ በራእይ ወደ እርሱ ቀረበ። እርሱም በድንጋጤ ትኩር ብሎ ወደ መልአኩ በመመልከት በጥያቄ ተሞላ። መልአኩም የጸሎቱንና የምጽዋቱን በእግዚአብሔር ፊት መታሰብ ካበሰረለት በኋላ፥ ማድረግ የሚገባውን ገለጸለት። ማድረግ የሚገባው ወደ ኢዮጴ ሰዎችን በመላክ ጴጥሮስን ማስመጣት ነው። ስለዚህም ከሎሌዎቹ ሁለት፥ እነርሱን በመንገዳቸው ይጠብቅ ዘንድ ደግሞ አንድን ወታደር ጨምሮ ወደ ኢዮጴ ላካቸው።

ይህ እግዚአብሔር እያደረገ ያለው አሕዛብን ወደ መንግስቱ የማፍለስ ታላቅ ሥራ በአሕዛብም ሆነ በአይሁድ ዘንድ በቀላሉ ሊታመን የማይችልና ተቀባይነት ለማግኘቱ እጠራጣሪ ጉዳይ በመሆኑ እግዚአብሔርም ትልቅ ትኩረት ሲሰጠው ይታያል። ቆርኔሌዎስን ለማላመን ራእይን ማሳየት እንዳስፈለገው፥ ጴጥሮስንም ለማላመን ራእይን ማሳየት ነበረበት። መልእክተኞቹ ወደ ከተማ ሳይገቡ ጴጥሮስ ትእዛዝን ከጌታ ይቀበል ጀመር። ጴጥሮስ ወደ ጣራ ለጸሎት ሲወጣ የስምዖን ቤተ ሰዎች መራቡን እውቀው ምግብ እያዘጋጁለት ነበር። እግዚአብሔር ለጴጥሮስ መልእክቱን ሲያስተላልፍ ጴጥሮስ የነበረበትን ሁኔታ ሉቃስ «ተመስጠ» ይለዋል። በዚህ ራእይ ጴጥሮስ በፍጹም ሊቀበለው የማይችለውን ነገር አየ። በሰማይና በምድር ካሉ ፍጥረታት በባህሉም ሆነ በሃይማኖቱ እንዲበላ ያልተፈቀደለትን አራዊትና ወፎች ተመለከተ። ከላይ የመጣለትን፦ «ጴጥሮስ ሆይ ተነሣና እርደህ ብላ» የሚለውን ትእዛዝ ላለመቀበል ባሰው ችሎታ ተጣጣረ። ይህ ሁኔታ ሦስት ጊዜ ከተከናወነ በኋላ፦ «እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው» የሚለው ምላሽ የክርክሩ ፍጻሜ ሆነ።

ጴጥሮስና የቆርኔሌዎስ መልእክተኞች ተገናኙ፤ በተመለከተው ራእይ ግራ ተጋብቶ የነበረውም ጴጥሮስ የራእዩን ምስጢር ቀስ በቀስ መገንዘብ ጀመረ። ለካስ የተመለከተው ሁሉ የምግብ ጉዳይ ሳይሆን የሕይወት ጉዳይ ነው። ጴጥሮስ እንግዶቹን በሚገባ ካስተናገደ በኋላ፥ በነገው ወደ ኢዮጴ ተጉዞ ከቆርኔሌዎስ ጋር ተገናኘ። በዚያም የተደረገው ተአምር የዓለምን ታሪክ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለወጠው። ለአሕዛብ ወንጌል ተሰበከ፥ እነርሱም ልባቸውን ለጌታ

ከፈቱ፥ ደህንነትንና የውኃን ጥምቀት፥ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ቄምር ተቀበሉ።



«የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክን ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን? ከሰማይ ይልቅ ከፍ ይላል፤ ምን ልታደርግ ትችላለህ? ከሲኦልም ይልቅ ይጠልቃል፤ ምን ልታውቅ ትችላለህ?» (ኢዮብ 11፥8)። አዎን፥ ምንም አናውቅም። የእግዚአብሔርን መንገድ አናውቅም። እግዚአብሔር በምን መልክ ሊሠራ እንደሚወድ ስለማናውቅ ዝም ብለን ብንታዘዘው ነገር ሁሉ ይሰምርልናል። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ አገልግሎታችን ከባህላችንና በአካባቢያችን ካለው ሁኔታ ሲያልፍ አናየውም። እግዚአብሔርን በባህላችን፥ እግዚአብሔርን ከሰዎች በተማርነው ወግ፥ እግዚአብሔርን ታሪክን ብንመረምርም እንኳ ጅማሬውን ፈጽሞ ልናገኘው በማንችለው የሃይማኖት ሕግና ስርአት ወስነንና ተብትበን፦ «አቤቱ ጌታ ሆይ ሥራህን ሥራ» እያልን ብንጮህ፥ ብንጸምና ብንጸልይ ምንም አዲስ ነገር አናመጣም።

ለመሆኑ እንደ ጴጥሮስ ለእግዚአብሔር ሥራ ልቁም ባይ ማን ነበር? እስከ ሞት ድረስ ጌታን ለመከተል የፎከረ ይህ ሰው፥ ጌታ እስኪነበኘው ድረስ እግዚአብሔርን በራሱ የግምት ሳጥን ውስጥ አስቀምጦና ወስኖ የሚመላለስ አገልጋይ ነበር። ከጴጥሮስ እንደምንማረው፥ የጠራንን እግዚአብሔር መወሰን የለብንም። እግዚአብሔርን አንወስነው ስንል ምን ማለታችን ነው? የሚከተሉትን ነጥቦች እንመልከት።

I. መልካምነትህ ለክርስቲያኖች ብቻ አይሁን (9፥32–43)

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፥ ጴጥሮስ በየስፍራው ሲዘዋወር ሳለ በልዳ ኤንያን አግኝቶ ከነበረበት ደዌ በጌታ ኃይል ፈወሰው። ይህንንም ለማድረግ ኤንያ ክርስቲያን መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ አልተጨነቀም። ኤንያ ከደቀ መዛሙርት አንዱ ቢሆን ኖሮ ያንን አሳብ ወንጌላዊው ሉቃስ ጠቅሶት እንደሚያልፍ አያጠራጥርም ነበር። ጴጥሮስ አማኝ መሆኑ ያልተረጋገጠለትን ኤንያን ምንም ሳይጠይቅ በጌታ ስም ከፈወሰው በኋላ ወደ ኢዮጴ በመሄድ ጣቢታ የተሰኘችውን ደቀ

መዝሙር ከሞት ለማስነሳት ጌታ ተጠቀመበት። የጌታ እጅ ለክርስቲያኑም ሆነ ለዓለማዊው የተዘረጋች መሆኗን በዚህ እንማራለን።

እግዚአብሔር ለማያምኑትም ይገደዋልን? በእርግጥም ይገደዋል። እግዚአብሔር ለፈጠረው ፍጥረቱ ሁሉ ባይገደው ኖሮ ለሰው ሁሉ መልካም እናደርግ ዘንድ ባልመከረን ነበር (ገላ. 6፥10)። እኛ ግን ከክርስቲያን ዓለማዊ፥ ከዓለማዊ ደግሞ ክርስቲያን ስናማርጥ፥ ጌታን እንወስነዋለን። በዚህም አድራጎታችን እውነተኛ ርህራሄ ከእኛ ከመራቁም በላይ፥ ለማያምኑ ሰዎች መልካም በማድረጋችን ጌታ ተጠቅሞ ሊሠራ ያቀደውን ድንቅ ሥራ እናሰናክለዋለን። በተለይም ደግሞ ሰዎች ወደ ደህንነት የመምጣት ተስፋን ሲያሳዩን ብቻ መልካምን ለማድረግ እጆቻችን ሲዘረጉ፥ ሁኔታቸው ደግሞ ተስፋ የሌለው ሲመስል እጆቻችን የሚሰበሰቡ ከሆነ፥ የክርስቶስ እውነተኛ ርህራሄ በውስጣችን ሰርጾ እንዳልገባ ያሳያል። የጌታን እጅ እንዳናስረው ከፈለግን፥ የመልካምነታችን በር ለክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን ለሰው ሁሉ የተከፈተ ይሁን።



አንዳንድ ጊዜ መልካም ማድረግ ያለብን ለክርስቲያኖች ብቻ አይደለም ብለን ሚዛናችንን ስተን ጌታ የሰጠንን በረከት ሁሉ በማይሆን ስፍራ ላይ ስናባክነው እንገኛለን። ሌላ ጊዜ ደግሞ መልካም ሥራችን ሁሉ በክርስቲያን ወገኖቻችን ብቻ ተወስኖ ይቀራል። ስለዚህም ሌላው ዓለም ሲሰቃይ እጃችንን አጣምረን እንቀመጣለን። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። «ለሰው ሁሉ» መልካም አድርጉ ብሎ ያዘዘን ቃል፦ «ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ» (ገላ. 6፥10) በማለት ነገሩን ሚዛናዊ አድርጎ እንደደመደመው አትዘንጋ።

II. ማንንም ሰው የሚያጸይፍ ነው አትበል (10፥1–33)።

ይህ ነገር መነካት የለበትም ብለን የደመደምነውን ነገር የማይነካ መሆኑን ማን ነው ያስተማረን? ይህ ከቶ መቀመስ የለበትም ያልነውንስ ነገር የማይቀመስ መሆኑን ከማን ሰማን? ይህንን ነገርስ እንዴት ለማየት ዓይናችንን እንከፍታለን ብለን የወሰንነውን ነገር የማይታይ መሆኑን ከማን ተማርን? የማንሄድበት ስፍራ የማይኬድበት መሆኑን ማን ነው የደነገገልን? የእግዚአብሔር ቃል ነው ወይስ የሰው ወግ? ለጴጥሮስ

እነዚህን ነገሮች የደነገለት ከአባቶቹ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ባህላዊ እምነት ነበር። ስለዚህም፥ እግዚአብሔር የቀደሰው በእርሱ ፊት ያልተቀደሰ፥ እግዚአብሔር የባረከው በእርሱ ፊት እርኩስ፥ እግዚአብሔር የመረጠው ደግሞ በእርሱ ፊት የተጣለ ነበር። ይህንን ሁሉ አልፎ ከተማረ በኋላ ነበር፦ «ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው እርኩስና የሚያስጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ» በማለት የተናገረው።

በዘመናችን ብዙ ዓይነት ሰዎች ወደ ጌታ ቤት ይመጣሉ። እነዚህን ሰዎች እንደ አመጣጣቸው ካልተቀበልናቸውና ገና የውጭ ሁኔታቸውን ዓይተን ከተጸየፍናቸው፥ ግን ይሆን ለእነዚህ ሰዎች የመዳን ተስፋ የሚሆናቸው? ሰዎች ወደ ጌታ ቤት ገና ሲመጡ ሁኔታቸውን አይተን ደረጃ መስጠትና የሚያስጸይፈውንና የማያስጸይፈውን መወሰን የእኛ ድርሻ አይደለም። በክርስቶስ ያላመነ ሁሉ መጨረሻው ያው ነው። «ልዩነት የለምና ሁሉ ኃጢአትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል» (ሮሜ 3፥24)።

ይህንን ባለማወቃችን ነው ዛሬ በሰው ዓይን ሲታዩ እጅጉን አስቀያሚ ሁኔታ ላይ ያሉ የሚመስሉትን ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ አንዳንድ ዓለማዊ የእርዳታ ድርጅቶች በበለጠ ሁኔታ ችግራቸውን ሲገነዘቡላቸውና ሲቀበሏቸው የምናየው። ስለዚህም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ማከናወን የምትችለውን ሥራ እነዚህ ድርጅቶች በገንዘብ ኃይልና በተለያየ የሥነ ልቦና ጥበብ ሊፈቱት በከንቱ ሲታገሉ ይታያሉ። የክርስቶስ ደም የማያነጻው እድፍ፥ የማይለውጠውም ሕይወት የለምና ከእንግዲህ ወዲህ ማንንም ሰው እርኩስና የሚያስጸይፍ ነው በማለት ጌታን አንወስነው። በምትኩ ሰዎችን ከነቆሻሻቸውና ከነመጥፎ ስማቸው አቅፈን በክርስቶስ ወደሚገኝ ንጽህናና መልካምነት ልናሸጋግራቸው ተጠርተናል።

III. ጌታ የሚሠራው በዚህ መንገድ ብቻ ነው አትበል (10፥34–48)።

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን በመጠበቅ ብዙ ቀናት ቆይተው ነበር። በመጨረሻም መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ተንበርክከው ወይም ቆመው

ሳይሆን ተቀምጠው ነበር። በምዕራፍ ስምንት ውስጥ እንደተመለከትነው የሰማርያ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጴጥሮስና ዮሐንስ እጃቸውን ጭነው እንዲጸልዩላቸው እግዚአብሔር ፈለገ። በዚህ በምዕራፍ አስር ውስጥ ደግሞ ጴጥሮስ ገና ስብከቱን ሳይጨርስ መንፈስ ቅዱስ ሲያጸርጠውና የቆርኔሌዎስን ቤት ሲያጥለቀልቀው እንመለከታለን። በተጠቀሱት በሦስቱም ክፍሎች ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በተለያየ መልኩ መውረዱ የሚያሳየን እግዚአብሔር መሥራት የፈለገውን ነገር በፈለገው መንገድ እንደሚሠራ ነው። እርሱ በእኛ ልምምድ አይወሰንም። ሁል ጊዜ አዲስን ነገር ማድረግ ይወዳል። ሰው ግን በባህሪው ለውጥን አይወድም። ትናንት በለመደው መንገድ ብቻ መራመድን ይፈልጋል። ይህ ባህሪው ዘወትር አዲስን ነገር ማድረግ ከሚወደው ከጌታ ባህሪይ ጋር ፈጽሞ አብሮ አይሄድም።

እኛ የክርስቶስ አገልጋዮች ጌታን ሳንወስነው በመሳት በመካከላችን እንዲሠራ ከፈለግን፥ ጌታ የራሱን ሥራ በራሱ ጊዜና በራሱ መንገድ እንዲያከናውን ሥፍራውን እንልቀቅለት። በተለይም ከዚህ በፊት አይተነው በማናውቀው መልኩ ጌታ ሊንቀሳቀስ ሲፈልግ፦ «በዚህ አካባቢ አገልግሎታችንን በዚህ ዓይነት ሁኔታ አይደለም የምናከናውነው» ብለን በራችንን ከመዝጋታችን በፊት ለጌታ መንፈስ ጊዜን እንስጠው። ያን ጊዜ ጌታ ከአዲስ ልምምድ ወደ አዲስ ልምምድ ያሸጋግረን ዘንድ፦ «እነሆ፥ አዲስ ነገርን አደርጋለሁ፤ እርሱም አሁን ይበቅላል» (ኢሳ. 43፥19) የሚለውን የተስፋ ቃሉን ያድስልናል።



አንዳንድ ጊዜ ጌታ የሚሠራው በዚህ መንገድ ብቻ ነው በሚል አሳብ ተይዘን ጌታ ሊያለማምደን ያለውን አዲስ ልምምድ አፍነን እናስቀራለን። ሌላ ጊዜ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ዘመን አመጣሽ ልምምዶችን ከጌታ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን ሳንመረምር በራችንን ከፍተን እናስተናግዳለን። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። እግዚአብሔር የአዲስ ነገር አምላክ መሆኑን በማመን ለሚሰጥህ ማንኛውም አዲስ ነገር ልበ ሰፊ ሁን። ነገር ግን በፊትህ የሚመጣን ማንኛውንም እንግዳ ልምምድ ከማስተናገድህ በፊት ሁሉን በቃሉ መርምር።

እንደ አገልጋዮች፥ የእግዚአብሔርን ኃይል በራሳችን ግምት አስረን እንዳንወስነው አብዝተን መጠንቀቅ ይጠበቅብናል። ይህንንም ለማድረግ እንዲረዱን የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች እንመልከት።

1) ከባህል ክርስትና እንጠበቅ። የምናደርጋቸውን ነገሮች ከእኛ በፊት ያንን ሲያደርጉ ያየናቸው አገልጋዮች ስላደረጉት ከሆነ የምናደርገው አገልግሎታችን በባህል የተተበተበ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። «ይህ ነገር መደረግ ያለበት በዚህ መንገድ ብቻ ነው» ማለትን ከመረጥን መጽሐፍ ቅዱሳዊውንም ማስረጃ አብሮ ማዘጋጀቱ ውጤቱን ያማረ ያደርገዋል።

2) የሌሎችን ልምምድ ቀብረን የራሳችንን ልምምድ ብቻ አናጋንን። እኛ ባለፍንበት ያሳለፈን ጌታ ወገኖቻችንንም ማለፍ በሚገባቸው ልምምድ ውስጥ አሳልፎአቸዋል። ዘወትር የእነርሱ ልምምድ የተሳሳተ፥ የእኛ ግን ትክክለኛ መስሎ ሲታየን ጥንቃቄን እንውሰድ። የሌሎች ልምምድ እንደ ቃሉ እስከሆነ ድረስ ዋጋ ልንሰጠው ይገባናል።

3) ፍሬን እንጂ ጅማሬን አይተን አንፍረድ። ማንኛውም ከስህተት የሆነ ነገር መልካም ፍሬን ለማፍራት አይችልም። ስለዚህም ቸኩለን ከመፍረዳችን በፊት ፍሬን እንመልከት። «ወንድሞቼ ሆይ፥ በለስ ወይራን ወይስ ወይን በለስን ልታፈራ ትችላለችን» (ያዕ. 3፥ 12)?

10

እድገትህን ለካው

ምዕራፍ 11፥1–30



ጴጥሮስ ከጌታ ራእይን ተቀብሎ ለአሕዛብ ባበረከተው አገልግሎት ድልን ተቀዳጅቶ በተራራ ላይ በደስታ ሳለ በድንገት በኢየሩሳሌም ሲያገለግሉ ከነበሩት ወገኖቹ ዘንድ የተቃውሞ ድምጽን ሰማ። አሕዛብ በእግዚአብሔር መንፈስ የመጎብኘታቸው ዜና ጴጥሮስን ቀድሞ ወደ ኢየሩሳሌም ደርሶ ኖሮ ከተገረዙት ወገን የሆኑት ክርስቲያኖች አሳት ለብሰው አሳት ጎርሰው ጠበቁት። እነዚህ ማስተዋል የራቃቸው ሰዎች እግዚአብሔር አሕዛብን በምህረቱና በቸርነቱ መጎብኘቱ ሳያስገርማቸው ጴጥሮስ ከአሕዛብ ጋር መተባበሩ አበሳጫቸው። ጴጥሮስ ያደረገውን ነገር ሁሉ ከማስረጃ ጋር ማብራራት ነበረበት። ፍሬ ነገሩንም ሲያስር እንዲህ አለ፦ «እንግዲህ እግዚአብሔር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላመነው ለእኛ ደግሞ እንደ ሰጠን ያን ስጦታ ለእነርሱ ከሰጠ፥ እግዚአብሔርን ለመከልከል እችል ዘንድ እኔ ማን ነበርኩ (ቁ. 17)?» ይህም ምስክርነት ሰሚዎቹን አስደሰታቸው፥ እግዚአብሔርንም አከበሩ።

ወገኖችን ሁሉ በየስፍራው የበተነው የእስጢፋኖስ ሞት የወንጌልን መልካም ዜና አሕዛብ ሁሉ ይሰሙ ዘንድ መጠቀሚያ ምክንያት ሆነ። ወንጌል እስከ አንጾኪያ ደረሰ። ቀድሞ ለአይሁድ ብቻ ይናገሩ የነበሩት ሁሉ አሁን ለግሪክ ሰዎችም ሳይቀር ወንጌልን ሰበኩ። ቁጥራቸውም እጅግ የበዛ አማኞችን እንዳፈሩ በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ያሉ ወገኖች በሰሙ ጊዜ በርናባስን ወደ አንጾኪያ ላኩላቸው። መንፈስ ቅዱስና እምነት የሞላበት ይህ ደግ ሰው፥ በአንጾኪያ በነበሩ ወገኖች መካከል የነበረውን ጸጋ ተመልክቶ ተደሰተ፤ ወደ ጠርሴስም በመሄድ ሳውልን ካገኘው በኋላ ወደ አንጾኪያ አብረው ተመለሱ። ደቀ መዛሙርትም ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን የሚለውን ስም በተቀዳጁበት በአንጾኪያ አንድ ዓመት ሙሉ እያስተማሩ ተቀመጡ።

በዚያም ወራት ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ወርደው ከነበሩት ነቢያት መካከል አጋቦስ የሚሉት አንድ ሰው ተነሥቶ በዓለም ሊመጣ ስላለው ራብ አመለከተ። ደቀ መዛሙርቱም ይህን የእግዚአብሔር ቃል ታዝዘው በበርናባስና በሳውል እጅ በይሁዳ ላሉ ወገኖች እርዳታን ላኩ።



«ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አስብ፥ ይህንም አዘውትር» (1ጢሞ. 4፥ 15) የሚለው ቃል ልንዘነጋው የማይገባን ታላቅ ምክር ነው። ምክንያቱም በሕይወታችን በማናድግበት ጊዜ ለሌሎች አገልጋዮችና ለጌታ ሥራ እንቅፋት እንሆናለንና ነው። የሚያድግ ሕይወት ከሌለን ዘወትር ነገሮችን በራሳችን ጠባብ መነፅር ብቻ እየተመለከትን የጌታን አሠራር ስንቃወም እንገኛለን።

ጴጥሮስ በሕይወታቸው ባላደጉ አገልጋዮች ምክንያት ያሳለፈው የተቃውሞ እሳት ቀላል አይደለም። የእርሱን ሕይወት ለአደጋ ከማጋለጥ አልፎ በክርስቶስ ተከታዮችና በአይሁድ መካከል የነበረውን የተረጋጋ ፍትጊያ እንደገና የሚያነሳሳና ወገኖችን ለብዙ ስደት የሚዳርግ ሁኔታ ነበር። ተቃውሞው የተነሳው ከወገኖች ዘንድ መሆኑ ጴጥሮስን ስህተተኛ ቢያስመስለውም፥ እርሱ ግን ያደረገውን የሚያውቅ አገልጋይ ነበር። ጌታ ተናግሮኛል በሚል ሳቢያ በስሜት ያልሄደ፥ ነገር ግን ከሰማይ የመጣለትን ትእዛዝ ፈትኖ፥ አውጥቶና አውርዶ፥ ከጌታ መሆኑንም በሚገባ አረጋግጦ የተራመደ ሰው ነበር። ይህንንም ሁኔታ ለሌሎች በትህትና ለማስረዳት የተሰናዳ አገልጋይ ነበር።

ከዚህ ምዕራፍ ስለ እድገት የምንማራቸው ትምህርቶች አሉን። በመጀመሪያ ታላቁን የእድገትን ጠንቅ እናያለን። በመቀጠልም የእድገት ምልክቱ ምን እንደሆነ እንመለከታለን። ከዚያም የእድገትን ውጤት እንማራለን።

I. ጭቅጭቅ፦ የእድገት ጠንቅ (11፥ 1–18)።

የጴጥሮስን ወደ አሕዛብ ሄዶ ወንጌልን መስበክ በመቃወም ለክርክር ተነስተውበት የነበሩት ወገኖች፦ «ይህ ነገር ከጌታ ይሆንን?» ብለው ራሳቸውን ሳይጠይቁ በግልፍተኝነትና በጭፍንነት የተነሱ ሰዎች ነበሩ። ጴጥሮስ ከጌታ የተቀበለው እነርሱ ግን ገና ያልደረሱበት ደረጃ መኖሩን ለማወቅ መከራ ሲያደርጉ አይታዩም። ሌላው ቢቀር፦

«ስለዚህ ነገር ጌታ ምን ይላል?» በማለት ቃሉንና መንፈስ ቅዱስን ማማከሩ እንኳ አይከፋም ነበር። ይህም ሁኔታ በጴጥሮስና በተቃዋሚዎቹ መካከል ያለውን የእድገት ልዩነት ያሳያል።

በዘመናችን ያሉት አብያተ ክርስቲያናትም ሆኑ በውስጣቸው ያሉ አገልጋዮች መንፈሳዊ እድገታቸው ከሚለካበት መለኪያ አንዱ ይህ ጭቅጭቅ የሚሉት ነቀርሳ በአገልግሎታቸው በመኖሩና ባለመኖሩ ነው። ጭቅጭቅ የእድገት ጠንቅ ነው። የሚያሳዝነው ነገር ግን ብዙ ፍሬ ነገር ልንወያይባቸው የምንችላቸው ስብሰባዎቻችን ዘወትር በጭቅጭቅ ሲባክኑ ማየታችን ነው። የአገልጋዮች ስብሰባ ሲጠራ መጀመሪያ በማስታወሻችን ላይ የምናሰፍረው የምንከራከርባቸውን ነጥቦች ከሆነ ማደጋችን ምኑ ላይ ነው? በመሪዎች ስብሰባ ጭቅጭቅ፤ በአባሎች ስብሰባ ጭቅጭቅ፤ ማን ይስበክ ጭቅጭቅ፤ ማን ይዘምር ጭቅጭቅ፤ እገሌ ሰምን አያገለግልም ጭቅጭቅ፤ እገሌ ለምን አገለገለ ጭቅጭቅ፤ እገሌ ከእኛ ጋር ወደ ተቃቃሩት ወገኖች ዘንድ በመሄድ የሰው ድንበር የማያግደውን የክርስቶስን ወንጌል ስለሰበከ ጭቅጭቅ ከሆነ፥ ክርስቶስ ኢየሱስ በመካከላችን እንዴት ሊሠራ ይችላል?

ሐዋርያው ጳውሎስ ሰጎልማሶቹ አገልጋዮች ለጢሞቴዎስና ለቲቶ የሰጠው መመሪያ ዛሬም ይሠራል። የእግዚአብሔርን አገልግሎት በአደራ የተቀበለ አገልጋይ ከጭቅጭቅ የራቀ ሊሆን ይገባዋል (1ጢሞ. 3፥ 3፤ ቲቶ 1፥ 7)። የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ እያደመጡ መንጋውን ሊመሩ እንጂ ሊጨቃጨቁ አልተጠሩም። ዲያቆናት በትህትና ሊያገለግሉ እንጂ በሆነ ባልሆነ ቡድን እየፈጠሩ እንዲጨቃጨቁ ጌታ አልጠራቸውም። መዘምራን ከጌታ ዝማሬን እየተቀበሉ ስሙን እንዲባርኩ፥ ለሕዝቡም በረከት እንዲሆኑ እንጂ ማለቂያ የሌለው የእርስ በርስ ክስ ውስጥ እየገቡና እየተናናቁ በጭቅጭቅ መንፈስ በጉባኤ ፊት እንዲቆሙ ጌታ አልጠራቸውም። እንዲሁም በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ አገልጋዮች ሁሉ ለአገልግሎት በቅተንበታል ብለው ያመኑበትን እድገታቸውን በጭምተኛነታቸው ያሳዩ። ነገር ግን በብዙ አካባቢዎች እንደምናየው እስካሁን ከዚህ ሁሉ ችግር አልዳንንምና ጌታ በማስተዋል የበለጸጉ አገልጋዮችንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በየስፍራው ያስነሳልን።

II. ጸጋን ማየት፦ የእድገት ምልክት (11፥19–26)።

በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ አገልጋዮች ዘንድ ያለው የእድገት ልዩነት ያስገርማል። ግማሹ የሌላውን ስህተት እየቆጠረ ሲጨቃጨቅ ግማሹ ግን የሰውን ጸጋ ለማየት ልቡን ሲከፍት ይታያል። በበርናባስ ሕይወት የሚታየው ይህ ዓይነቱ የሚባርክ ባህሪይ ነው። እነዚያ ከጴጥሮስ ጋር ሲከራከሩ የነበሩ የተገረዙት ወገኖች የአሕዛብን ቆሻሻ ጎን ብቻ ተመልክተው የጴጥሮስን ከአሕዛብ ጋር መተባበር ሲያወግዙ፥ በርናባስ ግን እግዚአብሔር በአሕዛብ ውስጥ ያስቀመጠውን የከበረ ጸጋ አይቶ ደስ ሲሰኝ ከዚያም አልፎ ሲያበረታታቸው ይታያል። ይህ ትልቅ የእድገት ምልክት ነው።

ይህ አገልጋይ ወደ ጌታ ከመምጣቱ በፊት ብዙ አበሳሽቷል? ያደግን አገልጋዮች ከሆንን ትናንት ያሳለፈውን ሳይሆን ዛሬ ክርስቶስ የሰጠውን ጸጋ እንመለከታለን፤ ያለፈውን ሕይወቱን እያሰበ በጥፋተኝነት ስሜት እንዳይታሰርም እናበረታታዋለን። በዚያኛውስ አገልጋይ ሕይወት ውስጥ እንደ ጌታ ቃል ያልሆነ ነገር ይታያል? ያደግን አገልጋዮች ከሆንን ድካሙን ብቻ እየቆጠርን ከመፍረድ እንቆጠባለን፤ ጌታ በሕይወቱ ያስቀመጠውን ስጦታና ጸጋ እንዲያቀጣጥል እያበረታታነው፥ ከስህተቱም እንዲመለስ እየመከርንና እየገሰጽነው አብረነው እንቆማለን። ይህንን ሁሉ ለማድረግ ግን በሕይወታችን እናድግ ዘንድ ያስፈልገናል፥ በሰው ሕይወት ውስጥ ክርስቶስ ያስቀመጠውን ጸጋ ማየት የእድገት ምልክት ነውና።

III. ጌታን ማዳመጥ፦ የእድገት ውጤት (11፥27–30)።

በኢየሩሳሌም በነበረችው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሦስት ዓይነት ክርስቲያኖች ነበሩ። ጴጥሮስ ያደረገውን ነገር ወስደው ቄፍንነት በተሞላው ችኮላ ለመጨቃጨቅ ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡትና በሕይወታቸው ያሳደጉት የመጀመሪያዎቹ ሲሆኑ፥ ሁለተኛዎቹ ደግሞ እንደ በርናባስ ዓይነቶቹ ከሞቅሞቅ ይልቅ ጸጋን ማየትን የመረጡት ታላቅ የእድገት ምልክት የሚታይባቸው አገልጋዮች ናቸው። አሁን ደግሞ በሦስተኛ ደረጃ የምንመለከተው የእድገታቸው ውጤት ጎልቶ

የሚታየውንና የጌታን ድምጽ በማዳመጥ የበለጸጉትን እንደነ አጋቦስ ያሉትን አገልጋዮች ነው። አጋቦስ ሞቅሞቅንና የተለያዩ የሥጋ ሥራዎችን ወደ ጎላ ጥሎ የጌታን ድምጽ ለማዳመጥ ራሱን የሰጠ አገልጋይ ምሳሌ ነው። በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህንን ያህል የእድገት ልዩነት ያላቸው ሰዎች መገኘታቸው ያስገርማል። ግማሾቹ በሞቅሞቅ ጊዜአቸውን ሲያባክኑ ሌሎች ግን የጌታን ድምጽ ለማዳመጥና እርሱ የሚለውን ለመታዘዝ ልቦናቸውን ሲከፍቱ ይታያሉ።

አንድ አገልጋይ ከጌታ የማዳመጥ ሕይወት በሚርቀው ጊዜ ነው ነገሮችን በራሱ ማስተዋል እያብላላ ጨቅጫቃና ተከራካሪ የሚሆነው። ይህ ዓይነቱ አገልጋይ የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነትና ድምጽ ሳይጠይቅ በራሱ ግምትና በብዙሃኑ አሳብ ብቻ የሚመራ አገልጋይ ነው። ስለዚህም ተከራክሮና ተጨቃጭቆ ከማሸነፍ በቀር ሌላ መንገድ ለእርሱ መሸነፍ እንጂ መፍትሄ አይደለም። በአንጻሩ፥ በሕይወቱ ያደገ አገልጋይ የጌታን ነገር የሚያስተውል አገልጋይ ነው። የረጋና የጽሞና ሕይወት ይታይበታል። ስለዚህም እንደ አጋቦስ ከጌታ እያደመጠ ለወገኖቹ የሚጠቅምን ቃል ሲያመጣ እንጂ ሲነታረክ አይታይም። ከሰው ጋር ከሚነጋገርበት ጊዜ ከጌታ ጋር የሚነጋገርበት ጊዜ ይበልጣል።

ለአገልግሎታችን እድገት ዋነኛ ጠንቅ ከሆነው ግለቂያ ከሌለው የሞቅሞቅ ሕይወት እንድንድን፥ የሚከተሉትን መመሪያዎች ብንከተላቸው ከዚህ በፊት ጌታ ካስተማረን እውነቶች ጋር ተጨምረው ይጠቅሙናል ብዬ አምናለሁ።

1) በነገር ሁሉ አሸናፊና ተሰሚ ሆኖ የመውጣት መንፈስ እንዳያጠቃን ልባችንን እንጠብቅ። በአገልግሎት አካባቢ ሌሎችም ሆኑ እኛ ስለምናረጋቸው አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ጥያቄዎች ቢነሱ መጀመሪያ መመለስ ያለብን ጥያቄ፦ «ይህ ነገር የጌታ ፈቃድ ነው ወይስ አይደለም?» የሚለውን መሆን አለበት። የጌታ ፈቃድ ሆኖ ከተገኘን እርሱ የፈቀደውን ይሥራ ብለን መንገዱን ከመልቀቅ በስተቀር አማራጭ የለንም። ነገሩ የጌታ ፈቃድ ላለመሆኑ በማያወላውል ሁኔታ ከተረጋገጠ ያንን ነገር የማስቆም ሥልጣን እንዳለን ለማሳየት በእልህ ሳይሆን በማስተዋልና በትህትና ሁኔታዎች የሚስተካከሉበትን መንገድ ብንፈጥር ታማኝነታችን የበዛ ይሆናል።

2) *ጌታ እነርሱን ከመውደድ ያልከለከለውን የሰዎችን ሁኔታና ማንነት እየቆጠርን በእግዚአብሔር ቤት ሊኖራቸው የሚገባውን ሰፍራ ከመወሰን እንቆጠብ።* የእግዚአብሔር ቤት ለደካሞች እንጂ ለበረቱት አይደለችም፥ ለቆሸሹት እንጂ ለነጹት አይደለችም፥ ለታመሙት እንጂ ለጤነኞች አይደለችም። በሰዎች ውስጥ ያለውን ጸጋ እንመልከት። በሌሎች ሕይወት ውስጥ ከሁሉ በፊት ክርስቶስን እንይ።

3) *ሕይወት ለማይሆን ነገር ማለቂያ የሌለው ክርክር ውስጥ ከመግባት እንጠበቅ።* ብዙ ጊዜ በክርክርና በጭቅጭቅ ዘመናችንን የምናባክንባቸው ጉዳዮች ክርክሩን ብናሸንፍም ባናሸንፍም እለማደጋችንን ከማሳየት በቀር ምንም ለውጥ የማያመጡ ነገሮች ናቸው። ከልባችን ሆነን ብናስተውል፥ ለጭቅጭቅ ቀርቶ ለሕይወት ለሚውሉ ጉዳዮች እንኳ ለመሮጥ በቂ ጊዜ እንደሌለን እንገነዘባለን።

11

ማስተዋል ይኑርህ

ምዕራፍ 12፥ 1–25



ንጉሥ ሄሮድስን ሰይጣን በድንገት መጥቶ በቤተ ክርስቲያን ላይ ስደትን እንዲያስነሳ ከእንቅልፉ የቀሰቀሰው ይመስላል። ይህ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሰው ሄሮድስ ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን ይገዛ የነበረው የታላቁ ሄሮድስ የልጅ ልጅ ነው። የአይሁድ በሄሮድስ ቤተ ሰብ ላይ ያላቸው ጥላቻ እጅግ የከፋ ቢሆንም ሄሮድስ በብልሃት የያዛቸው ይመስላል። ስለዚህም ያዕቆብን በሰይፍ ከገደለ በኋላ አይሁድን ደስ ያሰኘ ስለመሰለው ጴጥሮስን ደግሞ ያዘው። ሄሮድስ የቂጣ በዓል በሚከበርበት ወራት በጴጥሮስ ላይ ምንም ዓይነት የፍርድ እርምጃ ለመውሰድ አለመፈለጉ ምናልባት አይሁድ በበዓሉ ምክንያት የተጨናነቀ ፕሮግራም ስለሚኖራቸው እነርሱን ለማስደሰት ለሚያደርገው ነገር ምንም ዓይነት ምላሽ እንደማይሰጡት ገምቶ ይሆን?

በቤተ ክርስቲያን ግን ስለ ጴጥሮስ አብዝቶ ጸሎት ይደረግ ነበር። የጴጥሮስ ፍጻሜ በነገሥታት ንጉሥ በእግዚአብሔር እጅ እንጂ በሄሮድስ ወይም በአይሁድ እጅ አልነበረም። ሄሮድስ ጴጥሮስን ለፍርድ ሊያወጣበት ያሰበባት ያቺ ቀን ሳትነጋ የጌታ መልአክ ጴጥሮስ ታስሮበት ወደ ነበረበት ወኅኒ ተላከ። የጴጥሮስ በመከራ መካከል ሆኖ እንደዚያ በሰላም ማንቀላፋት ያስደንቃል። ከዚያ በላይ የሚያስደንቀው ግን መልአኩ ጴጥሮስን ከእንቅልፉ ቀስቅሶ ከእስር ቤት እየመራ እስከሚያወጣው ድረስ ነገሩ ለጴጥሮስ ግልጽ አለመሆኑ ነው። ይህ ሁሉ ሁኔታ ለጴጥሮስ ራእይ ወይም ሕልም ስለመሰለው ምናልባት ከእንቅልፍ ለመንቃት ሙከራ ሳያደርግ አይቀርም። ነገሩ ግን እውን ነበር። በእውነትም እግዚአብሔር ጴጥሮስን ከአሳዳጆቹ ታድነታል።

ጴጥሮስ መጀመሪያ ከወኅኒ ሲወጣ የሄደው ወገኖች ተሰብስበው ሲጸልዩበት ወደ ነበረበት ወደ ማርቆስ ቤት ነበር። በሩንም ባንኳኳ ጊዜ ሮዴ የተሰኘችው ገረድ በሩን ለመክፈት ቀረበች። ሮዴ ጴጥሮስ መሆኑን በማወቋ ምክንያት በደስታ መፈንደቋና በሩን ሳትከፍት

ዜናውን ለማብሰር ወደ ውስጥ መሮጧ ክርስቲያን ነበረች ለሚል ግምት ይጋብዛል። ጴጥሮስ ተፈታ ከሚሏቸው ይልቅ መልአክ ተገለጠ ቢሏቸው የሚቀልላቸው እነዚህ የጸሎት ሰዎች በመጠራጠር ደጁን ከፍተው ጴጥሮስ መሆኑን አረጋገጡ፥ እርሱም ወደ ውስጥ ገብቶ ጌታ ያደረገውን ድንቅ ከመሰከረላቸውና ለክርስቶስ ወንድም ለያዕቆብ እንዲሁም ለሌሎች ወንድሞች እንዲነግሩ ካዘዛቸው በኋላ ወጥቶ ሄደ።

በዚያች ሌሊት መገረም የሞላው በማርቆስ ቤት ብቻ አልነበረም። ጴጥሮስን ይጠብቁ በነበሩት ቄፍሮች ዘንድም ታላቅ መገረም የተሞላ ሁከት ነበር። የሁከቱ መንስኤ፦ «ጴጥሮስን ምን አግኝቶት ይሆን?» የሚል ነበር። ጴጥሮስን አስፈልጎ ያጣው ሄሮድስ ጠባቂዎችን ከመረመረ በኋላ የሞትን ፍርድ ፈረደባቸው።

ሄሮድስ ከጢሮስና ከሲዶና ሰዎች ጋር የተነካካበት ጉዳይ በግልጽ ባይታወቅም፥ ምናልባት ጢሮስና ሲዶና የሚዲትራንያን ወደቦች ስለነበሩ በቂሣሪያና በእነዚህ ሁለት የወደብ ከተሞች መካከል ከንግድ ፉክክር የመነጨ ጠብ ተነስቶ ይሆናል ብሎ መገመቱ ከእውነት የራቀ አይሆንም። ያም ሆነ ይህ፥ በቢትወደዱ አስታራቂነት የጀመሩትን የእርቅ ድርድር ሳይጨርሱ ሄሮድስ በእግዚአብሔር መልአክ ተመትቶ ሞተ። የመቀሰፉ መንስኤ ግልጽ ነው፥ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ለራሱ ወስዷልና።

የእግዚአብሔር ቃል ግን እያደገ ሄደ። የሮም ነገሥታት እየመጡ ያልፉ ነበር፥ የፖለቲካውም ሁኔታ ይቀያየር ነበር፥ የጌታ ቃል ግን ጸንቶ ሁሉን ያሳልፍ ነበር። ይህንን የማይሞተውንና የማይሻረውን ሕያው ቃል ይዘው ነበር በርናባስና ሳውል ከኢየሩሳሌም በመንፈስ ቅዱስ ተልከው የወጡት። ከብዙ ትግልና ከብዙ ፍሬ በኋላ ማርቆስን ይዘው ወደ መጡበት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።

ለተጠራበት ዘመንና ሕዝብ የደህንነትን ድምጽ ሲያስተጋባ የነበረው ነብዩ ኢሳይያስ (42፥19–20) ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ ማስተዋል ማጣት ሲናገር እንዲህ አለ፦ «ከባሪያዬ በቀር ዕውር ማን ነው? እንደምልከው መልእክተኛዬስ በቀር ደንቆሮ የሆነ ማን ነው? እንደ ፍጹሙ ወይስ እንደ እግዚአብሔር ባሪያ እውር የሆነ ማን ነው? ብዙ ነገርን ታያላችሁ ነገር ግን አትጠባበቁትም፤ ጆሮአችሁም

ተከፍተዋል፥ ነገር ግን አትሰሙም»። በዘመኑ ከስደት ወደ ስደት ሲንገላታ የነበረው የእግዚአብሔር ሕዝብ የማዳኑን ክንድ እንዳያስተውል መንፈሳዊ ድንዛዜ ወርዶበት ነበር።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አስራ ሁለት ውስጥም የተለየ ያለማስተዋል ሁኔታ ይታያል። ምንም እንኳ እነ ጴጥሮስ የደረሰባቸው ስደት በኢሳይያስ ዘመን እንደነበረው የእግዚአብሔር ሕዝብ ከኃጢአታቸው የተነሳ ባይሆንም፥ ጌታ ለጸለዩት ጸሎት መልስን ይዞ ሲመጣ ያስተዋሉ አይመስልም። በሕይወታችን ያለማስተዋል ዘልቆ ሲገባ የመጀመሪያ ምልክቱ የጸለይነውን የጸሎት መልስ አለማየት ነው። መከራ በሚደርስብን ጊዜ እንጸልያለን። እርስ በርሳችን የጸሎትን ርዕስ እየተከፋፈልን በጸሎት እንተጋለን። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ እንደምንጸልይላቸው ለማያውቁ ወገኖችም ሳይቀር እንጸልይላቸዋለን። የእግዚአብሔርን ሕዝብ በስደት የሚያስጨንቁት አምባገነኖች ሲበዙ ጌታ ለሕዝቡ እንዲበቀል አብዝተን ወደ እርሱ እንጮሃለን። መጸለዩንስ ጸለይን፥ የጸሎት መልሳችንን ስንቶቻችን እያስተዋልን እንመላለሳለን? ማስተዋል ከጎደለው ሕይወት እንድንድን የሚከተሉትን ፍሬ አሳቦች እናጢናቸው።

I. ጌታን የነገ ብቻ አምላክ አናድርገው (12፥1–11)።

ጴጥሮስ ከሄሮድስ በተነሳው ቁጣ ምክንያት ወደ ወኅኒ ሲጣል በውስጡ ከነበረው ሰላም የተነሳ ከሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር። ይህ የሚያሳየን ጴጥሮስ የነበረበትን ሁኔታ ለእምላኩ ከነገረ በኋላ ጌታ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሊያድነው እንደሚችል ተማምኖ ማረፉን ነው። እንደጠበቀውም እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ከነበረበት እስራት ሊፈታው ወደደ። ጴጥሮስ ግን ሁኔታውን አላስተዋለም ነበር። ጌታ በዚያን ወቅት እያደረገለት የነበረውን ተአምር ከማስተዋል ይልቅ ገና ወደፊት የሚፈጸም ራእይ አድርጎ ማመን ቀለለው። ነገሩ ቀላል ነበር። እግዚአብሔር የጴጥሮስን ሁኔታ ተመለከተ፥ የውስጡን ጭንቅት አደመጠ፥ መልስንም ላከለት። ጴጥሮስ ግን ጌታን የነገ ብቻ አምላክ አድርጎት ነበርና ነገሩን ራእይ ነው ብሎ ለመደምደም ሞከረ።

በሕይወታችን በዚህ ዓይነቱ አለማስተዋል የምናልፍባቸው ጊዜአቶች ጥቂቶች አይደሉም። ስብከታችን፥ ዝማሬአችን፥ ሟውውታችንና የእቅዳችን አቅጣጫ፦ «እንድ ቀን ጌታ ይሠራል» በሚል የነገ ተስፋ ብቻ ተሞልቶ ዛሬ ጌታ እየሠራ ያለውን ድንቅና ተአምራት ሳናስተውል እንዳናልፈው ጥንቃቄ ያስፈልገናል። ጌታ፦ «በመካከላችሁ ድንቅን ነገር አደርጋለሁ» እያለ በወደፊት ተስፋ ብቻ ከዓመት ዓመት የሚያሸጋግረን ከሆነ እኛ አገልጋዮች የምስኪኖች ምስኪን ነን። ጌታ ኢየሱስ ዛሬም ይሠራል! ዛሬም እየፈወስ ነው። ዛሬም ነፍሳትን ከእጋንንት እስራት እየፈታ ነው። ዛሬም ነፍሳትን እየለወጠ ነው። «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው» (ዕብ. 13፥8)። የትናንት ብቻ አይደለም፥ የነገም ብቻ አይደለም፥ ኢየሱሳችን የዛሬም ነው!



ጌታን የነገ እምላክ አናድርገው ስንል አንዳንድ ጊዜ እንደምናደርገው ጌታ ይሠራል በሚል የወደፊት ውጥን ውስጥ ብቻ በድንዛዜ እንዳንኖር መጠንቀቅ እንደሚያስፈልገን መነጋገራችን ነው። ይህም ማለት ጌታ ስለነገ እየገለጸና እየተናገረ በተስፋ እንድንጠብቀው የሚፈልግበት ጊዜ በፍጹም የለም ማለታችን አይደለም። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ስለነገ ጌታ የገለጸልህን ተስፋ በትዕግስት ስትጠባበቅ ዛሬ እያደረገ ያለውን ታላቅ ሥራውን እንዳትዘነጋ ጥንቃቄ አይለይህ።

II. ሁሉን ነገር መንፈሳዊ አናድርገው (12፥12–17)።

ጴጥሮስን ጋርዶት ከነበረው ያላነሰ አለማስተዋል ለእርሱ ሲጸልዩ በነበሩት ወገኖች ላይም አንጎብቦ ነበር። ለጴጥሮስ የጸለዩት ጌታ ከሄሮድስ እጅ እንዲታደገው ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ይህም ትጋታቸው ትልቅ ምላሌ ይሆነናል። ሆኖም ጌታ ጸሎታቸውን ሰምቶ መልሱን እቤታቸው ድረስ ሲያመጣው ማመን ያስቸገራቸው ለምን ይሆን? በእርግጥም አላስተዋሉም ነበር ከማለት በቀር ሌላ ትንታኔ ልንሰጠው የሚያስቸግር ሁኔታ ነው። የጸሎታቸው መልስ ከጠበቁት በላይ ፈጥኖ የመመለሱ ሁኔታ በእርግጥም ለማመን ሊያስቸግር ይችል ይሆናል። የእነርሱ አለማስተዋል ሁኔታ ከጴጥሮስ ለየት ያለ

ይመስላል። የእነርሱ ያለማስተዋል መንስኤ፥ ነገርን ሁሉ «መንፈሳዊ» የማድረግ ሁኔታ ነበር። አሁንም ሁኔታው ቀላል ነበር። እግዚአብሔር ጴጥሮስ በመከራ ውስጥ እንዳለ ተመለከተ፥ የወገኖችንም እንባ ቆጠረ፥ መልሳቸውንም ይዘላቸው መጣ። እነርሱ ግን አላስተዋሉም ነበር። የጴጥሮስን መፈታት ከማመን ይልቅ የመላእክትን መገለጥ ማመን ቀለላቸው። ለዚህ ሁሉ የዳረጋቸው ነገሮችን ሁሉ «መንፈሳዊ» የማድረግ ዝንባሌ ነበር።

ከዚህም ዓይነት ሁኔታ የዚህ ዘመን አገልጋዮች ጥንቃቄ ይጠበቅብናል። ጌታን የተለያዩ ጥያቄዎችን ዘወትር እንጠይቀዋለን። ጌታም መልስን ይሰጠናል። ይህ ዓይነቱ ሕይወት የዘወትር ልምምዳችን ነው፥ ሲሆንም ይገባዋል። ነገር ግን ለሆነው ነገር ሁሉ ያልተሰጠውን መንፈሳዊ ምስጢር ልንሰጠው ስንጥር እንስታለን። ያለምናቸውን ሕልሞች በሙሉ መንፈሳዊ ትርጉም ለመስጠት «ጸጉር ስንጠቃ» ውስጥ ስንገባ፥ «በኢየሱስ ስም» ብለን መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስንገልጥ ላገኘነው ጥቅስ ሁሉ በዚያን ወቅት ወደ እኛ እንደመጣ መንፈሳዊ መገለጥ አድርገን ለመውሰድ ስንል ብቻ ስንለጥጠው፥ ዓይናችንን ስንጨፍን ለታየን በአእምሮአችን ተስሎ ለቀረ ቅርጽ ሁሉ መንፈሳዊ ትርጉም ስናክልበት፥ ያን ጊዜ ወደ ማስተዋል ጎዳና ልባችንን የምንመልስበት ጊዜ መድረሱን እንዘንጋ። ከእግዚአብሔር የሚሰጠን ማንኛውም ነገር መንፈሳዊ ነው። እኛ ምንም ነገር ብናደርግ መንፈሳዊነቱን ልንቀንሰውም ሆነ ልንጨምረው አንችልምና በማስተዋል እንመላለስ።



አንዳንድ ጊዜ ሁሉን ነገር «መንፈሳዊ» ለማድረግ ስንሞክር የጌታን መሠረታዊ አሠራር እንስተዋለን። ሌላ ጊዜ ደግሞ መንፈሳዊ ምስጢራትን ጌታ ሊገልጥልንና ሊያለማምደን ሲፈልግ ከለመድነው ሕይወት የተለየ አዲስ ልምምድ ውስጥ ላለመግባት ከጌታ ጋር እንታገላለን። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ከጌታ የምትቀበለው ማናቸውም ልምምድ የእንተን እርዳታ የማይፈልግ ራሱን የቻለ መንፈሳዊ መሆኑን አትዘንጋ። ነገር ግን ይህን እውነት ካለልክ ወስደህ ከጊዜ ወደ ጊዜ ጌታ ወደ ሕይወትህ የሚያመጣቸውን ልዩ መንፈሳዊ ልምምዶች ከማስተዋል እንዳትደነዝዝ ልብህን ጠብቅ።

III. የጌታን የበቀል እጅ እናስተውል (12፥18–25)።

ጌታ ጴጥሮስን ከአስር ቤት በአስደናቂ ሁኔታ ነጻ በማውጣት ብቻ አስገራሚ ሥራውን አላቆመም ነበር። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ለእርሱ የሚጸልዩትም ቁምር ማመን እስኪያስቸግራቸው ድረስ ለጸሎታቸው መልስን በመስጠት አስገርሟቸው ነበር። በተጨማሪም፥ ለአገልጋዮቹ ማላወቅ የፈለገው ነገር ነበር። ይኸውም የክብሩ ተቀናቃኝ የነበረውን ሄሮድስን መቅጣት እንደሚችል ነው። እግዚአብሔር ትናንትና አገልጋዮቹን ሲያሳድዱበትና ሲጨፈጭፉበት የነበሩትን የመስቀሉን ጠላቶች ዝም አለ ማለት ዛሬም ዝም ብሎ ያልፋል ማለት አይደለም። ስለዚህም ሄሮድስን የትል መንጋ ሰደደበት፥ እስኪሞትም ድረስ ቦጥቡጠው ጨረሱት።

እግዚአብሔር የሚቃወሙትን እንደሚበቀል እናውቃለን። የጌታ ቃል እንደሚያስተምረን በሕዝቡ ላይ እንዳሻቸው በሚነሱት ተቃዋሚዎቹ ላይ ጌታ እንደሚፈርድባቸው እንገነዘባለን። አንዳንድ የእግዚአብሔርን ሰዎች በሰቆቃ ውስጥ ያሳለፉ የመስቀል ጠላቶች ኑሯቸውን በሰላም የቀጠሉ ቢመስለንም እንኳ፥ የጌታ ቁጣ ፈጥኖ የሚነድበት ጊዜ አንደሚመጣ እንዘንጋ። ይህንን እውነት መገንዘብ ከማጉረምረም ሕይወት ይጠብቀናል።

በዚህ በዘመናችን ክርስቲያኖችን መግቢያ ሲያሳጡ የነበሩ ሁሉ ዛሬ የት እንዳሉ ግልጽ ነው። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ግን እንዳበበች አለች። እግዚአብሔር ያዕቆብን «በምድረ በዳ በጥማት፥ የነፋስ ጩኸትም በሞላበት ውድማ አገኘው፤ ከበቡው ተጠነቀቀለትም፤ እንደ ዓይን ብሌን ጠበቀው» (ዘዳግ. 32፥10)። ጌታ ለአገልጋዮቹም እንደዚሁ ይጠነቀቃል፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲነኩበት የዓይኑን ብሌን የነኩበትን ያህል ያንገበግበዋልና (ዘካ. 2፥8)። ትናንትናና ከትናንት ወዲያ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የተነሱትን ዝም ብሎ አልፎአልና ዛሬም ዝም ብሎ ያልፋቸዋል ብሎ መደምደም ማስተዋል የጎደለው አመለካከት ነው።



አንዳንድ ጊዜ ጌታ በእርሱና በሕዝቡ ላይ የሚነሱትን የመስቀል ጠላቶች አሁኑኑ ካልቀጣ በእርግጥም በመካከላችን እየሠራ መሆኑን እንጠራጠራለን። ሌላ ጊዜ ደግሞ በጌታ

ሥራ ላይ የሚነሱት ሁሉ እንዳሻቸው ሆነው እንዲያልፉ የጌታ የማይለወጥ ፈቃዱ እንደሆነ አድርገን እንቆጥራለን። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ማንን ዛሬ ማንን ደግሞ በመጨረሻው የፍርድ ቀን የመቅጣቱ ውሳኔ የጌታ መሆኑን አትዘንጋ።

ማስተዋል ከጎደለው ሕይወት እንድንድን መጸለይ ተገቢ ነው። መጸለይም ብቻ አይደለም ከዚያም አልፈን መውሰድ ያሉብንን ጥንቃቄዎች ለመውሰድ ዝግጁዎች መሆን ያሻናል። ይህንን ለማድረግ ማስተዋላችንን የሚሰርቁትን እንቅፋቶች ማወቅ መልካም ጅማሬ ነውና የሚከተሉት አሳቦች ይጠቅሙን ይሆናል።

1) ዘወትር የምንጸልያቸውን ጸሎቶች በማስተዋል እንጸልያቸው። ይህንን ካላደረግን ጸሎት ልማድ ብቻ ይሆንና የትኛው እንደተመለሰና የትኛው እንዳልተመለሰ ባለማስተዋል በድንግዝግዝ እንመላለሳለን። ጌታ የመለሳቸውን ጸሎቶች ሳያስተውሉ ዘወትር ከለቅሶ ሕይወት አለመላቀቅ የዚህ ዓይነቱ ሕይወት ምልክቱ ይሆን?

2) እግዚአብሔርን በእኛ መንገድ ብቻ አንጠብቀው። አንዳንድ ጊዜ ከሰማይ ብርሃን ተገልጦ እስኪነበኝን ስንጠባበቅ ጌታ በጉያችን ያስቀመጠልንን በረከት እንስተዋለን። ከመጠን ያለፍን «መንፈሳዊ» ስንሆን ጌታ ሊሠራ የወደደውን መሠረታዊ የአሠራር ዘዴ ልንስተው እንችላለን።

3) ማንኛውንም የእግዚአብሔር ሥራ ከመናቅም ሆነ ከማጋነን እንጠበቅ። አንዳንድ ጊዜ ጌታ ያልፈወሰውን ፈወሰ፥ ያልተናገረውን ተናገረ፥ ያልለመጠውን ለመጠ፥ ያልተገለጠውን ደግሞ ተገለጠ ብለን መመስከር ያለብን ይመስለናል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ለጌታ ክብር ለመመስከር ከተደረጉልን ነገሮች «ርቀን» እንመርጥለታለን። እግዚአብሔር የተጋነነን ነገር አይባርክም። ጌታ ያደረገውንም ነገር መደባበቁ ለክብሩ አይውልም።

12

በእግዚአብሔር ዕረፍ

ምዕራፍ 13፥1–52



በርናባስና ሳውል አገልግሎታቸውን ፈጽመው ከኢየሩሳሌም ከተመለሱ በኋላ ከነቢያትና ከመምህራን ጋር በጾምና በአምልኮ ሲተጉ ሳሉ መንፈስ ቅዱስ ለሥራው እንደሚፈልጋቸው በተቀሩት አገልጋዮች ፊት አረጋገጠላቸው። ይህ መልእክት በምን ዓይነት መልኩ እንደተገለጠላቸው ሉቃስ በግልጽ ባይነግረንም፥ ለመንፈስ ቅዱስ በመታዘዝ እጆቻቸውን ጭነው በመጸለይ እንዳለናበቷቸው ገልጿል። እነርሱም ተነስተው ወደ ሴሌውቅያ ተጓዙ። ይህ የአገልግልት ጉዞ የሳውል (ጳውሎስ) የመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞ ነው። ክርስቶስ ኢየሱስ ከማረጉ በፊት ባዘዘው መሠረት ወንጌል በኢየሩሳሌም፥ በይሁዳና ከዚያም አልፎ በሰማርያ ተሰበከ። አሁን ደግሞ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ለአሕዛብ የሚዳረስበት ወቅት መጣ።

በርናባስና ሳውል ከሴሌውቅያ አልፈው ወደ ቆጵሮስ ሄዱ። በዚያም ስልማና በምትባል ደሴት ወንጌልን ሰበኩ። አንድም ስፍራ ሳይቀራቸው ደሴቲቱን በወንጌል ሲያዳርሷት ማርቆስ እነርሱን ከማገልገል ወደ ኋላ አላለም ነበር። ሉቃስ ከሰጠን መግለጫ እንደምንረዳው፥ የስልማና ደሴት አገረ ገዢ የሆነው ሰርግዮስ ወንጌልን ለመስማት በተመኘ ጊዜ የተቃወመውን ጠንቋዩን ኤልማስን እግዚአብሔር በጳውሎስ ተጠቅሞ እንዳሳወረው፥ አገረ ገዢውም ከጌታ ትምህርት የተነሳ በጌታ እንዳመነ እንገነዘባለን። ከዚህ ጊዜ አንስቶ ሉቃስ ሳውልን ጳውሎስ ብሎ መጥራት ይጀምራል።

የሚቀጥለው የበርናባስና የጳውሎስ ጉዞ ወደ አንጾኪያ ነበር። ማርቆስ ከእነ ጳውሎስ ተለይቶ ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለሱ ምንም ዓይነት ማብራሪያ ያልተሰጠ ቢሆንም፥ ጳውሎስ በነገሩ እንዳልተስማማ ግልጽ ነው (15፥35)። በሰንበትም ቀን ወደ ምኩራብ ገብተው በተቀመጡ ጊዜ ብዙም ሳይቆይ የአገልግሎት በር ሲከፈትላቸው ይታያል። ጳውሎስም በዚያ ስፍራ የሰበከው ስብከት ፍሬ ነገር፥

እስጢፋኖስ ከመገደሉ በፊት የተናገረውን የመከላከያ ምላሽ ይመስላል። በመጀመሪያ ወደ ቀድሞ ታሪክ መለስ በማለት ከኦሪት ዘጸአት ጀምሮ ዳዊት እስከነገሰበት ዘመን ድረስ የሆነውን ካብራራ በኋላ እግዚአብሔር ከዳዊት ዘር በሆነው በኢየሱስ አማካኝነት መድኃኒትን ለእስራኤል እንዳመጣ ገለጸ። በሁለተኛ ደረጃ የዮሐንስን ለክርስቶስ መንገድ ጠራጊነት ከገለጸ በኋላ ጥርት ባለ ሁኔታ ወንጌልን ሰበከ። የሙሴ ሕግ ማንንም ያድን ዘንድ እንደማይቻለው፥ በክርስቶስ ማመን ግን ጽድቅን እንደሚያጎናጽፍ በድፍረት ሰበከ። በሦስተኛ ደረጃ ጳውሎስ ሰሚዎቹን ከእርሱ ያደመጡትን ቸል እንዳይሉ ካስጠነቀቀ በኋላ ንግግሩን አጠናቀቀ።

ዘወትር ወንጌል ሲሰበክ እንደሚሆን ሁሉ ገሚሶቹ አመኑ ገሚሶቹ ግን አልተቀበሉትም። ነገሩ ግን በዚህ ብቻ አላቆመም። በሁለተኛው ሰንበት አይሁድ በቅንአት እስኪቃጠሉ ድረስ አብዛኛዎቹ የከተማው ሕዝብ ወንጌልን ለመስማት ተሰበሰበ። ጳውሎስም ሳይፈራ የክርስቶስን ወንጌል ቢቀበሉ እድሉ በፊታቸው እንዳለ፥ ባይቀበሉ ግን ወደ አሕዛብ ዘወር እንደሚሉ ካስገነዘባቸውና ብዙዎችን አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ካፈለሰ በኋላ በተነሳባቸው ስደት ምክንያት የእግራቸውን ትቢያ አራግፈው ወደ ኢቆንዮን ተጓዙ።



በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ፡- «ዕረፉ፥ እኔም አምላክ እንደ ሆንኩ እወቁ» (46፥10) የሚልን የምክር ቃል እናገኛለን። በተለይም እኛ የጸጋው ዘመን አማኞች ሁሉን በመስቀሉ ሞት ባከናወነልን በጌታ በኢየሱስ ሙሉ በሙሉ መደገፍና ማረፍ አለብን። በሕይወታችንና በአገልግሎታችን የምናደርገውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ በእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ ውስጥ ተከልለን እንደማድረግ የሚመቸን የተሻለ ስፍራ እንደሌለ ለጥቂት ጊዜ እንኳ ከጌታ ጋር አብረን የተጓዝን ክርስቲያኖች እናውቀዋለን። ነገር ግን ይህን በጌታ የመደገፍን ሕይወት ቀስ በቀስ በምናጣበት ጊዜ የመቅበዝበዝ ሕይወት እየተተካ ይሄዳል። ልባችንም በጌታ ስላላረፈ በአገልግሎታችን የሚያልፈው ነገር ሁሉ ጥያቄን በአእምሮአችን ረጭቶ ያልፋል። የእግዚአብሔር አሠራሩ አልገባችሁ ይለናል።

እግዚአብሔር ለምን አልተናገረኝም? ጌታ ሐሰተኞችን ለምን ዝም ይላል? ጌታ ለምን አይጠቀምብኝም? ለምንስ በሮች ሁሉ ተዘጉ? የሚሉትና እነዚህን የመሳሰሉት ጥያቄዎች ካለማቋረጥ በሕይወታችን በሚመላለሱበት ጊዜ በጌታ ላይ የማረፋችን ልምምድ እየተናጋ መሄዱን እንዘንጋ። ጌታ ግን የሚያደርገውን የሚያውቅ አምላክ ነው። የእኛን በእርሱ ላይ ማረፍ ብቻ ይፈልጋል። እኛ፦ «ጌታ ሆይ አንተ ሁሉን በዓላማ የምታደርግ አምላክ ነህ» በማለት ሁሉንም ጥያቄአችንን ለእርሱ አስረክበን በምናርፍበት ጊዜ እኛ በፈለግነው ጊዜና ሁኔታ አይሁን እንጂ በጌታ ጊዜ ድንቅን ነገር ማየት እንጀምራለን።

በርናባስና ሳውል አገልግሎታቸውን ጨርሰው ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሱ በኋላ በሕይወታቸው የተከናወነውን ሁኔታ ብንከታተል በጌታ ላይ ስለማረፍ የማያዳግም ትምህርት ልናገኝ እንችላለንና በሦስት ነጥቦች ከፍለን እንመልከተው።

I. እኛን ለሥራው መለየት የጌታ ድርሻ ነው (13÷1–3)።

በአንጾኪያ በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመንበርከክና ጌታን በማምለክ የሚገኘውን ዕረፍት ያስተዋሉ አገልጋዮች ነበሩ። እነዚህ አገልጋዮች ሲያመልኩና ሲጠሙ ሳሉ መንፈስ ቅዱስ ለሥራው የሚፈልጋቸውን በርናባስንና ሳውልን ለያቸው። እነርሱም ለመንፈስ ቅዱስ ምርጫ አሜን በማለት ለእግዚአብሔር ጸጋ አደራ ከሰጡአቸው በኋላ አሰናበቱአቸው።

ይህ የጠቀስነው ክፍል ትልቅ በጌታ ላይ የማረፍ ምሳሌ ነው። በሕይወታችን ያለውን የጌታን ፈቃድ ለመለየት በእርሱ ላይ በማረፍ መንበርከክ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው። ጌታ እኛን ሊያሰማራ ከፈለገው የአገልግሎት መስክ ሊያስቀረን የሚችል ብቸኛ ኃይል የእኛ ሁኔታ ነው። አንዳንድ ጊዜ ይህንና ያንን ለማድረግ ስንሯሯጥ እኛ ለጌታ ለማድረግ የፈለግናቸውን ብዙ ነገሮች በማድረግ ብቻ እንባክናለን። ጌታን ግን ይህ አያስደስተውም። ለጌታ ብለን ያላዘዘንንና ያልጠራንን መቶ ነገሮች ከምናከናውን፥ እርሱ ያዘዘንን አንዲት ነገር ብናደርግ፡ ጌታንም እናስደስተዋለን ለእክሊልም የሚበቃ አገልግሎት አከናውነን እናልፋለን። ጌታን ሳያደምጡና በረጋ መንፈስ

የመንፈስ ቅዱስን አሳብ ሳይረዱ ለአገልግሎት መሮጥ መቅበዝበዝን ያስከትላል። ሙሉ በሙሉ በጌታ በመደገፍና በማረፍ ውጤታማ አገልግሎት ማገልገል ይቻላል።

II. ጠላታችንን መቅጣት የጌታ ድርሻ ነው (13÷4–12)።

በርናባስና ሳውል ለአገልግሎት ገና ከመውጣታቸው የወንጌል ጠላት የሆነው ዲያቢሎስ ሊቋቋማቸው ተገናኛቸው። ጠላታቸው ዲያቢሎስ እንጂ ጠንቋዩ ኤልማስ አልነበረም። ለዚህም ነው ሳውል በሥጋው ሊቋቋመው ያልሞከረው ። ከጠንቋዩ ጀርባ የመናፍስት ኃይል ነበረ፥ በሳውል ውስጥ ግን የነገሥታት ንጉሥ የሆነው ኢየሱስ ነበረ። ጌታ በበርናባስና በሳውል አገልግሎት ውስጥ የነበረውን ፈቃድ ለመፈጸም ይህ የሰይጣን ሥራ ከመንገድ መወገድ ነበረበት። ይህ በሥጋ የማይቻል ነገር ነው። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ግን ተቻለ።

ወደ አገልግሎት በጌታ ተልከን በምንወጣበት ጊዜ ዘወትር የሰይጣንን ተቃውሞ እንደሚመጣ መጠበቅ አለብን። ከሚመጣውም ማንኛውም ዓይነት ተቃውሞ በድል ለመውጣት በሥጋችን ምንም ነገር ለማድረግ ስለማይቻለን አሁንም ሙሉ በሙሉ በጌታ መደገፍ ያስፈልገናል። ከእኛ የሚጠበቀው በመንፈስ የተሞላ ሕይወት ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስ ማንኛውንም የሰይጣን እንቅስቃሴ የመለየትና ከመንገድ የማስወገድ ኃይልና ስልጣን አለው።

III. ለአገልግሎታችን በርን መክፈት የጌታ ድርሻ ነው (13÷13–52)።

ጳውሎስና በርናባስ በጌታ የማረፍን ምስጢር በመላት እየተረዱና እየተለማመዱ በመሄድ ላይ ሳሉ፥ አዲስ ልምምድ በጎዳናቸው ላይ አጋጠማቸው። ጥሪያቸውንስ አወቁ፤ በመንገዳቸውም የሚያጋጥማቸውን የሰይጣን እንቅፋት ሊያስወግድ የሚችለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑንም ተገነዘቡ። አሁን ደግሞ ጌታ የሰጣቸውን የአገልግሎት ጥሪ በመላት ሊጠቀመብት ወደሚችሉበት ወደ ምኩራብ ደርሰዋል። ወንጌልን ለመስበክ ግን ምንም ዓይነት በር አይታይም (ቁ.

13-14)። የነበራቸው ምርጫ ጌታ ከፈቀደ በርን ሊከፍትሳቸው እንደሚችል በማመን ቁጭ ማለት ነበር። ይህንንም በማድረጋቸው ጌታ በርን ከፈተላቸው።

ይህ ታሪክ እንደ አገልጋዮች የማያዳግም ትምህርት አግኝተን ልባችንን ማሳረፍ እንደሚገባን ያሳያል። ጌታ ጥሪውን ግልጽ አድርጎልን፥ በጠላታችንም ላይ ድልን በድል እያነናጸፈን ሳለ በውስጣችን የሚነድደውን የአገልግሎት እሳት ለማውጣትና ለመጠቀም በሮች ሁሉ የተዘጉብን ሲመስለን ማጉረምረምና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንዳንገባ ልናስተውል ይገባናል። በመጀመሪያ ማድረግ የሚገባን፥ በእግዚአብሔር በመተማመንና በማረፍ ቁጭ ማለት ነው። ይህንን እውነት አለማስተዋል ለብዙ ስህተት ያጋልጠናል። በብዙዎቻችን ከተለመዱት ስህተቶች አንዱ ለአገልግሎታችን በር መዘጋት ምክንያት ነው ብለን የምናስበውን ሰው በክፉ ማንሳትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ምሳሽን መስጠት ነው።

የጠራን እግዚአብሔር በርንም ለመክፈት አይሳነውም በማለት በምናርፍበት ጊዜ መልካምን እናደርጋለን። ጌታ በፊልድልፍያ ቤተ ክርስቲያን ደስ እንደተሰኘ በእኛም ደስ ይለዋል፥ ጊዜውን ጠብቆ ሊያስተምረን የሚወደውን ካስተማረን በኋላ እንዲህ ይለናል፦ «ሥራህን አውቃለሁ፥ እነሆ በአንተ ፊት የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፤ ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃልና፥ ስሜንም አልካድክምና (ራእይ 3፥8)።

ሁሉንም ለጌታ ጥሎ ማረፍ ትልቅ የበረከት ምንጭ ነው። አገልጋይ ሙሉ በሙሉ በጌታ መደገፉን ትቶ በሥጋው መቅበዝበዝ በሚጀምርበት ጊዜ የሚከተሉት ድካሞች ያጠቁታል።

1) የማጉረምረም ሕይወት። ስለሆነውም ስላልሆነውም ዘወትር የሚያጉረመርም አገልጋይ በፍጹም በጌታ ላይ ማረፍን ያልተማረ አገልጋይ ነው። እንዲህ ዓይነቱ አገልጋይ በሆነ ባልሆነው ከሌሎች አገልጋዮች ጋር ሲጋጭ ይታያል። ዘወትር ያልተደረገን እንጂ የተደረገን ነገር አይቆጥርም። ስለተከፈተለት በር ጌታን ከማመስገን ይልቅ ስላልተከፈተው በር ማጉረምረም ይቀናዋል። በጌታ ልቡ ያረፈ

አገልጋይ በር አልተከፈተም ብሎ አይጣላም፥ በምትኩ እስኪከፈትለት ድረስ እያንኳኳ በምስጋና ይቆያል።

2) የሰይጣንንና የሥጋን ሥራ ለይቶ ማወቅ ይሳነዋል። አንድ አገልጋይ ሙሉ ለሙሉ በጌታው ልቡን ካላሳረፈ ነገሮችን የሚመዝነው በራሱ አስተሳሰብ ነው። የመንፈስ ቅዱስን አሳብ ከመጠየቁ በፊት የሁኔታዎችን መንስኤ በራሱ መንገድ ለመረዳት ይጥራል። ስለዚህም የሰይጣንና የሥጋ ሥራ ይማታበታል። እንዳንድ ጊዜ የሥጋ ሥራ ሁኔታዎችን እያተራመሰ ሳለ ሰይጣንን ሲገስጽ ጊዜውን በከንቱ ያባክናል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ሰይጣን በረቀቀ ዘዴው እየተተናኮለው ሳለ ነገሮችን ሁሉ ከሰው ጋር እያገናኘ በሥጋው ከሌሎች ጋር ሲጋጭ ይታያል። አንድ አገልጋይ ልቡ በጌታው ላይ ሲያርፍ ብቻ በረጋ መንፈስ ሆኖ ሁኔታዎችን ይመረምራል፥ እንዳመጣጣቸውም ይመልሳቸዋል።

3) የብልጠት ሕይወት ይታይበታል። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፥ አገልጋይ በመጀመሪያ ጥሪውን ለማወቅ፥ ከዚያም አልፎ በአገልግሎት ጎዳናው ላይ የሚገጥመውን የጠላት ኃይል ለመቋቋም፥ በተጨማሪም የአገልግሎት በር ፊጽሞ ዝግት ዝግትግት በሚልበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ በጌታው በማረፍ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ መጠበቅ አለበት። ይህ ዓይነቱ በእግዚአብሔር የማረፍ ሕይወት በሚጎድሰው ጊዜ የብልጠት ሕይወት ሊያጠቃው ይጀምራል። የተመኘው የአገልግሎት መስክ ውስጥ ለመሰማራት ጌታን ከማማከር ይልቅ በራሱ ጥበብ ነገሮችን ያመቻቻል። የጥበብን ቋንቋ ተጠቅሞ ሰዎችን ያሳምናል። በፊቱ የሚቋቋመውን የጠላት ውጊያ በክርስቶስ ስም ከመቃወም ይልቅ ከዚያ ሁኔታ የሚወጣበትን መንገድ ሲያወጣና ሲያወርድ ይታያል። በጌታ ልቡ ያረፈ አገልጋይ እንዲህ አይደለም። የደረሰበት ደረጃና በሕይወቱ የሚያልፈው ነገር ሁሉ በጌታ ፍጹም ፈቃድ እንደሆነ ያውቃል ስለዚህም ሁኔታዎችንና ሰዎችን በብልጠቱ ለመቆጣጠር ከመጣር ይልቅ በመጀመሪያ በጌታ መመራትን ያስቀድማል።

13

የሕይወት ውጣ ውረድና ጸጋው

ምዕራፍ 14፥ 1–28



ጳውሎስና በርናባስ ከአንጾኪያ ተሰድደው እስኪወጡ ድረስ ወንጌልን ከሰበኩ በኋላ ወደ ኢቆንዮን ተጓዙ። እንደልማዳቸውም ወደ አይሁድ ምኩራብ ገብተው ከአይሁድና ከግሪክ ሰዎች ብዙ እስኪያምኑ ድረስ ወንጌልን ሰበኩ። አይሁድ ግን በነገሩ ደስ አልተሰኙምና ኃይለኛ ስደት አነሣሡባቸው። ሁኔታውም የከተማው ሕዝብ ለሁለት እስኪከፈል ድረስ እጅግ የከፋ ነበር። አሕዛብና አይሁድም ሐዋርያትን ሊወግሯቸው ባሰቡ ጊዜ፥ አሳባቸውን አውቀው ልስጥራንና ደርቤን ወደሚባሉት ከተሞች ሸሹ።

በልስጥራን ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ተከናወኑ። የመጀመሪያው ፈውስ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ የጳውሎስ መወገር ነው። ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ አንካሳ የነበረ አንድ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ በጌታ ኃይል ቀጥ ብሎ ለመቆም ቻለ። ከተደረገው ተአምራት የተነሳ በሥፍራው የነበሩት ሰዎች አማልክት ሰዎችን መስለው ወደ እነርሱ እንደ ወረዱ ቆጥረው፥ በርናባስን ድያ፥ ጳውሎስን ደግሞ ሄርሜን ብለው የአማልክትን ስም ሰጧቸው። በአካባቢውም በነበረው ቤተ መቅደስ የነበረው የድያ ካህን ኮርማዎችንና የአበባን አክሊሎች በማምጣት ሊሰዋላቸው እንደፈለገ ወሬው ወደ ሐዋርያት በደረሰ ጊዜ በርናባስና ጳውሎስ ልብሳቸውን በመቅደድና ሕዝቡን በመማጸን በጭንቅ አስቆሟቸው።

ብዙም ሳይቆይ አይሁድ ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን ገስግሰው በመድረስና ሕዝቡን በማባበል ጳውሎስን ወገሩት። የሞተም መስሎአቸው ከከተማ አውጥተው ጣሉት። ጳውሎስ ግን ከወደቀበት ተነስቶ ወደ ከተማ ገባ፥ በነገውም ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤን በመውጣትና ወንጌልን በመስበክ ብዙዎችን ደቀ መዛሙርት ካደረጉ በኋላ ቤተ ክርስቲያንን አጽንተው ተለዩአቸው። በጉዞአቸውም «በጸ ስድያ አልፈው ወደ ጵንፍልያ መጡ፥ በጴርጌንም ቃሉን ከተናገሩ

በኋላ ወደ አጣልያ ወረዱ፥ ከዚያም ስለ ፈጸሙት ሥራ ለእግዚአብሔር ጸጋ አደራ ወደ ተሰጡበት ወደ አንጾኪያ በመርከብ ሄዱ። በደረሱም ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑን ሰብስበው እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ሁሉ ለአሕዛብም የሃይማኖትን ደጅ እንደ ከፈተላቸው ተናገሩ። ከደቀ መዛሙርትም ጋር አያሌ ቀን ኖሩ።» ጳውሎስ ወደ ገላትያ ሰዎች መልእክቱን የጻፈው በዚህ ጊዜ እንደሆነ ይታመናል።



ሕይወት ብርቱ ሰልፍ ነው። ሰው በሕይወት ዘመኑ የሚያሳልፈው ውጣ ውረድ ተመዝኖ አያልቅም። ባለፉት ዘመናት ሆኖአል አሁንም እየሆነ ነው ለወደፊትም ይቀጥላል። ይህ የሕይወት ውጣ ውረድ የሚሉት ነገር ክርስቲያንና ዓለማዊ አይልም። ለእርሱ ሁሉም አንድ ናቸው። ዓይነቱና መጠኑ ግን ይለያያል። በተለይም የክርስቶስ አገልጋይ የሚያልፍበት ውጣ ውረድ ለየት ያለ ነው። ነገር ግን ጌታ ስሙ ይባረክ እርዳታው ወደር የማይገኝለት ነውና ዘወትር አገልጋዮቹን በድል ያወጣቸዋል። ስለዚህ ዓይነቱ የሕይወት ውጣ ውረድ ሲናገር ጳውሎስ እንዲህ አለ፦ «መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፤ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ። ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» (ፊልጵ. 4፥ 12–13)።

በሕይወቱ የጌታ ጥሪ ላለበት ሰው ወደ አገልግሎት እንደ መውጣት የሚያጓጓው ነገር የለም። ከዚያ ጉጉቱና ጥማቱ ጋር ግን አገልግሎት ማለት ሰልፍ ማለት እንደሆነ በሚገባ ተረድቶ ራሱን ካሳዘጋጀ ብዙ ሳይቆይ ተስፋ መቁረጥ ያቆላስለዋል። ይህንን ለመቋቋም አገልጋይ ሙሉ በሙሉ በጌታ ጸጋ ላይ መደገፍ አለበት። የተጠራነው በጸጋ ነው፥ የምናገለግለው በጸጋ ነው፥ የምንቆመውም በጸጋ ነው። ለዚህ ክፍል በተመደበልን ምዕራፍ ውስጥ ሐዋርያት ካሳለፉት ሁኔታ የሕይወትን ውጣ ውረድና የክርስቶስን መጠን የሌለው የጸጋ ብዛት አስመልክቶ የምንማረውን እንመልከት።

I. ጸጋው በሽለቆ ውስጥ ያሳልፍሃል (14፥1–7)።

ጳውሎስና በርናባስ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢቆንዮን ሞትን ፊት ለፊት ተገናኙት። እንዲህ ዓይነቱ ለሞት የሚያደርሰው የመወገር መከራ በምኩራብ ውስጥ ይደርስብናል ብለው በፍጹም ሊያስቡ የማይችሉት ነገር ነው። በአይሁድ ዘንድ በምኩራብ አካባቢ የዚህ ዓነቱን ፍርድ በሰዎች ላይ ማሳለፍ ያልተለመደ ድርጊት ነው። ስለዚህም ከነበሩበት ከተማ ሸሽተው እስኪያመልጡ ድረስ ግራ መጋባት ውስጥ ወድቀው ነበር።

አገልጋይ በአገልግሎት ዘመኑ የሽለቆን ሕይወት እንደ ጳውሎስና በርናባስ ሞትን በመጋፈጥ ብቻ ሳይሆን በተለያየ መልኩ መጠበቅ አለበት። ሁሉም መልካም ነው ብለን ባሰብንበት ባልተጠበቀ ሰዓት የበረከትን ሕይወት ለመስረቅ የሚነሳ ፈተና አይጠፋምና ዘወትር ንቁዎች ልንሆን ይገባናል። አብረውን በአገልግሎት ይሰለፋሉ ያልናቸው ሰዎች ዋነኛ ተቃዋሚዎቻችን ሆነው ስናገኛቸው ሽለቆ ውስጥ መግባታችን ጥርጥር የለውም። ትልቅ መሳካትን የጠበቅንበት አገልግሎት እየሞተ ሲሄድ፥ ጌታም ሰጥቶን የነበረው አይዞህ የሚል ቃል ከምናልፍበት ሁኔታ የተነሳ ትርጉም ሲያጣ ወደ ሽለቆ መውረዳችን አይቀርም። ሕይወታችን ሲደርቅ፥ የጸሎት መንፈስ ሲርቀንና ቃሉን ማንበብ ሲሳነን፥ አገልግሎት እንኳ ትርጉም ሲያጣ፥ የሽለቆ ሕይወት ማለት ምን እንደሆነ ማወቃችን አይቀርም። ነገር ግን ታምነን ብንቆም ተስፋ አለን። እነዚህ የምናልፍባቸው ልምምዶች ባለንበት የሽለቆ ሕይወት ውስጥ ተሸንፎ የመቅረትን ድምጽ ሲያስተጋቡ፥ ረዳታችን እግዚአብሔር ደግሞ እንዲህ ሊለን ይነሳል፦ «እግዚአብሔር የተራሮች አምላክ ነው እንጂ የሸለቆ አምላክ አይደለም ብለዋልና ይህን ታላቅ ቁፍራ ሁሉ በእጅህ አሳልፌ እሰጠዋለሁ፥ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንኩ ታውቃላችሁ» (1 ነገሥ. 21፥28)። ጌታ ኢየሱስ የድል አምላክ ነውና አንፍራ! እኛ ከእርሱ ጋር ከተጣበቅን በጌታ ያልተሞከረና ያልተፈተነ ሕይወት ውስጥ በፍጹም እንገባም። በምናልፍበት ጎዳና ሁሉ ጌታ በረከት አለው። «በለቅሶ ሸለቆ ውስጥ በወሰነው ስፍራ የሕግ መምህር በረከትን ይሰጣልና (መዝ. 84፥6)።»



አንዳንድ ጊዜ በሽለቆ ሕይወት ውስጥ ስንገባ መማር የሚገባንን ተምረን ሳንጨርስ ያንን ከመሰለ ሕይወት በራሳችን ለመውጣት ስንታገልና ስናጉረመርም እንገኛለን። ሌላ ጊዜ ደግሞ በራሳችን ቸልተኝነትና በሕይወታችን አቅፈን ከያዝነው የተሰወረ ኃጢአት የተነሳ ሕይወታችን ደክሞ ሳለ ጌታ ፈቅዶ የሰጠን የሕይወት ሽለቆ ይመስል፦ «ጌታ አንድ ቀን ያወጣኛል» በሚል የማይሞላ ተስፋ የመታደሻ ዘመናችንን እናራዝማለን። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ሕይወትህ በሚደርቅበትና የሽለቆ ሕይወት በሚያጠቃህ ጊዜ ጌታ ብቻ ከእንደዚያ ዓይነቱ ሕይወት ሊያወጣህ እንደሚችል በመተማመን በጸሎት በፊቱ ውደቅ። ነገር ግን በመጀመሪያ ወደዚያ ዓይነት ሕይወት ውስጥ የገባኸው የጌታን ቃልና የመንፈስ ቅዱስን ወቀሳ ቸል በማለትህ ምክንያት መሆኑንና አለመሆኑን ለይተህ እወቅ፥ በኃጢአት ምክንያት የሚመጣ የድካም ሕይወትና ጌታ አገልጋዮቹ እንዲያልፉበት የሚፈቅደው የሽለቆ ሕይወት ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸውና።

II. ጸጋው በተራራ ላይ ይጠብቅሃል (14፥8–18)።

በልስጥራን ከተደረገው ተአምር የተነሳ ጳውሎስና በርናባስ ከነበሩበት የሽለቆ ሕይወት በቅጽበት ወጥተው በተራራ ላይ ተቀመጡ። ነገር ግን በድንገት የገቡበት የተራራ ሕይወት ብዙም የሚያዝናና አልነበረም። ብዙ ላይቆዩ እንደ አማልክት እስኪታዩ ድረስ ከፍ ከፍ አሉ። ጌታ በጸጋው ባይደግፋቸው ኖሮ እጅግ የሚያስፈራ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ።

በክርስትና ሕይወትና በአገልግሎት ጎዳና ስንሄድ በአንድ ዓይነት የሕይወት ልምምድ ብቻ ለማለፍ መጠበቅ የለብንም። ከሽለቆ ሕይወት ለመውጣት የምንጸጥወውን እኛን ደካሞቹን ጌታ በክንፎቹ አንስቶ በተራራ ላይ አውጥቶ የማስፈንደቅ ኃይል እንዳለው ፈቃዱም እንደሆነ አንጠራጠር። ከተራራ ሕይወት ጋር የሚመጣውን ሃላፊነት ግን አንዘንጋ። ነገር ሁሉ ሲሳካ፥ በሰዎች ሁሉ ፊት ሞገስንና ተወዳጅነትን እያፈራን ስንሄድ፥ ትናንት የእኔ ነገር አበቃለት ካልንበት ሕይወት በቅጽበት ጌታ አውጥቶ ድልን በድል ሲያነናጽፈን፥ ያን ጊዜ ልባችንን አብዝተን እንጠብቅ። በጌታ ብርታት ብቻ ትናንት ከሽለቆ

ሕይወት እንደወጣን፥ ዛሬም ከተራራ ላይ ተንከባልለን እንዳንወድቅ የሚጠብቀን የክርስቶስ ጸጋ ብቻ መሆኑን አንርሳ። ይህንን አንዘንጋ፦ «ትዕቢት ጥፋትን፥ ኩራ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል» (ምሳ. 16፥18)።

III. ጸጋው ከሞት ደጃፍ ያወጣሃል (14፥19–28)።

ከሞት ደጃፍ ደርሶ መመለስን የመሰለ ልምምድ ምን አለ? ሐዋርያው ጳውሎስ አልፎበታል። የአይሁድን ዛቻ ፈርቶ ወደ ልስጥራን ቢሸሽ ተከትለውት በመሄድ ወገሩት፥ የሞተም መስሎአቸው ከከተማው ውጭ አውጥተው ጣሉት። ጳውሎስን ተወግሮ ከወደቀበት የሞት ጣር ያስነሳው የጌታ ጸጋ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ሰዎችን በመውገር በሺህ የሚቆጠሩ ዓመታት ልምምድ የነበራቸው አይሁድ፥ ሰው በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ቢወገር እንደሚሞት ጠንቅቀው ያውቃሉ። ሐዋርያው ጳውሎስንም ከወገሩት በኋላ መሞቱንና አለመሞቱን ማወቅ ከብዶአቸው አይደለም ጥለውት የሄዱት፥ ባላቸው ልምምድ ተጠቅመው መሞቱን ሳያረጋግጡ አልቀሩም። በሐዋርያው ጳውሎስ ሥራውን ያልጨረሰው የናዝሬቱ ኢየሱስ ግን የሞትን ጥላ ከላዩ ላይ ገፈፈ፥ እንደገናም ሕያው አደረገው።

ዛሬም አገልጋዮችን በተለያየ መልኩ የሞት ጥላ ያንገዳግዳቸዋል። ጌታ የጠራቸውን ጥሪ ሳይፈጽሙ በአጭሩ እንዲቀጩ ጠላት የማያደርገው ጥረት የለም። በተለይም በሕይወታቸው የሚቃጠለውን የአገልግሎት ጥሪ በቁም ነገር ወስደው ለጌታ ክብር ለመቆም የወሰኑትን አገልጋዮች ጠላታችን ሰይጣን በተቻለው ፍጥነት ሊያጠፋቸው ይጥራል። የጌታ ጸጋ ግን ከጠላት ተንኮል በላይ መሆኑን አንዘንጋ። አገልጋዮቹን ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠብቃል። ለጊዜው ጌታ ዝም ያለ ቢመስልም እንኳ፥ ጌታ በነገር ሁሉ ዓላማ አለውና ታግሠን እንጠብቀው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንኑ ያለፈበትን መከራ አስታውሶ የጻፈውን ማሰቡ መልካም ነው፦ «በእን ጰኪያናበኢቆኒዮን በልስጥራንም የሆነብኝን የታገሥሁትንም ስደት ታውቃለህ ጌታም ከሁሉ አዳነኝ» (1ጢሞ. 3፥11)።

እንደተነጋገርነው አገልጋይ በሚያልፍበት ጎዳና ሁሉ በጌታ ጸጋ መደገፍና የመጨረሻ ተስፋው እርሱ እንደሆነ ማወቅ አለበት። አገልጋይ በዚህ ዓለም ውስጥ እስከኖረ ድረስ የሽለቆና የተራራ ሕይወቶች በኑሮው እንደሚፈራረቁ እሙን ነው። አንዳንድ ሰዎች አገልጋይ ከጌታ ጋር በይበልጥ የሚጣበቀው በመከራ ውስጥ ሲያልፍ ነው ብለው ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ አገልጋይ በተራራ ሕይወት ላይ መመላለሱ የመጽናቱ ምልክት እንደሆነ አድርገው ይገምታሉ። እነዚህ አሳቦች እውነትነትን ያዘሉ ሆነው ሳሉ ሙሉ በሙሉ እውነት አይደሉም። የአገልጋይን መጽናትና አለመጽናት የሚወስነው በሕይወቱ የሚያልፈውን ከፍታም ሆነ ዝቅታ በጌታ ጸጋ ብቻ ተደግፎ መቀበሉ ነው። ስለዚህም አገልጋይ በተራራ ላይ ሲፈነድቅ፥ ከዚያም ወርዶ በሸለቆ ውስጥ ሲያለቅስ፥ ነገሩም ከዚያ ከፍቶ ከሞት ደጃፍ እንኳ ቢደርስ በዚያን ወቅት ምን ማድረግ እንዳለበት ማወቁ ሕይወቱን ይጠብቀዋል። አገልጋይ በተራራም ሆነ በሸለቆ ሕይወት ውስጥ ሲገባ የሚከተሉትን አሳቦች በልቡ ቢይዝ ይጠቅሙታል።

1) ከማናቸውም ከባድ ውሳኔ ለጊዜው እንቆጠብ። በጊዜው በምናልፍበት የደስታ ወይም የኀዘን ስሜት ብቻ ተገፋፍተን የማያዛልቅ ውሳኔ ውስጥ ከመግባት መጠንቀቅ አለብን። በጊዜው እየተለማመድን ካለንበት የተራራ ሕይወት የተነሳ ስሜታችን ከፍ ስላለ ይህንና ያንን አደርጋለሁ ብለን፥ በኋላ የጋለው ስሜታችን ሲበርድ የምንጸጸትበትን ውሳኔ ከመወሰን እንጠበቅ። በአንጻሩ ደግሞ የጊዜው ሁኔታችን ብዙም የማያጓጓ በሚሆንበት ጊዜና ስሜታችን ዝቅ በሚልበት ጊዜ የተስፋ መቁረጥ ውሳኔዎችን እንዳናደርግና ሁኔታችን መለስ ሲል፦ «ምን ሆኜ ነው ይህንን የወሰንኩት» እንዳንል እናስተውል። እንደ አገልጋዮች የምንወስናቸውን ውሳኔዎች በእግዚአብሔር ቃል ተመርተንና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተማክረን ማድረጉ ከጸጸት ይጠብቀናል።

2) ከትዕቢት ልባችንን እንጠብቅ። በተራራ ላይ በምንፈነጥበት ጊዜ እኔ አለሁ ባይነት እንዳያጠቃንና በብርታታችን የቆምን እንዳይመስለን እናስተውል። ትዕቢት ውስጣዊ ነው። ስለዚህም በእንደበታችን፦ «የማልጠቅም ባሪያ ነኝ» እያልን በልባችን ውስጥ ስውር ትዕቢት እንዳይነግሥ መጠንቀቁ ይበጀናል።

3) ሃላፊነታችንን አንዘንጋ። ከሕይወት ውጣ ውረድ ጋር የሚመጣ ሃላፊነት ሌሎችን እኛ ባለፍንበት ሁኔታ የሚያልፉትን ወገኖች የማጽናት ሃላፊነት ነው። ትናንት ያለፍንበትና በጣም አሳስቦን የነበረው አስፈሪ ሁኔታ ዛሬ ጌታ በድል ካወጣን በኋላ ዘወር ብለን ስንመለከተው ቀላል ሆኖ ይታየናል። ምክንያቱም ጌታ በድል አሳልፎና ውስጣችንን አጠንክሮ ስላወጣን ነው። ለዚህ ነው ገና ያንን ፈተና ለመቋቋም ያልበቁትን ወገኖቻችንን፦ «አይዞአችሁ፥ እኔን ያሳለፈ አምላክ እናንተንም ያሳልፋችኋል» በማለት የማጽናናት ሃላፊነት ያለብን።

14

የመንፈስ አንድነት

ምዕራፍ 15፥1–16፥5



የጌታ ቃል ሲገለጽ በማይቻል ፍጥነትና ብርታት የአይሁድን ክልል በመጣስ ወደ አሕዛብ ዘልቆ መግባቱ እጅግ ያስገርማል። ለዚህም ታላቅ ሥራ የታጨው ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታ በአጠገቡ ካቆመለት ታማኝ አገልጋይ ከበርናባስ ጋር ከጌታ ተረክቦት የነበረውን የመጀመሪያውን የወንጌል ተልዕኮ በሚገባ በማጠናቀቅ ሳለ፥ አንዳንዶች የክርስቶስን ወንጌል ለማጣመም የተነሱ አይሁድ፦ «እንደ ሙሴ ሥርአት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም» በማለት የተለየ ወንጌል ለወንድሞች ያስተምሩ ጀመር። እነዚህ ሰዎች ይህንን ለየት ያለ ወንጌል ከማስተማር አልፈው ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር እጥብቀው ይከራከሩ ነበር። ነገሩ በከፋ ጊዜ ጳውሎስና በርናባስ ከሌሎች መልእክተኞች ጋር ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ በዚያ ካሉት ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ጋር በሽንጎ ተቀምጠው እንዲወያዩና ውሳኔን እንዲያስተላልፉ ተቆረጠ። ከነበሩበትም ከአንጾኪያ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዙ በመንገድ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት እየታገዙና እነርሱም የአሕዛብን መመለስ እየተረኩ በፊንቄና በሰማርያ አለፉ።

የተነሳውን ጥያቄ ለመፍታት የተሰበሰበው የሐዋርያትና የሽማግሌዎች ጉባኤ ለረጅም ሰዓት ቢሰበሰብም ከክርክር አላለፈም። በዚያን ጊዜ ነበር ጴጥሮስ ተነስቶ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል እግዚአብሔር እንዳልለየና ራሳቸው አይሁድ ሊሸከሙት ያልቻሉትን ቀንበር በአሕዛብ ላይ በመጫን እግዚአብሔርን መፈታተን እንደማይገባቸው ያብራራው። ከዚያም፥ ጳውሎስና በርናባስ ጌታ በአሕዛብ ዘንድ ያደረገውን በመተረክ የጴጥሮስን ንግግር ሲያጠናክሩት፥ ያዕቆብ (የክርስቶስ ወንድም) ደግሞ በመቀበል ወደ ውሳኔ የሚያመራን ማሰሪያ አበጀለት። በንግግሩም፥ በብሉይ ኪዳን ላይቀር ለአሕዛብ ስፍራ እንደሰጣቸው ከአሞጽ ምዕራፍ ስድስት በመጥቀስ፥ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ያሉት አሕዛብ «ከጣኦት ርኩሰትና ከዝሙት

ከታነቀም ከደምም ይርቁ ዘንድ እንድንጽፍላቸው እቆርጣለሁ» (15፥ 20) በማለት በሽንጎው ስም ወሰነ። አሕዛብ ይጠነቀቁ ዘንድ ከተነገራቸው አራት ነገሮች ሦስቱ ምግብን የሚመለከቱ ነገሮች መሆናቸው፥ በአይሁድ ባሕል መሠረት አንድ ሰው የሚበላው የምግብ ዓይነትና የአበላሉ ዘዴ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን ያሳያል።

ውሳኔው ሸንጎውን ደስ ባሰኘው ጊዜ ይሁዳና ሲላስን ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ወደ አንጾኪያ ውሳኔውን ከያዘ ደብዳቤ ጋር ላኩ። ይህ በአሕዛብ ላይ የተጣነን ተገቢ ያልሆነ ቀንበር የሚሰብረው የውሳኔ ደብዳቤ በአንጾኪያ ተነበበ። ከደብዳቤው መነበብ ጋር የይሁዳና የሲላስ የነቢይነት አገልግሎት ታክሎ በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ደስታና በረከት አመጣ።

ጳውሎስና በርናባስ ወንጌልን እየሰበኩ በአንጾኪያ ከሰነበቱ በኋላ ተመልሰው ቀድሞ ያገለገሉአቸውን ከተሞች ለመጎብኘት ወሰኑ። (ይህም የጳውሎስ ሁለተኛው የሚስዮናዊ ጉዞ ነው)። በዚህ ጊዜ ነበር በበርናባስና በጳውሎስ መካከል ታላቅ አለመግባባት የተነሳው። በርናባስ ማርቆስ ከእነርሱ ጋር ይሂድ ዘንድ መፈለጉ ለጳውሎስ አልተዋጠለትም ነበር፦ «ከእነርሱ ዘንድ ከጵንፍልያ ተለይቶ ነበርና፥ ወደ ሥራም ከእነርሱ ጋር አልመጣም ነበርና» (15፥ 38) ጳውሎስና በርናባስ የነበራቸውን የአሳብ ልዩነት ማስታረቅ በተሳናቸው ጊዜ መለያየት ነበረባቸው። በርናባስ ማርቆስን በመምረጥ በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄደ። ጳውሎስ ግን ሲላስን በመምረጥ በሶርያና በኪልቅያ ይዞር ነበር።

ከምዕራፍ አስራ አምስት ወጥተን የምዕራፍ አስራ ስድስትን የመጀመሪያ አምስት ቁጥሮች ስንመለከት፥ ጳውሎስ ወደ ደርቤንና ወደ ልስጥራን በደረሰ ጊዜ በአባቱ ግሪክ በእናቱ ደግሞ አይሁድ የሆነውን ለወደፊት አገልግሎቱ እጅግ የሚጠቅመውን ጢሞቴዎስን ተገናኘው። በአካባቢው ከነበሩት ወገኖች ምስክርነትን ከተቀበለና ለሰዎች አእምሮ ለመጠንቀቅ ሲል ከገረዘው በኋላ ከእርሱ ጋር ይወጣ ዘንድ ወሰደው። አብያተ ክርስቲያናትም ይበረቱና ይበዙ ነበር።



በማንኛውም የአገልግሎት መስክ የተሰማሩ አገልጋዮች የመንፈስ አንድነት ከሌላቸው ብዙ ሳይቆይ የአገልግሎታቸው መሠረት መናጋቱ አይቀርም። አንድነት የነገር ሁሉ

መሠረት ነው። አንድነት ማስተዋል የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። አንድነት ውሳኔን ይጠይቃል። ከዚያም አልፎ አንድነት ዋጋን ያስከፍላል። ዋጋን ሳይከፍልና ሳይጎዳ የመንፈስን አንድነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጠበቅ የሚችል አገልጋይ የለም። አንድነት፦ «እኔ የቆምኩት ለጌታ ክብር ነው» በሚል አሳብ ብቻ ለሰዎች ሳይጠነቀቁ ከመገስገስ የበለጠ ማስተዋልን የሚጠይቅ ነገር ነው። አንድነት ማለት የቆምንበትን ዓላማ ተገንዝበን ጌታን የሚያስደስተውን እየመረመርን ለሰው አእምሮ በሚመች ሁኔታ ነገሮችን ማከናወን ማለት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ መንፈስ አንድነት እንዲህ በማለት ያስተምረናል፦ «እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ፤ በትህትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግስትም፤ እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ፤ በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ (ኤፌ. 4፥ 1-3)።» ጳውሎስ «የመንፈስ አንድነት» ብሎ የሚጠራው አሳብ እስከ ዛሬ ከሰጠነው ስፍራ የበለጠ ሥፍራ ልንሰጠውና በተግባር ልናውለው የሚገባ እውነት ነው። ብዙ ጊዜ ግን በመልካም የተጀመረ አገልግሎት ከአንድነት ጉድለት የተነሳ ህልውናው ሲያበቃለት ይታያል። በግሩም ሁኔታ የተገነቡ አገልግሎቶች የመንፈስ አንድነት በመጥፋቱ ሲፈርሱ ይታያሉ። ለመሆኑ በአገልሎታችን ውስጥ የመንፈስ አንድነት እንዳይኖር የከለከሉን ነገሮች ምን ይሆኑ? የመንፈስ አንድነታችንን ሊመርዙ የሚችሉ ብዙ ነጥቦች መዘርዘር ስንችል በንባብ ከፍላችን ውስጥ በግልጽ የምናያቸውን ሦስት የመንፈስ አንድነት ጠንቆች እንመልከት።

I. ከቃሉ ያለፈ ሕጋዊነት (15፥ 1–29)።

እግዚአብሔር አሕዛብን በወንጌል በነበኝበት ወቅት አጥብቀው ሲቃወሙ የነበሩት አይሁድ እንደገና አዲስ የሚታኘክ አሳብ በማግኘታቸው ደስ ሳይሰኙ አልቀሩም። የሚናገሩትን ነገር በሰማይም ሆነ በምድር የሚሰማቸው አጡ እንጂ ለማለት የፈለጉት ይህን ይመስላል፦ «አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገቡ ዘንድ ስትተባበሯቸው ታገስናችሁ፥ ዛሬ ደግሞ የሙሴን ሕግ ሳይከተሉ

እንዲጸድቁ ትመኛላችሁን?» ይህንንም ውሳኔ ይዘው ሥራዬ ብለው የተለየ ወንጌል ማስተማርን ተያያዙት። በመካከላቸውም ብዙ ጥልና ክርክር እስኪሆን ድረስ ቤተ ክርስቲያን ታወከች።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰዎች ላይ ያልማነባቸውን ቀንበር ስንሞንባቸው፥ የእንድነት መሰረት እንደሚናጋ ከዚህ ከፍል እንማራለን። በተለይም አመለካከታቸውን፥ ሁኔታቸውን፥ ገጽታቸውን፥ አለባበሳቸውንና ወደ እኛ ከመምጣታቸው በፊት የነበሩበትን ልምምድ መቀበል በሚያስችግረን ጊዜ ፈጥነን ወደ ፍርድ እንዳንሮጥ መጠንቀቅ ያስፈልገናል። ወደ ክርስቶስ የተመለሰ ሰው ሁሉ መሸከም ያለበት ቀንበር አለ። ያም ቀንበር የሰው ቀንበር ሳይሆን የጌታ ቀንበር ነው። «ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁ ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና» (ማቴ. 11፥29–30)።

በሰዎች ላይ እኛ እነርሱ ባሉበት ደረጃ በነበርንበት ጊዜ መሸከም ያልቻልነውን ሸክም ስንሞንባቸው ልባቸውን እናሻክረዋለን። ከኃጢአት ሁሉ ነጻ የሚያወጣውን የመስቀሉን ኃይል መስበክን ትተን፦ «ይህን አድርጉ፥ ያንን ደግሞ አታድርጉ» የሚልን መልእክት ብቻ ስንሞላቸው፥ የተባሉትን ሁሉ በጥረታቸው ማድረግ ስለሚሳናቸው፥ ራሳቸውን በደሙ እንደተዋጀ ሰው ሳይሆን እንደምናምንቴ መቁጠር ይጀምራሉ። የምንደረድርላቸውን የሕግ ብዛት ለመፈጸም ይፈልጋሉ፥ ነገር ግን አንዱ ሲሳካላቸው ሌላው ደግሞ አልሆን ሲላቸው፤ አንዱ ሲነሱ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲወድቁ፥ ግራ ግብት ይላቸዋል። በዚህም ምክንያት ከሚመጣው የዝቅተኛነት መንፈስ የተነሳ ራሳቸውን ከሕብረት ማግለል ይጀምራሉ። የክርስቶስን መሞትና ከሞት መነሳት፥ በደሙም የሚገኘውን ነጻነት በሥልጣን ማወጅ ሕግን ከመስበክ የበለጠ የመለወጥ ኃይል አለው። «ስለዚህ ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የዞሩትን እንዳናስቸግራቸው» (15፥19)።

ቁም ነገሩ ያለው አጠያያቂ ሁኔታዎች ሲከሰቱ በምን መልኩ እንደምንይዛቸው ነው። ሰዎችን በችኮላ፦ «ይህን አድርጉና ያንን ደግሞ አታድርጉ» ከማለታችን በፊት የሰዎቹን ሁኔታ በእነርሱ ቦታ ሆነን ለማየት እንሞክር። ለምሳሌ፥ ሲራመድ ለሚያነክስ ሰው፦

«ስትራመድ አታነክስ!» የሚልን ሕግ ከማውጣታችን በፊት፦ «ይህ ሰው ለምንድነው የሚያነክሰው?» ብለን ሁኔታውን ከእኛ ቦታ ብቻ ሳይሆን ከሰውየው ቦታ ላይ በመሆን ብንመለከተው ማስተዋላችን የሰፋ ይሆናል።

ቤተ ክርስቲያን የሰዎችን ሁኔታ በመቀበልና ባለመቀበል እሳብ መካከል ስትዋዥቅ፥ ስለዚህ ጉዳይ በበለጠ ሁኔታ ለማሰብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መመለሱ በጣም ጠቃሚ ነው።

1) ቃሉ ምን ይላል? በማንም ሰው ላይ ማንኛውንም ዓይነት የሕግ ቀንበር ከመጫናችን በፊት፦ «የእግዚአብሔር ቃል ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላል?» ብለን በመጠየቅ የሚጠበቅብንን እውነት ጠንቅቀን ማወቅ ችኩሎ ከመፍረድ ያድነናል።

2) እኔስ ፍጹም ነኝን? በሰዎች ላይ ስለ ድካማቸውም ሆነ ስለሚያመጡት አሳብ በችኮላ በምንፈርድበት ጊዜ ራሳችንን ለፍርድ ምቹ አድርገን እንዳስቀመጥን ማወቅ አለብን። ዛሬ በሰዎች ላይ ፈጥነን የፈረድን፥ እኛ ነገ በስህተት ውስጥ ስንገኝ ከሰዎች ልናገኝ የምንመኘውን ምህረት እንደማናገኝ እንወቅ፤ ስለፈረድን ይፈረድብናል። «እኔስ ፍጹም ነኝን?» ብሎ መጠየቅ የሌሎችን ስህተት እይተን፦ «እኔ ማን ነኝ?» ብለን እንድናልፋቸው ሳይሆን፥ ፍርድን ትተን በትህትና እንድንቀርባቸው ነው።

3) ይህንን ሁኔታ በምን መልክ ልቅረበው? የሰዎች ሁኔታና አረማመድ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ ሆኖ በምናገኘው ጊዜ ወደ እነዚያ ሰዎች በምን መልኩ ቀርበን ከመንገዳቸው እንደምንመልሳቸው በሚገባ እናስብበት ይገባል። «ቢሰማ ይሰማ፥ ባይሰማ ደግሞ ይጠፋታል» የሚል አቀራረብ ካለን ዓላማችን ነፍስን የማዳን ሳይሆን ሰዎችን የመገሰጽ ብቻ ያስመስለዋል። ተግሳጽ የሚያስፈልገውን ፍቅር በተሞላበት ሁኔታ እንድንገስጸው፥ ድጋፍ የሚያስፈልገውን ካለመሰልቸት እንድንደግፈው፥ ትምህርት ለሚያስፈልገው ደግሞ በትጋት እንድናስተምረው ተጠርተናል።



አንዳንድ ሰዎች ከቃሉ ያለፈ ሕጋዊነት ውስጥ ገብተው ከርስቶስ ደሙን በማፍሰስ ያነናጸፈንን የጸጋ ስጦታ ችላ ሲሉ ይታያሉ። ሌሎች ደግሞ ጸጋን መከለያ አድርገው እንዳሻቸው ሲመላለሱ ይቃጣቸዋል። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ።

ከክርስቶስ ጸጋ ተለይተህ ጌታን በአንዳችም ልታስደስተው እንደማትችል አውቀህ ከቃሉ ካለፈ ሕጋዊነት ተጠበቅ። ነገር ግን ጌታን መታዘዝህ እርሱን የመውደድህ ዋነኛ መለኪያ መሆኑንም አትዘንጋ።

II. የአሳብ ልዩነትን እንደ ግል ጥላቻ መውሰድ (15፥30–41)።

ጳውሎስና በርናባስ የተጠመዱበት ደስ የማያሰኝ ያለማስተዋል መረብ ይህ ነበር። በአገልግሎት ጉዞ ላይ እያሉ አንድ አለመግባባት ተፈጠረ። በርናባስ የማርቆስን ከእነርሱ ጋር ለአገልግሎት መውጣት በመልካም ሲያየው፥ ጳውሎስ ግን ማርቆስን ለዚያ ሥራ ተገቢ ሆኖ አላገኘውም ነበር። ይህንን የአሳብ አለመግባባት ረጋ ባለ ሁኔታ ተወያይተው ሊፈቱት ሲችሉ፥ እርስ በርሳቸው እስኪለያዩ ድረስ ተጣሉ።

ይህ ዓይነቱ ሁኔታ በአገልግሎታችን ዘወትር ይታያል። አገልጋዮች በጠረጴዛ ዙሪያ ተሰብስበን ስለ ጌታ ሥራ ስንወያይ የተለያየ አሳብ መቅረቡ እሙን ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዘወትር የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይጠፋም። ይህም ደግሞ በጣም ጤናማ የሆነ ነገር ነው። አንድ አገልጋይ አንድን አሳብ ሲያመጣ ያንን አሳብ በእግዚአብሔር ቃል የሚመረምር ሌላ አገልጋይ መኖሩና ለጥያቄ እጹን መዘርጋቱ ትልቅ በረከት መሆኑን አንዘንጋ። ተሰባስበን ለጌታ ሥራ መነጋገራችን ለዚሁ አይደለምን? ብዙዎቻችን ግን ነገሩን በዚህ መልክ አናየውም። ሌላ አገልጋይ እኛ ካቀረብነውን አሳብ ተቃራኒ የሆነን አሳብ ካመጣ ያ ሰው ከእኛ ጋር የግል ችግር ወይም ጥላቻ እንዳለው አድርገን መቁጠር ስለሚቀናን አእምሮአችን ፈጥኖ ይቆሽሻል። ከዚያችም ዕለት አንስቶ ይህ ሰው ለሚያቀርበው አሳብ ሁሉ ልዩ ትርጉም መስጠት እንጀምራለን። አንድ ጊዜ ይህ ሰው ዘወትር በእኛ ላይ የጠላትነትና የተቃውሞ አሳብ እንዳለው አድርገን ራሳችንን ካሳመንነው በኋላ በመካከላችን ለሚነሳው ጠብና መከፋፋት ወሰን አይኖረውም።

አብሮን በወንጌል ከሚደክም የጌታ ባሪያ ጋር በአሳብ በማንግባባበት ጊዜ እንደኛችን ዝቅ ብለንና ተሸንፈን ቋጠሮውን

ለመፍታት ካልተጋን የእንድነት መሠረት ይናጋል። ይህንንም ለማድረግ የሚከተሉት ነጥቦች ይረዱናል ብዬ አምናለሁ።

1) ጌታና ሌሎች የጌታ አገልጋዮች ምን ይላሉ? በአገልጋዮች መካከል የአሳብ አለመጣጣም ሲነሳ፥ የጌታን አሳብ ለማወቅ ቃሉና መንፈስ ቅዱስ ምን እንደሚሉ ለማወቅ ጆሮአችንን ወደ እርሱ ማዘንበል አለብን። ይህንን ስናደርግ ጌታ በተለያየ ልምምድ ያበሰላቸውንም አገልጋዮቹንም ተጠቅሞ ሊመራን እንደሚችል እንዘንጋ። ጌታ የሚለው ካለምንም ማወላወል መጽናት አለበት።

2) ወንድሜ ትክክል ይሆን? በማንኛውም አሳብ ላይ በግትርነት ትክክለኞች ሆነን ለመገኘት ከመጣጣራችን በፊት፥ የሌላኛው አገልጋይ አሳብ ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ለማወቅ ልባችንን ብንከፍት ሁኔታውን በአዲስ መልክ ልንመለከተው እንችላለን። የተሳሳትን መስሎ ከታየንም፦ «ተሳስቼ ነበር» በማለት ራሳችንን ብናዋርድ ማሸነፍ እንጂ መሸነፍ አይደለም። ይህንን ለማድረግ ግን በመጀመሪያ ሌሎች የእኛን አሳብ ብቻ እንዲሰሙልን እየሮህን ከመናገራችን በፊት እነርሱ አሳባቸውን እስኪጨርሱ ድረስ ማድመጥን እንማር።

3) ይህ ልዩነት ለመለያየት የሚያበቃ ነውን? አንዳንድ ጊዜ አገልጋዮች የሚለያዩበትና የሚከፋፈሉበት ነገር ቀላልነት አስቂኝ ነው። ምናልባት እነርሱም ትንሽ ሰንበት ብለውና በጊዜው ካለባቸው የስሜት መጋል መለስ ብለው ያበጣበጣቸውን ጉዳይ ቢያዩት ያስገርማቸው ይሆናል። ስለዚህም አብዛኞቹ ልዩነቶቻችን የሚያወያዩ እንጂ የሚያለያዩ እንዳልሆኑ ተረድተን የተሰጠንን አደራ በታማኝነትና በማስተዋል ለመወጣት እንትጋ።



አንዳንዶች «አንድነት በልዩነት» በሚል ሳቢያ ፈጽሞ ከክርስቶስ ወንጌል የራቀ አስተሳሰብና አቋም ያላቸውን ሰዎች ለማቀፍ ሲጥሩ ይታያሉ። ሌሎች ደግሞ መሰረታዊ ባልሆኑ ነገሮች ቢለያዩና ቢከፋፈሉ ለታላቁ የእግዚአብሔር ሥራ ሊውል የሚገባውን ጉልበታቸውን በከንቱ ያባክናሉ። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ለክርስቶስ መስቀል ጠላት የሚሆንን ማናቸውም ዓይነት አሳብ ከመቃወም ወደ ኋላ አትበል። ይህ ማለት ግን የቃሉን እውነት

የማይቀናቀንን ጥቃቅን የአሳብ ልዩነት እየለቀሙ መከፋፈል እንዳልሆነ አስተውል።

III. ለሰዎች አእምሮ አለመጠንቀቅ (16፥1–5)።

ጳውሎስ ከበርናባስ ተለይቶ በአገልግሎት በሚዘዋወርበት ጊዜ በመንገዱ ላይ ጢሞቴዎስን ተገናኘው። ይህንን ብላቴና ማግኘቱና ለአገልግሎት መውሰዱ ፍጹም የሆነ የጌታ ፈቃድ ለመሆኑ በቀረው የአገልግሎት ዘመናቸው ያፈሩት ፍሬ ምስክር ነው። ይህንን ለማከናወን ግን ከጳውሎስ ትልቅ ማስተዋል ይጠበቅበት ነበር። በዚያ ለነበሩት ላልበሰሉት አይሁድ አእምሮ መጠንቀቅ ነበረበት። ጢሞቴዎስ ምንም እንኳ በእናቱ አይሁዳዊ ቢሆን አባቱ የግሪክ ሰው መሆኑ ስለሚታወቅ በአካባቢው ሳሉ አይሁድ አእምሮ ለመጠንቀቅ ሲል ብቻ ጳውሎስ ይገርዘው ዘንድ ወሰነ።

እግዚአብሔር እኛን አገልጋዮቹን በዚች ምድር ላይ ያስቀመጠን ስሙን እንድናስከብርና የጠፋውን የሰውን ዘር ከእርሱ ጋር እንድናስታርቅ ነው። ታዲያ አንዳንድ ጊዜ ይህንን እንዘነጋና የምናደርጋቸውን አገልግሎቶች፦ «ዋናው ቁም ነገር ጌታ መክበሩ ነው» በሚል ብቸኛ አሳብ ለሰዎች አእምሮ በማይመች ሁኔታ ስናከናውናቸው እንገኛለን። ተግባራችን እንደ ጌታ ቃልና ፈቃድ ሆኖ ሳለ አደራረጋችን በአካባቢያችን ያሉ እኛ የደረስንበት ደረጃ ያልደረሱ ሰዎች የሚሰናከሉበት ይሆንና መልካሙን ነገር ልናጠፋ እንችላለን።

ጌታን ለማስከበር የምንሮጠውን ያህል ለሰዎችም አእምሮ መጠንቀቅን መማር ያስፈልገናል። እዎን «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» (መዝ. 111፥10)፤ «ወንድምህም የሚሰናከልበትን አለማድረግ መልካም ነው» (ሮሜ 14፥21)። በእንደዚህ ዓይነት የማስተዋል ሕይወት ውስጥ የሚመላለስ አገልጋይ ዘወትር የሚከተሉትን ጥያቄዎች የሚጠይቅ አገልጋይ ነው።

1) ነገሮችን የማደርገው ለሰዎች ጎሊና እየተጠነቀቅሁ ነው? የምናደርገው ማንኛውም ዓይነት አገልግሎት የጌታ ፈቃድ መሆኑን ብቻ ማረጋገጥ በቂ አይደለም። የአደራረጋችን ሁኔታና ዘይቤ ለሰዎች

አእምሮ የሚመች መሆን አለበት። ለሰዎች መታነጽና በረከት ካልሆነ ጥቅሙ ምኑ ላይ ነው?

2) ለሰዎች አእምሮ እየተጠነቀቅሁ ነው ወይስ ሰውን እየፈራሁ? በእነዚህ ሁለት አሳቦች መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። አገልጋይ ለሰው አእምሮ መጠንቀቅ እንጂ ሰውን መፍራት የለበትም።

3) የማደርገው ነገር ምን ያህል አሰፈላጊ ነገር ነው? አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን የማሰናከል ደረጃ ድረስ ራሳችንን የምናጋልጥበት ነገር ምንም ጥቅም የማይሰጥና ከነጭራሹ ብንተወው የማይጎዳ ነገር ነውና አንደኛችንን ብንተወው ይሰምርልናል።



«ለጌታ ክብር ብቻ ነው የምቆመው» የሚለውን እውነተኛ አመለካከታችንን ካለልክ ወስደን በሕይወታቸው ያልጠነከሩትን ሰዎች በድርጊታችን ስናሰናክል ማየት ያሳዝናል። በአንጻሩ ደግሞ ለሰዎች አእምሮ ለመጠንቀቅ ስንል የጌታን ክብር እንዳንጥልና ሰዎች ከሚሰናከሉ፦ «ይሄ ይቅር፥ ያ ይቅር» ስንል የክርስቶስን ወንጌል ባዶ እንዳናስቀረው ያሰጋናል። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። የወንጌልን እውነት በምንም ነገር አትለውጥ። ሆኖም የወንጌልን እውነት በተግባር ለማዋል በምታደርገው ጥረት ለሰዎች አእምሮ የመጠንቀቁን ተግባርህን እንዳትዘነጋው አስተውል።

15

የእግዚአብሔር ልዕልና

ምዕራፍ 16፥6–40



ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ የአገልግሎት ቡድን ጋር ከተደባለቀ በኋላ በእስያ ቃሉን ለመናገር ሙከራ አደረጉ። ምናልባት ወደ እስያ ለመሄድ ማሰባቸው በዚያ ያሉትን የሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት ወገኖች ለመጎብኘትም ፈልገው ይሆናል (ራእ. 2–4)፥ መንፈስ ቅዱስ ግን ከለከላቸው። እቅጣጫቸውንም በመቀየር ወደ ቢታንያ ይሄዱ ዘንድ ሞከሩ፥ አሁንም የጌታ መንፈስ አልፈቀደላቸውም ነበር። ወደ ምዕራብ ተጉዘው ጢሮአዳ በደረሱ ጊዜ ራእይ ወደ መቄዶንያ ይወጡ ዘንድ ለጳውሎስ አመለከተው። ይህንንም ታዝዘው ጉዞአቸውን እቀኑ። «እነርሱ» ይል የነበረው የሉቃስ አነጋገር «እኛ» ወደሚል አነጋገር መለወጡ ሉቃስ ከእነ ጳውሎስ ጋር መደባለቁን ያመለክታል።

ጥቂት ከተሞችን ካቋረጡ በኋላ ወደ ፊልጵስዩስ ደረሱ። በፊልጵስዩስ ምኩራብ ያለ አይመስልም፥ ስለዚህም በወንዝ አጠገብ የመሰብሰብ ልማድ ነበራቸውና እነ ጳውሎስ ሴቶች ተሰብስበው የነበሩበትን ስፍራ ፈልገው አገኙት። በዚያን ስፍራ ነበር ከትያጥሮን ከተማ የመጣችን ልድያ በመባል የታወቀችን ነጋዴ ጌታ የነካት። ልድያ ምንም እንኳ እግዚአብሔርን የምታውቅ ሴት ብትሆንም ጌታን እንደ ግል አዳኟ መቀበል ነበረባት። አምናም ከቤተ ሰዎችዋ ጋር ተጠመቀች፤ እነ ጳውሎስንም በእንግድነት ተቀበለቻቸው።

ወደ ጸሎት ስፍራ በወጡም ጊዜ መጀመሪያ የተገናኘቻቸው ለጌቶችዋ እየጠነቆለች ብዙ ትርፍ ታመጣ የነበረች ገረድ ነበረች። የእርሱዋ ከአጋንንት እስራት መፈታት ጌቶችዋን አስቆጣቸው፥ የትርፋቸው ተስፋ ወጥቶአልና። በዚህም ምክንያት እነ ጳውሎስን ወደ እስር ቤት ጣሉአቸው። በመንፈቀ ሌሊት ጳውሎስና ሲላስ ምስጋናን ሲያዜሙ የወኅኒው መሠረት ተናወጠ፥ ደጆች ሁሉ ተከፈቱ፥ እስራት ተፈታ፥ ጌታም ባሪያዎቹን ይታደግ ዘንድ በኃይል ተነሳ። ይህ ሁኔታ

ለእነ ጳውሎስ መፈታት ብቻ ሳይሆን ለጠባቂውም የመዳን መንገድ ሆነ። ይህ የወኅኒ ጠባቂ የወንጌልን ቃል ከእነ ጳውሎስ እንደበት ከሰማ በኋላ ከቤተ ሰዎቹ ጋር አምኖ ተጠመቀ።

በወኅኒ የተደረገውን ተአምር ያላዩትና ያልሰሙት ገዢዎች እነ ጳውሎስ ይፈቱ ዘንድ ሎሌዎቻቸውን ቢልኩም፥ ካለ አግባብ የተደበደቡት እነ ጳውሎስ የሮሜ ዜግነታቸውን በመግለጽ በድብቅ ሳይሆን በግልጽ ይቅርታ ተጠይቀው እንዲፈቱ ጥያቄ አቀረቡ። ከዚያም በልመና ወጥተው ወደ ልድያ ቤት ገቡ፥ ወንድሞችንም አጽናንተው ሄዱ።



«የአምላክ መንገድ ፍጹም ነው» (2ሳሙ. 22፥31) የሚለው ቃል የታመነ ነው። እኛም ባሪያዎቹ ይህንን ፍጹም የሆነውን የአምላካችንን መንገድ ለማወቅና ለመረዳት በምናደርገው የማያቋርጥ ጉዞ ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን አገልጋዮች ጠይቀን በፍጹም መልስ የማናገኝላቸው ጥያቄዎች ሊኖሩን እንደሚችሉ መረዳትና ይህንን እውነት መቀበል ልባችንን ያሳርፈዋል። በክርስትና ብዙ ስለ ቆየን ብዙ ልምምዶች ይኖሩን ይሆናል፥ ነገር ግን የመንፈሳዊውን ምስጢር ሁሉ እጠናቅቀን አላወቅንም። መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገብተን ከዘመናት በፊት የመለኮት ትምህርት እዋቂዎች ሲመራመሩበት የኖሩትን እውነት አንድ በአንድ ልንተነትን እንችል ይሆናል፥ ነገር ግን አሁንም እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ እንዳላወቅነው ልባችን ሊቀበለው ይገባል። በግል ሕይወታችንና ከወገኖች ጋር ባለን ሕይወት በቃሉና በጸሎት የተጋን ልንሆንም እንችላለን፥ ያም ቢሆን ጥልቅ የሆነውን የክርስቶስን ምስጢር አንድንጀምረው እንጂ ፈጽመን እንድንረዳ አያደርገንም።

እግዚአብሔር ልዑል ነው! በልዕልናውም ከሁሉ በላይ ነግሦ ይኖራል። ልዑል ስለሆነ የፈለገውን ነገር በፈለገው ሰዓት የማድረግ መብትና ሥልጣን አለው። ስለዚህም አገልጋይ የእግዚአብሔርን መንገድ ለመረዳት በሚያደርገው ጉዞው በፍጹም መልስ ያጣለትና ከአእምሮው በላይ የሚሆን ነገር ሲገጥመው፦ «እግዚአብሔር ልዑል ነው፥ የሚያደርገውን ያውቃል» ማለትን ይማር ዘንድ ይገባዋል።

ለዚህ ክፍል በመደብነው የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ ውስጥ የእግዚአብሔርን ልዕልና አጉልተው የሚያሳዩንን ሦስት ነጥቦች እንመልከት።

I. ለምን የልድያን ልብ ጌታ ከፈተላት (16፥6–15)?

በፊልጵስዩስ በወንዝ አጠገብ ተሰብስበው ከነበሩት ሴቶች መካከል የነበረችው ልድያ የጌታን ቃል ሰምታ ለመለወጥ ደቂቃም አልወሰደባትም ነበር። እንዲያውም በሕይወቷ የተከናወነው ለውጥ እጅግ አስገራሚ ከመሆኑ የተነሳ ቤቷ የወገኖች መናኸሪያ ሆነ። እንግዲህ ጥያቄው እዚህ ላይ ነው፥ እስከዚያ ቀን ድረስ ወንጌል ሲሰበክ ሰምተው አሻፈረኝ ያሉትን አይሁድና አሕዛብ እንደ ልድያ ጌታ የልባቸውን ደንዳናነት አሽንፎ ለምን የሕይወትን ለውጥ አልሰጣቸውም?

ይህንን ጥያቄ ምናልባት በቃላት አውጥተን ባንናገረውም በብዙዎቻችን ውስጥ የሚመላለስ ጥያቄ ነው። ለምን ለአንዳንዶች ወንጌልን መመስከር እጅግ ይከብዳል? ለምን ደንዳና ልባቸውን ጌታ በቀላሉ አይሰብርልንም? ለምን አንዳንዶችን ጌታ በቀላሉ ይለውጣቸዋል? ይህንን አላብ በጠለቀ ሁኔታ ለመወያየት ራሱን የቻለ መጽሐፍ ይወጣዋል። ነገር ግን አንድ እጅግ ቀላል የሆነ እውነት አለ። ይህንንም እውነት መረዳት ለብዙ ጥያቄዎቻችን መልስ ይሆነናል። እግዚአብሔር ልዑል ስለሆነ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የፈለገውን የመሥራት መብት አለው።

የእኛ የአገልጋዮች ሃላፊነት በጸሎት እየተጋንና የኃይለኛውን ቤት እያሰርን ወንጌሉን በእምነት መዝራት ሲሆን፥ ነፍሳትን የመለወጡ ሃላፊነት የጌታ ነው። እኛ ከጌታ ጋር እስከተራመድን ድረስ በአገልግሎታችን የሚሆነው ሁሉ በጌታ ፈቃድ ውስጥ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልገናል። አንዳንዶች በቀላሉ የምናቀርብላቸውን የሕይወት ጥሪ አንዲቀበሉ ጌታ ልባቸውን ሲከፍትላቸው፥ ሌሎች ደግሞ ነገርን ሁሉ በማጣመም የወንጌልን ሥራ እጅግ ሲያከብዱብን ይገኛሉ። እግዚአብሔር ግን ይህንን ሁሉ የሚያይና የሚሠራውን የሚያውቅ አምላክ ነው። «እንግዲህ ምን እንላለን? በእግዚአብሔር ዘንድ አመጻ

አለ ወይ? አይደለም። ለሙሴ የምምረውን ሁሉ እምረዋለሁ ለምራራለትም ሁሉ እራራለታለሁ ይላልና» (ሮሜ 9፥14–15)።

II. ለምን ጠንቋይቱ ገረድ አልተቀጣችም (16፥16–24)?

ጳውሎስ በአገልግሎት ጎዳናው ላይ ጠንቋይ ሲያጋጥመው ይህ የመጀመሪያው ጊዜ አይደለም። ከዚህ በፊት የመጀመሪያውን የሚሲዮናዊ ተልዕኮውን ከመንፈስ ቅዱስ ተቀብሎ ከአንጾኪያ በወጣ ጊዜ ብዙ ሳይቆይ ጠንቋዩ ኤልማስ እንደተገናኘው እናስታውሳለን (13፥4–12)። ጠንቋዩ ኤልማስና ይህቺ በዚህ ክፍል የተጠቀሰችው ጠንቋይ ገረድ በሰይጣን እስራት የተተበተቡና ከእነርሱ በላይ በሆነ ኃይል ተይዘው የሚመላለሱ፥ እንደሌላው የደህንነት ምስጢር እንዳልገባው ማንኛውም ሰው ከጌታ ምህረት የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ናቸው። ጌታ ኤልማስን ሲቀጣው፥ ይህቺን ገረድ ግን ከእስራቷ ሲፈታት እንመለከታለን። ምናልባት ኤልማስ ጳውሎስን በግልጽ ስለተቃወመው ነው የተቀጣው ልንል እንችላለን። ነገር ግን ከኤልማስና ከገረዲቱ አንደበት ይወጣ የነበረው ቃል የተለያየ መልእክት ያዘለ ቢሆንም እንኳ በሁለቱም ውስጥ ይሠራ የነበረው ሽንገላ የተሞላው የጨለማው ገዢ ዲያቢሎስ እንደነበር ጥርጥር የለውም። በአጋንንት ትብታብ የታሰሩትን እነዚህን ሁለት ጠንቋዮች ተመለከትን። አንዱ ቅጣትን ተቀበለ ፥ ሌላኛይቱ ደግሞ ምህረትን አገኘች። ሁለቱንም የያዛቸው አንድ መንፈስ ነው። ለሁለቱም የተለያየ ምላሽ የሰጣቸው አንዱ ቸር እግዚአብሔር ነው። ለምን?

እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ብዙ ጊዜ በአገልግሎታችን ይነሳብናል። የተለያዩ ሰዎች ዓይናቸው በዚህ ዓለም ገዢ በመታወሩ ምክንያት በእግዚአብሔር ሕዝብና ሥራ ላይ ሲነሱ ይታያሉ። እንዳንዶቹ በከፋ ሁኔታ ቅጣታቸውን ሲቀበሉ፥ ሌሎቹ ደግሞ፦ «ቀድሞ እንዲህ ነበርኩ፥ ዛሬ ግን ጌታ በምህረቱ ለዚህ አበቃኝ» ብለው ሲመሰክሩ ይሰማሉ። ሌሎቹ ለምን ተቀጡ፥ ለምንስ እነዚህ ምህረትን አገኙ? ለእንደዚህ ዓይነቱ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ብንጥርም ለሌላ ጥያቄ በርን ከመክፈት በስተቀር ብዙም አንራመድም። ያለን ግልጽና አጭር መልስ፦ «እግዚአብሔር የወደደውን የሚሠራ ልዑልና የተፈራ አምላክ ስለሆነ

ነው» የሚል ይሆናል። «እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም፥ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ» (ሮሜ 9፥16)።

III. ለምን እነ ጳውሎስ በቀላሉ ከእስር ተፈቱ (16፥25–40)?

የእግዚአብሔርን ልዕልና የብዙዎች ልብ ሲደነድን የልድያን ልብ በመክፈቱ፥ ወይም ጌታ አንደኛውን ጠንቋይ ቀጥቶ ለሌላኛይቱ ደግሞ ምህረትን በማድረጉ ብቻ አይደለም የምናየው። አንዳንዶች ለጌታ ስም ሲሉ በግፈኞች እጅ የወደቁ ሐዋርያት በዚያው ተሰይፈው ሲቀሩ፥ ሌሎች ደግሞ በብዙ መከራና ጭንቅ ሲለቀቁ የእነ ጳውሎስ ተለምኖ ከእስር ቤት መውጣት ያስገርማል! ምናልባት፦ «ነገሩ የቀለለላቸው የሮሜ ሰዎች ስለ ነበሩ ነው» ልንል እንችላለን። ነገር ግን የሮሜ ዜግነታቸው ያላዳናቸው ጊዜም እንዳለ እንዘንጋ። ከዚያም አልፎ፥ እግዚአብሔር ከሮማዊነት የበለጠ ምክንያት አምጥቶ እንደ ሌባ ተደብድበው የታሰሩትን ሐዋርያት እንደ ንጉሥ ተለምነው እንዲወጡ ያደርግ ዘንድ ይቻለዋል።

ይህ ዓይነቱ የእግዚአብሔር አሠራር ዛሬም በዘመናችን ይታያል። ዛሬ የጌታ ባሪያዎች በተለያየ መከራ ውስጥ ያልፋሉ። እንዳንዶቹ በእስከፊ ስቃይ ውስጥ ያለፉ፥ ከዚያም አልፈው እስከ ሞት የተሰጡ አሉ። ሌሎች ደግሞ ጌታ ታድጓቸውና ቁስላቸው ድኖላቸው በሰላም የሚወጡና የሚገቡ አሉ። ታዲያ ከመከራቸው የወጡት እነዚህኞቹ ለጌታ ሲሉ ከተጎሳቆሉት ከእነዚያኞቹ የበለጠ እምነት አላቸው ማለት ነውን? አይደለም! እግዚአብሔር ከልዕልናው የተነሳ እያንዳንዶቹን ባሪያዎቹን ለእርሱ ክብር በሚውሉበት በተለያየ መንገድ ማላለፍን ስለሚፈቅድ ብቻ ነው። በዕብራውያን አሥራ አንድ ውስጥ ከተጠቀሱት የእምነት አርበኞች መካከል ገሚሶቹ በእምነት ድል የነሱና ከሰይፍ ስለት ያመለጡ፥ ገሚሶቹ ደግሞ በእምነት በሰይፍ ተገድለው የሞቱ አይደሉምን? ለዚህ ሁሉ ያለን መልስ፦ «እግዚአብሔር ልዑል ነው፥ የሚያደርገውን ያውቃል» የሚል ይሆናል።

በእግዚአብሔር አሠራር ግራ የምንጋባባቸው ጊዜአት እንዳሉ ዘወትር መዘንጋት የለብንም። አሳቡና መንገዱ፥ አሠራሩና አደራረጉ ሁሉ ከሰው ልጆች የተለየ ነው። ሰማይንና ምድርን ሲሠራ ማንም

አላማከረውም። እኛንም ልጆቹን ከእናታችን ማህፀን ሲፈጥረን ማንም፦ «ለምን እንዲህ ታደርጋለህ?» ያለው የለም። ዛሬም ቢሆን በአገልጋዮቹ ሕይወት የፈቀደውን መሥራት መብቱም ሆነ ሥልጣኑ የእርሱ ነው።

የእግዚአብሔር አሠራር ለአእምሮአችን ጥያቄ በሚፈጥርበት ጊዜና እኛም ለሥልጣኑ ለመገዛት በምንወስንበት ጊዜ ማስተዋል የሚገቡን ብዙ ነገሮች እንዳሉን አንዘንጋ። ከእነዚያ ነገሮች ጥቂቶቹን እንመልከት።

1) ቃሉን ከማጣመም እንጠንቀቅ። እግዚአብሔር በእኛም ሆነ በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውሎጥ እያደረገ ስላለው ምስጢሩ ስላልገባን ነገር መልስን ለማግኘት ስንል ብቻ ቃሉን ማጣመም ተገቢ አይደለም። ብዙ ጊዜ ለዚህ የምንጋለጠው እንደ አገልጋዮች ለሁሉ ነገር መልስ ያለን ሰዎች መስለን ለመቅረብ በምንሞክርበት ጊዜ ነው። ምንም እንኳ ጌታ ብዙ ያለማመደን አገልጋዮቹ ብንሆንና ምስጢራትንም ሁሉ ብናውቅ፥ አሁንም ውስን ሰዎች እንደሆንን በመቀበል፦ «እግዚአብሔር ምን ለማድረግ እንደ ፈለገ አልገባኝም» ማለትን፥ ካስፈለገም ከዚያ አልፈን፦ «አላውቅም» ማለትን እንማር።

2) በሰውም ሆነ በራሳችን ልምምድ ላይ ብቻ ተመርኩዘን «እውነትን» እንዳንመሠርት እንጠንቀቅ። እውነትን እውነት የሚያሰኘው ሰዎች ያንን ነገር ስለ ተለማመዱት ወይም ስላልተለማመዱት ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ያንን እውነት ስላጸደቀው ብቻ ነው። ለምሳሌ፥ ለበሽተኞች ለብዙ ዘመን ጸልዮ የጌታን የፈውስ ክንድ አንዱም እንኳ ያላየ ሰው፦ «እግዚአብሔር በሐዋርያት ዘመን እንጂ በዚህ ዘመን አይፈውስም» ቢል ይሳሳታል። እውነት ብንለማመዳትም ባንለማመዳትም ያው እውነት ነች። እኛ በእርስዋ ላይ ያለን አመለካከት ይለዋወጣል እንጂ እርሷ አትለወጥም።

3) በጠራን እንታመን። እንደ አሳቡ የተጠራን እኛ አገልጋዮች እግዚአብሔርን በመውደድ እስከ ተመላለስን ድረስ ምንም ነገር ጌታ ከፈቀደለት ድንበር እንደማያልፍ ማወቅ ይገባናል። ይህን ማወቅ ልባችንን ያሳርፈዋል። ግራ ከመጋባትም ወጥተን የጌታን እጅ ጥርት ባለ ሁኔታ ማየት እንጀምራለን።

16

መገረዝ ያለባቸው ነውሮች

ምዕራፍ 17፥1–34



ከእነ ጳውሎስ ጋር ራሱን በመቁጠር፦ «እኛ» በማለት ይተርክ የነበረው ሉቃስ በድንገት አነጋገሩን፦ «እነርሱ» በማለት ሲቀይረው ይታያል። ምናልባት ሉቃስ ከእነ ጳውሎስ የአገልግሎት ቡድን ተለይቶ በፊልጵስዩስ የተጀመረችውን አዲስ ቤተ ክርስቲያን ለማጽናት ወደ ኋላ ቀርቶ ይሆን?

የእነ ጳውሎስ የአገልግሎት ቡድን በአንፊጳልና በአጵሎንያም አልፎ ወደ ተሰሎንቄ ደረሰ። ጳውሎስም እንደ ልማዱ በምኩራብ የወንጌል ሥራውን ቀጠለ። ቀድሞ በነበረው አገልግሎት በሚያስገርም ድንቅና ተአምራት ጌታ ኃይሉን ያሳይ ነበር። በዚህ በተሰሎንቄ አገልግሎቱ ግን እግዚአብሔር የሰጠውን የእውቀትና የማስተዋል ችሎታውን ሲጠቀምበት ይታያል። ከመጻሕፍት እየጠቀሰ፥ እየተረጎመና እያስረዳ ብዙዎችን ከእርሱ ጋር እንዲተባበሩ አደረገ።

እንደተለመደውም ተቃውሞ ተነሳ። አይሁድ በድንገት ላስነሱት የተቃውሞ እርምጃ በቀላሉና በቅርቡ አመቺ ሆነው ያገኟቸው በየሰፍራው የሚዞሩትን ሥራ ፈቶች ነበርና እነርሱን ሰብስበው ከተማውን አወኩ። እነ ጳውሎስ ይገኙበታል ብለው ወደ አመኑበት ወደ ኢያሶን ቤት በመሄድም ባጡአቸው ጊዜ ኢያሶንንና በዚያ ያገኙአቸውን አንዳንድ ወንድሞች ለፍርድ ወደ ከተማው አለቆች ጎተቷቸው። እነ ጳውሎስ ከደረሰባቸው፦ «ቄሳርን ለመገልበጥ ሞክረዋል» የሚል ክስ ዋስ በመጥራት ተለቀቁ።

ጳውሎስና ሲላስ በፍጥነት ከተሰሎንቄ መውጣት ነበረባቸው። በወንድሞች እርዳታ ወደ ቤሪያ ከደረሱ በኋላ፥ እንደ ልማዳቸው በምኩራብ ቃሉን ይዘሩ ጀመር። አብዛኞቹ የአይሁድ ከተሞች የክርስቶስ ወንጌል ሲሰበክላቸው ግድ የለሽነት ይታይባቸው ነበር። ስለዚህም ክርስትናን የሚቃወሙት፦ «እውነት አይደለም» በማለት ሳይሆን ለባሕላቸው ወይም ለፖለቲካቸው ስለማይመቻቸው ይመስላል።

የቤሪያ ሰዎች ግን እንዲህ አልነበሩም። ጳውሎስ የሚናገረውን ቃል ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እያመሳከሩ እውነትነቱን ይፈትኑ ነበር። የጳውሎስንም ስብከት እውነተኛነት እያረጋገጡ ወደ እምነት የመጡት ቁጥር እጅግ ብዙ ነበር።

ጳውሎስ በቤርያ ወንጌልን እንደ ሰበከ የሰሙት አይሁድ ወደዚያ መጥተው ሕዝቡን አወኩ። የአይሁድ ሁከት ጳውሎስን ብቻ የሚያሰጋው ነበርና ሲላስና ጢሞቴዎስ በቤርያ ሲቀሩ ወንድሞች ጳውሎስን ወደ አቴና እንዲሸሽ ረዱት። ጳውሎስ ወደ አቴና ተሰድዶ መሄዱ ለጊዜው ደስ የማያሰኝ ሁኔታ ቢመስልም እግዚአብሔር ግን ስደትን ተጠቅሞ አዲስ የአገልግሎት በር የመክፈት ኃይሉን አሳየበት።

አቴና የፍልስፍና መናኸሪያ በመሆኑዋ በውስጥዋ የማይታይ የሃይማኖት ዓይነት የለም። ጳውሎስ በአቴና ሲላስንና ጢሞቴዎስን በመጠበቅ ላይ ሳለ በዚያ የነበረውን የጣኦት መላት በተመለከተ ጊዜ መንፈሱ ተበሳጨበት። ከሚሰማው ሁሉ ጋር የወንጌልን እውነት ይነጋገር የነበረው ጳውሎስ በድንገት ኤፌቆሮሳዊነትና ኢስጦኢክነት የተባሉ ፍልስፍናዎችን ከሚከተሉ ፈላስፎች ጋር ተገናኘ። ኤፌቆሮሶች ፍርሃትን፥ ጭንቀትንና ስለ ሞት ማሰብን አስወግዶ ጊዜአዊ ደስታ ላይ ማተኮርን የሚያስተምሩ ፈላስፎች ሲሆኑ፥ ኢስጦኢኮች ደግሞ ሰው ካለምንም የአማልክት ወይም የመለኮት እርዳታ የተመኘበት ደረጃ ይደርሳል ብሎ የሚያስተምር ፍልስፍና ነው። የአቴና ሰዎች በተለያየ የፍልስፍና ትምህርት የተለከፉና አዲስን ነገር ከመስማት ሌላ ሥራ የሌላቸው መሆናቸውን ሉቃስ ይመሰክርልናል።

የአቴና ሰዎች በከተማቸው ከተከሉት መሠዊያዎች መካከል፦ «ለማይታወቅ አምላክ» የሚል ጽሑፍ ይገኝበታል። ጳውሎስ ይህንን ጽሕፈት አስታኮ የወንጌልን እውነት አበሰረ። ይህ የአቴና ሰዎች የማይታወቅ ብለው የሰየሙት አምላክ ማንና ምን እንደሆነ በግልጽ አይታወቅም። ምናልባት፦ «እስካሁን ያልሰማነው አምላክ ይኖር ይሆናል» በሚል ጥርጣሬ ለማንኛውም ብለው የሰየሙት ስም ይሆን? ያም ሆነ ይህ ጳውሎስ ይህንን እድል ለወንጌል ስብከቱ መክፈቻ አድርጎ ሲጠቀምበት ይታያል።

ይህ እነርሱ የማያውቁት አምላክ ዓለሙንና በእርሱ ያለውን የፈጠረ አንዱና እውነተኛው እግዚአብሔር ነው። የራሳቸው የግሪክ ባለ

ቅኔዎች ከክርስቶስ ልደት ከብዙ ዓመታት በፊት፦ «እኛ ደግሞ ዘመዶቹ ነንና» ብለዋል። እንዲሁም ደግሞ፦ «በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን» ሲሉ መስክረዋል። ይህንን በማስታከክ ነበር ጳውሎስ ወንጌልን ለግሪክ ሰዎች ያበሰረው።

የጳውሎስ የማጠቃለያ አሳብ ሰሚዎቹን አስደነጣቸው። የሙታን ትንሳኤ ሊታገሱት የሚችሉት ትምህርት ባለመሆኑ፦ «እኩሌቶቹ አፌዙበት፥ እኩሌቶቹ ግን፥ ስለዚህ ነገር ደግመን እንሰማሃለን አሉት።» የአቴናው የጳውሎስ አገልግሎት ውጤታማ ባይመስልም፥ በጥቂቱ አማኞችን አትርፎአል።

ከዚህ ምዕራፍ ዋና ዋና ክንውኖች በመነሳት ስለ ወንጌል ስርጭትና የተለያዩም ሰዎች ለወንጌል ስለሚኖራቸው ምላሽ ብዙ ትምህርቶች ማግኘት እንችላለን። ሆኖም ይህ የወንጌል ስርጭት በጳውሎስ እጅ ሲከናወን ሳለ በጎዳናው ከገጠሙትን የተለያዩ ሰዎች ባህሪያት በመነሳት ልንቀስም የምንችለውን ትምህርት እንድንመለከት እሻለሁ።

አገልጋይ አኗኗሩ ከአሕዛብ ጋር ይመሳሰል ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። አሕዛብን የተበተበ እስራት አገልጋይን ያጠምደው ዘንድም ተገቢ አይደለም። አሕዛብን የዚህ ዓለም ክፋት ካልተለወጠው የአጋም ባህሪያቸው ጋር ተደብሎ ለሰይጣን እስራት ሲዳርጋቸው ፍላጎቱም እንኳ ቢኖራቸው ካለባቸው እስራት መፈታት አይችሉም። ክርስቲያን፥ በተለይም የልዑል አምላክ ባሪያ፥ ለአንድ ደቂቃ እንኳ ለዚህ ዓለም አሠራርና ለጠላቱ ለዲያቢሎስ ሽንገላ መገዛት የለበትም። በእጥሩ፥ ክርስቲያኖች ዓለማውያንን ካሰራቸው ትብታብ በጌታ ስም መፈታት አለባቸው! ይህም እንዲሆን የልብ መገረዝ ያስፈልጋል (ሮሜ 2፥ 29)።

መገረዝ ደስ የሚያሰኝ ልምምድ አይደለም። አንድን ነገር ለረጅም ጊዜ አቅፈን ከያዝነው፥ እንደ አንዱ አካላችን ሆኖ ከእኛ ጋር ይዋሃዳል። በዚህም ምክንያት ከእኛ ጋር ከመዋሃዱና ከመጣበቁ የተነሳ፥ ተላቀቁ ብለው ቢጎትቱንም ለመላቀቅ አይሆንልንም። ያንን ከእኛ ጋር የተጣበቀውን ነገር ከእኛ የሚያላቅቀው ኃይል ቢኖር የመገረዝ ኃይል ነው። ይህም መገረዝ የሚሉት አሠራር ስቃይ ያለበት

የአሠራር ዘዴ ስለሆነ ብዙ ጊዜ እንሸሸዋለን። ስለዚህም መሸከም የማይገባንን ነውር ተሸክመን እንመላለሳለን። ነውሩ ከእኛ ጋር ለረጅም ጊዜ ስለቆየና ስለለመድነው አናስተውለውም እንጂ፥ በዙሪያችን ያለ ፍጥረት ሁሉ በግልጽ ያየዋል። እንደዚህ በምንሆንበት ጊዜ ያለን ምርጫ ራሳችንን በማዋረድ ያለብንን ነውር ለማስወገድ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ነው።

ከዚህ በመቀጠል የምንመለከተው ከአገልጋይ ሕይወት ውስጥ መገረዝ ያለባቸውን በጣም የተለመዱትን ነውሮች ነው።

I. የሥራ ፈትነት ነውር (17፥ 1–9)።

ጳውሎስ በተሰሎንቄ ባለው ምኩራብ ከመጻሕፍት እየጠቀሰ የክርስቶስን ሞትና ትንሳኤ ሲነጋገር ሳለ ከግሪክ ሰዎችና ከከበሩት ብዙዎችን ማርኮ ነበር። ይህንን የተመለከቱ አይሁድ ግን ቀንተው ስደትን አስነሱበት። ለዚህም ተንኮላቸው ይተባበሩአቸው ዘንድ በቅርቡና በቀላሉ ያገኙት ሥራ ፈቶችን ነበር። ይህም የሚያሳየን፥ ሥራ ፈትነት የክፉ አሳብ፥ የተንኮልና የክፋት ሁሉ በር መሆኑን ነው። ለጌታ ቅዱስ አገልግሎት የተለየ ማንኛውም አገልጋይ ከሥራ ፈትነት እስራት ነጻ መሆን አለበት። የክርስቶስ ብርሃን የበራለት አንድ አገልጋይ ራእይ የበዛለት ሰው ነው። ስለዚህም ፈጽሞ የሚሠራው ነገር ማጣት የለበትም።

ብዙ ጊዜ የሚያጠቁንን የሥራ ፈትነት ዓይነቶች በሚከተሉት ነጥቦች ጠቅልለን እንመልከታቸው።

1) ከጸሎትና ቃሉን ከማንበብ ሥራ መፍታት። ብዙዎቻችን ከጸሎትና ቃሉን ከማንበብ ልማዳችን ወደ ኋላ የምንለው ሕይወታችን በሚቀዘቅዝበት ጊዜ ነው። ይህ በየዕለቱ ሕይወታችንን ልንመረምርበት የሚገባን ጉዳይ ነው። ዕለት በዕለት እየተጋ በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ የማይመራ አገልጋይ በሁኔታዎችና በሰዎች የሚመራ አገልጋይ ነው።

ሌሎቻችንን ደግሞ በጸሎትና ቃሉን በማንበብ እንዳንተጋ ያደረገን በሕይወታችን ቅድሚያ መስጠት የሚገባንን ነገር አለማወቃችን ነው። ለምሳሌ ጠዋት ከመኝታችን በምንነሳበት ጊዜ ሁለት ማድረግ የምንፈልጋቸው ነገሮች ቢኖሩን የትኛውን መጀመሪያ ማድረግ

እንደሚገባን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ዘወትር መቅደም ያለበት አስቸኳይና አስፈላጊ የሆነው ነገር ነው። ጸሎትና ቃሉን ማንበብ ለአገልጋይ አስፍላጊም አስቸኳይም ጉዳይ ነውና ከሁሉ ነገር በፊት መቅደም አለበት።

በሌሎች አገልጋዮች ላይ መደገፍም ብዙዎችን በግላቸው ከመጸለይና ቃሉን ከማንበብ ሥራ አስፈትቶአል። ከሌሎች ጋር መጸለይና ከእግራቸው ስር ሆኖ ቃሉን መማር እጅግ አስፈላጊ ነገር ሆኖ ሳለ፥ ያንን ብቻ የሕይወታችን መደገፊያ ካደረግነው ክርስቶስን በግላችን ማወቅ ያስቸግረናል። በሰዎች ብቻ የምንደገፍ አገልጋዮች ስንሆን አንድ ቀን እግዚአብሔር ፈቅዶ በሥራና በተለያየ ምክንያት ከወገኖች ጋር ያለን ሕብረት ለጥቂት ጊዜ ቢቋረጥ ክርስትናውም አብሮ ይቀራል። «ሳታቋርጡ ጸልዩ» (1ተሰ. 5፥ 17)። «የቃልን ወተት ተመኙ» (1ጴጥ. 2፥ 3)።

2) ከአገልግሎትና ለወገኖች መልካምን ከማድረግ ሥራ መፍታት። ክርስቲያን በጸሎትና ቃሉን በማንበብ ብቻ መወሰን የለበትም። ነገር ግን ያንን በማድረግ ያዳበረውን መንፈሳዊ ጡንቻ ለተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶችና እንዲሁም ለወገኖች መልካምን ነገር በማድረግ ሊያውለው ይገባል። በአገልግሎትና በወገኖች ሕብረት ሳይሳተፍ ገለል ብሎ የሚኖር ክርስቲያን ጤናማ ሕይወት እንደሌለው ያሳያል።

አብዛኛውን ጊዜ ከወገኖችና ከአገልግሎት ገለል ብሎ ለመኖር «በቂ» የሚመስሉ ምክንያቶች አሉን። ለምሳሌ፦ «ብዙ ተጎድቻለሁ» የሚለው ምክንያት በጣም ከተለመዱት ምክንያቶች አንዱ ሲሆን፥ የባለ ምክንያቱን አለመብሰል ያሳያል። አገልጋይ ከልምምዱ ሁሉ በመማር በይበልጥ ለጌታው ክብር የሚውልበትን ቦታና ሁኔታ እያጠና ይመላለሳል እንጂ ከወገኖች ፍቅር መሸሽ ተገቢ አይደለም። ለሰዎችና ለጌታ ሥራ ላደረግነው መልካምነት ሁሉ መልካም ምላሽን ከጠበቅን፥ የቆምንለት ዓላማ ከጌታ ክብር አልፎ ሌላም የተሰወረ የውስጥ ምኞትን እንዳዘለ ያሳያል።

በአገልግሎት ላለመሳተፍ፦ «ጌታ አልተናገረኝም» የሚልም ምክንያት የሚሰጥ ክርስቲያን የሚናገረውን ማስተዋል ይገባዋል።

ይህንን ምክንያት ከመሰንዘራችን በፊት የልባችንን አሳብ መመርመርና በርግጥም የጌታን ምሪት በየዋህነት እየጠበቅን መሆናችንንና አለመሆናችንን ማወቅ ትልቅ ማስተዋል ነው። ልባችንን መርምረን አሳባችንን ከተረዳን በኋላ ሁለት ነገሮችን እናድርግ። በመጀመሪያ ይህንን፦ «ጌታ አልተናገረኝም» የሚለውን አባባል ከአገልግሎት ለመራቅ ላደረግነው ውሳኔ የመሸሻ ምክንያት አድርገን የተጠቀምንበት መሆኑን ከተስማማን፥ ከጌታ አደራ ለመሸሽ ስላደረግነው ጥረት ንስሐ በመግባት አረማመዳችንን እናስተካክል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፦ «ጌታ አልተናገረኝም» ያልነው በእውነትም ከልባችን ከሆነና የጌታን ፊት እየፈለግን ከሆነ፥ እንደውም በወገኖች ሕብረት መታጀባችን የጌታን ምሪት ለማግኘት ተጨማሪ ኃይል መሆኑን እውቀን ሕብረታችንን ማፋፋም ለብዙ በረከት በርን ይከፍትልናል።

«ጊዜ የለኝም» ለሚለው ምክንያታችን አብዛኛውን ጊዜአችንን በምንና ከማን ጋር እያጠፋነው እንዳለን መመርመሩ አሜር መልስ ነው። «ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው» (መክ. 3፥ 1)። «ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ፥ የምትነቃቁም፥ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ» (1ቆሮ. 15፥ 58) የሚለውን ምክር በቁም ነገር ወስደን በጌታ ሥራ ካልተጋን፥ ቁጭ ብለን ለጌታ ክብር በሚሮጡት አገልጋዮች ላይ የምንፈርድ ሰዎች እንሆናለንና እናስብበት።

3) ተቀጥሮ ከመሥራት ሥራ መፍታት። አንድ ሰው ባለው እውቀት፥ ሙያና ልምምድ ሥራ ለማግኘት ጥሮና ግሮ በር ሁሉ ሲዘጋበት፦ «ጌታ ሆይ አስበኝ» ብሎ ከመጮህ ሌላ ብዙም አማራጭ የለውም። ነገር ግን ጌታ የሥራን በር፥ ችሎታንና ጉልበትን ከጤንነት ጋር ጨምሮ ሰጥቶን ሳለ በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ ስንፈታ ራሳችንን ለክፉ ነገር እናጋልጣለን።

አንዳንዶቻችንን እንዳንሠራ የሚያደርገን ስንፍና ነው። ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች በታታሪነታችን የታወቅን እንጂ በስንፍናችን የጌታን ስም የምናሰድብ መሆን የለብንም። «ጌታ ያውቃል፥ ከልኩ አያልፍም» የሚለውም የአንዳንዶቻችን ምክንያት መጠቀስ ያለበት አሳብ ነው። እኛ የሰው ልጆች ላባችንን አንጠፍጥፈን

እንበላ ዘንድ እግዚአብሔር ደንግጎአል። ይህ ትእዛዝ ደግሞ ክርስቲያንና ዓለማዊ አይልም። ከእነዚህ ከላይ ከጠቀስናቸው ሁለት ምክንያቶች ትንሽ ረቀቅ ያለው ደግሞ፦ «ሳልሠራ ካገኘሁ ለምን እለፋለሁ» የሚለው ምክንያት ነው። ይህ ምክንያት ለስርቆትና ለውሸት ከመዳረጉም በላይ፥ በተለያዩ በፍጹም መሥራት የማይችሉትን ሰዎች ለመርዳት በቆሙ የድጎማ ተቋሞች ላይ ካለአግባብ የመደገፍን ባህሪይ የሚያስፋፋ ምክንያት በመሆኑ አጥብቀን ልንሸሸው ይገባናል።

«ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርአት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናል። እንደነዚህ ያሉትን በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን። እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ (2ተሰ. 3፥ 11–13)።

II. የወሬኛነት ነውር (17፥ 10–22)።

አይሁድ በእነ ጳውሎስ ላይ ክፉዎችን አስነስተው ያስከተሉት ስደት ጳውሎስን ወደ አቴና ይሄድ ዘንድ ምክንያት ሆነው። በዚያም እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ ሰዎች ጋር በየቀኑ ሲነጋገር ላለ የተለያዩ ፈላስፎች ተገናኙት። የሚናገረውንም የወንጌል ቃል ይሰሙት ነበር። እነዚህን ሰዎች ሉቃስ እንዲህ ሲል ያስተዋውቃቸዋል፦ «የአቴና ሰዎች ሁሉና በዚያ የኖሩ እንግዶች አዲስ ነገርን ከመናገርና ከመስማት በቀር በሌላ ጉዳይ አይውሉም ነበርና» (ቁ. 21)። የአቴና ሰዎች ወሬኛነት እንግዶቻቸውን ሳይቀር የመበከል ኃይል የነበረው ክፉ አስራት ነበር።

ይህ ዓይነቱ ሕይወት በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳይነግሥ አገልጋይ ከወሬ ሕይወቱን መጠበቅ አለበት። በወሬ ምክንያት የብዙዎች ሕብረት ይፈርሳል፥ የብዙዎች ትዳር ይበጠበጣል፥ የብዙዎች ምስክርነት ይበላሻል፥ ብዙ መሠራት የሚገባው የጌታ ሥራ ላልተወሰነ ጊዜ ይተላለፋል። ለመሆኑ ወሬ በአገልግሎታችን ውስጥ ያላስከተለው ክፉ ነገር ምንድን ነው? የአስተዋይ አገልጋይ መለዮው አንደበቱን ከወሬ መግታቱ ነው።

አገልጋይ ከተለያዩ የወሬ ዓይነቶች ራሱን መጠበቅ አለበት። አንዳንድ ሰዎች ፈጽሞ ያልተወራን ነገር በመፍጠር የማውራት ልማድ አለባቸው። ይህ ዓይነቱ ባህሪይ ፈጽሞ ከአገልጋይ ሕይወት የማይጠበቅ ነው። ሌሎች ሰዎች ደግሞ የተወራችውን ትንሿን ወሬ በመያዝ በማጋነንና ውሸትን በመጨማመር የማራባት ልማድ አለባቸው። ከዚህም ዓይነቱ ሕይወት አገልጋይ ራሱን መጠበቅ አለበት። ከተጠቀሱት የወሬ ዓይነቶች ደግሞ ትንሽ ለየት ያለውና ለማውራትም ሆነ ለመስማት ለሰዎች ህሊና ትንች ቀለል የሚለው የወሬ ዓይነት፥ እውነት ሆኖ ሳለ ነገር ግን ሰዎችን ፈጽሞ የማያንጽን ወሬ ማራባት ነው። ይህ ዓይነቱ ወሬ እውነትነት ያለው ቢሆንም በመወራቱ ወገኖችን የማያንጽ ከሆነ ፈጽሞ መቆም ያለበት ሁኔታ ነው። በአጭሩ፥ አገልጋይ ያልተወራን ወሬ ፈጥሮ ከማውራት፥ ትንሹን ወሬ አጋንኖ ከማውራትና ነገሩ እውነትም ቢሆን ለሰዎች የማያንጽ ከሆነ አንደበቱን ቢጠብቅ ትልቅ ማስተዋል ነው።

የሚከተሉት ነጥቦች ወሬ በየአካባቢው ሲነፍስ እንዴት መመላለስ እንደሚገባን መሠረታዊ አሳቦችን ይሰጡናል።

1) ለምንድነው ይህንን ወሬ የምሰማውና የማወራው ብለን ራሳችንን እንጠይቅ። ማንኛውም የምንሰማውና የምናወራው ነገር ለእግዚአብሔር ክብር መዋሉንና አለመዋሉን ፈትነን ማወቅ መልካም ነው። የማወራው ነገር ለሚሰሙን ያንጻል? በወገኖች መካከል መከፋፈልን ይዘራ ይሆን? በዚያ ወሬ በመሳተፌ የማመጣው መልካም ነገር አለኝ? የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች መመለስ የዘወትር ተግባራችን ቢሆን፥ በወሬ ከሚመጣ ወጥመድ እንጠበቃለን።

2) ወሬ የሚያመጣልንን ሰው በቀላሉ መልቀቅ የለብንም። አንዳንድ ሰዎች ባወሩት ወሬ ምክንያት በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በተለያዩ ሰዎች ላይ ለደረሰው ጉስቁልና በተጠያቂነት ላይያዙ ስላለፉ ለወደፊትም ወሬን ለማራባት ይቀልላቸዋል። አገልጋዮችና ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያውክ ወሬን የሚነዙትን ሰዎች እውነቱ እስኪወጣና በተግባራቸው ተጸጽተው ንስሐ እስኪገቡ ድረስ በፍቅር፥ በየዋህነትና ስርአትን በተከተለ መንገድ አጥብቀው መከታተል ይገባቸዋል። እንደ አገልጋዮች ወሬን ወደ እኛ የሚያመጣልንን ሰው

የምንመልስበት የተለያዩ መንገዶች አሉን። ለምሳሌ፥ ወሬን ወደ እኛ ለሚያመጣው ሰው ያንን ወሬ ከየት እንዳመጣው የመናገር ሃላፊነት እንዳለበት በትህትና መግለጽ እንችላለን። ወሬውን ከየት እንዳመጣው ለመናገር ፈቃደኛ ካልሆነ፥ ራሱ ፈጥሮ ያወራው እንደሆነ አድርገን መቀበላችንን በረጋ መንፈስ በመግለጽ ነገሩን ወደ ብርሃን እንደምናወጣው ማሳወቁ መልካም መደምደሚያ ይሆናል።

3) አረማመዳችንን በጥንቃቄ እናድርግ። በተለይም በዘመናችን የቤተ ክርስቲያንንና የአገልጋዮቿን ታማኝነት ለማጥፋት በተደጋገመ ሁኔታ ወሬ ይነፍላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ለአገልግሎት ያለንን ትጋት ከመቸውም ይበልጥ ብንጨምር፥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ አንድነት የምንተጋ መሆናችንን ለጠላታችን ለዲያቢሎስ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለማይፈልጉ ሰዎች እናሳያቸዋለን። ይህንን የምናደርግበት አንዱ መንገድ ከወገኖች ጋር በተገናኘን ቁጥር ለጥቂት ጊዜም ቢሆን በመጸለይ ሲሆን፥ ይህም የጠላትን ሥራ ከማፍረሱ በላይ አንድነታችንን የመጠበቅ ኃይል ይኖረዋል። በተጨማሪም፥ በየጊዜው ለሚነሳ ወሬ ልባችንን በመክፈት በተለያዩ ሰዎች ላይ ፊታችንን የመለወጥ ተጽእኖ እንዳያድርብን መጠንቀቅ ያስፈልገናል። እነዚህን ከላይ የጠቀስናቸውን ነጥቦች ለመከተል መጀመሪያ እኛ ራሳችን ከወሬኛነት መፈታት አለብን። ከዚያም በሌሎች ሰዎች ላይ ያለውን የወሬኛነትን መንፈስ ለመቋቋም እንችላለን።

III. የጣያት ነውር (17፥23–34)።

ጳውሎስን ያስቸገረው የሥራ ፈቶች ሰዎች ከአይሁድ ጋር መተባበር ወይም አዲስ ነገርን በማውራት የተጠመዱት የአቴና ሰዎች ሁኔታ ብቻ አልነበረም። ከዚህ ሁሉ ነገር ጋር ተጨምሮ በአቴና የሞላው የጣኦት ብዛት አበሳጭቶት ነበር። እነዚህ ሰዎች የሚያመልኩአቸው አማልክት ከመብዛታቸው የተነሳ፦ «ለማይታወቅ አምላክ» ብለው መሰዊያን እስኪያበጁ ድረስ ታውረው ነበር። ይህ ዓይነቱ እስራት ደግሞ የጣያት እስራት ይባላል።

ለመሆኑ ጣያት፥ በአገልጋይ ሕይወት ውስጥ እንዴት ሊገባ ይችላል? እኛ አገልጋዮች እግዚአብሔርን በሚገባ በማናውቅበት ጊዜ

ሰዎችንና ሁኔታዎችን ከጌታ እናስቀድማለን። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ጣያት በእኛ ዘንድ ነገሠ ማለት ነው። በእኛና በእግዚአብሔር መካከል የገባ ማንኛውም ነገር ጣያት ይባላል። ጣያት በብዙ መልኩ ወደ አገልጋይ ሕይወት ሾልኮ ሊገባ ይችላል። ስለዚህም ዝርዝር እናውጣ ብንል ጊዜና ቦታ አይበቃንም። ለጊዜው በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ነጥቦች ብቻ ተመልክተን እናልፋለን።

1) አገልጋይን ከአገልጋይ ሰናበላለጥ ጌታን እንረሳለን። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እንደ ፈቀደ ስጦታን የሚያከፋፍልና እንዳሻው የሚጠቀምበት ከሆነ የእኛ አንዱን አገልጋይ ከሌላው አገልጋይ ጋር ማበላለጥ ስፍራ ልንሰጠው የማይገባ ስህተት ነው። እገሌ ከእገሌ ይበልጣል በምንልበት ጊዜ ደሙን ያፈሰሰልንን ጌታችንን እየዘነጋን መሆኑን አንርሳ። ጌታን ከማየት ይልቅ ሰዎችን በማየት የተሞላን ስንሆን በእግዚአብሔርና በእኛ መካከል ሰው እንደገባና ጣያታችን እንደሆነ እናስታውስ። ከሰው ሰው ስንመርጥ ከምርጫችን ጌታን አስወጣነው ማለት ነው። አንዱን የምናወርድበትን ስህተት ስንፈልግበት፥ ሌላውን ደግሞ የምንከብበትን መንገድ ስንሻ የክርስቶስ ስም መነሳቱ ይቀርና «የአጵሎስና የጳውሎስ» ስም ብቻ በአንደበታችን ይሞላል። ጣያት ከእኛ እንዲርቅ እንደ ጳውሎስ፦ «ሰውን በክርስቶስ አውቃለሁ» የሚል አቋም ያስፈልገናል።

2) እኛ የፈለግነው ነገር በፈለግነው ጊዜና መንገድ ይሁን ሰንል ጌታን እንረሳለን። ቀደም ብዬ የገለጽኩት አገልጋዮችን ከአገልጋዮች ስናበላልጥ ጌታን በመዘንጋት ጣያትን በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ልናስገባ እንደምንችል ሲሆን፥ አሁን ደግሞ ራሳችንን ከሌሎች የበላይ ስናደርግ በጌታና በእኛ መካከል «እኔነት» የሚባል ጣያት ልናቆም እንደምንችል አብራራለሁ።

ሁሉም ነገር እኔ በምፈልገው መንገድ መሆን አለበት የሚል አገልጋይ ራሱን ከሌሎች የተሻለ አድርጎ የሚያስብ አገልጋይ ነው። ስለዚህም፥ እግዚአብሔር በሌሎች ወገኖች ሊያመጣ የሚችለውን መልካም ነገር ለመቀበል የተዘጋጀ ልብ ስለሌለው የእርሱ አሳብ ብቻ ትክክለኛ ይመስለዋል። እንዲህ ዓይነቱ አገልጋይ የእርሱ አሳብ በሌሎች አሳብ ላይ ዘወትር የበላይ ሆኖ እንዲገኝ በመጣሩ ሳያስበው

በእግዚአብሔር አሳብ ላይ ሲነሳ ይገኛል። የጌታን አሳብ ዘንግቶ ዘወትር የግሉን መንገድ የሚያሳድድ አገልጋይ ወደ ማስተዋሉ በመመለስ መንገዱን ለእግዚአብሔር መልቀቅ ይገባዋል። ይህ ዓይነቱ አገልጋይ በቶሎ ሕይወቱን መርምሮ በጌታ ጸጋ ካላስተካከለ ዘወትር በሰዎች አገልግሎት ውስጥ የስህተትን ምክንያት የሚፈልግ የክስ ሰው ይወጣዋል። ነገር ግን እንደ እውነተኛ አገልጋይ ወደ ማስተዋሉ ቢመጣ፥ ስላልጸለየለትና በጉድለቱ ስላላገዘው ሰውና ሁኔታ የችኮላና የፍርድ አሳብ ከመስጠት ይቆጠባል። እኔነት በቀላሉ የማይለቅ በሽታ ነው።

3) ፍርድን ከጌታ በምንቀማበት ጊዜ ጌታን እንረሳለን። በአርምጃው እግዚአብሔርን የዘነጋ አገልጋይ ዘወትር በሰው መነሻ አሳብ ላይ ሲፈርድ ይገኛል። የአንድን ሰው የውስጥ አሳብ ጠንቅቆ የሚያውቀው አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ሆኖ ሳለ፥ ከውጭ በሚያየው ሁኔታ ብቻ በመመራት፦ «እገሌ እንዲህ ያደረገው በዚህ ምክንያት ነው» በማለት የሚፈርድ አገልጋይ በዚህ ክፍል ውስጥ ይመደባል። በሰዎች ላይ የመፍረድ ዝንባሌ የሚያጠቃው አገልጋይ ለደረሰበት ደስ የማያሰኝ ልምምድ ሁሉ፦ «ለዚህ የበቃሁት በእገሌ ምክንያት ነው» በማለት በሌሎች ላይ መፍረድ ይቀናዋል። ይህ የሚያሳየው የአገልጋዩን ፈጽሞ በጌታ አለመታመን ነው። ጌታን በልቡ ዙፋን ላይ ያነገሠ አገልጋይ ለሚደርስበት ነገር ሁሉ ምላሹ፦ «እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ነው፥ እራሱ ደስ የሚያሰኘውን ያደርጋል» የሚል ይሆናል።

ከሕይወቱ የፍርድን መንፈስ ያላስወገደ አገልጋይ የድፍረት ውሳኔን የመወሰን ዝንባሌ ይኖረዋል። «ሁለተኛ በዚህ አገልግሎት አልቆምም»፤ «ከዛሬ ጀምሬ በፍጹም ወደ እገሌ ቤት አግሬን አላነሳም» የሚሉትና የመሳሰሉት አባባሎች ከድፍረት የሚመነጩ አባባሎች ናቸውና አገልጋይ ልቡን ሊጠብቅ ይገባዋል። የአገልጋይ ሕይወት በእግዚአብሔር መንፈስ መመራት አለበት እንጂ በፍርድና በድፍረት መንፈስ መመራት የለበትም።

ከአገልጋይ ሕይወት ውስጥ መገረዝ ያለባቸውን ሦስት አሳቦች ዘርዝሬአለሁ። የሥራ ፈትነት፥ የወሬኛነትና የጣኦት አስራቶች ሁሉ ከአገልጋይ ሕይወት ስፍራ እስኪያጡ ድረስ የአገልጋይ ልብ መገረዝ

አለበት። አገልጋይ ከሕይወቱ መገረዝ ያለባቸውን ድካሞች በሚከተሉት መንገዶች ከፍሎ እንዲመለከታቸው እፈልጋለሁ።

- እግዚአብሔር ብቻ ሊያከናውነው የሚችል መገረዝ። አንዳንድ በአገልጋዮች ሕይወት የነገሠ ነውር ጌታ በመንፈስ ቅዱሱ ኃይል በጣቶሶ ካልጣለው በስተቀር ምንም ነገር አይበግረውም። «በሕይወትም እንድትኖር፥ አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ እንድትወድድ አምላክህ እግዚአብሔር ልብህን የዘርህንም ልብ ይገርዛል» (ዘዳግ. 30፥6)። ይህ ዓይነቱ የልብ መገረዝ የሚያስፈልገው ነውር፥ በየኮንፍራንሱ በመገኘት አይገረዝም። ወይም ደግሞ በክርስትና ስለቆየን አይገረዝም። ለምሳሌ፥ ወሬኛነትን ከዚህ ክፍል ልንመድበው እንችላለን። በወሬኛነት የተተበተበ አገልጋይ የጌታ መንፈስ መጥቶ ሕይወቱን ካልገለባበጠው በስተቀር የእግዚአብሔርን መንጋ እንደበጠበጠ ይኖራል።
- ሌሎች ሊያከናውኑት የሚችሉት መገረዝ። ይህንን አሳብ በኢያሱ ምዕራፍ አምስት ውስጥ የተጻፈውን በመደገፍ እንመልከተው። ኢያሱ በእስራኤል መካከል የነበሩትን ሽለፈታሞች በገረዘበት ወቅት እግዚአብሔር፦ «ዛሬ የግብፅን ነውር ከእናንተ ላይ አንከባልያለሁ» (ቁ.9) ብሎ ተናገራቸው። ይህ ነውር ይንከባለል ዘንድ ግርዛቱን ኢያሱ ማከናወን ነበረበት። በእኛም ሕይወት ጌታ በአጠገባችን ባቆመልን አገልጋዮች አማካኝነት ሊገረዙ የሚችሉ ነውሮች ቢኖሩ ጌታ በእነርሱ ተጠቅሞ ይገርዘንና ይቀርጸን ዘንድ ልንፈቅድለት ይገባናል። በሕይወታችን ያስቸገረን ነውር ሁሉ እንዲገረዝ ከፈለግን፥ አማካሪዎች ይመክሩን ዘንድ፥ አረኞች ይመሩን ዘንድ፥ አስተማሪዎች ያስተምሩን ዘንድ ልንፈቅድላቸው፥ ስጦታቸውንም አክብረንና ራሳችንን አዋርደን ወደ እነርሱ ልንሄድ ይገባናል። የተግሳጽ ቃል ሲመጣ ልባችንን እንዳናደነድን እንጠንቀቅ። ከዚያም አልፎ ቢያስፈልግ ሌሎች አገልጋዮች እጃቸውን እንዲጭኑብንና እንዲጸልዩልን ዝቅ ብንል ያልጠበቅነው ተአምር በሕይወታችን እንዲከናወን በርን እንከፍታለን።

- ራሳችን ልናከናውነው የሚገባን መገረዝ። ሰው ወደ እግዚአብሔር ከመጸለዩ በፊት በልቡ ያለውን ቂም ማስወገድ አለበት (ማቴ. 5፥ 23–24)። ሰው ወደ ወንድሙ ለእርዳታ ከመቅረቡ በፊት ውሸትንና ሽንገላን ከውስጡ ማስወገድ አለበት። እግዚአብሔርም ሆነ ሰዎች ይረዱን ዘንድ በመጀመሪያ እኛ ልናስወግዳቸው የሚገቡን ነውሮች አሉን። ይህንን እውነት የሚከተለው ቃል እንዲህ በማለት ይደግፈዋል፦ «እንግዲህ አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ የጌቶችም ጌታ፥ ታላቅ አምላክ ኃያልም የሚያስፈራም፥ በፍርድ የማያደላ፥ መማለጃም የማይቀበል ነውና እናንተ የልባችሁን ሸለፈት ግረዙ፥ ከእንግዲህ ወዲህም አንገተ ደንዳና አትሁኑ» (ዘዳግ. 10፥ 16)።

17

ማመን የሌለብህ ውሸቶች

ምዕራፍ 18፥ 1–28



አቴናን ከለቀቀ በኋላ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ በማለፍ የራሱን ማረፊያ ማዘጋጀት ነበረበትና እንደ እርሱ ድንኳን በመስፋት የሚተዳደሩትን አቂላንና ጵርስቅላን አግኝቶ ከእነርሱ ጋር በመሆን የድንኳን መስፋት ሥራውን አብሮ ተያያዘው። አቂላና ጵርስቅላ ከሮሜ በቀላውዴዎስ ትእዛዝ ተባርረው የመጡ ድንኳን ሰፊዎች ናቸው። ምናልባትም ወደ ቆሮንቶስ ከመምጣታቸው በፊት ወደ ጌታ የመጡ ይመስላሉ። ጳውሎስ ለዕለት ኑሮው ሲል ይህንን የጉልበት ሥራ መሥራቱ ለጌታ ከብር ከመቆም አልከለከለውም ነበር። በየሰንበቱ እየወጣ ወንጌልን ይሰብክ ነበር።

ሲላስና ጢሞቴዎስም ጳውሎስን ባለበት በወንጌል ሲተጋ ሳለ ደረሱበት። ምናልባትም ከመቄዶንያ ገንዘብን ይዘው በመምጣት በበለጠ ነጻነት ወንጌልን ለመስበክ ይችል ዘንድ እንዳበቁት ይታመናል (ፊልጵ. 4፥ 15)። ጳውሎስ ሁለቱንም ወደ ተሰሎንቄ የጻፋቸውን መልእክቶቹን በዚህን ጊዜ እንደጻፋቸውም ይታመናል። በዚያም እንደተለመደው ሁሉ የክርስቶስ ወንጌል ስደትን አስከተለ።

የኢዮስጦስ ቤት ከምኩራብ አጠገብ በመሆኑ የምኩራብ አለቃ ሰነበረው ለቀርስጶስ ከነቤተሰቡ በጌታ የማመኛ ምክንያት ሆነው። ብዙዎች የቆሮንቶስ ሰዎችም አምነውና ተጠምቀው ወደ ጌታ መንግሥት ተደባለቁ። ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሲመጣ በጥቂቱም ቢሆን ተስፋ መቁረጥ እንደ ተጫጫነው መገመት አያዳግትም። የአቴና አገልግሎቱ እምብዛም ውጤት አልታየበትም። ምናልባትም ቀደም ሲል የተደበደበበት ቁስሉ ሙሉ በሙሉ አልዳነለትም ብለው የሚያምኑም አሉ (16፥ 23)። በደረሰበት ከተማ ሁሉ የጠበቀው ስደትና ተቃውሞ ነበርና፥ ምናልባት ወደ ሌላ አቅጣጫ የማምሪያው ሰዓት የደረሰ ሳይመስለው አልቀረም። እግዚአብሔር ለጳውሎስ በራእይ የተናገረው የመጽናኛ ቃል በጊዜው የሚያስፈልገው መልእክት ነበር። ጳውሎስ በዚህ

በሰዓቱ ሰደረሰለት የማጽናኛ ቃል ተበረታትቶ በአዲስ ጉልበት ለዓመት ተኩል የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማረ በቆሮንቶስ ከረመ።

ጋልዮስ በአካይያ የአገረ ገዥነቱን ስፍራ የተረከበው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ከመጣ በኋላ ነው ተብሎ ይገመታል። አይሁድም የአገረ ገዥውን ለነገሩ እንግዳነት ተገን በማድረግ ክላቸውን እንደ አዲስ ያቀረቡ ይመስላሉ። ጋልዮስ እርሱን በሚመለከት ጉዳይና በአይሁድ የውስጥ ክርክር መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቆ የማወቅ ማስተዋል ነበረውና አይሁድን ከፍርድ ወንበር ፊት አስወጣቸው። የግሪክ ሰዎች የመቱት የምኩራብ አለቃ ሶስቴንስ፥ ምናልባት ቀደም ሲል ወደ ጌታ በመጣው በቀርስጶስ ስፍራ የተተካ ሳይሆን አይቀርም (ቁ.8)። በዚህ በፍርድ ወንበር ፊት የተከሰተው ሁኔታ የሚያሳየው የሮም ሕግ በአይሁድ የሃይማኖት ጉዳይ ውስጥ እንደማይገባ ነው።

ከጋልዮስ ቅን ፍርድ የተነሳ ነጻነቱን ያገኘው ጳውሎስ፥ በቆሮንቶስ ብዙ ቀን ከተቀመጠ በኋላ ወንድሞቹን ተሰናብቶ በመርከብ ወደ ሶርያ ሄደ። ይህም ጉዞው የሦስተኛው የሚስዮናዊ ተልዕኮው ጅማሬ ነበር። «ስለት ነበረበትና ራሱን በክንክራኦስ ተላጨ» (ቁ.18) የሚለው አላብ ጳውሎስ ምንም እንኳ ሙሉ በሙሉ በመለወጥ ለክርስቶስ የቆመ አገልጋይ ቢሆንም፥ ይህንን የናዝራዊነት ስለት መሳሉ በመጠኑም ቢሆን የአይሁድነት ባህሉን እንዳልተወ የሚያንጸባርቅ መልእክት አለው። ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን በደረሰ ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር የነበሩትን ጵርስቅላና አቂላን በዚያ በመተው ወደ ምኵራብ ገብቶ ከአይሁድ ጋር ከተነጋገረ በኋላ በመርከብ ተሳፍሮ ወደ ቂሳርያ ተጓዘ። ከዚያም ወደ አንጾኪያ፥ ወደ ገላትያና ወደ ፍርግያ በተራ አለፈ።

ሉቃስ የጳውሎስን ሁኔታ ለጊዜው በመተው ወደ ኤፌሶን የወረደውን የአጵሎስን ታሪክ በአጭሩ ይተርክልን ጀመር። ይህ በወገኑ የእስክንድርያ የሆነ ሰው በመጻሕፍት እውቀት የበረታና የጌታን መንገድ የተማረ ሰው ነበር። ስለ ክርስቶስ ይናገርና ያስተምር የነበረው ነገር ትክክል ቢሆንም እንኳ፥ የሚያውቀው የዮሐንስን የንስሐ ጥምቀት ብቻ ነበርና ጵርስቅላና አቂላ ወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ ቢትክክል ገለጡለት። አጵሎስም ከወንድሞች መጽናናትንና የድጋፍ ደብዳቤን ተቀብሎ ወደ አካይያ ሄደ። በዚያም

አምነው የነበሩትን በጸጋ ያገለግላቸው ነበር። አይሁድን ግን እናውቃለን ከሚሉት ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እየገለጠ በብርቱ ያስረዳቸው ነበር።



አገልጋይን አገልጋይ የሚያደርገው ታማኝነቱ እንጂ ሌሎች ያዩትን ስላየ ወይም የተመኘውን ነገር ስላገኘ አይደለም። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር አሠራር ከአገልጋዩ ፍላጎት ጋር እየተጋጨ ለአገልጋዩ ግር የሚልበት ጊዜም አለ። ስለዚህም አገልጋይ ፍሬውንና ጌታን ሲያገለግል የሚኖርበትን ኑሮውን እያየ፦ «በዚህ ሁኔታ እንዴት ጌታን ላከብረው እችላለሁ?» በሚል ጥያቄ ሊሞላ ይችላል። እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ተሞልቶ የሚመላለስ አገልጋይ ልቡን በሚከተለው ቃል ማላረፍ ይገባዋል፦ «ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም» (ኤር. 29፥ 11)።

የእግዚአብሔር ጥሪ በሕይወቱ ያለ ማንኛውም አገልጋይ፦ «አገልግሎቴን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ማከናወን አለብኝ» ብሎ የሚያምንባቸው አምነቶች አሉት። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ አነዚያ ያመናቸው ነገሮች ላይሆኑ ሲቀሩ ይፈተናል። ይህ ዓይነት ጥያቄ ያለበት አገልጋይ በመጀመሪያ አነዚያን ያመናቸውን አሳቦች፦ «እግዚአብሔር በዚህ መልኩ እንዳገለግለው ፈቅዶአል ወይ?» በሚለው ጥያቄ ሊመዝናቸው ይገባል። አንዳንድ ጊዜ ወደ አገልጋይ ሕይወት መጥተው የሚበጠብጡት አሳቦች ፈጽመው ከእውነት የራቁ ሆነው ሳለ፥ አገልጋይ ስላመናቸው ብቻ ብዙ ይፈትኑታል። ከዚህ በመቀጠል በምዕራፍ አስራ ስምንት ውስጥ የምናገኛቸውን አገልጋይ በቀላሉ የሚያምናቸውን ውሸቶች አብራራለሁ።

I. ሙሉ ጊዜን የመስጠት ጉዳይ (18፥ 1–4)።

አንድ አገልጋይ ጌታ እንዲጠቀምበት የግድ ሙሉ ጊዜውን የሰጠ መሆን የለበትም። ለዚህ አሳብ እውነተኛነት ትልቁ ምሳሌአችን የጳውሎስ ሕይወት ነው። ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ በመጣ ጊዜ ከአቂላና ከጵርስቅላ ጋር አብሮ ድንኳን በመስፋት ሲተዳደር እንመለከታለን። ሐዋርያው ጳውሎስን የሚያክል የክርስቶስን ጥልቅ ምስጢር ለዓለም

ሁሉ ለመግለጽ የተጠራ አገልጋይ፥ ጳውሎስን የሚያክል ነፍሳት በለብከቱ የዳኑ፥ ሙታን በእጁ የተነሱ አገልጋይ፥ ድንኳን እየሰፋ ጌታን ሲያገለግል እንዴት ጌታ ዝም አለ?

ጌታ የጳውሎስን ሁኔታ አይቶ ዝም አላለም። ጳውሎስ በምን ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ቢያገለግል የበለጠ ፍሬአማ እንደሚሆን ጌታ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ በጉልበቱ እየሠራ ያገለግለው ዘንድ ወደደ፥ ጸጋውንም አበዛለት። ጳውሎስም ይህ ምስጢር የገባው አገልጋይ ስለነበር ሲያጉረመርም አይታይም። እንደውም ለጌታ ክብር ሲያልፍበት የሚገባው ሁኔታ እንደሆነ በመጥቀስ ይናገራል (1ቆሮ. 4፥12፤ 2ቆሮ. 11፥7)።

አገልጋይ ሆይ፥ በአንተም ሕይወት ቁም ነገሩ ሙሉ ጊዜህን መስጠትህና አለመስጠትህ ሳይሆን ጌታህ በሕይወትህ መክበሩ ነው። በዚህ አሳብ ልብህን ካላላረፍከው፥ ትግልህና ሩጫህ ጌታን ማስከበር መሆኑ ይቀርና ሌሎች የደረሳቸው ወግ ይድረሰኝ የሚል ይሆንብሃል። ይህ ደግሞ ወደ ቁልቁል ሊወስድህ የሚችል ሁኔታ ነውና ልታስብበት ይገባል። በምን ዓይነት ሁኔታ ብትኖር ጌታ በሕይወትህ ያለውን ዓላማ ለመፈጸም እንደሚመቸው አንተ አታውቅም። ስለዚህ፥ እግዚአብሔር ራሱ በምን መልኩ እንደምታገለግለው እስከሚመክርህ ድረስ ባለህ ጊዜ ተሰለፍ። እግዚአብሔር ያሸከመህን የተለያየ የሥራና የቤተ ሰብ ሃላፊነት ከተወጣህ በኋላ የቀረህን ጊዜ ለጌታ ክብር ብትሮጥለት ያለህን ሙሉ ጊዜ ተጠቀምክበት ማለት ነው። አገልግሎትህ ብቻ ሳይሆን የተቀሩትም የዕለት ኑሮህን ለማሸነፍ የምትደክምባቸው ጊዜአት ሁሉ የጌታ እንደሆኑ አስታውስ።



አንዳንዶች ጌታ እንዲጠቀምባቸው የግድ ሙሉ ጊዜአቸውን ለአገልግሎት እስከሚሰጡ ድረስ መጠበቅ ያለባቸው ይመስላቸውና ጊዜአቸውን በከንቱ ያባክናሉ። ሌሎች ደግሞ እግዚአብሔር በፈታቸው ያስቀመጠላቸው አገልግሎት በጊዜ እጥረት ምክንያት ሲተጓጎል እያዩ በበለጠ ሁኔታ ጊዜአቸውን ለጌታ ለመስጠት አስፈላጊውን ነገር ከማድረግ በቸልተኛነት ያልፋሉ። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ኢየሱስ ጌታ ነው ብሎ ለማወጅ ሙሉ ጊዜን መስጠት እንደማያስፈልገው አትዘንጋ። ነገር ግን የጌታ ሥራ የእንተን

ሙሉ ጊዜ የሚጠይቅ ሆኖ ካገኘኸው የሚጠበቅብህን ለማድረግ በእምነት ከመውጣት ወደ ኋላ አትበል።

II. ፍሬን በዓይን የማየት ጉዳይ (18፥5–23)።

አገልጋይ ጌታ እንዲጠቀምበት የግድ ፍሬውን ወዲያውኑ ማየት የለበትም። በዚህ ክፍል ውስጥ እንደምንመለከተው፥ ጌታ ጳውሎስን፦ «ነገር ግን ተናገር ዝምም አትበል፤ በዚህ ከተማ ብዙ ሕዝብ አሉኝና» (ቁ.10) ብሎ ከተናገረው በኋላ በስደት ምክንያት ያንን ስፍራ ትቶ እስከሚሄድ ድረስ ለአንድ ዓመት ተኩል ሲያገለግል ነፍሳት ሲድኑ አንመለከትም። ነፍሳት ድነው ቢሆን ኖሮ ሉቃስ ጠቅሶት እንደሚያልፍ አያጠራጥርም። ታዲያ ጌታ የተናገረውን ነገር የማይፈጽም አምላክ ነውን? አይደለም! ጌታ የተናገረውን በሚገባ ይፈጽማል፥ ነገር ግን በራሱ ጊዜ ነው የሚፈጽመው። ጳውሎስ በዚያች ከተማ የዘራውን ዘር ጌታ ፍሬ እንደሰጠው ጥርጥር የለውም። ጳውሎስ ግን ፍሬውን ሊያየውም ላያየውም ይችላል።

እንዱን አገልጋይ ሙሉ ጊዜውን አለመስጠቱ ሊፈትነው፥ ሌላውን ደግሞ የአገልግሎቱን ፍሬ ፈጥኖ አለማየቱ ይፈታተነዋል። «ጌታ የሚጠቀምብኝ ከሆነ ፍሬው የት አለ?» በሚል አሳብ ደክሞ ተስፋ እንዳይቆርጥ አገልጋይ ልቡን መጠበቅ አለበት። እግዚአብሔር አንድን አገልጋይ ይጠቀምበታል ማለት ያ ሰው ፍሬውን እጅ በእጅ ይረከባል ማለት አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ፍሬአችንን ሳናይ የምናልፍበት ወቅት እንዳለም ማስታወስ አለብን። «እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፥ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና ነገር ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት» (ዕብ. 11፥13) ተብሎ የተነገረላቸው፥ ከጌታ የተቀበሉትንና ያመኑትን ተስፋ በዓይናቸው ሳያዩ ያለፉት የእምነት አርበኞች ናቸው። እኛም እንደዚሁ ጌታ እንዲጠቀምብን ፍሬአችንን በቶሎ ማግኘት እንደሌለብን አውቀን ለአገልግሎታችን በእምነት እንትጋ። «እንግዲህ ሁል ጊዜ ታምነን በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና» (2ቆሮ. 5፥6)።



አንዳንዶች በአገልግሎታቸው ፈጥነው ፍሬን ካላዩ ተስፋ ወደ መቁረጥ ሕይወት ውስጥ በቀላሉ ይገባሉ። ሌሎች ደግሞ

አገልግሎታቸው በተለያየ እሾክ ታንቆና ፍሬ አጥቶ ከቀን ወደቀን እየደረቀ ሲሄድ፦ «እግዚአብሔር አንድ ቀን ይሠራል» በሚል እምነት ራሳቸውን መመርመር የተሳናቸውም አሉ። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። እውነት ነው፥ በአገልግሎትህ ፍሬን በቶሎ አላየህም ማለት ጌታ አልተጠቀመብህም ማለት አይደለም። ይህ እውነት ግን ሚዛናዊነትን ይጠይቃል። በአገልግሎትህ ፍሬን ያላየህበት ምክንያቱ የጌታ ጊዜ ጉዳይ ሳይሆን የተለያየ ድካምና የኃጢያት ሰበብ እንዳይሆን ዘወትር ልብህን ከመመርመር አትቆጠብ።

III. **የእውቀት ጉዳይ** (18፥24–28)።

ከጳውሎስ ሁኔታ አገልጋይ በጌታ መጠራቱንና ጌታ የሚጠቀምበት መሆኑን ለማረጋገጥ ሙሉ ጊዜውን መስጠት፥ እንዲሁም ደግሞ ፍሬውን ወዲያውኑ ማየት እንደሌለበት ተማርን። አሁን ደግሞ ከአጵሎስ ሕይወት አንድ ተጨማሪ ነገርን እንማራለን። አገልጋይ ጌታ እንዲጠቀምበት ሁሉን ያወቀ ሰው መሆን የለበትም።

አጵሎስ በመጻሕፍት እውቀት የበረታ ሰው ሆኖ ሳለ አንድ የሚጎድለው ነገር ነበር፥ ስለእግዚአብሔር መንግሥት የነበረው እውቀት የተወሰነ ነበር። ይህ ውስን እውቀቱ ግን ስለ ክርስቶስ ከመናገርና ከማስተማር አልከለከለውም ነበር። በመንፈስ እየተቃጠለ ስለክርቶስ በትክክል ያስተምር ነበር። ጵርስቅላና አቂላም ሁኔታውን ዓይተው ስለ እግዚአብሔር መንግስት በይበልጥ አስተማሩት።

አንድ አገልጋይ ጌታ እንዲጠቀምበት ሁሉን ጠንቅቆ እስከሚያውቅ ድረስ ከጠበቀ፥ ጌታን ሳያገለግል እድሜውን በመጠበቅ እንደሚያጠፋ እሙን ነው። ነገር ግን አገልጋይ በመጀመሪያ እንደ አጵሎስ ስለ ክርስቶስ የሚያምነው መሰረታዊ እምነቱ ትክክል መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ባለው እውነትና እውቀት መሰለፍ አለበት። መሰረታዊውና አስፈላጊው ነገር ስለ ክርስቶስ የምናውቀው ነገር ትክክለኛነቱ እንጂ ብዛቱ አይደለም። ክርስቶስን የማወቅ ጉዞአችን ማለቂያ የሌለው ጥልቅ ምስጢር ነው። ያንንም ምስጢር ጌታ ከዕለት ወደ ዕለት በይበልጥ እንዲገልጽልን በጸሎት መጋደል አለብን (ኤፌ. 1፥15–23)። አገልጋይ በበለጠ ለመማር ትሁትና ዝግጁ የሆነ መንፈስ

እንጂ ሁሉን ያወቀ አእምሮ አያስፈልገውም። ይህን እውነት በመዘንጋት አገልጋዮች የክርስቶስን ታላቅነት ለማወጅ ቀነ ቀጠሮ መስጠት አይገባቸውም።



ጌታን ለማገልገል በእውቀታቸው የተወሰነ ደረጃ መድረስ ያለባቸው የሚመስላቸው አገልጋዮች ጊዜአቸውንና የጌታን ጸጋ በከንቱ ያባክናሉ። በአንጻሩ ደግሞ ስለ እምነታቸውም ሆነ እምነታቸውን ስለሚነካ ነገር በቂ እውቀት ይኖራቸው ዘንድ ለመማር የማይጥሩ አገልጋዮች በእድገታቸው ውስኖች ይሆናሉ። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ስለክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በድፍረት ለማወጅ፦ «አላውቅም» የሚል የዝቅተኛነት ስሜት እንዳያጠቃህ ልብህን ጠብቅ። ነገር ግን ማወቅ የሚገቡህን የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮች ደግሞ ከመማር አትቦዝን።

አገልጋይ በቀላሉ ሊያምናቸው የሚችላቸውን ሦስት የተሳሳቱ አመለካከቶችን ተመለከትን። እነርሱም ባጭሩ፥ ሙሉ ጊዜን የመስጠት ጉዳይ፥ በአገልግሎት ፍሬን የማየት ጉዳይና ስለ አገልጋይ የእውቀት መጠን ጉዳይ ናቸው። አገልጋይ እነዚህን ነጥቦች አስመልክቶ የሰጠሁትን ምክር በሥራ ላይ ለማዋል እንዲቀልለው የሚከተሉትን ተጨማሪ ምክሮች ለማከል እወዳለሁ።

1) አገልጋይ ባለው ጊዜና ችሎታ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊም ሆነ ከዚያ ውጭ ያለውን እውቀቱን ለማዳበር ይጣጣር። በተለይም ፍልስፍናና እውቀት በበዛበት በዚህ ዘመን በተለያየ መልኩ በእግዚአብሔር አሳብ ላይ የሚነሱትን ተቃዋሚዎች አፍ ለማዘጋት የተዘጋጁ አገልጋዮች ቤተ ክርስቲያን አጥብቃ ትፈልጋለች።

2) አገልጋይ ዘወትር ከውድድር መንፈስ ልቡን ይጠብቅ። ለአገልግሎት ሙሉ ጊዜአችንን ለመስጠት የምንፈልገው ጌታ በዚያ መልኩ ስለጠራን እንጂ፦ «ሌሎች ስለወጡ እኔም መውጣት አለብኝ» በሚል ስሜት መሆን የለበትም። እውቀታችንን ለማዳበር የምንጥረው ለጌታ ክብር ይውል ዘንድ እንጂ ሌሎች የደረሱበት እንድንደርስ መሆን የለበትም። በአገልግሎታችን ፍሬን የምንጠማው የክርስቶስን ስም ከፍ ከፍ ለማድረግ እንጂ ገናና ሆነን ለመታወቅ ወይም ደግሞ የእኛ ቤተ ክርስቲያን በአካባቢያችን ካለችው ቤተ ክርስቲያን በቁጥር በልጣ

እንድትታይ መሆን የሰበትም። ሁሉን ነገር ለጌታ ክብር ብቻ ማድረግን ስንማር ከውድድር መንፈስ እንጠበቃለን። የአገልጋይ አክሊሉ ታማኝነቱ እንጂ ታዋቂነቱ ወይም የሌሎች ወግ ስለደረሰው አይደለም። ይህን እውነት የተረዳ አገልጋይ እውነተኛ፥ ጥምትና የአገልግሎት ምስጢር የገባው አገልጋይ ነው። ስለዚህም አገልጋይ ለአክሊል ከማያበቃ ከታይታ አገልግሎት እንዲድን ዘወትር ራሱን የመመርምር ብቻ ሳይሆን የውሳኔም ሕይወት ይኖረው ዘንድ ያስፈልጋል።

3) አገልጋይ በልቡ የሚመጣለትን አሳብና ምኞት ሁሉ እግዚአብሔር ከጠራው ጥሪ ጋር መስማማቱን ያረጋግጥ። የአንዳንዶች ጥሪ የግድ ሙሉ ጊዜን የሚያሰጥ ጥሪ ነው። የሌሎች ጥሪ ደግሞ የግድ ትምህርት ቤት ገብተው እውቀትን እንዲቀስሙ የሚገፋፋ ጥሪ ነው። ይህንን ሁሉ ለይቶ ማወቅ የአገልጋይ ሃላፊነት ነው። እግዚአብሔር ከፈቀደ የተማሩት ያላከናወኑትን ሥራ ባልተማሩት ማከናወን ይችላል። እርሱ ከወሰነ ሙሉ ጊዜአቸውን የሰጡ አገልጋዮች ያልሠሩትን ሥራ የተጣበበ ጊዜ ያላቸው ሰዎች እንዲሠሩት ጸጋውን ሊያበዛላቸው ይቻለዋል። ሁሉም ነገር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሲሆን ይሰምራል።

18

ሕብረት ከእግዚአብሔር ጋር

ምዕራፍ 19፥ 1– 41



ሉቃስ አጵሎስን በቆሮንቶስ በመተው ወደ ኤፌሶን የተሸጋገረውን የጳውሎስን ሁኔታ ይተርክ ጀመር። ጳውሎስ ከጥቂት ወራት በፊት ወደ ኤፌሶን በመጣበት ወቅት መልካም አቀባበል አጋጥሞት ስለነበር (18፥ 20) አሁን በሙሉ ልብ ወደ ኤፌሶን የመጣ ይመስላል። በኤፌሶንም ጉድለት ያለበት እምነትን የያዙ አንዳንድ ደቀ መዛሙርትን አገኘ። የጳውሎስ የመጀመሪያ ጥያቄው፦ «ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?» (ቁ. 2) የሚል ነበር። ከእነዚህ ደቀ መዛሙርት መልስ የምንረዳው መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆነ የማያውቁ አማኞች እንደነበሩ ነው። እነዚህ ደቀ መዛሙርት ምንም እንኳ በኢየሱስ የማመን ሁኔታ ቢታይባቸውም፥ ከዮሐንስ ጥምቀት ሌላ የሚያውቁት ነገር አልነበረም። ጳውሎስም፥ «ዮሐንስስ ከእርሱ በኋላ በሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ለሕዝብ እየተናገረ በንስሐ ጥምቀት አጠመቀ አላቸው» (ቁ.4)። እነርሱም በኢየሱስ ስም ተጠምቀው፥ በጳውሎስ እጅ መጫን አማካኝነት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ በልሳኖችም ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ። ይህ በዚህ ክፍል የተከሰተው የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ በበዓለ ኀምሳ ዕለት (2፥ 4)፥ በሰማርያና (8፥ 17)፥ እንዲሁም በቂሳርያ (10፥ 46) ከተከሰተው ልምምድ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ለአማኝ መሰረታዊ የሆነ የእግዚአብሔር አሠራር ነው።

ጳውሎስ ወደ ምኩራብ በመግባት ያስተምር የነበረውን እውነት አንዳንዶች ባለመቀበል የስድብን ቃል ቢናገሩም፥ ጳውሎስ ግን ደቀ መዛሙርትን በመለየት ሰው ሁሉ ወንጌልን እስኪሰማ ድረስ መናገሩን አላቆመም ነበር። ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈውን የመጀመሪያውን መልእክቱን በዚህ ጊዜ እንደጻፈው ይታመናል።

እግዚአብሔር በጳውሎስ ጨርቅ ለድውዮች ፈውስ በአጋንንት ለታሰሩት ደግሞ ነጻነትን ያጎናጽፍ በነበረበት በዚያን ወቅት፥

አጋንንትን እያወጡ የሚዞሩ አይሁድ በየቦታው ተሰማርተው ነበር። «ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ ስም» እያሉ አጋንንትን ለማውጣት የሞከሩትን አንዳንዶቹን አጋንንቱ፦ «ኢየሱስንስ አውቀዋለሁ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ እናንተስ እነማን ናችሁ?» በማለት አቆሰላቸው። የእግዚአብሔርም ፍርሃት በሰው ሁሉ ላይ ወደቀ። የጌታ የኢየሱስ ስምም ከመከበሩ የተነሳ አምነው ከነበሩት ሰዎች ብዙዎቹ በንስሐ፥ ከአስማተኞችም ጥቂት ያልሆኑ መጽሐፋቸውን በማቃጠል ይመጡ ነበር።

ጳውሎስ ያገለግሉት የነበሩትን ጢሞቴዎስንና ኤርስጦንን ወደ መቄዶንያ ልኮ በእስያ የቆየበት ወቅት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የላከውን ሁለተኛውን መልእክቱን የጻፈበት ጊዜ እንደሆነ ይታመናል። በዚያም የአርጤምስን ቤተ መቅደስ ምስሎች እየሠራ ለአንጥረኞች ብዙ ትርፍ ያስገኝ የነበረ ብር ሠሪው ድሜጥሮስ፥ በጳውሎስ ስብከት አማካኝነት የአንጥረኛነት ሥራቸውና የአርጤምስ መቅደስ ሊናቅ እንደሆነ አንጥረኞችን ሰብስቦ በማሳመን በቁጣ ሞላቸው። ይህቺ አርጤምስ በመባል የታወቀችው አምላካቸው፥ በብዙ ጡቶች የምትመሰል፥ ተፈጥሮን የምትገዛና ዘር የምትሰጥ አምላክ ነች ብለው የሚያምኑባት ጣያት ስትሆን፥ እርሷን የሚቃወም ማንም ሰው ቢኖር ራሱን ለአደጋ ያጋልጣል ብለው ያምናሉ።

ኤፌሶን የአርጤምስን አምልኮ ለረጅም ጊዜ ያስተናገደች የንግድ መናኸሪያ ነች። ስለዚህም የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት በሚል ጩኸት ከተማው በሙሉ ተደባለቀ። ብዙዎቹ ለምን እንደተሰበሰቡ ወደማያውቁበት ወደዚያ ትርምስምስ መካከል ለመግባት የጓጓው ጳውሎስ በወዳጆቹ ልመና ከአሳቡ ተገታ። የከተማው ጸሐፊም ሕዝቡን በማረጋጋት እነዚህ ክርስቲያኖች የሠሩት ወንጀል ካለ የሮም መንግሥት በደነገገው ጉባኤ እንደሚፈታ፥ አለበለዚያ ግን እነድሜጥሮስ የግል ጠብ ካላቸው ለራሳቸው እንዲሟገቱ በማብራራት ጉባኤውን በተነው።

የክርስትና እምነታችንን ከሌሎች እምነቶች ለየት ከሚያደርገው እውነት አንዱ የስላሴ ምስጢር ነው። ይህንን ምስጢር የሚያስተምሩንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች መዘርዘሩ ከዚህ መጽሐፍ ዓላማ ያለፈ ጥልቅ አሳብ በመሆኑ ያንን

ተወት በማድረግ ለጊዜው መማር የሚገባንን ብቻ ተምረን ለማለፍ እንሞክራለን።

ወደ ክርስቶስ የመጡ አዳዲስ አማኞች መማር ከሚገባቸው መሰረታዊ ነገሮች አንዱ የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስን እውነት ነው። አጀማመራቸው እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆኖ ሳለ ቀስ በቀስ የተወሰዱ የተለያዩ የስህተት ትምህርቶችን መንስኤ ስንመለከት ችግራቸው የስላሴን ምስጢር ካለመቀበል ወይም ከማጣመም እምብዛም ርቆ አናገኘውም። የተለያየ የስህተት ትምህርት በወገኖች መካከል እንዳይገባ ዋናው መከላከያችን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማስተማር ነው። «እንደ ስህተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕጻናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም» (ኤፌ. 4፥ 14)።

አንድ አገልጋይ የስላሴን ምስጢር ጠንቅቆ ማወቅ የሚገባው ለመሆኑ አከራካሪ ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን ከዚያም አልፎ አንድም ሦስትም ከሆነው አምላኩ ጋር እንከን የሌለው ሕብረት ይኖረው ዘንድ ይገባል። ይህንን ሕብረቱን በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ሊያጠናክር ይችላል? ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ ውስጥ የምንማረውን እንመልከት።

I. ሕብረት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር (19፥ 1–10)።

ጳውሎስ በኤፌሶን አማኞች፦ «ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?» ብሎ የጠየቃቸውን ሰዎች ሉቃስ፦ «ደቀ መዛሙርት» ይላቸዋል። አንድ ሰው ደቀ መዝሙር ለመሆን በመጀመሪያ በክርስቶስ አምኖ መዳን አለበት። እነዚህ በክርስቶስ አምነው የነበሩ ደቀ መዛሙርት ለጳውሎስ ጥያቄ የነበራቸው መልስ፦ «አልተቀበልንም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ስንኳ አልሰማንም» የሚል ነበር። የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሆነው መንፈስ ቅዱስን በጭራሽ አለማወቃቸው ቢያሳዝንም፥ ጥፋቱ የእነርሱ አይመስልም። ያልተማሩትን እንዴት አድርገው ያውቁታል? የእነርሱ የክርስትና ሁኔታ በንስሐ ላይ አቁሞ ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ሙላት አማካኝነት ሊመጣ የሚችለውን የድል ሕይወት ያስተዋወቃቸው አንድም አገልጋይ አልነበረም።

አንድ አገልጋይ በክርስቶስ የሚያላድጋቸውን ወገኖች በመንፈስ ቅዱስ መላት ሊመጣ የሚችለውን ልዩ የድልና የበረከት ሕይወት እንዲለማመዱ መንገድን ካልከፈተላቸው ትልቅ በረከትን ይነፍጋቸዋል። ከዚያም አልፎ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ መላት በሥልጣን ካልተሰበከና፥ ምእመናንም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያላቸውን ሕብረት እንዲያጠናክሩ ካልተበረታቱ ሕይወት ከንስሐ አያልፍም። ቃሉ፦ «መንፈስ ይመላችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ» (ኤፌ. 5፥ 18) እንደሚል፥ በክርስቶስ የሚያምን ክርስቲያን ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ መላት ተለይቶ ሕይወቱ ባዶ እንደሆነ መገንዘብ አለበት።

የመንፈስ ቅዱስ መላት የጎደለው ጸሎት ድርቀት ያጠቃው ጸሎት ነው። የመንፈስ ቅዱስ መላት የጎደለው አገልጋይ አገልግሎቱ ፈጽሞ የማይወጣ ዳገት ይሆንበታል። በአጠቃላይ አንድ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ መላት ካልተመላለሰ በሕይወቱ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ለማክበር እንደማይችል አገልጋዮች ሁሉ ሊያስተጋቡት የሚገባቸው አውነት ነው።

II. ሕብረት ከወልድ ጋር (19፥ 11–22)።

ጳውሎስ በኤፌሶን ላገኛቸው ደቀ መዛሙርት የመንፈስ ቅዱስን መላት ካስተዋወቀ በኋላ በእስያ ለሁለት ዓመት ወንጌልን ሰበከ። በአገልግሎቱም እግዚአብሔር የሚያስገርም ተአምራት ያደርግ ነበር። በዚያም አጋንንትን እያወጡ ከሚዞሩት አይሁድ መካከል አንዳንዶች፦ «ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ እናምላችኋለን እያሉ ክፉዎች መናፍስት ባሉባቸው ላይ የጌታን የኢየሱስን ስም ይጠሩባቸው ዘንድ ሞከሩ» (ቁ. 13)። በዚህ አድራጎት ተሰማርተው ከነበሩት መካከል የካህናት አለቃ የነበረው የአስቄዋ ሰባት ልጆች ይህ ተግባራቸው ዋጋ አስከፈላቸው። «ክፉው መንፈስ ግን መልሶ፦ ኢየሱስን አውቀዋለሁ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ እናንተስ እነማን ናችሁ? አላቸው። ክፉው መንፈስም ያለበት ሰው ዘለለባቸው ቆስለውም ከዚያ ቤት ዕራቁታቸውን እስኪሸሹ ድረስ በረታባቸው አሸነፋቸውም» (ቁ. 15–16)።

ኢየሱስ በአጋንንት ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው አምላክ ነው። ጳውሎስ ደግሞ ኢየሱስን በሚገባ ያወቀና የጠበቀ ሕብረት ያለው

የእግዚአብሔር ሰው ነው። ስለዚህም፥ አጋንንት በፊታቸው ሊቆሙ አይችሉም። የአስቄዋ ልጆችና መሰሎቻቸው ግን በግላቸው ከክርስቶስ ጋር ሕብረት የሌላቸው፥ ስለክርስቶስ በመስማት ብቻ ያወቁ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ስለ ክርስቶስ በእእምሮ እውቀት የበለጸጉ፥ የግል ሕብረት ግን ፈጽሞ የሌላቸው በመሆናቸው የክርስቶስን ስም በመጥራት አጋንንት እንዲታዘዙአቸው ማድረግ አልቻሉም።

ይህም እውነት ቤተ ክርስቲያን አጥብቃ ምእመኖቿን ልታስተምረው የሚገባት እውነት ነው። አንድ ክርስቲያን በሕይወቱ በአጋንንት ሥራ ላይ በሥልጣን ይመላለስ ዘንድ በጨለማ ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለውን ክርስቶስን በግሉ ያውቀውና ሥልጣኑንም ይገነዘብ ዘንድ ያስፈልገዋል። ክርስቲያን በሕይወቱ ከክርስቶስ ጋር ያለውን ሕብረት ሳይጠብቅ እንዳሻው እየተመላለሰ በአጋንንት ላይ የሚያደርገው ውጊያ ውጤታማነቱ አስተማማኝ አይደለም። ለዚህ ነው በአንድ ወቅት አጋንንትን ለማውጣት ሲደክሙ ውለው ያቃታቸውን ደቀ መዛምርቱን፦ «እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምን ነው?» ባሉት ጊዜ ጌታ፦ «ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው» ብሎ የመለሰላቸው (ማቴ. 17፥ 14–20)። ቤተ ክርስቲያን ምእመኖቿ በአጋንንት ሥራ ላይ በድል እንዲመላለሱ ከፈለገች፥ በሁሉም ላይ ሥልጣን ከተሰጠው ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን ሕብረት ያጠናክሩና ያስተካክሉ ዘንድ አብዝታ ማስተማር ይገባታል።

III. ሕብረት ከአብ ጋር (19፥ 23–41)።

በዚህ እያጠናን ባለነው ምዕራፍ ውስጥ፥ ጳውሎስ በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስን ያልተዋወቁ ደቀ መዛሙርት አግኝቶ አስተዋወቃቸው። ከዚያም በመቀጠል፥ የወልድ ነገር ያልገባቸው አይሁድ ከክርስቶስ ጋር የጠበቀ ሕብረት ያለው አማኝ ብቻ ሊያደርግ የሚቻለውን ነገር ለማድረግ ሲሞክሩና የአጋንንት መጫወቻ ሲሆኑ ተመለከትን። አሁን ደግሞ የምንመለከተው፥ ከአብ ጋር ሕብረት የሌላቸውን ሰዎች ባህሪይ ነው።

ጳውሎስ ገና በእስያ ሳለ ድሜጥሮስ የሚሉት የአርጤምስን ምስሎች በብር እየሠራ ያተርፍ የነበረ እንጥረኛ ሰዎች በክርስቶስ አምነው እርሱ የሚሠራውን የእማልክት ምስል መግዛታቸውን

እንዳያቆሙ፥ ትርፉም እንዳይጎድልበት ሲል ሕዝቡን ሁሉ አስተባብሮ በጳውሎስ ላይ አስነሳ። ከዚህም የተነሳ በነበረው ረብሻ መካከል ከነበሩት ሰዎች ብዙዎቹ ስለ ምን እንደተሰበሰቡ አላወቁም ነበር። እነዚህ ሰዎች ምንም ክርስቲያኖች ባይሆኑም እንኳ የእግዚአብሔር አብን ታላቅነትና በአማልክትና በፍጥረት ሁሉ ላይ ያለውን ሥልጣን በሌላ ተራ አምላክ መለወጣቸው ትምህርት ሰጥቶን የሚያልፍ ሁኔታ ነው።

ዛሬም በየአብያተ ክርስቲያናቱ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር አብን ታላቅነት ችላ እንዳይሉና በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል ጣያትን እንዳይተክል ሊመከሩ የሚያስፈልጋቸው እውነት ነው። ከእግዚአብሔር ይልቅ በገንዘብ የሚመኩ፥ ከአምላካቸው ይልቅ በሰው የሚደገፉ፥ ሁሉን ሊያደርግላቸው ከሚችለው ከኤልሻዳዩ ከእግዚአብሔር ይልቅ መፍትሄን ለማግኘት ወዲያና ወዲህ የሚሯሯጡ ቢኖሩ መመኪያቸውን ጌታ እግዚአብሔርን እንዲያደርጉ ይመከሩ። ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ከማጥፋት ይልቅ ከሚያዝናኗቸው ሰዎች ጋር በሚያዝናና ቦታ ማሳለፍ የሚቀናቸው ከዚህ ተግባራቸው እንዲታረሙ ሊገሰጹ ይገባል። ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ምእመኖቿ የቤተ ክርስቲያን መልእክት ግልጽ መሆን አለበት። አገልጋዮች ማንንም ሳይፈሩ በእግዚአብሔር ታላቅነት ላይ የሚነሳን ማንኛውንም አሳብ በፍቅር መገሰጽ አለባቸው። ነገር ግን ይህንን ማድረግ ይችሉ ዘንድ በመጀመሪያ የአገልጋዮችም ሕይወት ከተለያየ የስውር ጣኦት ነጻ እንዲወጣ ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነው። እንደሌሎች አስትንፋስ እንደሌላቸው ሰው ሠራሽ አማልክት ደባል አይፈልግም። ስለዚህም ክርስቲያን ግራና ቀኝ ሳይል በልቡ ዙፋን ላይ እግዚአብሔርን ብቻ በማንገሥ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ጤናማ ሕብረት ምንም ነገር እንዳይመርዝበት ሊጠነቀቅ ይገባዋል።

አንድ ክርስቲያን ሕይወቱ ሙሉና በበረከት የተትረፈረፈ እንዲሆን ከፈለገ ከእግዚአብሔር አብ፥ ከእግዚአብሔር ወልድና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር ሕብረቱን በማጠናከር፥ ይህንን ሕብረቱን የሚቀናቀኑትን ማናቸውም ነገሮች እየመነጠረ ማውጣት አለበት። ይህንንም ለማድረግ የሚከተሉት ነጥቦች መንደርደሪያ ይሆኑታል ብዬ አምናለሁ። ክርስቲያኖች በሙላት ከእግዚአብሔር ጋር

ሕብረት እንዳይኖራቸው ከሚያደርጉት በጣም ከተለመዱት ጠንቆች መካከል የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

1) ባለን መርካት። እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑት ሁሉ ከሙላቱ እንዲካፈሉ ፈቃዱ ነው። ስለዚህም ባለን ልምምድ መርካት አይገባንም። ለምሳሌ፥ እጁን ዘርግቶ እግዚአብሔርን በማምለክ የሚገኘውን የሙላት ሕይወት ያልተገነዘበ ሰው በንስሐ ከሚመጣው የእርካታ ሕይወት አያልፍም። እምን፥ በንስሐ የሚመጣ ልዩ በረከት አለ። ነገር ግን በዚያ ብቻ በመወሰን ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ፊት በቀረበ ጊዜ ሁሉ ከዚያ ያለፈ ልምምድ ውስጥ ለመግባት ራሱን ካልሰጠ ባለው ረክቶ ይቀመጣል። ክርስቲያን ዘወትር በንስሐ ብቻ ከማልቀስ አልፎ ከእምልኮ፥ ከዝማሬና ከመሳሰሉት ሊገኝ የሚችለውን እግዚአብሔርን የማወቅ ሕይወት ለመለማመድ መትጋት ያስፈልገዋል።

2) ዋጋን አለመክፈል። የእግዚአብሔር በረከት ነጻ ስጦታ ነው፥ ነገር ግን ዋጋ ያስከፍላል። ይህ ራሱን በራሱ የሚቃረን አባባል ይመስላል፥ ነገር ግን አይደለም። እግዚአብሔር እኛን ልጆቹን ይባርከን ዘንድ ዋጋ እንድንከፍል ይፈልጋል። ያንንም ዋጋ ለመክፈል እንችል ዘንድ ጸጋው የሚመጣው ከእርሱ ስለሆነና በራሳችን የምንከፍለው ምንም ስለሌለን በረከቱና ስጦታው ነጻ ሆነ ማለት ነው። ከእግዚአብሔር አብ ጋር የበለጠ ሕብረት ማድረግ ዋጋን ይጠይቃል። በሰውና በተለያዩ መልስን በፍጥነት ሊሰጡን በሚችሉ ሁኔታዎች ተተግኖ ከማለፍ ይልቅ በእግዚአብሔር ታምኖና የማይታይን ተስፋ ጨብጦ በእምነት መጓዝ ዋጋ ያስከፍላል። እግዚአብሔር ወልድን በቅርብ አውቀነው በሕይወታችን ድንቅን እንዲሠራ ከፈለግን ዋጋ መክፈል አለብን። በጸሎት መጋደሉና በክርስቶስ ያለንን ሥልጣን ለማወቅ ቃሉን በማንበብ መትጋቱ የጊዜና የእንቅልፍ፥ ሌሎችንም የሚያጓጉ ጉዳዮችን የመተው ዋጋን ያስከፍላል። በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሙላት መመላለስ ዋጋ ያስከፍላል፥ ተቃዋሚዎችን ያስነሳል። መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን በሙላት ሲሠራ ማየት ሥጋም ሆነ ሰይጣን አይሆንላቸውምና ይቃወመሩናል። ዋጋ ሳይከፈል በረከት የለም።

3) ተጣምሞ ማደግ። ይህ ዓይነቱ ጠንቅ ብዙዎችን እንቆ ያስቀረ አደገኛ መሰናክል ነው። አንድ ሰው በክርስትና ሕይወቱ

ከጅማሬው እንደ እግዚአብሔር ቃል ያልሆነን ነገር ተምሮ ካደገ፥ ከዚያ ዓይነቱ ልምምድ መላቀቅ በጣም ያስቸግረዋል። በዚያም ልምምዱ ብዙ ከቆየ በኋላ እውነቱን መስማት በሚጀምርበት ጊዜ ግራ መጋባት ይጀምራል። ይህንን ዓይነቱን ችግር በሁለት መንገድ መፍታት ይቻላል። በመጀመሪያ፥ ክርስቲያኖች በባህል ክርስትናና በሰው ልምምድ ተመርተው ምንም ዓይነት እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት ነገሩን በእግዚአብሔር ቃል የመመርመር ሕይወትን መለማመድ ያሻቸዋል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፥ ማንኛውም ክርስቲያን ቀደም ብሎ የተማረው የተጣመመ እውነት ካለ፦ «እኔ የማምነው በዚህ መልኩ ነበር አሁን ግን ጌታ አስተማረኝ» በማለት ወደ እውነት ቢመለስ ትልቅ የእድገት ምልክት እንጂ የሚያሳፍር እርምጃ አይደለም።

19

መጥረቢያህን ሳለው

ምዕራፍ 20፥ 1–21፥ 16



በኤፌሶን የነበረው ሁከት ካለፈ በኋላ ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ ሄደ። በዚያም አገር አልፎ ወደ ግሪክ አገር በመውጣት ሦስት ወር ተቀመጠ። ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች መልዕክቱን የጻፈው በዚህን ጊዜ በቆሮንቶስ ከተማ ሆኖ እንደነበር ይታመናል። ከዚያም ወደ ሶርያ በመርከብ ለመሄድ የነበረውን እቅድ በአይሁድ ሴራ አማካኝነት በመቀየር በመቄዶንያ አልፎ ለመሄድ ከፊልጵስዩስ በመርከብ ተሳፈረ። የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ሉቃስ እንደገና ከጳውሎስ የአገልግሎት ቡድን ጋር በመደባለቁ፦ «እኛ» በማለት ትረካውን ይቀጥላል።

በዕለተ እሁድ እንጀራን ለመቁረስ በተሰበሰቡበት በጢሮአደ ጳውሎስ ነገሩን በማርዘሙ ምክንያት በመስኮት ተቀምጦ የነበረው አውጤኪስ አንቀላፍቶ ወደቀ። የህክምና አዋቂው ሉቃስ እንደመሰከረው፥ ይህ ሰው ሞቶ ነበር። እግዚአብሔር ግን በጳውሎስ ተጠቅሞ ከሞት አስነሳው።

ጢሮአዳን ከለቀቁ በኋላ ጳውሎስ በእግሩ ለመጓዝ በመውደዱ፥ ሉቃስና አብረውት ያሉት ሰዎች በመርከብ ቀድመውት በመሄድ በአሶን ተገናኙት። ጳውሎስ ያንን አካባቢ ለመልቀቅ ቸኩሎ ነበርና ወደ ኤፌሶን ከመሄድ ይልቅ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ከኤፌሶን እርሱ ወደ አለበት ወደ ሚሊጢን ይመጡ ዘንድ ልኮ አስጠራቸው። ለሽማግሌዎቹ የተናገራቸው ቃል በሦስት ይከፈላል። በመጀመሪያ፥ በእነርሱ መካከል የነበረው አገልግሎቱ መልካምና እንከን የማይወጣለት እንደነበር በሚገባ አስረዳቸው (19–27)። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን አደራ በሚገባ እንዲወጡ አስጠነቀቃቸው (28–31)። በመጨረሻም፥ በመልካም ምክር ካበረታታቸው በኋላ ሰጸጋው ቃል አደራ በመስጠት በጸሎት አብሯቸው

ወደቀ (32–38)። «ከእንግዲህ ፊቴን አታዩም ስላሳቸው ነገር እጅግ አዘኑ። እስከ መርከብም ድረስ ሸኙት።»

በመርከብ ተጉዘው ወደ ጢሮስ በደረሱ ጊዜ መርከቡ ሸክሙን እስኪያራግፍ በዚያ ካገኟቸው ደቀ መዛሙርት ጋር ሰባት ቀን ተቀመጡ። የጢሮስ ወገኖች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይወጣ ቢመክሩትም፥ እርሱ ግን ከመሄድ አልተመለሰም ነበር። ስለዚህም በጸሎት ተሰነባብተው ተለያዩ።

እነ ጳውሎስ በጉዞአቸው፥ አንድ ቀን በእካ ከወንድሞች ጋር ካሳለፉ በኋላ ወደ ቂሳርያ በመውጣት ትንቢት የሚናገሩ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች ባሉት በወንጌላዊው በፊልጶስ ቤት በመግባት አያሌ ቀን ተቀመጡ። በዚያን ጊዜ ነበር ነብዩ አጋቦስ ከይሁዳ በመምጣት በኢየሩሳሌም ጳውሎስን ስለሚጠብቀው መከራ ያመለከተው። አሁንም ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ከመሄድ ወደ ኋላ አላለም ነበር። በዚህም ውሳኔው መሰረት ወደ ኢየሩሳሌም በመውጣት ወደ ምናሶን ቤት ተመርተው ገቡ። በዚህም ጳውሎስ ሦስተኛውን የሚስዮናዊ ጉዞውን አጠናቀቀ።

አንተ ለማለት የምትፈልገውን አሳብ እንድትናገር በፍጹም ጊዜ ሳይሰጥህ ካለማቋረጥ የሚያወራ ሰው አጋጥሞህ ያውቃል? እንዲህ ዓይነቱ ሰው ሲያወራ ለሌሎች እድል እንደማይሰጥ የሚነግረው ሰው ጠላቱ ነው። ብዙ የሚያወራ ሰው ብዙ እንደሚያወራ ሲነገረው ደስ ስለማይለው፥ የሚመክረውን ሰው ንግግር በማቋረጥ ብዙ እንደማያወራ ለማሳመን ሲል ብዙ ያወራል። ከሌሎች የማይሰማ ሰው መጥረቢያውን ለመሳል ፈቃደኝነት የሌለውን በደነዝ መጥረቢያ ሲታገል ጊዜውን የሚያባክንን ሰው ይመስላል። ቢያስተውል፥ ቁጭ ብሎ መጥረቢያውን ለመሳል ከሚያጠፋው ጊዜ ይልቅ በደነዝ መጥረቢያ ሲታገል የሚያሳልፈው ጊዜ እንደሚበልጥ ይረዳል። ከሌሎች የማይሰማ ሰው መኪናውን አቁሞ ነዳጅ ለመቅዳት ጊዜ የሌለውን ሰው ይመስላል። ነዳጅ ለመቅዳት ከሚያጠፋው ጊዜ ይልቅ በግማሽ መንገድ ላይ ነዳጅ አልቆበት በመንከራተት የሚያጠፋው ጊዜ ይበልጣል። «ቃልን የሚያዳምጥ መልካም ነገርን ያገኛል» (ምሳ. 16፥ 20)

ከሌሎች መስማት እንዴት የተባረከ ነገር ነው! ከሌሎች በመስማት ሰዎች እኛ የሌለንበትን ጊዜና ቦታ ጠብቀው ስለ እኛ የሚያወሩብንን አጉል ባህሪያችንን እናስተካክላለን። ከሌሎች በመስማት በፈታችን ካለው ወጥመድ እናመልጣለን። ከሌሎች በመስማት ብዙ ያላወቅናቸውን ነገሮች እናውቃለን። ከሁሉም በላይ፥ ከሌሎች በመስማት ተናጋሪዎቹ የሚያደምጣቸው ያጡበትን የውስጥ ችግራቸውን አውጥተውና ዝክዝክ አድርገው ነግረውን እንዲተነፍሱ እናደርጋቸዋለን። ከሌሎች በመስማት ትርፍ እንጂ ኪሳራ የለም። «ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ... ይሁን» (ያዕ. 1፥ 19)።

ከሰዎች አለማዳመጥ የሚያስከትለው ችግር ክርስቲያንና ዓለማዊ አይልም። በተለይም ይህ መልካም ባህሪይ ከአገልጋይ ሕይወት በሚርቅበት ጊዜ ትልቅ የአገልግሎት መሰናክል ሊሆን ይችላል። ስለዚህም፥ አገልጋይ ሊያስብበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ከዚህ በመቀጠል የምንመለከተው፥ አገልጋይ በምን አካባቢ አጥብቆ የማዳመጥ ባህሪውን ማዳበር እንደሚገባው ነው።

I. ስለ አገልግሎትህ መስማት (20፥ 1–16)።

ጳውሎስ በጢሮአዳ በነበረበት ወቅት እንጆራ ለመቁረስ ተሰብስበው ለነበሩት ወገኖች ንግግር ሲያደርግ ነገሩን ማስረዘሙን ሉቃስ ሳይሸሽግ ጽፏል (ቁ. 7)። በዚያን ጊዜ ነበር አውጢኪስ የሚሉት ሰው እንቅልፍ ተጫጭኖት ከመስኮት ወድቆ የሞተው። የጳውሎስ ንግግር ምን ያህል ቢረዝም ይሆን ሉቃስ «ጎበዝ» ብሎ የሚጠራውን ጠንካራ ሰው አሸንፎ በእንቅልፍ የጣለው? ጳውሎስ መልእክትን ማስረዘሙ የዘወትር ተግባሩ መሆኑን ባናውቅም፥ ከተከሰተው ሁኔታ የምንማረው እውነት አለን።

ከዚህ ታሪክ እንድንማር የምፈልገውን እውነት በጥያቄ መልክ ላቅርበው። ጳውሎስ በዚያን ምሽት ሲናገር ንግግሩን እያስረዘመ እንዳለ የመከረው ሰው ይኖር ይሆን? የመከረው ሰው ካለስ ጳውሎስ ሁኔታውን ለማረም ፈቃደኝነት ይኖረው ይሆን? የጳውሎስን ታሪክ ለጊዜው ቆም ላድርግና ለአንባቢዬ እንዳንድ ጥያቄዎችን ልሰንዝር። በአገልግሎትህ

ሌሎች የሚያዩት ለአንተ ግን ግልጽ ያልሆነ ድካም ሊኖርብህ እንደሚችል ታውቃለህ? ወገኖች ይህንን ድካምህን በወንድምነት በግልጽ ቢነግሩህ ደስ ይልሃል ወይስ ትከፋለህ? ምናልባት ስትሰብክና ስታስተምር ሳታስተውለው ነገር ትደጋግምና ታበዛ ይሆናል። ምናልባት ስትዘምር ድምጽህ አብረውህ ከሚዘምሩት አገልጋዮች ተለይቶ ካለልክ እየወጣ የዜማውን ቃና እየረበሸ ይሆናል። በአገልጋዮች ስብሰባ ላይ ከምትሰጠው አላብ ብዛትና ርዝመት የተነሳ ለሌሎች እድል መስጠት ተስኖህ ይሆን? እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ድካሞች ቢኖሩብህና ወገኖችህ ቀርበው ሊመክሩህ ቢወዱ ምን ያህል ፈቃደኛ ነህ? ወገኖች ያለብህን ችግር እንዲነግሩህ የሚጋብዝ ሕይወት ይኑርህ።



አንዳዶች በአገልግሎታቸው ላይ ያለውን ጉድለት ሰዎች ሊነግሩአቸው ሲሹ ከመስማት አሻፈረኝ ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ሰዎች በእነርሱ ላይ ምን አስተሳሰብ እንዳላቸው ለማወቅ በመጨነቅ ጊዜአቸውን ያጠፋሉ። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። ስላለብህ ድካም ከሰው ምክር መቀበል ትልቅ ማስተዋል እንደሆነ አትዘንጋ። ነገር ግን ቁም ነገሩ ያንተ ሕይወት በበለጠ ተስተካክሎ ጌታህ በአንተ መክበሩ እንጂ ሰዎች በአንተ ላይ ያላቸው ግምት አለመሆኑን አትርሳ።

II. ከወገኖች ጋር ስላለህ የየዕለት ኑሮ መስማት (20፥ 17–38)።

ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ከመሄዱ በፊት የቤተ ክርስቲያን ሽማግልዎችን ሰብስቦ በተናገረበት ወቅት፥ ከእነርሱ ጋር የኖረበትን ሦስት ዓመታት መለስ ብሎ በመመልከት የነበረው እርምጃ እንከን የማይወጣለት መሆኑን በድፍረት ነበር የተናገረው። «ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም» (ቁ. 33) የሚለውም ቃሉ ይህንኑ የሚያስረግጥ ነው። በኑሮውም ካላያቸው ምሳሌነት አንዱ፥ ከመቀበል ይልቅ መስጠት ትልቅ የበረከት ምንጭ እንደሆነ ነው (ቁ.35)።

አገልጋይ ከክርስቲያኖች ጋር የሚገናኘው በአገልግሎት ብቻ ላይሆን በየዕለት ኑሮውም በብዙ መንገድ ይገናኛል። በዚህም ዕለት በዕለት ከክርስቲያኖች ጋር ባለው ግንኙነቱ ምንም እንኳ በማስተዋል

ቢመላለስ፥ ትንሽም ብትሆን እንከን እንደሚገኝበት መገንዘብ አለበት። የአገልጋይ የመጀመሪያ መመሪያው ዘወትር ከሌሎች ከመቀበል ይልቅ መስጠት ሊሆን ይገባዋል። ሌሎች ጊዜአቸውን እንዲሰውልን ከመጠበቃችን በፊት እኛ ያንኑ ብናደርግ መልካም እናደርጋለን። ሌሎች ፍቅር እንዲሰጡን ከመጠበቅ ከእኛ የሚጠበቅብንን ፍቅር ብንሰግላቸው ትልቅ ማስተዋል ነው።

ጥቂት ነገሮችን በምሳሌነት ብንመለከት እንድንማር የፈለኩትን ነጥብ በበለጠ መረዳት እንችላለን። ለምሳሌ፥ አገልጋይ የሚያውቃቸው ወገኖች በሙሉ በደረሰባቸው ሃዘን ላይ ተገኝቶ ቢያጽናናቸው፥ በደስታቸው ጊዜ ደግሞ ጥሪያቸውን አክብሮ ቢገኝላቸው ደስታው ነው። ነገር ግን ሁሉም ጋር ለመገኘት ሳያደርሰው ይችላል። ስለዚህም መድረስ የሚችለው ቦታ ደርሶ ያልቻለውን ከመተው በቀር ሌላ ምርጫ የለውም። ታዲያ አገልጋይ ይህንን እውነት እያወቀ የእርሱ ተራ ደርሶ ከሰዎች መጽናናትን በሚጠብቅበት ጊዜ፥ እንዲሁም ወገኖች በደስታው ላይ እንዲገኙ በሚመኝበት ጊዜ ባሰባቸው የኑሮ ሁኔታ ምክንያት በጎኑ ያልተገኙትን ወገኖች እየቆጠረ በልቡ ቅሬታን መያዝ የለበትም። ይህ በምሳሌነት የጠቀስኩት ጉዳይ ብዙም ልንጨነቅበት የሚገባን ሁኔታ አይመስልም። ነገር ግን ለዚህ ከንቱ ድካም ራሳቸውን የሰጡትን ወገኖች ልብ ሲያቃቅር ተገኝቷል። የወገኖች ልብ ሲቃቃር ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ያዝናል። መንፈስ ቅዱስ ሲያዝን በመካከላችን መሥራት ይሳነዋል። ታዲያ ትልቅ በረከት አመለጠን ማለት አይደለምን? ይህ ዓይነቱ ድካም የወገኖችን ሕብረት በየጊዜው ያናጋ ሁኔታ ነውና አገልጋይ ይህንን የመሳሰለውን ቀስ በቀስ ለአገልግሎቱ ጠንቅ ሊሆን የሚችል ባህሪውን በሰዎች ምክር ብርታት ማስወገድ አለበት።

III. ጌታ በሌሎች የሚናገርህን መስማት (21፥ 1–16)።

ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቆርጦ በተነሳበት መጠን መንፈስ ቅዱስ በባሪያዎቹ በኢየሩሳሌም እስራት እንደሚቆየው ደጋግሞ ነግሮታል። አንዳንዶቹም በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድም መክረውታል (ቁ. 4)። ይህንኑ መልእክት ከነብዩ ከአጋቦስም ደግሞ ሰምቶአል። ጳውሎስን ግን በተለያዩ የእግዚአብሔር

ሰዎች እማካኝነት የመጣለት ድምጽ ወደ ኢየሩሳሌም ከመሄድ አልመለሰውም ነበር። ከዚያን ጊዜ እንስቶ እስከ አሁን ድረስ የጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ የጌታ ፈቃድ ይሁንና አይሁን አከራካሪ ጉዳይ ነው።

ከተከሰተው ሁኔታ የምንወስደው ቁም ነገር ቢኖር የሚከተለው ነው። እግዚአብሔር በአገልጋዮቹ ሊናገረን ቢወድ ልባችን ምን ያህል ክፍት ነው? ጌታ በሰዎች መልእክትን ወደ እኛ የሚያመጣበት ብዙ ምክንያቶች አሉት። እንዳንድ ጊዜ ለማድረግ ቆርጠን የተነሳንለት ነገር አሳባችንን ወጥሮ ከመያዙ የተነሳ ጌታን ለማዳመጥ ስለሚሳነን እግዚአብሔር የግድ ሌሎችን ልኮ ሊናገረን ይፈቅዳል። ሌላ ጊዜ ደግሞ በሕይወታችን የምንለማመደው ኃጢአት ካለ ከጌታ እንዳንሰማ ስለሚጋርደን ጌታ ለእኛ ለማስተላለፍ የፈለገውን መልእክት የግድ በሰዎች ማስተላለፍ ያስፈልገዋል። ስለዚህም ዘወትር ጌታ በሰዎች ሊናገረን ለሚወደው ነገር ክፍት እንድንሆንለት ይፈልጋል።

ይህ ችግር ብዙውን ጊዜ ለሌሎች ከጌታ መልእክትን የማስተላለፍ ልምምድ ያላቸውን አገልጋዮች የሚያጠቃ ችግር ነውና እነዚህ አገልጋዮች የበለጠ ማስተዋል ይጠበቅባቸዋል። ሁል ጊዜ፦ «ለሌሎች ምን መልእክት አለኝ» የሚል አሳብ ብቻ ካለንና፦ «ጌታ ዛሬ በሌሎች ምን ይናገረኝ ይሆን?» ብለን ዝም የምንልባቸው ጊዜአቶች ከሌሉን ብዙ በረከት እምልጦናል።



እንዳንዶች በሌሎች አገልጋዮች ከጌታ የሚመጣላቸውን መልእክት ላለመቀበል ልባቸውን እደንድነው ይታያሉ። ሌሎች ደግሞ በእግዚአብሔር ስም የተነገረን ነገር ሁሉ በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት በፍጹም ሳይመረምሩ እሜን ብለው ይቀበላሉ። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። በሰዎች ሊመጣልህ ለሚችለው የእግዚአብሔር መልእክት ዘወትር ዝግጁ የመሆንህን ያህል፥ ሁሉን ነገር በቃሉ የምትመረምር አገልጋይ ለመሆን ትጋ።

ከሌሎች መስማት አለብን የሚለውን አሳብ ብቻ ተመልክተን ያንን እንዳናደርግ የሚዋጉንን ነገሮች ሳንጠቅስ ብናልፍ ትምህርታችን ጎዶሎ ይሆንብናል። በዚህ ዘመን ያለን አገልጋዮች ለምን ከሌሎች መስማት ይሳነናል? የሚከተሉትን ነጥቦች እንመልከት።

1) ሁሉን ነገር ያወቅን ሲመስለን። አገልጋይ ራሱን በእካባቢው ካሉት አገልጋዮች የተሻለ አድርጎ በሚያስብበት ጊዜ፥ ሌሎች ከእርሱ እንዲሰሙ እንጂ እርሱ ከሌሎች መስማትን አይፈልግም። ሰባኪ ስብከቱን እስከሚጨርስ ድረስ ሌሎች እንዲሰሙት የመፈለጉን ያህል እርሱም ሌሎች ሲሰብኩ ጸጥ ብሎ ያዳምጥ ዘንድ ይገባዋል። ጌታ ይህንን እንድናገር በልቤ አሳስቦኛል የሚልም ሰው ሌሎች መልእክቱን እንዲሰሙት የመፈለጉን ያህል እርሱም ከሌሎች ለመስማት ዝቅ ይበል። ዘማሪውም ሲዘምር ተሰሚነትን እንደሚናፍቅ ሁሉ እርሱም ሌሎች ሲዘምሩ ለመስማት ቁጭ ይበል። መካሪውም እንደመከረ ምክርን ለመቀበል ልቡን ይክፈት። እኛ ብቻ ሁሉን ያወቅን አይምሰለን። ሁል ጊዜ በልምምድም ሆነ በእውቀት የሚበልጡን ሰዎች እንዳሉ እንዘንጋ።

2) ፍርሃት። አንዳንድ አገልጋዮች ሰዎች በእነርሱ ላይ ያዩትን ድካም ሲነግሯቸው የፈረዱባቸውና ፈጽመው የናቋቸው ስለሚመስላቸው ለሰዎች እድልን አይሰጡም። በተለይም ቀደም ሲል፦ «ከጌታ የመጣ መልእክት ነው» በሚል ሳቢያ የቆሰሉ አገልጋዮች ይህ ፍርሃት ያጠቃቸዋል። እንዲህ ዓይነቱ ቁስል ፈጥኖ ሊፈወስ ይገባዋል።

3) ግትረኛነት። «ጌታ የመራኝን እስካደረግሁኝ ድረስ ሰው ስለሚለው አይገደኝም» በሚል ጭፍንነት የሚራመድ አገልጋይ ራሱን ለጥፋት ከመዳረግ አያልፍም። አገልጋይ ከጌታ አገልጋዮች ጋር አብሮ የሚሠራ ትሁት ሰው ይሆን ዘንድ ይገባዋል እንጂ ግትረኛነት ከእርሱ አይጠበቅም።

4) የሰዎችን ሁኔታ አለመለየት። አገልጋይ ምንም ዓይነት ግሩም ሰው ቢሆን፥ እርሱነቱን የማይወዱና የማይቀበሉት ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ማስታወስ አለበት። ስለዚህም በፍቅር ሊመክሩት ወደ እርሱ በሚመጡትና ዘወትር በእርሱ ላይ ለመፍረድ በማይተኙ ሰዎች መካከል ለመለየት ይጣጣር።

20

ለፈተና ሁሉ የተዘጋጀህ ሁን
(ክፍል አንድ)
ምዕራፍ 21፥17–23፥35



በብዙ ምክር ተነግሮት ወደ ኋላ ያላለው ጳውሎስ እንደተመኘው ወደ ኢየሩሳሌም ደረሰ። በኢየሩሳሌም የነበሩ ወንድሞች በደስታ ከተቀበሉአቸውና የጳውሎስን ምስክርነት ካደመጡ በኋላ እነርሱም ለመናገር የፈለጉትን አሳብ ገለጹ። በኢየሩሳሌም ባሱት አይሁድ ዘንድ ብዙም ሰላም የሰፈነ አይመስልም። ከአይሁድ ወገን የሆኑት አማኞች ጳውሎስ ወደ ጌታ የመጡትን አሕዛብ እንዳይገረዙ ያስተምራል ብለው ከሰሱት። በክርስቶስ አምነው የነበሩት አሕዛብ ማድረግ ያለባቸው ነገር ሁሉ ቀደም ሲል በኢየሩሳሌሙ ጉባኤ በተላለፈው ውሳኔ መሰረት በጽሑፍ ተገልጸአል። አሁን ግን ከአይሁድ ወገን የሆኑት ክርስቲያኖች ጳውሎስ የሙሴን ሕግ ላለመቃወሙ ማረጋገጫን ፈለጉ። ስለዚህም በኢየሩሳሌም ያሉ በማስተዋል የተሞሉ ወገኖች ነገሩን ለማብረድ ጳውሎስ ማድረግ ያለበትን አዘጋጅተው ጠበቁት። እቅዳቸው ይህንን ይመስል ነበር። ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ከነበሩ ስሰት ከነበረባቸው አራት ሰዎች ጋር የመንጻትን ስርአት እንዲፈጽምና ስለ እያንዳንዳቸው መስዋእትን እንዲያቀርቡ አሳሰቡት። በዚህም አድራጎቱ ሲከሰሱት የነበሩት ሁሉ በእርግጥም ጳውሎስ ሕጉን እየጠበቀ በሥርዓት የሚመላለስ ሰው እንደሆነ ያውቃሉ። ጳውሎስም ከወገኖቹ የመጣለትን ምክር በመቀበል የተባለውን በሚገባ ፈጸመ።

ጳውሎስ የመንጻት ጊዜውን በማጠናቀቅ ላይ ሳለ፥ ከእስያ የመጡ አይሁድ በጳውሎስ ላይ ተነሱ። የኤፌሶኑን ጥሮፊሞስን ወደ መቅደስ አገባው የሚል ሰበብ አመጡ እንጂ ይህንን ምክንያት ባይሰጡ ኖሮ ጳውሎስን የሚከሱበት ሌላ መንገድ መፈለጋቸው አይቀርም ነበር። በአይሁድ እምነት መሰረት አሕዛብ ወደ መቅደሱ የውጪኛው ክፍል እንጂ ወደ ውስጥ ይገቡ ዘንድ አይፈቀድላቸውም ነበር። በዚህም ሰበብ የጳውሎስ የመከራ ዘመን ጀመረ።

ጳውሎስን ይዘው ሊገድሉት በፈለጉ ጊዜ ወሬው ለሮፍራው ሻለቃ በመድረሱ በታላቅ ሮፍራ ደርሶ ጳውሎስን ከመደብደብ አስጣላቸው። እውነቱን ለማወቅ የጓጓው ሻለቃ ከግፊያው መካከል አስወጥቶ ጳውሎስን ወሰደው። ጳውሎስም ራሱን ለሻለቃው ካስተዋወቀና ለሕዝቡ ያለውን ምላሽ እንዲናገር ፈቃድን ከተቀበለ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ።

በመጀመሪያ ጳውሎስ እውነተኛ አይሁድ ለመሆኑ የማረጋገጫ ቃላትን ሰነዘረ። የትውልድ ስፍራው፥ ትምህርቱ፥ ለአይሁድ ሕግ ያለው ቅንአትና ክርስቲያኖችን ማሳደዱ ለዚህ ይመሰክሩለታል። በመቀጠልም፥ በደማስቆ መንገድ ሳለ ጌታ እንዴት እንደተገለጸለት ከተረከ በኋላ፥ ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሰ በኋላ በመቅደስ የመጣለትን መገለጥ አብራራ። ይህ በኢየሩሳሌም ተሰጠኝ የሚለው መገለጥ በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አልተገለጸም።

አሕዛብ የሚለውን ቃል ከጳውሎስ አንደበት ሲወጣ የሰሙት አይሁድ መታገስ ስላቃታቸው፦ «አስወግደው» እያሉ በታላቅ ድምጽ በሮኹ ጊዜ፥ የሻለቃው ምክንያቱን በይበልጥ ለማወቅ ስለወደደ እየገረፉ እንዲመረምሩት አዘዘ። ለመግረፍ በጠፍር በገተሩት ጊዜ ነበር ጳውሎስ ከዚህ ሁሉ ክፉ አድራጎት ነጻ ሊያወጣው የሚችለውን የሮም ዜግነቱን አስመርኩ፡ አቤቱታ ያቀረበው። ሻለቃውም በመፍራት በካህናት አለቆች ፊት አቆመው።

በካህናት አለቆች ፊት የነበረው ጉባኤ እጅግ አስቸጋሪ ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ሕሊናው በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ እንደሆነ በማስረገጥ ንግግሩን በመጀመር ሳለ ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ የጳውሎስ አፍ ይመታ ዘንድ አዘዘ። አንዳንዶች ጳውሎስ በሊቀ ካህናቱ ላይ የድፍረት ቃል የተናገረው የዓይን ችግር ስለነበረበት ሊቀ ካህናት መሆኑን ሳያውቅ ነው ብለው ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ ጳውሎስ የተናገረውን የሚያውቅ እንደነበረና የተናገረውም ነገር ምንም ስህተት የሌለበት እንደነበረ ያምናሉ።

ጳውሎስ ዘዴውን በመለወጥ፥ የራሱን ፈሪሳዊነት በመግለጽ፥ የተፈረደበት ስለ ተስፋና ስለ ሙታን መነሳት መሆኑን ለማስታወቅ ጮኸ። ይህ አነጋገሩ በተስፋና በሙታን መነሳት በሚያምኑት በፈሪሳውያንና በእነዚህ ነገሮች ፈጽሞ በማያምኑት በሰዱቃውያን መካከል

መከፋፈልን ፈጠረ። ክርክሩ ሲበረታና የጳውሎስ ደህንነት ሲያሰጋ ሻለቃው ጳውሎስን ወደ ሰፈሩ አስወሰደው።

በነጋታውም ጳውሎስ ሌሊቱን በተገለጸለት በእግዚአብሔር ተበረታትቶ ሲነሳ፥ ከአርባ የሚበልጡ አይሁድ ጳውሎስን ሳይገድሉ እንዳይበሉ በእልህ ተነሱ። ለዚህም ተንኮላቸው መንገድን ሲቀይሉ ሳለ የጳውሎስ የእህት ልጅ ስለሰማ፥ በመጀመሪያ ለጳውሎስ ከዚያም ለሻለቃው ነገሩን ገለጸ። ሻለቃውም ብላቴናውን ምስጢሩን እንዲጠብቅ ካዘዘው በኋላ ጳውሎስን በጦር አላጅቦ ወደ ፊሊክስ ከደብዳቤ ጋር ላከው። የጳውሎስን ንጹህነት ከደብዳቤው የተገነዘበው ፊሊክስ የጳውሎስ ከሳሾች እስኪመጡ ድረስ በሄሮድስ ግቢ ውስጥ እንዲጠበቅ አዘዘ።



የአንድን አገልጋይ በፈተና መጽናት የሚወስነው የፈተናው ብርታት ሳይሆን የአገልጋዩ አያያዝ ነው። ለዚህ ነው የእግዚአብሔር ጸጋ ለሁለቱም ዝግጁ ሆኖ ሳለ አንዱን የጣለ ፈተና ሌላኛውን የሚያልፈው። አገልጋይ በፈተና ውስጥ በሚያልፍበት ወቅት የሚያደርገውን በጥንቃቄ ማወቅ አለበት። እውነተኛ ክርስትና ካለ ፈተና አለ። ፈተና የሌለበት ክርስትና እድገት የሌለው ክርስትና ነው። እንደውም አገልጋይ እምነቱ ሲፈተን ደስ ሊሰኝ ይገባዋል። ያዕቆብም እንዲሁ ይመክረናል፦ «ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግስትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት» (ያዕ. 1፥2–3)።

አገልጋይ ለሚመጣበት ፈተና የሚኖረው ምላሽ እንደፈተናው ዓይነት መለያየቱ ግልጽ ነው። ሆኖም፥ ምንም ዓይነት ምላሽ ቢኖረውም አንኳ ከጌታ ተለይቶ የትም መድረስ አይችልም። በዚህ ክፍል የምንመለከተው አሳብ እግዚአብሔር በፈተና ለተጠነቁት አገልጋዮቹ ያዘጋጀውን ጸጋ ነው። ከዚህ በመቀጠል እነዚህን ነጥቦች እንመልከት።

I. በፈተና ጊዜ ድፍረት (21፥17–22፥21)።

ጳውሎስ የወገኖቹን ምክር ተቀብሎ ሰዎችን ይዞ የመንጻቱን ስርአት በማጠናቀቅ ላይ እንዳለ ከእስያ የመጡ አይሁድ ስደት አስነስተውበት በሻለቃው ፊት ለመቅረብ በቃ። በዚያም በተሰበሰበው

ሕዝብ ሁሉ ፊት ከጌታ ስለተቀበለው ጥሪ ያደረገው ንግግር ታላቅ ግልጽነት የተሞላ ነበር። እንዲህ ዓይነቱ ድፍረት የሚመጣው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው።

እንደ አገልጋዮች ከዚህ የምንማረው ምስጢር ቢኖር፥ ፈተና ዙሪያችንን ዘግቶ በሚያስጨንቀን ጊዜ የቆምንለትን ዓላማችንን በግልጽነት ለመናገር ድፍረት ይኖረን ዘንድ እግዚአብሔር እንደሚያስችለን ነው። አገልጋይ ተቃዋሚዎች ስለበዙበት የበለጠ ድፍረት ሊኖረው እንጂ ሊያፍር አይገባውም። አንባቱን ቀና አድርጎ የተቃዋሚዎቹን ዓይን እየተመለከተ የጠራውን የክርስቶስን ክብር በግልጽ የመናገር ድፍረት ይኖረው ዘንድ ያስፈልጋል። በሥራ፥ በትምህርት ቤትም ሆነ በተለያየ የሕብረተሰብ ኑሮ ውስጥ የተሰማራ አገልጋይ የቆመለትን እምነት የሚጠይቁና የሚገዳደሩ የሰይጣን መልእክተኞች በየስፍራው እንደማይጠፉና ይህ በእርሱ እንዳልተጀመረ በማወቅ የጠራውን ጌታ ለማስከበር አስቀድሞ መወሰን አለበት። ይህንን ውሳኔ ለወሰነ አገልጋይ፦ «እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ፥ ይላል እግዚአብሔር» (ኤር. 1፥8)።

II. በፈተና ጊዜ ጥበብ (22፥22–23፥10)።

ጳውሎስ በሻለቃው ፈቃድ ለሕዝቡ የመሰለው ግልጽነት የተሞላ ንግግሩ የተሰበሰበውን ሰው ሁሉ አስቆጣው። የሕዝቡ ጩኸት የሻለቃውን በጳውሎስ ላይ የበለጠ ምርመራ ያደርግ ዘንድ በመገፋፋቱ፥ እየገረፉ እንዲመረምሩት አዘዘ። ከግርፋት እንደማያመልጥ የተመለከተው ጳውሎስ በመጀመሪያ ከአንደበቱ የወጣው ቃል፦ «የሮሜን ሰው ያለ ፍርድ ትገርፉ ዘንድ ተፈቅዶላችኋልን?» (22፥25) የሚል ነበር። ይህም ጉዳይ በባለሥልጣኖቹ ላይ ትልቅ ፍርሃትን አሳደረ። ጳውሎስ ይህ ዓይነቱን በሰዎች ላይ ጥያቄ የሚያሳድር ጥበብ የተሞላበት አነጋገር በእግዚአብሔር እርዳታ ማስታወሱ አመን ነው።

ጳውሎስ በማግስቱ በደረሰበትም ክስ በተመሳሳይ ሁኔታ ከእግዚአብሔር የጥበብ አነጋገር ሲመጣለት እንመለከታለን። በዚያም ጊዜ፦ በጉባኤው መካከል ሰዱቃውያንና ፈሪሳውያን መገኘታቸውን ዓይቶ፦ «ወንድሞቼ እኔ ፈሪሳዊ የፈሪሳዊም ልጅ ነኝ ስለ ተስፋና ስለ

ሙታን መነሳት ይፈርዱብኛል ብሎ በሸንጎው ጮኸ» (23፥6)። ይህም አባባሉ የተሰበሰበውን ሕዝብ አበጣበጠው። ይህንንስ የመሰለው ጥበብ የተሞላው አነጋገር ከመንፈስ ቅዱስ ዘንድ ካልተላከ ከወዴት ይመጣል?

አገልጋይ ወደ ፈተና ደጅ በቀረበ ጊዜ ለሚደርስበት ጥያቄ ሁሉ መልስን ከጌታ ለመቀበል ልቡን ማዘጋጀት ይገባዋል። የእግዚአብሔርን ባሪያዎች በመክሰስ በብዙ ሺህ ዓመታት ልምድ ባለው በዲያቢሎስ ተገፍቶ የሚመጣን ክስ ለመቋቋም አገልጋይ ከመንፈስ ቅዱስ ጥበብን ካልተቀበለ በስተቀር እጅግ አስቸጋሪ ይሆንበታል። ለዚህ ነው ቃሉም እንዲህ እያለ የሚመክረን፦ «ወደ ምኩራቦችና ወደ መኳንንቶችም ወደ ገዦዎችም ሲጎትቱአችሁ፥ እንዴት ወይም ምን እንድትመልሱ ወይም እንድትናገሩ አትጨነቁ፤ መንፈስ ቅዱስ በዚያች ሰዓት ልትናገሩት የሚገባችሁን ያስተምራችኋልና» (ሉቃ. 12፥11–12)። አገልጋይ የሚችለውንና የሚጠበቅበትን ጥቂቱን ነገር ሲያደርግ፥ እግዚአብሔር ደግሞ ታላቁንና በሰው የማይቻለውን ተአምራት ያደርጋል።

III. በፈተና ጊዜ ደህንነት (23፥11–35)።

አይሁድ ከጳውሎስ አንደበት ከሚወጣው የጥበብ አነጋገር የተነሳ እርሱን ለማጥመድ ያላቸው ክፉ አላብ እንዳልሆነላቸው ባወቁ ጊዜ፥ ላይገድሉት እንዳይበሉና እንዳይጠጡ በመማማል ሴራን ጠነሰሱ። ይህንን ተንኮላቸውን እግዚአብሔር ያፈረሰባቸው የጳውሎስ የእኅት ልጅ ምክራቸውን አድምጦ ነገሩን ወደ ብርሃን እንዲያወጣው በማድረግ ነው። እግዚአብሔር እንደዚህም ዓይነት አገልጋዮቹን የማዳኛ መንገድ አለው። የአገልጋይ ልብ ግን የእግዚአብሔርን ማዳን ስማስተዋልና ለመቀበል ክፍት መሆን አለበት። ጳውሎስ፦ «እግዚአብሔር ገና ወደ ሮም እንድሄድ ፈቃዱ ነውና እንድም ነገር አይደርስብኝም፥ ስለዚህም ዝም ብዬ እጠብቀዋለሁ» በማለት የእኅቱን ልጅ ሊመልሰው ይችል ነበር። ነገር ግን ጳውሎስ ጌታ አገልጋዮቹን የሚታደግበት ብዙ መንገዶች እንዳሉት ያውቅ ነበርና መንገዱን ለጌታ ለቀቀ።

በዚህ ዘመንም ያለን አገልጋዮች ይህንን እውነት ልናስተውል ይገባናል። በፈተና በተከበብን ጊዜ እግዚአብሔር በምን መንገድ

እንደሚጎበኘን ስለማናውቅ ልባችንን ክፍት አድርገን እንጠብቀው። እግዚአብሔር አገልጋዮቹን የሚታደግበት የተለያዩ መንገዶች አሉት። ካሉትም መንገዶች የትኛውን መጠቀም እንደሚፈልግ የሚወስነው እርሱ ነው። «ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል (1ቆሮ. 10፥13)።

21

ለፈተና ሁሉ የተዘጋጀህ ሁን
(ክፍል ሁለት)
ምዕራፍ 24–26



ሉቃስ ከምዕራፍ 24 እስከ ምዕራፍ 26 ውስጥ የጳውሎስን የማያቋርጥ ፈተና መተረኩን ይቀጥላል። ሊቀ ካህናቱ ሐናንያና ጠበቃው ጠርጠሉስ ያሉበት የአይሁድ የከሳሾች ቡድን በአምስት ቀን ውስጥ ጳውሎስ ወደ ተወሰደበት ስፍራ ደረሰ። ጠበቃው ጠርጠሉስ ለፊልክስ ያቀረበው ውዳሴ ከንቱ ሽንገላ ለመሆኑ ለማንም አይሁዳዊ ግልጽ ነው። ጳውሎስ የተከሰሰው፥ በሁከት አነሳሽነት፥ በናዝራውያን ወገን የአመጽ መሪነትና፥ በቤተ መቅደስ አርካሽነት ነው።

ጳውሎስ በምላሹ የቀረበበትን የሁከት አነሳሽነትም ሆነ የአመጽ መሪነት ክስ ሲክድ፥ እነርሱ ኑፋቄ ብለው በሚጠሩት መንገድ ግን እግዚአብሔርን እንደሚያመልክ በግልጽነት አስረዳ። እንደ ጳውሎስ አመላለስ ከሆነ፥ ወደ ኢየሩሳሌም ከወጣ አሥራ ሁለት ቀን ብቻ እንደሆነውና ያም አመጻን ለማነሳሳት በቂ ጊዜ እንዳይደለ፤ በተጨማሪም ደግሞ ወደ መቅደስ የወጣበትን ምጽዋትንና መስዋእትን የማድረግ ዓላማ ሲፈጽም ሕዝብ እንዳልተሰበሰበና ምንም ሁከት እንዳልነበረ ገለጸ።

ሉስዩስ በመጣ ጊዜ ነገሩን እቆርጣለሁ ብሎ በቀጠሮ የቆየው ፊልክስ ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሚስቱ ከድሩሲላ ጋር በመሆን የጳውሎስን ምስክርነት ይሰማ ዘንድ ወደደ። የወንጌልን እውነት ሰምቶ የፈራው ፊልክስ ጳውሎስን በእስር ቤት በመተው በየጊዜው እያስመጣ ያነጋግረው ነበር። ፊልክስ ጳውሎስን ለሁለት ዓመት በእስር ቤት ያቆየው ጉቦን ፈልጎ ሲሆን፥ በመጨረሻም በፌስጦስ ሲተካ አይሁድን ለማስደሰት ሲል ጳውሎስን እንደ ታሰረ ተወው።

ፌስጦስ ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ፥ የአይሁድ መሪዎች ክሳቸውን ይዘው ቀረቡ። አይሁድ ጳውሎስን በመንገድ ሽምቅው ለመግደል ያላቸውን አሳብ ሳይገልጹ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ይላክ ዘንድ ለመኑ፥ ልመናቸው ግን አልሠራም። ጳውሎስም በቂሣርያም

ይከሱት ዘንድ በቆሙት በአይሁድ አለቆች ፊት ለፌስጦስ ሲናገር፥ ሊፋረድ በሚገባው በቂሣር ፊት እንደቆመና ምንም በደል እንዳልተገኘበት አብራራ።

ፌስጦስ አይሁድን ደስ ለማሰኘት መፈለጉን ጳውሎስ ያስተዋለ ይመስላል፥ ስለዚህም ወደ ቄሣር አቤት ለማለት ወሰነ። «ቄሣር» ማለት የሮም ንጉሠ ነገስታት የሚጠሩበት ስም ሲሆን፥ ይህ ወደ ቄሣር አቤት የማለት መብት የሮም ዜጎች አለልኝ የሚሉት መብታቸው ነው። ማንኛውም የሮም ዜጋ ተከሶ ከቄሣር በታች ወዳለ ባለሥልጣን ዘንድ ሲቀርብ፥ ፍርድን ከመቀበሉ በፊትም ሆነ ከተፈረደበት በኋላ ወደ ቄሣር አቤት የማለት መብት አለው። አንዴ ወደ ቄሣር አቤቱታ ከቀረበ በኋላ ጉዳዩ ወደ ሮም ይወሰድና ፍርዱ በንጉሠ ነገሥቱ በቄሣር እጅ ይተዋል። ጳውሎስ ወደ ቄሣር አቤት ያለው ይህንን የሮም ዜግነት መብቱን በመጠቀም ነበር።

ፌስጦስ የጳውሎስን ጉዳይ ወደ ቄሳር ሲያሸጋግር ስለ ክሱ ሁኔታ የሚያብራራ ደብዳቤም አብሮ በማከል መላክ ነበረበት። ነገር ግን በጳውሎስ ላይ የተሰነዘረው ክስ ግን ፍሬ ቢስ ስለነበር፥ የሚጽፈው ግራ ገብቶት ነበር። ስለዚህም በአካባቢው የነበረች የእንዲት አውራጃ ንጉሥ የነበረው አግሪጳ ከእህቱ ከበርኒቄ ጋር ለሰላምታ የመምጣታቸውን እድል በመጠቀም የጳውሎስን ጉዳይ ሰምተው አሳብ እንዲሰጡት የፈለገ ይመስላል። ፌስጦስም ጳውሎስን አስቀርቦ ጉዳዩን ለአግሪጳ አብራራለት።

ወደ ቄሣር ይግባኝ ያለው ጳውሎስ፥ በአግሪጳ ፊት የመፋረድ ግዴታ የለበትም። ነገር ግን የተሰጠውን እድል በመጠቀም የክርስቶስን ሕይወት ለዋቄነት ሊያበስር ወደደ። በንግግሩም፥ ክርስቶስ ተገናኝቶት ሕይወቱን ከመለወጡ በፊት የነበረበትን ሁኔታ፥ ከዚያም አልፎ በእንዴት ዓይነት አስገራሚ አኳኋን እንደተለወጠና ከተለወጠም በኋላ ያለበትን ሁኔታ በግልጽነት መሰከረ።

ፌስጦስ አብደሃል ብሎ ለተናገረው ቃል ምላሽን በፍጥነት ከሰጠ በኋላ፥ ጳውሎስ ንግግሩን ወደ ንጉስ አግሪጳ ዘወር ማድረጉ ምናልባት አግሪጳ ለወንጌል ፍላጎት ያደረበት መሆኑን ዓይቶ ነው ብሎ መገመት አያዳግትም። «በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህ» የሚለው

የአግሪጳ ምላሽ ከጳውሎስ ጋር እንደተግባቡ ሲያሳይ፥ ከወንበሩ መነሳቱ ደግሞ ለነገሩ ፍጻሜን ለመስጠት እንደፈለገ ይገልጻል። ያም ሆነ ይህ፥ ጉዳዩ ወደ ቄሣር አቤት ተብሎአልና ጳውሎስን ሊሰቁት ቢወዱ እንኳ የማይችሉበት ሁኔታ ላይ ነበሩ።



«ለፈተና ሁሉ የተዘጋጀህ ሁን» በሚለው በመጀመሪያው ክፍላችን ውስጥ የተመለከትነው፥ እግዚአብሔር ፈተና ለከበባቸው ባሪያዎቹ ስለሚሰጠው ጸጋ ነው። እነርሱም «ድፍረት»፥ «ጥበብ» እና «የመዳኛ መንገድ» ሲሆኑ፥ አገልጋይ እነዚህን እርዳታዎች ለመቀበል ዝግጁ መሆኑ የመጀመሪያ እርምጃው መሆን እንዳለበት ተመልክተናል። በዚህ «ለፈተና ሁሉ የተዘጋጀህ ሁን» በሚለው ክፍል የምንመለከተው፥ በፈተና ወቅት እግዚአብሔር የሚያደርግለትን የሚጠብቅ ያለ አገልጋይ ሊያደርጋቸው የሚገቡትን ነጥቦች ነው።

I. ከአቋራጭ መንገድ ተጠበቅ (24፥1–27)።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሃያ አራት ውስጥ የምንመለከተው ሐናንያና ጠበቃው ጠርጡስ ያላቸውን ክስ እንዳቀረቡ፥ ለዚያም ክስ ጳውሎስ ምላሽን እንደሰጠ ነው። ፊልክስ ግን የፍርዱን ሁኔታ ለመጎተት የወሰነ ይመስላል። ለምንድነው ፊልክስ ሁኔታውን ያዘገየው? ለዚህ ጥያቄ፥ ሉቃስ ከሰጠው ማብራሪያ የበለጠ መልስ ሊያገኝ የሚችል ሰው ያለ አይመስለኝም። «ያን ጊዜ ደግሞ እንዲፈታው ጳውሎስ ገንዘብ ይሰጠው ዘንድ ተስፋ አደረገ፤ ስለዚህም ደግሞ ብዙ ጊዜ እያስመጣ ያነጋግረው ነበር» (ቁ. 26)። ፊልክስ ከስልጣኑ ወርዶ በፊስጦስ እስኪተካ ድረስ የጳውሎስን ጉዳይ ለሁለት ዓመት ሙሉ መጎተቱ የሚያስገርም ነው። ጳውሎስ ጉቦን ከፍሎ ቢሆን ኖሮ የሁለት ዓመቱ መከራ በሁለት ሰዓት ውስጥ ሊወገድ ይችል ነበር። ጳውሎስ ግን በጌታው የታመነ አገልጋይ ነበርና የጉቦን አቋራጭ መንገድ ከመጠቀም ይልቅ ዝም ብሎ የጌታን ማዳን ለመጠበቅ ወሰነ።

በገንዘብ ኃይል ብዙ ጉዳይ ለማስፈጸም በሚቻልበት በዘመናችንም ይህ ዓይነቱ ሁኔታ አገልጋዮችን ይጋብዛል። አገልጋይ እግዚአብሔር ያዘጋጀለትን የመዳን መንገድ ከመጠበቅ ዝሎ የራሱን

አቋራጭ መንገድ ሲያመቻች እንዳይገኝ ሊያስተውል ይገባዋል። እግዚአብሔር በዚህ ሁኔታ እንዳስከብረው ጠርቶኛል ብለን ለክብሩ ስንቆም ከሚመጣው ፈተና ለማምለጥ ስንል አቋራጭ መንገድ በምንፈልግበት ጊዜ በመጀመሪያ ጌታን እናሳዝነዋለን። ከዚያም አልፈን ደግሞ ራሳችንን ለበለጠ ክፉ ነገር ልናጋልጥ እንችላለን። ምክንያቱም፥ የተጠቀምንበት አቋራጭ መንገድ ወዴት አቅጣጫ እንደሚወስደን ስለማናውቅ ነው። «ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች፥ ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው» (ምሳ. 14፥12)።

II. መብትህን ከማስከበር አትቆጠብ (25፥1–27)።

ጳውሎስ መብቱን ለማስከበር የወሰደውን እርምጃ በቀላሉ ለመመልከት በምዕራፍ ሃያ አምስት ውስጥ የተናገራቸውን ምላሾች ማስተዋሉ በቂ ነው። «የአይሁድን ሕግ ቢሆን መቅደስንም ቢሆን ቄሣርንም ቢሆን አንዳች ስንኳ አልበደልኩም» (ቁ. 8)። «እፋረድበት ዘንድ በሚገባኝ በቄሣር ፍርድ ወንበር ፊት ቆሜአለሁ» (ቁ. 10)። «እነዚህ የሚከሱኝ ክስ ከንቱ እንደሆነ ግን ለእነርሱ አሳልፎ ይሰጠኝ ዘንድ ማንም አይችልም» (ቁ. 11)። እነዚህ አባባሎች መብቱን ጠንቅቆ የሚያውቅና ያንንም መብቱን ለማስከበር ቆርጦ የተነሳ ሰው የሚናገራቸው ንግግሮች ናቸው። የጳውሎስ ፍላጎቱ በቄሣር ፊት መፋረድ ሲሆን፥ ይህንንም መብቱን ለማስከበር ባደረገው አቋም ወደ ቄሣር እንዲሄድ ተወሰነለት።

«በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ» (1ጴጥ. 3፥15)። አገልጋይ በተለያየ የኑሮ መስኩ እምነቱንና ለጌታው ያለውን አገልግሎት የሚቀናቀኑ የጠላት መልእክተኞች በሚነሱበት ጊዜ፥ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን መብቱን በሚገባ የተገነዘበና ያንንም ለማስከበር የቆመ ሊሆን ይገባዋል። አገልጋይ ያመነውን እምነቱን ጠንቅቆ የሚያውቅና ያወቀውንም ደግሞ በሚገባ ሁኔታ አብራርቶ ለመናገር ብቃት ያለው ቢሆን ለጥያቄ ሁሉ መልስ ለመስጠት የተዘጋጀ ይሆናል። አገልጋይ እግዚአብሔር ከየት አንስቶ እንዳመጣው፥ አሁን ደግሞ በምን ስፍራ

እንዳስቀመጠው፥ ወደ ፊትም የእግዚአብሔር ዓላማ በሕይወቱ ላይ ምን እንደሆነ ማወቁ ውስጡን ጠንካራ ያደርገዋል።

III. በጊዜውም አለጊዜውም ወንጌልን ስበክ (26፥1–32)።

በአግሪጳ ፊት የቀረበው ጳውሎስ ስለ ራሱ እንዲናገር በተፈቀደለት ጊዜ፥ በመጀመሪያ ለሕዝቡ፥ በመቀጠልም ለአግሪጳ የክርስቶስን ወንጌል አበሰረ። ጳውሎስ ከተነተነው ንግግሩ ሁሉ ማሰሪያ የሆነው አሳቡ እንዲህ ይላል፦ «በጥቂት ቢሆን ወይም በብዙ አንተ ብቻ አይደለህም ነገር ግን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ ደግሞ ከዚህ እስራቴ በቀር እንደ እኔ ይሆኑ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እለምናለሁ» (ቁ. 29)።

አገልጋይ ሊኖረው ከሚገቡት ጸጋዎች አንዱ፥ ካለው ዋና ዓላማ በፈተና ጊዜ አለማፈንገጥ ነው። የክርስቶስ ባሪያ ዋና ዓላማው ወንጌልን ማብሰር ነው። ስለዚህም በደረሰበት ፈተና ተደናግጦ ያንን ዓላማውን በመዘንጋት ሌሎች ነገሮች ላይ ሲያተኩር እንዳይገኝ ሊያስተውል ያስፈልገዋል። የመግቱና የክርክሩ ክፍለ ጊዜ ሁሉ አገልጋይ ወንጌልን የመስበክ ሥራውን ሊያዘናጉት አይገባም። «በእግዚአብሔር ፊት በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ባለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት፥ በመገለጡና በመንግስቱም እመክርሃለሁ፤ ቃሉን ስበክ፥ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፥ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም» (2ጢሞ. 4፥1-2)።

22

ለፈተና ሁሉ የተዘጋጀህ ሁን

(ክፍል ሦስት)

ምዕራፍ 27–28



በምዕራፍ ሃያ ሰባት እንደምናነበው፥ ጳውሎስ ወደ ሮም ይወሰድ ዘንድ ለዩልዮስ ታልፎ ተሰጠ። «በአድራሚጢስ መርከብ ገብተን ተነሳን» የሚለው የሉቃስ አገላለጽ፥ ሉቃስ እንደገና ከጳውሎስ ጋር አብሮ እንደሆነ ያሳየናል። የተሰሎንቄው አርስጥሮኮስ አብሮ በመርከቡ ላይ መሳፈሩ ምናልባት ጳውሎስን ለመርዳት ሳይሆን አይቀርም (ቆላ. 4፥19)። በሲዶና ጳውሎስ ወዳጆቹን እንዲጠይቅ ተፈቀደለት። ከዚያም ተነስተው ወደ ኢጣሊያ የሚሄድን መርከብ ወዳገኙበት ወደ ሙራ ተጓዙ። ጉዞው ቄንቀት የተሞላበት ቢሆንም እንኳ በብዙ መከራ መልካም ወደብ ወደምትባል ስፍራ ደረሱ።

ከጳውሎስ ምክር ይልቅ የመርከቡን መሪና ባለቤቱን ማመን የቀለለው የመቶ አለቃ ወደ ቀርጤስ ወደብ ይጓዙ ዘንድ ተማከረ። በጊዜአዊው ልከኛ የደቡብ ነፋስ በመታለል ጉዞአቸውን የቀጠሉት መርከበኞች ብዙ ሳይቆዩ አውራቂስ በሚሉት አውሎ ነፋስ በድንገት ተመቱ። መርከቡን መቆጣጠር ተስኖአቸው እስኪነዱ፥ ከዊንቱ ወደ ባሕር እስኪጥሉና፥ በፍጹም ፀሐይና ከዋክብትን ሳያዩ ለብዙ ቀናት እስኪቆዩ ድረስ በመሰቃየታቸው፥ እንድናለን የሚል ተስፋ ሁሉ ተቆርጦ ነበር።

ጳውሎስ የመቶ አለቃውን፥ የመርከቡን መሪና የመርከቡን ባለቤት ምክሩን ባለመቀበል ስላደረጉት የተሳሳተ ውሳኔ ከወቀሳቸው በኋላ፥ ጌታ በሌሊት ተገልጾ ጥበቃው ከእነርሱ ጋር እንደሆነ እንደተናገረው በመግለጽ አጽናናቸው። የጳውሎስም በእነርሱ መካከል መገኘት በመርከቡ ላይ ላሉት ሁሉ የመዳን ምክንያት ሆነ።

በአሥራ አራተኛው ሌሊት የሆነው ሁኔታ የመርከበኞቹን ራስ ወዳድነት በግልጽ ያሳያል። መርከበኞቹ መልሕቅ መጣል እንዳለባቸው አስመስለው በዚያው ለመሸሽ ያደረጉትን ሙከራ ጳውሎስ ስላወቀባቸው፥ ፊት ለፊት በመቃወም ሲያስተዋቸው እናነባለን። በዚያው ዕለት ነበር ጳ

ውሎስ በመርከቢቷ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ምግብ እንዲቀምሱ በመለመን እንዲመገቡ ያደረገው። ምግብም በልተው ከጠገቡ በኋላ ስንዴውን ወደ ባሕር እየጣሉ መርከቡን አቃለሉት።

በነጋ ጊዜ በደረሰባቸው የመርከብ አደጋ ምክንያት ወታደሮቹ ለማድረግ የቃጡት ሁኔታ መልካም አልነበረም። መርከቡ በሁለት ባሕር መካከል በመውደቁና በመሬት ላይ በመተከሉ፥ ከኋላ በሚገፋው ማዕበል ሳቢያ ይሰበር ጀመር። በዚያን ጊዜ ነበር ወታደሮቹ እስረኞቹ ዋኝተው እንዳያመልጡ ሊገድሉአቸው የተማከሩት። እግዚአብሔር ግን ለጳውሎስ ሲል የመቶ አለቃውን በመጠቀም ምክራቸውን ከንቱ በማድረጉ፥ ገሚሶቹ ራሳቸውን ወደ ባሕር በመጣል፥ ገሚሶቹ ደግሞ በሳንቃዎችና በመርከቡ ስባሪ በደኅና ወደ ምድር ደረሱ።

ምዕራፍ ሃያ ስምንት የሐዋርያት ሥራ የመጨረሻው ምዕራፍ ነው። ወደ ምድር በደህና የደረሱት መርከበኞች ሁለት ነገሮችን ለማወቅ የጓጉ ይመስላል። የደረሱባት ምድር ማን ትባል ይሆን? በምድሪቱ ያሉትስ ሰዎች በሰላም ይቀበሉአቸው ይሆን? ብዙም ሳይቆዩ ለሁለቱም መልስን አገኙ። ደሴቲቱ መላጥያ የምትባል ስትሆን፥ በውስጧ የሚኖሩትም አረማውያን በቸርነታቸው አስገረሙአቸው። በቁጥር 276 የነበሩት እነዚህ መርከበኞች ከብርዱ የተነሳ የነበሩበትን ሁኔታ በመመልከት የደሴቲቱ ነዋሪዎች እሳት አንድደው ተቀበሉአቸው። ጳውሎስ ቄራሮ አከማችቶ ወደ እሳት መጨመሩ፥ ይህንን ሥሌዎች መሥራት የሚገባቸውን ተግባር ለመፈጸም ራሱን ዝቅ እንዳደረገ ያሳያል። በዚያን ጊዜ ነበር እፉኝት ከሙቀቱ የተነሣ ወጥታ እጁን የነደፈችው። ካሁን ካሁን ተመርዞ ይሞታል ብለው ሲጠባበቁ የነበሩት አረማውያን የጠበቁት ሁኔታ ባለመሆኑ በመገረም፥ ቀድሞ እንደ ኃጢአተኛ ቆጥረውት የነበረውን ጳውሎስን አሁን እንደ አምላክ ይመለከቱት ጀመር።

ፑፕልዩስ የሚባለው የደሴት አለቃ ለእነ ጳውሎስ ቸርነት በማድረግ ሦስት ቀን በፍቅር አሳደራቸው። ይህም ሁኔታ በንዳድ ለታመመው ለፑፕልዩስ አባት፥ ከዚያም አልፎ በደሴቲቱ ደዌ ለነበረባቸው ሰዎች ሁሉ መፈወሻ ምክንያት ሆነ። በታላቅ ክብር

የሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ በመርከብ ተጭኖላቸው በእስክንድርያው መርከብ ተነሱ።

በሰራኩስ ሦስት ቀን፥ በሬጊዩ ደግሞ እንድ ቀን ከተቀመጡ በኋላ በደቡብ ነፋስ ተተግነው ወደ ፑቲዮሉስ መጡ። በዚያም ሊቀበሉአቸው የመጡትን ወንድሞች ባየ ጊዜ ጳውሎስ እግዚአብሔርን አመሰገነ። በመጨረሻም ጳውሎስ ወደ ሮሜ ገባ። በዚያም ከሚጠብቀው ከወታደር ጋር ለብቻው እንዲቀመጥ መፈቀዱ ምናልባት የሮሜ ዜግነት ስለነበረው ይሆን?

ጳውሎስ ወደ አዲስ ከተማ ሲገባ ምኩራቦችን መጎብኘት ልማዱ ነበር። በዚህን ጊዜ ግን በእስር ላይ ስለነበረ አይሁድን ለማግኘት እነርሱ ወደ እርሱ መምጣት ነበረባቸው እንጂ እርሱ ወደ እነርሱ ለመሄድ አልቻለም ነበር። የአይሁድን ታላላቆች ሰብስቦ የልቡን አሳወቃቸው። ለቄሳር አቤት በማለት ሮም ድረስ ለመፋረድ የደረሰው በሕዝቡ ላይ የሚከስበት ነገር ኖሮት ሳይሆን፥ በይሁዳ የነበሩት አይሁድ በነጻ እንዲለቀቅ ስላልወደዱ መሆኑን ገለጸላቸው። በኢየሩሳሌም ያሉት አይሁድ ለጳውሎስ ይህን ያህል ክብር ሰጥተው መሰብሰባቸውና ማነጋገራቸው የሚያስገርም ነው። እንደውም ከይሁዳ ስለ እርሱ የሰሙት መጥፎ ነገር እንደሌለ ከገለጹለት በኋላ ደግመው ሊሰሙት እንደሚወዱ ገልጸው በቀጠሮ ተለዩት።

በቀነ ቀጠሮአቸው ለተገኙት አይሁድ ስለእግዚአብሔር መንግሥት በሚገባ መሰከረላቸው። በመካከላቸው ስለሰሙት ቃል የተነሳውን መከፋፈል የተመለከተው ጳውሎስ፥ ከትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ ስድስት በመጥቀስ አይሁድ አልቀበል ያሉትን በረከት እግዚአብሔር ለአሕዛብ እንደላከው ተናገረ። «ይህንም በተናገረ ጊዜ አይሁድ እርስ በርሳቸው እጅግ እየተከራከሩ ሄዱ» (28፥ 29)።

ወንጌላዊው ሉቃስ እንዲህ ሲል የሐዋርያት ሥራ መጽሐፉን ያጠቃልላል፦ «ጳውሎስም በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፥ ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ ይቀበል ነበር ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግስት እየሰበከ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ ያስተምር ነበር» (28፥30–31)። ሉቃስ የጳውሎስን ታሪክ በእንዲህ ዓይነት በተንጠለጠለ ሁኔታ ሲተወው፦ «ጳ

ውሎስ እምን ደረሰ?» የሚል ጥያቄ መነሳቱ እሙን ነው። ለዚህ ጥያቄ መልስን ለማግኘት የሚችል ሰው ባይገኝም፥ ብዙ ግምቶች መሰንዘራቸው አልቀረም። አንዳንዶች የሮም ሁለት ዓመት ቆይታው እንደተፈጸመ (28፥30) ጳውሎስ በቄሳር የፍርድ ወንበር ፊት በመቅረብ የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል ብለው ያምናሉ። የጳውሎስ ፍጻሜ ይህ ከሆነ፥ ሉቃስ ሳይጠቅሰው ማለፉ ሊመለስ የማይቻልን ጥያቄ ማስነሳቱ እሙን ነው። ብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች እንደሚደግፉት፥ የጳውሎስ ከሳሾች በሮም ባለመቅረባቸውና ከሳቸውም ደካማ ስለነበረ በነጻ በመለቀቅ በበለጠ ሁኔታ ወንጌልን ከሰበከ በኋላ በሮማውያን እጅ ተገድሎአል ብለው ያምናሉ። በዚህም መሰረት፥ ጳውሎስ በሮም አስር ቤት ላለ ወደ ኤፌሶን ሰዎች፥ ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች፥ ወደ ቆላስይስ ሰዎችና ወደ ፊልሞና የላካቸውን መልእክቶቹን የጻፈ ሲሆን፥ ከዚያም ከተፈታ በኋላ፥ ሁለቱን ወደ ጢሞቴዎስ መልእክቶቹንና ወደ ቲቶ የላከውን መልእክቱን ዊምር እንደጻፈ ይነገራል። ያም ሆነ ይህ ጳውሎስ በሕይወቱ ክርስቶስን አስከብሮ ያለፈ ጀግና እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስም ታሪክም ይመሰክሩለታል።

«ለፈተና ሁሉ የተዘጋጀህ ሁን» በሚለው በመጀመሪያው ክፍሌ ውስጥ ከጳውሎስ የተማርነው፥ አገልጋይ በፈተናው ጊዜ ድፍረት፥ ጥበብና የመዳን መንገድ ጌታ እንደሚያዘጋጅለት እምኖ ዝግጁ እንዲሆን ነው። ይህንኑ አሳብ በመቀጠል በክፍል ሁለት ውስጥ አገልጋይ በመከራው ጊዜ ከአቋራጭ መንገድ ራሱን መጠበቅ እንዳለበት፥ መብቱን ለማስከበር መቆም እንደሚገባውና በጊዜውም አለጊዜውም ወንጌልን ለመስበክ መቆም እንዳለበት ተመልክተናል። በዚህ በመጨረሻው ክፍላችን የምንመለከታቸው ሦስት አስፈላጊ ትምህርቶች አሉን።

ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያስገርም ሰው ነበር። እውቀቱን፥ ልምምዱን፥ ያለውን ስጦታና ማንነቱን ሁሉ ለጌታ ክብር አሳልፎ የሰጠ አገልጋይ ነበር። ከቆመለት ዓላማ ግራ ቀኝ የማይል ብርቱ ሰው ነበር። በዚህም ጽናቱ አልቅሶና ወጥቶ ወርዶ ከተማረው ትምህርት፦ «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» (ሮሜ 8፥28) የሚል እጽናኝና እውነተኛ

ቃል በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ትቶ አለፈ። ከሐዋርያት ሥራ የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች የምንማረውን ይህንን ነው። የአገልጋይ ፈተናው በዝቶ ሲያስጨንቀውና ነገር ሁሉ ወደ ከፋት ያመራ ሲመስለው ልቡን በእግዚአብሔር በጎነት ሊያሳርፍ ይገባዋል። እግዚአብሔር የአገልጋይን የሰላም ዘመን ብቻ አይደለም የሚፈልገው፥ የመከራውንም ዘመን ለክብሩ ሊጠቀም ይሻል። ይህንን በበለጠ ለመረዳት የሚከተሉትን ነጥቦች እንመልከት።

I. መከራህ ለሌሎች በረከት ሲሆን (27፥1–44)።

ሉቃስ በምዕራፍ ሃያ ሰባት ውስጥ እንደተረከልን፥ ጳውሎስ በክርስቶስ ስላለው አገልግሎት ተይዞ መንገላታት ላያንሰው፥ በቄሳር ፊት ለመቆም በመርከብ ወደ ኢጣሊያ ሲሄድ ላለ የደረሰበት መከራ ይህ ነው አይባልም። ጌታ ኢየሱስ ግን የጳውሎስን የሰላም ዘመን ብቻ ሳይሆን የመከራውንም ዘመን ሳይቀር ለሌሎች በረከት አደረገው። የነበረበት መርከብ በማዕበል ተንገላትቶ ወደ ፊት የመኖር ተስፋ ሲጨልም፥ ጌታ ለጳውሎስ ተገልጾ የደህንነትን መልዕክት አበሰረለት። ያንንም መልእክት ተቀብሎ አብረውት ላሉት ሁሉ፦ «አይዞአችሁ ብዙ እመክራችኋለሁ፥ ይህ መርከብ እንጂ ከእናንተ አንድ ነፍስ እንኳ አይጠፋምና» (ቁ.22) በማለት አጽናናቸው። ጌታ ጳውሎስን በቄሣር ፊት ሊያቆመው ስለፈለገ፥ እርሱን ሊመጣ ካሰው የመርከብ አደጋ በደሙ ሲሸፍነው አብረው ላሉትም ሁሉ ደህንነት ሆነ። በተጨማሪም፥ የመርከብ ጉዞአቸው እጅግ በከፋ ጊዜ ወታደሮቹ ከእስረኞቹ ማንም ዋኝቶ እንዳያመልጥ በማሰት ሊገድሉአቸው ባሰቡ ጊዜ እግዚአብሔር ለጳውሎስ በመቶ አለቃው ፊት ሞገስን ሰጥቶት ነበርና የመቶ አለቃው ጳውሎስን ለማዳን ሲል የቀሩትንም አስረኞች አዳነ። ጳውሎስ በመከራ ውስጥ እንኳ ሆኖ ለሌሎች በረከት ሲሆን እንመለከታለን።

ይህን ሁኔታ ሳስብ በዘመናት ሁሉ በመከራቸው ለሌሎች በረከት የሆኑትን የእግዚአብሔር ባሪያዎች አስታውሳለሁ። ከምሳሌዎቻችን ሁሉ በላይ የሆነው ዋነኛ ምሳሌአችን ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ በመዋረዱ ስፍራ በመውረዱ እኛ የተከበረ ስፍራ አገኘን። እርሱ መኖሪያ አጥቶ በመንከራተቱ እኛ የሰማይን ቤት ተጎናጸፍን።

እርሱ በመጨነቁ እኛ ሰላማችን ተመለሰ። እርሱ ተጠልቶ ለእኛ ፍቅርን አስተምሮን ሄደ። እርሱ ሞቶ ለእኛ ሕይወት ሰጠን።

አገልጋይ የተጠራው ለዚህ ዓይነት አገልግሎት ነው። ሌሎች ይባረኩ ዘንድ እርሱ ቢነቀፍ፥ ሌሎች በክርስቶስ የሚገኘውን የደህንነት ክብር ይወርሱ ዘንድ እርሱ ቢናቅ፥ የሌሎች መብት ይከበር ዘንድ የራሱን መብት ቢጥል፥ ይህንን ሁሉ አገልጋይ እንደ ሙሉ ደስታ ሊቆጥረው ይገባል። ሰላም በሌለበት ስፍራ ሰላም ይሰፍን ዘንድ ቢጨነቅ፥ ጠብ በለፈነበት ስፍራ የእርቅ ምክንያት ለመሆን ትከሻውን ዝቅ ቢያደርግ፥ አንድነት በጠፋበት አካባቢ የአንድነት ምክንያት ለመሆን ዋጋ ቢከፍል፥ ይህ ሁሉ ለአገልጋይ ክብሩ ነው። አገልጋይ ሆይ፥ በመከራህ ሌሎች ይባረኩ ዘንድ ዝግጁ ነህ?

II. መከራህ እንደ ኃጢአተኛ ሲያስቆጥርህ (28፥1–10)።

ሰረጅም ጊዜ በማዕበል የተንገላቱት እነ ጳውሎስ በመጨረሻ መላጥያ ወደ ተሰኘች ደሴት በደህና በደረሱ ጊዜ ጳውሎስን ያልጠበቀው ሌላ ችግር አጋጠመው። የደሴቲቱ ሰዎች ያነደዱላቸውን እሳት በበለጠ ለማቀጣጠል ጳውሎስ ዊራሮ በመጨመር ላይ ሳለ ከእሳቱ ሙቀት የተነሳ እፉኝት ወጥታ ነደፈችው። ሁኔታውን የተመለከቱት አረማውያን ጳውሎስ በእፉኝት መነደፉ ኃጢአተኛ ስለሆነ ነው በማለት አሰቡ። ለጌታ ኢየሱስ ሲል ወዲያና ወዲህ የሚንከራተተው ጳውሎስ፥ በመንገዱ ላይ ያጋጠመው መከራ እንደኃጢአተኛ ሲያስቆጥረው ማየት ያሳዝናል።

ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች በየዘመኑ አሉ። ለክርስቶስ ኢየሱስ ክብር ሲል የሚሮጥ አገልጋይ የሚደርስበትን ፈተና እየቆጠሩ፦ «ይህ የደረሰብህ በሕይወትህ ኃጢአት ስላለብህ ነው» የሚሉ ሰዎች በሚነሱበት ጊዜ ልቡን በማጽናት ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረቱን ማጠናቀር አለበት እንጂ በፍጹም ተስፋ ሊቆርጥ አይገባውም። ነገር ግን አገልጋይ የደረሰበትን መከራ ዓይተው ሰዎች በሚፈርዱበት ጊዜ መጽናት እንዳለበት ሁሉ፥ እርሱም ሌሎች ወገኖቹ በችግርና በመከራ በሚያልፉበት ጊዜ ተመሳሳይ ፍርድ እንዳይሰጥ ማስተዋል ይገባዋል።



አንዳንዶች በሕይወታቸው የሚደርስባቸውን መከራ ሁሉ ቀድሞ በሰሩት ኃጢአት ምክንያት እንደደረሰባቸው እየቆጠሩ በጥፋተኝነት ስሜት ይዋዥቃሉ። ሌሎች ደግሞ በሕይወታቸው ካለው አለመታዘዝ የተነሳ የመጣባቸውን ችግር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመቁጠር በዝምታ ያልፋሉ። አንተ ግን ሚዛንህን ጠብቅ። መከራ ሲገጥምህ ራስህን መመርመር አስፈላጊና የመጀመሪያ እርምጃህ ሊሆን እንደሚገባው አስታውስ። ሆኖም ክርስቶስ በደሙ ያጠበውን ድካምህን እየጎተትክ በጥፋተኝነት ስሜት ከመዋዠቅ ልብህን ጠብቅ።

III. መከራህ የበለጠ በር ሲከፍትልህ (28፥11–31)።

ጳውሎስ በወራት የሚቆጠር የቄንቀት ጉዞ በእግዚአብሔር ምሕረት ካጠናቀቀ በኋላ ወደ ሮም ገባ። በዚያም ከደረሰ በኋላ ምንም እንኳ በእስራት የነበረ ሰው ቢሆንም፥ በታላቅ ነጻነት ይመላለስ ዘንድ ጌታ ነጻነትን አጎናጸፈው። ከሚጠብቀው ወታደር ጋር ሰብቻው እንዲቀመጥ ፈቃድ ማግኘቱ፥ የአይሁድን ታላላቆች ጠርቶ ስለራሱ ንጽህናና ስለጌታ ኢየሱስ አዳኝነት መመስከሩ፥ ከዚያም አልፎ በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀምጦ ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ በመቀበል ማንም ሳይከለክለው ስለ እግዚአብሔር መንግስት መስበኩ ትልቅ የአገልግሎት በር ነው። የእግዚአብሔርን አሠራር ለማያውቁ ሰዎች የጳውሎስ ሁኔታ አስራት ይመስላል፥ ጳውሎስ ግን በታላቅ ነጻነት ውስጥ ነበር ያለው። ለተመልካች ከአገልግሎት የተገለለ ይመስላል፥ ለጳውሎስ ግን ትልቅ የአገልግሎት በር ተከፍቶለት ነበር።

እግዚአብሔር ሌላን በር ሳይከፍት አንዱን በር አይዘጋም። ስለዚህም አገልጋይ በመከራ ውስጥ በማለፉ ምክንያት ነገሮች ሁሉ የተበለሻሹና በሮች ሁሉ የተዘጉ በሚመስለው ጊዜ፥ ከሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት የሚያገኘውን ትምህርት በማስተዋል፥ በመከራው ውስጥ የሚከፈትለትን በር ለመመልከት ዓይኑን መክፈት አለበት። አገልጋይ ይታሰራል እንጂ ወንጌል አይታሰርም። አገልጋይ ይገደላል እንጂ ወንጌል አይጠፋም። ይህንን እውነት በሕይወቱ ተለማምዶ የተመለከተው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፦ «ይህንም በመስበክ እንደ ክፉ

አድራጊ እስክታሰር ድረስ መከራ እቀበላለሁ፥ የእግዚአብሔር ቃል ግን አይታሰርም» (2ጢሞ. 2፥ 9)።

ባለፉት ሦስት ምዕራፎች ውስጥ አገልጋይ ለፈተና ሁሉ የተዘጋጀ ሊሆን እንደሚገባው በሰፊው ተመልክተናል። ከዚህ በመቀጠል፥ ለተመለከትናቸው አሳቦች ማሰሪያ የሚሆኑ ነጥቦችን እሰነዝራለሁ። አገልጋይ ለሚመጣበት ፈተና ተዘጋጅቶ መጠበቅ እንዲቻለው የሚከተሉትን አሳቦች ያስተውል።

1) አገልጋይ የማያቋርጥ ራሱን የመመርመርና የንስሐ ሕይወት ያስፈልገዋል። ራሱን እየመረመረ የማይመላለስ አገልጋይ የሚመጣበትን መከራ ከኃጢአቱ ጋር የማገናኘት ባህሪይ ይታይበታል። ችግር ሲደራረብበት በመጀመሪያ የሚታየው ያጠፋው ጥፋት ነው። ዘወትር በንስሐ የሚመላለስ አገልጋይ ኃጢአቱ በደሙ እንደታጠበለት ስለሚያምን የሚደርስበትን መከራ በእምነት እንጂ በፍርሃት ዓይን አይመለከተውም።

2) አገልጋይ የጌታን ድምጽ የመለየት ልምምድ ያስፈልገዋል። የእግዚአብሔርን ድምጽ የማያስተውል አገልጋይ ከጌታ የመጽናናትም ሆነ የምክር መልእክት መቀበል ያስቸግረዋል። በተለይም አገልጋይ በመከራ በሚያልፍበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማወቅ የግድ ድምጹን መስማትን መለማመድ ያስፈልገዋል።

3) አገልጋይ የደረሰበት መከራ ከየት አቅጣጫ እንደመጣበት የሚያስተውል ሕይወት ያስፈልገዋል። በአንደኛ ደረጃ፥ አገልጋይ እግዚአብሔርን በሚታዘዝበት ጊዜ የመከራ ዓይነት ከየአቅጣጫው ብቅ ይላል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አገልጋይ እግዚአብሔርን አልታዘዝም በሚልበት ወቅት ራሱን ለመከራ ያጋልጣል። በሦስተኛ ደረጃ፥ አገልጋይ በዚህች በተበላሸች ዓለም ውስጥ በመኖሩ በማንም ላይ እንደሚደርስ ሁሉ በእርሱም ላይ አንዳንድ መከራዎች እንደሚደርሱበት እሙን ነው። ስለዚህም፥ አገልጋይ መከራ ወደ እርሱ በሚመጣበት ጊዜ ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ከየትኛው አቅጣጫ እንደመጣ ማወቁ በምን መልኩ ሊጋፈጠው እንደሚችል እንዲያውቅ ይረዳዋል።

ETHIOPIAN EVANGELICAL BAPTIST CHURCH
9120 FERGUSON ROAD
DALLAS, TEXAS 75228